# "...እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?":–ክርስቶስ በኢትዮጵያውያን ዕይታ

በ

በልሁ ደሰለኝ

አዲስ አበባ

መጋቢት 1996 ዓ/ም

## ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ........................................... 7

መቅድም........................................... 9

መግቢያ........................................... 11

I. ክርስቶስ ማን ነው? .................... 14
(Ontological Christology)

1.1. ቅድመ ትሥጉት (ቅድመ ሥጋ መሆን) 14

1.1.1. የ"ቃል" ማንነት ........................ 15
1.1.2. የ"ቃል" ዘላለማዊነት ..................... 16
1.1.3. አካላዊ ቃል በግጻዌ መለኮት .............. 18
1.1.4. አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ነውን? ......... 21
1.1.5. "እግዚአብሔር" :- ሥላሴ? አብ? ወይስ ፍጹም አምላክ?...................... 22
1.1.6. አካላዊ ቃል በመልእክተኛአምሳያ (በአርአያ መልአክ) ተገልጧልን? ................. 26

1.2. ድኅረ ትሥጉት (ድኅረ ሥጋ መሆን) ........... 28

1.2.1. "ቃልም ሥጋ ሆነ" :-ሥጋ ለበሰ? ወይስ ሰው ሆነ? ................... 28
1.2.2. ስመ ሥጋዌ (የቃል ሥጋ መሆን ስሞቹ) 29
1.2.2.1. የአዳኝነት ስሞቹ:- 29
1.2.2.2. የሹመት ስሞቹ:- 31
1.2.2.3. የማንነት መገለጫ ስሞቹ:- 32
1.2.3. ክርስቶስ ፍጹም አምላክ (ራሱ እግዚአብሔር) ነውን? ........................................ 33
1.2.3.1. ስለ ክርስቶስ አምላክነት ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች... 34
1.2.3.2. ኢየሱስ ስለ ራሱ ምን ይላል? 35
1.2.3.3. የዮሐንስ "ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር" ምስክርነት...... 37
1.2.3.4. የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊና የሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነት 41

1.2.3.5. ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን
የካዱ ታሪካዊ ኑፋቄዎች................ 43

1.2.4. ክርስቶስ ፍጹም (ምሉዕ) ሰው ነውን?...... 48

1.2.4.1. ክርስቶስ ፍጹም ሰው
ስለ መሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች...50
1.2.4.2. ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት፤
ግን ሰው ነውን?.......................... 50
1.2.4.3. ክርስቶስ ኃጢአት ማድረግ አይችልም?
ወይስ ኃጢአት አለማድረግ ችሏል?...... 54
1.2.4.4. ክርስቶስ ከማርያም ሥጋና
ነፍስ ነስቷልን (ወስዷልን)? .............. 55
1.2.4.5. የክርስቶስን ሰው መሆን
የካዱ ታርካዊ ኑፋቄዎች................ 56

1.2.5. አምላክነት እና ትስብእት (ሰው መሆን)
በክርስቶስ ውስጥ ያላቸው ግንኙነት:- ... 58
1.2.5.1. ክርስቶስ በአካል ስንት ነው?...... 58
1.2.5.2. ክርስቶስ የአምላክና የሰው
ባሕርያት ድብልቅ? .............. 61
1.2.5.3. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን
ታሪካዊ አሰሳና የተዋሕዶ አስተምህሮት... 62
1.2.5.4. ክርስቶስ የአምላክና የሰው
"ተዋሕዶ" (አምላክ-ሰው)? .............. 71
1.2.5.5.የክርስቶስ አካል የ"ሰው"?፥ የ"ቃል"?፥
የ"ተዋሕዶ" ወይስ የሁለቱ ባሕርያት?...... 72
1.2.5.6. የቅዱስ ቄርሎስ ምስጢረ ሥጋዌ:-
“ተዋሕዶ”ወይስ “ተዋሕዶ በተዐቅቦ”? ......... 75
1.2.5.7. በአንድ ጊዜ ክርስቶስ አምላክም ሰውም
/አምላክ እና ሰው/? ......................... 79
1.2.5.8. የአርዮስ፥ የቅዱስ ቄርሎስ፥
የአውጣኬ፥ የኬልቄዶንና የተዋሕዶ
አስተምሕሮቶች ንጽጽር.................... 82

II. የክርስቶስ ግብራት ምን ምን ናቸው? ....................86
(Functional Christology)

2.1. ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያደረገው ምንድር ነው? ....86
2.1.1. መስቀሉና ሥርየት ......................... 88
2.1.2. የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ሞት ነውን? ...96

2.2. የክርስቶስ አገልግሎቶች:- ......................... 100
2.2.1. ነብይነት ............................................. 102
2.2.1.1. ክርስቶስ ነብይ አምላክ ነውን?.........102
2.2.1.2. የክርስቶስ ነቢይነት ልዩነቱ ምንድር ነው?.................... 102
2.2.2. ክህነት ................................................. 103
2.2.2.1. ክርስቶስ አማላጅ ነውን?........... 103
2.2.2.2. የክርስቶስ ክህነት ያስገኘው ልዩነት ምንድር ነው? ......................... 105
2.2.3. ንጉሥነት ........................................ 106
2.2.3.1. ክርስቶስ በግጻዌ መለኮት አቻ ንጉሥ ነውን?... ............................ 106
2.2.3.2. ክርስቶስ ልዩ ንግሥና ተቀብሏልን? ...107

2.3. የክርስቶስ ግብራት ደረጃዎች:- ....................... 108

2.3.1. ግብረ ትስብእት ............................. 108
/Human Functions/
2.3.2. ግብረ መለኮት ................................ 111
/Divine Functions/

ማጠቃለያ ................................................ 113
የምንጭ ማጣቀሻ ........................................ 117
የጥሬ ቃላት መፍቻ .................................... 120
ደጋፊ ማብራሪያ.......................................... 124
ዋቤ መጻሕፍት ........................................... 127

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት ውስጥ ዘወትር በቅዱስ መንፈሱ አብርሆት ያልተለየኝንና ኃይል የሆነኝ አምላኬን አመሰግናለሁ:: በመቀጠልም ይህቺን መጽሐፍ በዚህ መልክ እንድትወጣ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ላበረከቱልኝ:- በሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶቼ በየጊዜው በኢትዮጵያ አውድ አገር በቀል አስተምህሮቶች ላይ ጽሑፎችን እንዳቀርብ ላበረታቱኝ አስተማሪዎቼ የላቀ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ::

በተለይም የመመረቂያ ጽሑፍ አማካሪዬ የነበረትን ዶ/ር አቲቨ አትሬውስን እንዲሁም ዶ/ር አቲቨ ብሬያንን÷ አባታዊ ድጋፋቸው ያልተለየኝና የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ አስተያየታቸውን የለገሱልኝ ቄስ ዶ/ር ደበላ ብሬን÷ ላደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ ምላሽን በመስጠት የተባበሩኝን የጩራ መጽሔት አዘጋጅ አቶ ጸጋዬ ደምሴን እንዲሁም በድሕረ ምረቃ ጥናት ሂደቴ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ክርስቶስ ላይ በሊቃውንቶቿ የተጻፉ የጥንት መጽሐፍትንና ጽሑፎችን እንድጠቀም የተባበሩኝ÷የሊቃውንት ጉባዔ አባል ከሆኑት ከመሳከ ገነት አፍወርቅ የቃለ መጠይቅ ምላሾችን ጽሑፍ እንዳሰባስብ የረዱኝን የቤተመዘክር ጥንታዊ ጽሑፎች ክፍል ኃላፊ አቶ መሳኩን እንዲሁም በጉለሌ የካፑቺያን ፍራንሲስካን የካቶሊክ ሥነ መለኮት ኮሌጅ ቤተ መጻሕፍት ኃላፊን አባ ዮሐንስን አመሰግናለሁ::

© *Heywet Literature Services 2004*

*የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው*

**All Right Reserved**

የመጀመሪያው ዕትም 1996 ዓ/ም

*የአሳታሚው አድራሻ :-*

*ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት*

*ፖ. ሣ. ቁ. 698*

*ስልክ :- 76 33 28 /76 98 30*

*አዲስ አበባ ኢትዮጵያ*

*E mail*: hiwotlit@telecom. *net.et*

*የአዘጋጁ አድራሻ:-*

*በልሁ ደሰሰኝ*

*ፖ. ሣ. ቁ :- 101488*

*ስልክ:- 79 74 50 / 46 13 74*

*አዲስ አበባ ኢትዮጵያ*

*E mail: belihud@Yahoo.Com*

*mkcollege@telecom.net.et*

## ማስታወሻነቱ

*ይህች መጽሐፍ ለባለቤቴ ለወ/ሮ ጽጌ ደሜና ለልጃችን ለረድኤት በልሁ እንዲሁም ሁሌም የጸሎትና የምክር ድጋፋቸው ሳልተለየን ለወንድማችን መስፍን ሙልጌታና ለባለቤቱ ለወ/ሮ ወርቅነሽ ገብሩ÷ ለልጆቻቸው፡– ለዲቦራ÷ ለፌቨንና ለሔብሮን ማስታወሻ ትሁንልኝ!*

በመቀጠልም የመጀመሪያ ረቂቁን በማንበብ የማሻሻያና የማበረታቻ ሃሳቦችን የሰጡኝ የአገልግሎት ባልደረቦቼ የሆኑትን:- የጸጋ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ አካዳሚክ ዲን መምህር አፈወርቅ ኃይሉን÷ የኢትዮጵያ ሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት *ሬጅስተራር አቶ ወርቁ ኃማርያምን÷ ሥነ ጽሑፍን በማረም የረዳኙን አቶ ታፈሰ ታደሰንና ደህንን ኮርስ ከእኔ ጋር የወሰደ ተማሪዬ የሆነውን ተስፋዬ መካንንን÷ የተረዳሁትን እውነት በንባብ ለማቅረብ በምሳሌነታቸው እንዲሁም በምክራቸው ያበረታቱኝንና የረጅም ግዜ ህልሜ እውን እንዲሆን ከጎኔ ያልተለዩኝን በድሩ ሁሴን÷ ኃይሉ ቸርነትንና ለበደ በከፊን÷* ከእረኝነት አገልግሎታቸው የጊዜ ውጥረት ባሻገር እግዚአብሔር ለእጆቻቸው ባስተማረው ስልፍ የመጽሐፉን የሽፋን ሥዕል በማዘጋጀት የተባበሩኝን መጋቢ ደድንቃቸው ለገሠ እንዲሁም የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ የተየበችልኝንና በመ/ክ ኮሌጅ ነጻ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለች እህት መና በቀለን ላመሰግን እወዳለሁ::

በመጨረሻም በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት ዘወትር ከአጠገቤ በመሆን ያበረታቱኝ ባለቤቴን ጽጌ ደሜንና ልጆችን ህጻን ረድኤት በለሁንን እንዲሁም በጸሎትና በተለያየ መንገድ ያገዙኝን የመ/ክ ኮሌጅ መምህራንንና አስተዳደር እንዲሁም ተማሪዎቼን በሙሉ እግዚአብሔር ይባርክልኝ ለማለት እወዳለሁ::

በልሁ ደለለኝ
መጋቢት 1996 ዓ/ም
አዲስ አበባ

# መቅድም

አስተርዕዮተ እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች የደረሰበትን መንገድ ስንመለከት በሰዎች ባህልና ቋንቋ መሆኑ ግልጽ ነው:: ስለዚህም እግዚአብሔር በሰዎች የመግባቢያ ቋንቋ፥ የየእለቱ እንቅስቃሴን በሚያከናውኑበት ባህላዊ የኑሮ ዘዬና በአጠቃላይ እውቀትን ሲቀስሙ በሚያስችሏቸው መንገዶች ራሱን ገልጧል:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ከሰው ራሱን እንዳልደበቀ ያስረዳናል::

ይሁንና በዘመናችን የእግዚአብሔር እውነት ውጤታማ በሆነ መንገድ አለማችንን ሳለመድረሱ በምክንያትነት ከምንጠቅሳቸው ውስጥ አንዱ የወንጌልን አለም አቀፋዊ እውነት ከአገርኛው አውድ ውጪ ለማሰራጨት በሚደረግ ጥረት የባህል ግጭት ውስጥ መውደቁ ነው:: አንድን እውነት ምንም ያህል እውነት ቢሆን አውዳዊ ባልሆነ መንገድ በተግባር ላይ ለማዋል መጣር ከሚገጥሙት መሰናክሎች የተነሳ ፍሬያማነቱን አጠያያቂ ያደርገዋል:: በዚህ ረገድ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ምስክርነት ከወሰዳቸው አንዱን መጥቀሱ መልካም ነው::

ይኸውም ከታሪካዊ ነገረ–ክርስቶስ በመነሳት እንደ ሊቅ «የፀጋ ልጅ» በመባል ለሚታወቀውና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለተወገዘው ቡድን መንስኤው የካቶሊክ ሚስዮናውያን እንጂ የፕሮቴስታንቱ ፒተር ኃይሊንግ አለመሆኑን መናገራቸውን ገልጿል:: እንዲያውም በእነኚህ አባት ገለፃ ፒተር ኃይሊንግ ስብከቱ «'እመን ብቻ ትድናለህ!' ነበር::» በማለት በአገር በቀሉ አስተምህሮ ላይ ተመስርቶ የእግዚአብሔርን እውነት የማሰራጨት ጠቀሜታን የሚያስገነዝብ ቁም ነገርን አስጨብጦናል::

የዚህ መጽሐፍ ደራሲ በሰሁ ደሰሰኝ በትምህርት ሂደቱ ወቅት ባደረገው ከፍተኛ ጥረት እጅግ መሠረታዊና ዓለም አቀፋዊ በሆነ የነገረ-ክርስቶስ እውነትና በኢትዮጵያውያን አባቶች በምድራችን በተደረጉ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔዎች ውጤት የሆኑ ጥንታዊ ሥነ ጽሑፎች ጥናት የአድንኖትን የምሥራች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስፋጨት የሚያስችለን የእግዚአብሔር እውነት ዘግቧል:: በኢትዮጵያ ምድር ወንጌልን በማሰራጨት ረገድ እያንዳንዱ ምዕመን ሊገነዘበው የሚገባውና የወንጌልን እውነት ቤተኛ የሚያደርግ አውዳዊነትን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

ይህ መጽሐፍ በሥነ መለኮት ኮሌጆች ለሚሰጡ የዶክትሪንና ታሪካዊ ሥነ መለኮት ኮርሶች በመማሪያ መጽሐፍነት ሲያገለግል ከመቻሉም በላይ እያንዳንዱ የቃሉ አገልጋይ የእግዚአብሔርን እውነት ከሚያገለግልባት ምድር አውድ አንጻር በመረዳት ጥበብ በሞላበት አገልግሎት እንዲሰማሩም ይረዳዋል:: በተጨማሪም ጸሐፊያንና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራንን ሥነ መለኮታዊ ሃሳቦችን በትክክል መግለጽ የሚያስችሉ ቃላት ግንዛቤ ከማስጨበጡም በላይ በነገረ ክርስቶስ ረገድ በብዙዎች አዕምሮ ለሚጉላሉ ጥያቄዎች የእግዚአብሔርን እውነት በተገቢ የፍልስፍናና አመክንዮት ፈቢጥ ማስጨበጥ የሚቻል መሆኑ እሙን ነው:: መልካም ንባብ!!

ቄስ ዶ/ር ደበላ ብሬ

የኢትዮጵያ ሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ተ/ቤት ዳሬክተር

## መግቢያ

ኢትጵያውያን በአለም የምንታወቅባቸው በርካታ ነገሮች አሉን:: በበጎ ነገሮቻችን የምንታወቀውንም ያህል ባሉብን ችግሮቻችንም እንታወቃለን:: በተለይ ለመንፈሳዊ ህይወታችን በችግርነት ከምንጠቅሳቸው ውስጥ ከታሪክ ከመማር ይልቅ የታሪክ ተማሪዎች መሆናችንና ያለንን ነገር እንዳለን አክብሮ ያለመያዛችን ናቸው:: ባለፉት ጥቂት የህይወት ዘመኖቼም የችግራችንን አስከፊነት ማስተዋል ችያለሁ::

አገር በቀል ለሆኑ ጥናታዊ ምርምሮች ባለቤቶች ሆነው የሚጠቀሱ የአገር ተወላጆች ያለመሆናቸው ምክንያቱም የአገራችን ሰዎች ትኩረት ከአገር ውጭ ባሉ ጥናቶች ላይ በመሆኑ ነው:: ስለዚህም በርካታ ኢትዮጵያውያን ለአገራችን ሥነ መለኮታዊ እሳቤዎች ትኩረት የለንም:: ይሁንና አገራችን በከርሰ ምድሯ ብቻ ሳይሆን በሥነ መለኮታዊ ትምህርቶቿም ልዩና በአለም ትኩረት የተቸራቸው ቅርሶች ባለቤት ናት::

በአዳም በደል ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ጥል ለማስወገድ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ወገን የሆነ አንድ መካከለኛ አስታራቂ ያስፈልግ ነበር:: ታዲያ መካከለኛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ (ሰው የሆነ አካላዊ ቃል) በምድር ሲመላለስ ሰዎች ሁሉ ስለ እርሱ የየራሳቸው የሆነ ግንዛቤ ነበራቸው:: በማቴ 16:13-17 ላይ ኢየሱስ ሰዎች እርሱን ማን ብለው እንደተረዱት ደቀመዛሙርቱን

በጠየቃቸው ወቅት የተሰጠው ምላሽ ሙሉ የሆነ መረዳትን የሚያንጸባርቅ አልነበረም:: ለጥያቄው ምላሾቻቸውን ካደመጠ በኋላም ወደ ደቀ መዛሙርቱ በማተኮር:- "... እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?" በማለት ለጠየቀው ጥያቄ ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ አስተርዕዮ (መገለጥ):- "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ " አለ::

ይሁንና የጴጥሮስም ምላሽ በጥቅሉ እውነት ቢሆንም ቀጣይና ጥልቀት ባለው መንገድ መልስ የሚሹ ጥያቄዎችን የሚያነሳሳ ነበር:: ለመሆኑ ክርስቶስ:- አምላክ?÷ ሰው? አምላክ እና ሰው?÷ አምላክ-ሰው?÷ የአምላክና የሰው ድብልቅ? ወይስ አምላክም ሰውም? ከታሪካዊ ሥነ መለኮት እንደምንረዳው ለእነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ የተለያዩ ቡድኖች አሉ:: አንባቢዎቼ:- ይህችን መጽሐፍ ከማንበባችሁ በፊት የእናንተን መልስ እንድትሰጡና ከንባብ ሂደታችሁ በኋላ ያገኛችሁትን የግንዛቤ ለውጥ መለካት እንድትችሉ ላበረታታችሁ እወዳለሁ!

በዚህ መጽሐፍ ልዳስሰው ወደተነሳሁበት ዓላማዬ ሳመራ ክርስቶስን ከኢትዮጵያውያን ዕይታ አንጻር በሚያስተዋወቅ ረገድ በኢትዮጵያዊያን የሥነ መለኮት መምሬዎች የአገር በቀል ነገረ ክርስቶስ ላይ በማተኮር በዘመናችን ያሉትን የተለያዩ እይታዎችን ለማስቃኘት እሞክራለሁ:: ስለዚህም ለአንባቢዎቼ ከቅድመ ግምታዊ አሳቤና ቀኖናዊ በሆነ መረዳት አስቀድሞ የተቆለፈ አዕምሮን ከመያዝ እንዲሁም "በእጅ ያለ ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል!" እንዲሉ ለአገር በቀል ሥነ መለኮት ትኩረት ከነፈገ አቀራረብ መታቀብን እመክራለሁ::

ከዚህም በተጨማሪ የአስተርዕዮተ እግዚአብሔርን ሚዛንነት በመጠቀም ከታሪካዊ ሥነ መለኮት ለመማር በተከፈተ ልብ በመቅረብ እንዲሁም የአውዳዊ ሥነ መለኮትን ጠቀሜታ በማጣጣም ልዑል የሆነ አምላክን ሰው ሆኖ ወደ ምድር በመምጣት የተረከልን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ሰው የሆነበትን ዐላማም ከኢትዮጵያዊ እይታ አንጻር ለመተንተን እሞክራለሁ።

በአንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን ዘንድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቀናጀና ወጥ የሆነ ነገረ ክርስቶስ እንደሌላት ሲነገር ይደመጣል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህን አስተምህሮ ጥልቀት ባለው መንገድ የሚያስረዱ መጽሐፍት ለህዝብ አለመቅረቧ ከሊቃውንቶቿ በስተቀር በሌሎች ዘንድ የዳበረ መረዳት እንዳይኖር ምክንያት ሆኗል። ስለዚህም በተለያዩ ጉባዔዎች በአገር በቀል መልኩ የዳበረ ነገረ ክርስቶስን በማቅረብ ግንዛቤን ማሳደግና የክርስቶስ ማንነት በእርሱ ከተፈጸመው የማዳን ተልዕኮ ጋር ያለውን ግንኙነት ከማስዳሰስም በላይ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ትክክለኛ አቋም ለማስገንዘብ እሞክራለሁ።

በመጨረሻም እያንዳንዱ ሰው በመጠንና በዓይነት ይለያይ እንጂ ሥነ መለኮት ወይም ስለ እግዚአብሔር የሚያውጠነጥነው ነገር ያለው እንደመሆኑ በዚህች መጽሐፍ ውስጥ የተዳሰሱትን [illegible] በማንበብ ከቅድመ ግምታዊ እሳቤ ተላቆ እውነትን በሃገርኛው አውድ በማሰራጨት የበለጠ ውጤታማ መሆን እንዲችል ይህችን መጽሐፍ አበረክታለሁ። ስለ መጽሐፍ አስተያየታችሁንና ጥያቄዎቻችሁን በአደራሻዬ መላክ ትችላላችሁ።

በልሁ ደለለኝ

መጋቢት 1996 ዓ/ም

## I. ክርስቶስ ማን ነው?
## (Ontological Christology)

የክርስትና እምነት የተመሠረተው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በማመን ላይ ነው:: ክርስትና የሚያስተምረውም ስለ ክርስቶስ ማንነትና በእርሱ ስለተፈጸመው ታላቅ የማዳን ስራ ነው:: ከዚህም የተነሳ የክርስትና ጀማሪውም ሆነ ፈጻሚው ጌታችን ኢየሱሰ ክርስቶስ እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል (ዕብ 12:2):: ክርስቶስ ባደረጋቸው ድርጊቶቹና ባስተማራቸው ትምህርቶቹ ላይም የክርስትና እምነት ተመሥርቶአል::

ለመሆኑ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን ነው? እርሱ ራሱ ለአገልግሎቱ ማእከላዊ የሆነ ጥያቄውን «እናንተስ እኔን ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ?» (ማቴ16:15) በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አቅርቦላቸው ነበር:: ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ መስጠት ያለመቻል ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ታላቅ ውድቀት ነው::

ክርስቶስ ማን እንደሆነ ለመረዳት በሚደረግ ጥናት ውስጥ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ማግኘት አለባቸው:- አንደኛው የእርሱን ማንነትና ባህርይ ማለትም ከእርሱነቱ አንጻር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከግብሩ (ከተግባሮቹ) አንጻር ምን እንዳደረገ እና በአሁኑም ወቅት የእርሱ ግብር ምን እንደሆነ በትክክል መግለጽ መቻል ነው:: እነዚህ ሁለቱ ነጥቦች ፈጽሞ መነጣጠል የማይገባቸው ናቸው::እርሱ ማን እንደሆነ ያለን ግንዛቤ ግብሩ ምን እንደሆነ ለሚኖረን መረዳት መሰረቱ ነው::

ስለዚህ «ክርስቶስ ማን ነው?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የእርሱን ማንነትና ባሕርይ አስቀድመን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ በመመስረት በብሉይ ኪዳን ዘመንና በአዲስ ኪዳን ዘመን በመከፋፈል በጥልቀት መመርመር ያሻል::

### 1.1. ቅድመ ትሥጉት (ቅድመ ሥጋ መሆን)

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ኢየሱስ በቤተልሄም ከድንግል ማሪያም ሲወለድ እያንዳንዱ ሰው በመወለድ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገኘ የእርሱም መገኘት እንዲሁ አልነበረም:: ሥጋ ሆኖ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት አስቀድሞ ነበረ፤ነገር ግን «ኢየሱስ» በመባል አይታወቅም::

በቅድመ ትሥጉት (ሥጋ መሆን) ክርስቶስ ማን ነበር? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን መዳሰስ ያሻል።

ብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ መልኩ እግዚአብሔርን በብዙ ቁጥር ስያሜ ይገልጸዋል። ለምሳሌ በዘፍ 1:1 ላይ «እግዚአብሔር» ተብሎ የተተረጎመው በእብራይስጥ «ኤሎሂም» ማለትም የአምላክን ከአንድ በላይ «ረቂቅ አካል» (person) ያለው መሆኑን አመላካችና የብዙ መጠሪያ ሆኖ ንግሥናንና ከኃሊነትን አመላካች ነው። በዘፍ 1:26 «እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር....»። በዚህ ጥቅስ መሠረት ደግሞ የእግዚአብሔርን አንድነትና ከአንድ በላይ ረቂቅ አካል ያለው መሆን አመላካች ሀሳብን ያዘሉ ቃላት እናገኛለን።

በአዲስ ኪዳን ብርሃን ከተመለከትነው ደግሞ በግልጽ አንዱ እግዚአብሔር በረቂቅ አካልነቱ ሦስት ማለትም አብ፣ወልድና መንፈስቅዱስ መሆኑን እንረዳለን (ማቴ 28:19)። ይህ የአዲስ ኪዳን አስተርዕዮት (መገለጥ) በዚህ ዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር በልጁ የተናገረው የመገለጡ ምልዐትን የሚያመለክተን ነው።

እንግዲህ በብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ መልኩ ከአንድ በላይ በሆነ ረቂቅ አካልነት እንዲሁም በአዲስ ኪዳን አብ ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ለሰው ልጆች ራሱን የገለጸው እግዚአብሔር ከሦስቱ ረቂቅ አካላት አንዱ የሆነውና ወልድ በመባል የተጠቀሰው ሥጋ ሆኖ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት *ቃል* በመባል ይታወቅ ነበር። ለመሆኑ ይህ *ቃል* ማን ነው?

### 1.1.1. የ "*ቃል*" ማንነት

ስለ እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪነት መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስተምረን *ኤሎሂም* በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን በመቀጠልም ፍጥረታትን በሙሉ በቃሉ እንደፈጠረ ግልጽ ያደርግልናል። እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰማይንና ምድርን የፈጠረው ከምንድር ወይም በምንድር ነው? *ኤሎሂም* የሰማይና የምድር ፈጣሪ መሆኑን (መፍጠሩን) እንጂ ከምንና በምን እንደፈጠረው ይህ የዘፍጥረት መጽሐፍ ክፍል አያመለክትም። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ግን በዕብ 11:3 «ዓለሞች በእግዚአብሔር *ቃል* እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» በማለት በአለማት አፈጣጠር የ*ቃል*ን ግብር ይተርክልናል። ሐዋርያው ዮሐንስም ሁሉ በእርሱ እንደሆነ በመተረኩ *ቃል* ፈጣሪ እንደሆነ

ያስረዳል (ዮሐ1:3)። ዳዊትም «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውን ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» (መዝ(33):6) በማለት የቃልን ፈጣሪነት ገልጧል።

ከዚህ በመነሳት ኤሎሂም ከአንድ በላይ (የብዙ) በሆነ ቁጥር ስያሜ መገለጡ ቃል ከረቂቅ አካላት አንዱ መሆኑን ከማመላከት ይልቅ በግጻዊ መለኮት የአንድ አምላክ የፈጣሪነት ግብር የተገለጸ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። በእርግጥ ይህ ቃል በዘፍጥረት መጽሐፍም ሆነ እንደ መዝሙረ ዳዊት ባሉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጠቀሰበት መንገድ የብሉይ ኪዳን አባቶች የእርሱን ረቂቅ አካልነት ሳይሆን ከፈጣሪ አፍ በሚወጣ በትእዛዝ መልክ ወይም ኤሎሂም አለማትን የፈጠረበት መንገድ ተደርጎ በሚወሰድ መልኩ የተገነዘቡት ነበር። ስለሆነም በአዲስ ኪዳናዊው የሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ የተሰጠ አብርሆት በብሉይ ባለው የመገለጥ ታናሽነት የእግዚአብሔርን ከአንድ በላይ ረቂቅ አካላት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አይቻልም።

ቃል በመዝ (110):3 ላይ በነብየ አምላክ ዳዊት ትንቢት አዘል ዝማሬ እንደተገለጸው «.... ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ።» በማለት እግዚአብሔር የተናገረለት÷ በመዝ 2:7 «እግዚአብሔርም አለኝ:- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ።» በማለት በመሲሃዊው ትንቢት የተጠቀሰለትና በዕብ 1:5 የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ከመላእክትስ እንኳ በኩር (የላቀ) እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ለመሆኑ ይህ ቃል ከጊዜ አንጻር አባት ከልጅ አስቀድሞ እንዲገኝ ከአብ በኋላ የተገኘ (የተወለደ) ነው? «አንተ ልጄ ነህ» ሲለው አብ ከወልድ በፊት እንደነበረ አመላካች ነውን? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሻቸውን በሚቀጥለው ርዕስ ሥር ለመግለጽ እሞክራለሁ:-

### 1.1.2. የ"ቃል" ዘላለማዊነት

ቅድመ አለም ወልድ የእግዚአብሔር ቃል በመባል ይታወቃል፤ ነገር ግን ከሰው አንደበት እንደሚወጣና ዝርው (የማይጨበጥ ÷ የማይዳሰስ) ቃል ሳይሆን በረቂቅ አካልነት ሆኖ «ማን?» እንጂ «ምን» የሚባል አይደለም። ስለዚህም «አካላዊ ቃል» ልንለው እንችላለን ።

ስለ አካለዊ ቃል (ወልድ) ዘላለማዊነት በሚክያስ 5:2 «... ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሚሆን ይወጣልኛል።» በማለት በቤተልሄም ከለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ (ወልድ) እንደሚወለድ ትንቢት ተናግሯል። እዚህ ላይ መረዳት የሚያሻን መሰረታዊ እውነት «ዘላለም» ማለት «ቅድመአለም» ማለት እንደሆነ ነው። አለም ከመፈጠሩ በፊት ጊዜ መቆጠር አልጀመረም። ይህም

ማለት የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ አልነበረም፥ አካላዊ ቃል (ወልድ) አለም ከመፈጠሩ በፊት ነበረ ስንል ዘላለማዊ ነው ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ ከአብ ጋር በማነጻጸር «ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መቼ ወልድ ተወለደ?» የሚል የጊዜ ማነጻጸሪያ ቃልን መጠቀም አንችልም። ስለዚህም ዘላለም ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚኖረን ትክክለኛ ግንዛቤ ላይ በመመስረት በወልድና በአብ መካከል የጊዜ ልዩነት እንደሌለ መረዳት ይቻላል።

ከዚህ እውነታ በመነሳት ነው ቅዱሳን አባቶች አካላዊ ቃል ከዘላለም የነበረ ነው እንጂ ከአብ በኋላ የተገኘ እንዳይደለ፥ በዘላለም መቅደም መቀዳደም እንደማይኖር ደግሞም ከዘላለም እግዚአብሔር አንድ እንደሆነም የመሰከሩት። የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስገነዝበን የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ የነበረው አርዮስ የተባለ ሰው ወልድ ከአብ ከመገኘቱ በፊት አልነበረም፥ ነገርግን ከጊዜ በፊት ተገኝቷል በማለት የእርስ በእርስ ተቃርኖ ያለውን አመለካከት ሰንዝሯል።[1] በዚህም አርዮስ "ዘላለም" የሚለው ቃል ትርጉም የጠፋበት፥ ለማስረዳት የተነሳውንም ነጥብ በአካላዊ ቃል ላይ አስቀድሞ በያዘው ቅድመ ግምታዊ እሳቤው (Pre-supposition) ተገዥነት ስለነበረ ምክንያታዊነት ይጎድለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም አርዮስ አካላዊ ቃልን ዘላለማዊ ፍጡር ለማለት የተነሳው በምሳሌ 8:22 ላይ «እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ በቀድሞ ስራው መጀመሪያ» የሚለውን ቃል በመጥቀስ ነው። ከዚህ ክፍል አውድ እንደምንረዳው «ጥበብ» በሰውኛው ዘይቤ የምትናገረውን ንግግር ነው። በቀጥታ ስለ ወልድ የሚናገር አለመሆኑን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ይህን አለማመላከታቸውን ማስተዋል ያሻል። በእርግጥም በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደሆነ የሚያመለክቱ ክፍሎች (1ቆሮ 1:24፣30፣ ቆላ 2:3) ሲሆኑ በመጽሐፈ ምሳሌ ጥበብ በሰውኛው ዘይቤ የተናገረችውን ለክርስቶስ የተነገረ መሆኑን ከምሳ 8 ላይ አያጣቅሱም። ይህ ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም አንጻር ጥንቃቄ ያሻዋል። በእርግጥም የምሳሌ ምዕራፍ ስምንትን አውድ ስንቃኝ ከፍጥረታት በፊት ጥበብ መወለዷን ቁ 25፥ ሰማያትን ሲዘረጋ ምድርን ሲመሰርት ዋና ሰራተኛ እንደሆነች ቁ 27-30 ወዘተ እንመለከታለን ሆኖም ግን ጥበብ ራሷም ብትሆን እንኳን ፍጥረት እንደሆነች ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተገኘች (የተወለደች) እንዲሁም ከእግዚአብሔር የማትነጠልና ከዘላለምም ከእርሱ ጋር እንደነበረች ይህ ክፍል ያስረዳናል። ታዲያ ለምን በምሳ 8:22 ላይ "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ፥ በቀድሞ ስራው መጀመሪያ።" ትላለች? የሚል ጥያቄን ያስነሳል።

ጥበብ እዚህ ላይ የምትናገርበት አገላለጽ የቃላት ፍቺ አወዛጋቢነት ያለበት ክፍል ነው። እግዚአብሔር «በቀድሞ ስራው መጀመሪያ» አደረገኝ የሚለው ሀሳብ የተገለጸበት ቃል *qànâ* በአርዮስ እሳቤ «መፍጠር» የሚልን ትርጉም ሲሰጠው ቀጥተኛ ትርጉሙ ግን ማስገኘት፥ የራስ ማድረግ (to get, acquire) ማለት ነው። ሲ.ኤፍ. በርኔይ የተባለው ሊቅ ማስገኘት (beget) ወላጅነት እንጂ ፈጣሪነትን የማያጠናክር እንደሆነ ይገልጻል።[2] የቃሉ ትርጉም በዘፍ 4፡1 ላይ ሔዋን ልጅ ከወለደች በኋላ «ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር ***አገኘሁ*** አለች» ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ነው።

እንግዲህ አርዮስ የወልድ ከአብ መውጣት «መፈጠር» (create) መባል አለበት ሲል፥ የቤተክርስቲያን አባቶች የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ግን «መገኘት» (beget) ማለትም «መወለድ» የሚል ትክክለኛ ትርጉሙ መሆኑን በማንሳት አርዮስ ተወግዟል። ይህ የመጽሐፈ ምሳሌ ክፍል የሚያወሳው ጥበብ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብ ከመሆኑ ጋር የሚጠቃቀስ ቢሆን እንኳ የጥበብን መፈጠር ሳይሆን ከእግዚአብሔር መገኘት (መወለድ) እንዲሁም በፍጥረት ሥራ ላይ ዋና ሠራተኛ መሆን አመላካች ነው። ለመሆኑ ይህ አካላዊ ቃል ዘላለማዊ ከመሆኑ ባሻገር ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ግንኙነት (በግጻዌ መለኮት ያካላዊ ቃል ስፍራን) በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

### 1.1.3. አካላዊ ቃል በግጻዌ መለኮት

ግጻዌ መለኮት ወይም የመለኮት አካላት ግንኙነት (God head) ዘላለማዊ የሆነ የእግዚአብሔርን፦ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያመለክት ቃል ነው። ታዲያ አካላዊ ቃል በዚህ ዘላለማዊ የመለኮት ረቂቅ አካላት ህብረት ያለው ስፍራ ምንድነው? ቃል የአብ ዘላለማዊ ልጁ ነው (መዝ (110)፡3)። እግዚአብሔር "ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ" ሲለው ከዘላለም (አለም ከመፈጠሩ በፊት) በአብና በወልድ መካከል የነበረው ግንኙነት የአባትነትና የልጅነት ግንኙነት መሆኑን ያመለክታል። ብዙ ሰዎች አካላዊ ቃል ወልድ የተባለው ድኅረ ትሥጉት ወይም ቃል ሥጋ ሆኖ ከመጣ በኋላ እንደሆነ ያስባሉ። ሆኖም ግን የአካላዊ ቃልን ዘላለማዊ ግንኙነት ሲያመለክት ወልድ (የእግዚአብሔር ልጅ) የሚል ስያሜን ተቀብሏል። ለመሆኑ ይህ ልጅነት ምን አይነት ልጅነት ነው?

አካላዊ ቃል ለአብ ያለው ዘላለማዊ ልጅነት ቅድመ ዓለም የነበረውና ድኅረ ዓለምም ያልተገሰሰ ልጅነት ነው። ከታሪክ እንደምንረዳው በእስክንድርያ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የነበረው አርዮስ የአካላዊ ቃልን የእግዚአብሔር ልጅ መሆን በፀጋና እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ሞገሱን

በማብዛቱ እንጂ በባሕርይ እንዳይደለ ተናግሯል:: አርዮስ ከዚህ በተጨማሪ ወልድ በአምላክነቱ ከአብ ጋር አንድ መለኮት ሳይሆን የተፈጠረ፥ ለለውጥ የተጋለጠና የሚሞት መለኮት ነበር በማለት ያምን ነበር::[3]

እ.ኤ.አ. በ 328 የእስክንድርያ ጳጳስ የነበረውና እስክንድርን የተካው ቅዱስ አትናቴዎስ ይህን የአርዮስን ትምህርት ያወገዘውን የ325ቱን የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ከጥቃት በመከላከል:- ክርስቶስ ከአብ ጋር አንድ በግሪኩ *homoousios* እንደሆነ አስረድቷል:: በዚህም አርዮስ ወልድን ከአብ ጋር ተመሳሳይ ነው የሚል አቋም ይዞ ነበር::[4] አርዮስ የአካላዊ ቃልን የእግዚአብሔር ልጅነት የተቃወመበት መሠረታዊ ሀሳቡ የመነጨው በአካላዊ ቃል ማንነት ላይ ባለው ጥያቄ ነበር:: በውኑ አካላዊ ቃል የአብ የፀጋ ልጅ ማለትም በፀጋና የአብ ሞገስ የበዛለት በመሆኑ ወልድ ተባለን? እግዚአብሔርን እውነተኛ አምላክ ከሚያሰኘው ማንነቱ አካላዊ ቃል ያልተጋራው ባሕርይ ነበርን? ከሌለስ የፀጋ ሳይሆን «የባሕርይ ልጁ» እንዳይሆን የሚከለክለው ምንድር ነው?

አካላዊ ቃል የአብ ዘላለማዊ ልጁ ብቻ ሳይሆን «የባሕርይ ልጁ» መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ መመልከት ይቻላል:: አርዮስ የቃልን ከአብ መገኘት ከጊዜ አንጻር የእርስ በርስ ተቃርኖ ባለው መንገድ አለም ሳይፈጠር ከአብ መገኘቱን በማንሳት የፀጋ አምላክ ወደሚል ድምዳሜ መጥቷል:: ይህ አርዮስም የሚስማማበት የወልድ ከአብ መገኘትና አካላዊ ቃልን ወልድ ያስኘው ልጅነት የተገኘው እንዴት ነው? ለሚለው ጥያቄ አስቀድሞ መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው:: በአዲስ ኪዳን በዮሐንስ ወንጌል 8:42 እና 16:28 ላይ ከእግዚአብሔር (ከአብ) ወጥቼ መጥቻለሁ በሚለው ሀሳብ በይበልጥ ግልጽ የሆነና በብሉይ ኪዳንም የነበረ ጽንሰ ሀሳብ ነው:: በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ «ከአብ ወጥቼ» ማለት ምን ማለት ነው? ይህስ ከአብ መገኘት (መውጣት) የፀጋ ወይስ የባሕርይ ልጅነትን አሰጠው?

አካላዊ ቃል ወልድ የሆነበት መንገድ ከአብ መውጣቱ (መገኘቱ) ነው:: ሆኖም ግን ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ፈጽሞ ያልነበረ ሳይሆን በአብ የነበረና ከአብ የወጣ መሆኑን ነው:: ስለዚህም አካላዊ ቃል በራሱ ልዩ አካል ከዘላለም በአብ አካል ነበረ:: እንዲሁም በራሱ ልዩ አካል ከዘላለም ከአብ ወጣ:: ይህ ደግሞ ወልድ (የእግዚአብሔር ልጅ) አሰኘው:: እንግዲህ ይህ ልጅነት ልዩና በምድራችን ከሚታወቁት ከፈቃደ ሥጋ ልጅነትም ሆነ በማደጎ ከመውሰድ (ምናልባት ከአርዮስ የፀጋ ልጅ ከሚለው ) ሃሳብ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ ነው:: ስለዚህ ልጅነት ሰይፈ ሥላሴ ሲገልጹ:– «ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ከአካል ባሕርይ ከባሕርይ ...»[5] የተወለደ መሆኑን ይገልጻሉ::

ይህን ልዩ የሆነ ልጅነት እንዴት እንደተገኘ በተነጋገርንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ስንዳስስ "አያም" ውስጥ የሚጥል ጥያቄ ሳይፈጠርብን አይቀርም:: ይኸውም:- አካላዊ ቃል ከአብ ከወጣ (ከተገኘ) አስገኚውም የተገኘውም እንዴት እኩል ዘላለማዊነት ይኖራቸዋል? ካስገኚው የተገኘው አይቀንስምን? እንደዚህ አይነቱ ጥያቄ አሁንም ግጸዌ መለኮትን ካለመረዳት የሚመነጭ ነው:: እንደ ናሁአዳም አገላለጽ:– "ልብ አለ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ከልብ ጋር÷ በልብ ዘንድ ያለው ቃል÷ ሀሳብ÷ ጥበብ÷ ከልብ ሲወጣ እንደሚገለጽና እንደሚታወቅ በሚያስረዳና» «ጸአት ወይም አወጣጥ» በተባለ ልደት ምክንያት ወልድ ተባለ እንጂ ተከፍሎ አለበት በሚያሰኝ አስገኝ አኳኝ ነበረው በሚያስብል የልደት አይነት አለመሆኑን መጻሕፍት ሁሉ ያስገነዝባሉ (ዘፍ 1:3፣ መዝ 33:6፣(148):1-6፣ ሚክ 5:2፣ ዮሐ 1:1-3፣ 8:42፣ 58፣ እብ 1:1-13)::"[6]

እንግዲህ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከዘላለም የየራሳቸው ረቂቅ አካላት ኖሯቸው በአብ አካል ነበሩ:: አሁንም ከዘላለም (ምንም መቀዳደም ሳይኖር) ወልድ ከአብ አካል በራሱ ልዩ አካል ከአብ ወጣ:: ይህ ከአብ መውጣቱ በአብ አካል ላይ ለውጥን የማያመጣው አካላዊ ቃል በራሱ ልዩ አካል በመውጣቱ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ አስቀድሜ ለማብራራት እንደሞከርኩት በዘላለም ውስጥ የጊዜ ስሌት አለመኖሩና ሁለቱም ዘላለም መሆኑን ማስተዋል ያሻል::

ሌላው ጥያቄ የአካላዊ ቃልን ዘላለማዊ የአብ ልጅነት ምን አይነት ልጅነት ብለን እንጥራው? የሚለው ነው:: ለዚህ ጥያቄ ከአብ ጋር በዘላለማዊነቱ÷ በመለኮትነቱና እግዚአብሔርን እውነተኛ አምላክ በሚያሰኙት ማናቸውም ባሕርያቱ ፍጹም እኩል ስለሆነ «የባሕርይ ልጅ» የሚለው ስያሜ ተስማሚና ትክክለኛ የአካላዊ ቃልን የእግዚአብሔር ልጅነት ገላጭ ነው:: ምንም እንኳ ስለ ልጅነት ስናነሳ ይህንን አይነት ልጅነት ሰምተን ሳናውቅ ብንችልም የባሕርይ ልጅ በሚለው ቃል ለመግለጽ የተፈለገው ከአብ ጋር ፍጹም አንድ የሆነ ባሕርይ ያለው መሆኑን ነው:: ለምሳሌ:- በምድራችን ሌሎች እንስሳትም ሆኑ ሰው ልጆችን ሲወልዱ የባሕርያቸውን ነው:: በምድር ላይ በኖርኩባቸው አመታት ሰምቼ የማላውቀው ከሰው ልጆች ተወልዶ የሌሎች እንስሳትን ባሕርይ የያዘ÷ እንዲሁም በተገላቢጦሹ ከሌሎች እንስሳት ተወልዶ የሰው ባሕርይ የያዘ ፍጥረት መኖሩን ነው:: ከዚህ በመነሳት የአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ልጅነት በባሕርይ ራሱን እግዚአብሔርን ወይም የአብ ትክክለኛ ባሕርይ ያለው ነው ለማለት ያስችላል:: ስለዚህ በዘመናችን አንዳንዶች የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውን ስያሜ ሲሰሙ «አላህ አይወልድም አይወለድም!» በማለት

ከሚከራከሩ ወገኖች ባልተናነሰ መንገድ የሩካቤ ዘበስጋ ልጅነትን ብቻ ማሰብ ትክክል አይደለም።

ወልድ ሰውን በማዳን የእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ዘመኑ ሲደርስ ወደ ምድር የተላከ አንድያ ልጁ ነው (ገላ 4:4 ከዮሐ 3:16 ጋር ይነጻጸር)። አንድያ ልጁ መሆኑ ሁለትያ የሌለበት የተለየ ልጅነትን (የባሕርይ ልጅነትን) ያመለክታል። ስለዚህ ከአርዮስ ስህተት በከፋና በሌላ አቅጣጫ በዚህ ዘመን በክርስቶስ በኩል ያገኘውንና እኛ ለእግዚአብሔር ልጆች የሆንበትን መንገድ ከአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ልጅነት ጋር ለማነጻጸር የሚደረጉ ሙከራዎች "ሰው አምላክ ነው" ከሚለው ጥንስስ የመነጩ በመሆናቸው ስለ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነት ተገቢውን ግንዛቤ መያዝ ያሻል። ታዲያ አካላዊ ቃል (ወልድ) ራሱ እግዚአብሔር ነውን?

### 1.1.4. አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ነውን?

ይህን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ላይ መመስረት ያስፈልጋል። ስለዚህም በዮሐ 1:1-5 ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አካላዊ ቃል የሚለውን መገንዘብ ያሻል። ዮሐንስ ስለ አካላዊ ቃል ከሌሎቹ ወንጌላት በተለየ መንገድ ከትሥጉት (ሥጋ መሆን) ሳይሆን ከዘላለም (ከጊዜ በፊት) የነበረውን ማንነት ከሚተርክ የእግዚአብሔር አስተርዮት ይዘግባል። በዮሐ 1:1 ላይ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ይላል።

በዚህ ጥቅስ የአካላዊ ቃልን እግዚአብሔር መሆን ለመነጋገር አስቀድመን የአንዳንድ ቃላትን ፍች ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። "በመጀመሪያው" የሚለው ቃል ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ቁጥር አንድን እንድናስብ ያደርገናል። ይህ አካላዊ ቃል ከምንም በፊት መሆኑንና ከዚያ በኋላ የተገኘ ሁሉ በእርሱ የተገኘ ወይም ያለ እርሱ የተገኘ ምንም የሌለ መሆኑን የሚያመለክት ቃል ነው።

ሌላው «...ነበረ» የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል ዘላለማዊነትን እንጂ በጊዜው ውስጥ ቀዳሚ መሆንን አያመለክትም። ምክንያቱም ቅድመ አለም የጊዜ ስሌት ስለሌለ ነው። "በመጀመሪያ ...ነበረ።" የሚለን አካላዊ ቃልን ነው። ስለ ቃል ደግሞ ዮሐንስ ወንጌሉን ሲጽፍ ከፍተኛ ትኩረት እንደሰጣቸው የሚታመኑ የግሪክ ሰዎችም ሆኑ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ የተሰጣቸው አይሁድ የየራሳቸው ግንዛቤ ነበራቸው።

ከዚያም «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም....»ቁ 3 በማለት በቃልና በእግዚአብሔር መካከል ከነበረው ግንኙነት በቃልና በተፈጥሮ መካከል ወዳለው ግንኙነት ያመራል:: በዚህም ያለ ቃል የሆነ (ህልውናውን ያገኘ) እንደሌለ ይገልጻል:: እንግዲህ አካላዊ ቃል ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያመላክት ነው:: በዚህ የዮሐንስ ወንጌል የመግቢያ ሃሳብ የቅድመ ትሥጉት አካል የሆነው የወልድን እግዚአብሔር መሆን ከተመለከትን የክፍሉን ሙሉ ሃሳብ በድኅረ ትሥጉት አካል ማንነት ረገድ ዮሐንስ የሰጠውን ምስክርነት በምንመለከትበት ክፍል ውስጥ በጥልቀት ለመመልከት እሞክራለሁ::

ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው "እግዚአብሔር" የሚለው ስያሜ:- ግጻዌ መለኮትን (የአብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስን ግንኙነት)? ÷ አብን? ወይስ ፍጹም አምላክነትን? አመላካች ነው:: ታዲያ «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

### 1.1.5. "እግዚአብሔር":- ሥላሴ? ÷ አብ? ወይስ ፍጹም መለኮት?

አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ስለ መሆኑ ስንነጋገር እግዚአብሔር በመለኮትነቱ ማለትም ከሁሉ የበላይ አምላክነቱ አንድ እንጂ ሦስት እንዳይደለ የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወደ አዕምሮአችን ይመጡብናል:: ስለዚህም የእግዚአብሔርን የመለኮት አንድነት የሚያፋልስ እሳቤ እንዳይደለ እናስተውላለን:: መጽሐፍ ቅዱስ አካላዊ ቃል ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአምላክነቱ እኩል መለኮት መሆኑን ያመለክተናል:: ይህ ማለት ግን አካላዊ ቃል ራሱ ግጻዌ መለኮት (አብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) ነው ማለት አይደለም:: አካላዊ ቃል አብ እንዳይደለ የሚያብራራልን በአብ ዘንድ እንደነበረ የሚገልጸው ሃሳብ እርሱ ራሱ የተለየ ረቂቅ አካል መሆኑን የሚገልጽ ስለሆነ ነው:: ስለ አካላዊ ቃል ራሱ እግዚአብሔር መሆን ካነሳን በዮሐ 1:1 ላይ "ቃልም እግዚአብሔር ነበረ::" ሲል "እግዚብሔር" ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያሻል::

በእብራይስጥ ኤሎሂም የሚለው ይህ የእግዚአብሔር ስም የእግዚአብሔርን ገዢነትና ጌትነት አመላካችና ከፈጣሪነት ተግባሩ ጋር የተያያዘ ስያሜ ነው:: ይህ የእግዚአብሔር ስም በየቋንቋው ከሁሉ በላይ ለሆነ የአለማት ፈጣሪና ገዢ ብርቱና ሀያል እንደሆነ ለሚታሰብ አንድ ታላቅ አምላክ የሚሰጥ ስያሜን በመውሰድና አውዳዊ በማድረግ ይተረጎማል:: ከዚህም የተነሳ ከደቡብ ኢትዮጵያ አንድ ብሔር ከወንጌል ብስራት በፊት ከአጠቃላይ መገለጥ ከተገኘ እውቀት በመነሳት የሁሉ

ፈጣሪ የሆነ አንድ ሁሉን የሚገዛ አምላክ አለ፥ እርሱም:- "መገኖ" ይባላል ተብሎ ይታመን ነበር:: ወንጌል ወደዚህ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከገባ በኋላም ለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ለተገለጸው አምላክ ስያሜ የብሔሩን መጠሪያ "መገኖ" የሚለውን ቃል መጠቀሙና ማንነቱ በግልጽ ማሳወቁ አስፈላጊ ሆኗል::

«እግዚአብሔር» ወደሚለውና ከግዕዝ ወደ አማርኛ ስያሜ ስንመጣም አንድ ቀን እመኖሪያ ቤቴ ግቢዬ ውስጥ ሳለሁ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ የእስልምና ሃይማኖት ሰባኪ የሰማሁትን ትርጓሜ አልረሳውም:: ይህ ሰው ለሰበካ ሲዞር እኔ ወዳለሁበት ቤት መጥቶ ድንገት በር ያንኳኳል:: እኔም ከዚህ ሰው ጋር መነጋገር ስጀምር ወደ መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር እውነት አመራሁት:: እርሱ ግን የሚያምነው በአላህ እንደሆነና «እግዚአብሔር» የሚለውን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተወረሰውን ቃል ፍቺ «ግዛ–ብሔር» ማለትም "ብሔርን ግዛ!" የሚል በመሆኑ የአንድ የአማራ ብሔር ገዢ ስለሆነ ይህን ስም ለአለማት ፈጣሪና ለሁሉ ገዢ መጠቀም፥ በዚህም ስም የሚጠራውንም ማመን በአንድ ብሔር ገዢ እንደማመን እንደሚቆጥረው ገለጸልኝ:: የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በዚህ ስም ትርጉም ላይ መጠነኛ ጥናት ለማድረግ በመሞከር የደረሰኩበትን ድምዳሜ ክርስቶስ ፍጹም መለኮት (ራሱ እግዚአብሔር) መሆኑን በማንሳት በሚደረገው በዚህ ርእስ ገለጻ ስር ማስፈር አስፈላጊ እንደሆነ አሰባለሁ::

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በርካታ ኃይማኖታዊ ቃላትን ለህዝብ ያስተዋወቁት «ዘጠኙ ቅዱሳን» በመባል የሚታወቁትና በ480ዓ.ም ከተለያዩ አገሮች የአሃዱ ባህርይ ባህል ተከታዮች በመሆናቸው ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የሃይማኖት አባቶች እንደሆኑ ይታመናል:: ምንም እንኳን ይህ እግዚአብሔር የሚለውን ስያሜ ጅማሬ በማንና እንዴት እንደሆነ ካመሳከርኳቸው የታሪክ ማስረጃዎች መገንዘብ ባልችልም በትርጉም አንጻር ግን ምን ማለት እንደሆነ ሁለት የተለያዩ ግንዛቤዎችን መጥቀስ ይቻላል::

እግዚአብሔር የሚለው ስም የሁለት ቃላት ጥምረት እንደሆነና "እግዚ" ማለት ጌታ ሲሆን "ብሔር" ማለት ሕዝብ ማለትም በስፋት አለማትን አመላካችነትም እንዳለው ለመረዳት ችያለሁ:: በዚህ መሰረት ጥምር ቃላቱ የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ማለት "የአለማት ገዢ (ጌታ)" ማለት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ወደ ሦስት ጥሬ የግእዝ ቃላት በመክፈል «እግዚ» ማለት ጌታ፥ «አብ» ማለትም አባት እና «ሔር» ማለት ሰራጺ ማለት ሲሆን በአጠቃላይ ወልድ፥ አብና መንፈስ ቅዱስን አመላካች ሆኖ "ጌታ" የሚለው ወልድን፥ "አብ" የሚለው እግዚአብሔር አብን እና

«ሔር» የሚለው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከአብ የሰረጸ እንደሆነ የምታምነውን መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክት በመሆኑ እግዚአብሔር ማለት አብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማለት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::


እንግዲህ ይህ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በመጀመሪያው ትርጉሙ በብሉይ ኪዳን ዘመን በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ሳይውል እንደማይቀር ለመገመት የሚያስችለን ኢትዮጵያ ብሉይን አስቀድማ የተቀበለች ሀገር መሆኗን ታሪክ ማመላከቱ ማስረጃ ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ በተለይ ሁለተኛው ትርጉም ሥላሴን የሚያመለክት ግልጽ ሀሳብ ኢትዮጵያ አስቀድማ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይዛ ነበር ማለቱ አዳጋችና አወዛጋቢም ነው:: «ቃል እግዚአብሔር ነበረ::» የሚለው የዮሐንስ አገላለጽ ከመጀመሪያው ትርጉም አንጻር ለማለት የታሰበ ቢሆንም ይህ ትርጉሙ «የዓለም ጌታ» የሚለው የብሉይ ኪዳን ዘመን ስያሜ ከሆነ ለአብ ሳይሰጥ አይቀርም:: ምናልባትም በቀድሞው የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ ኤሎሂም እና ያሀዌ የተሰኙት ሁለቱም የዕብራይስጥ ስያሜዎች እግዚአብሔር ተብለው መተረጎማቸው ስያሜው ስለ ሥላሴ የሚገልጽ ሃሳብን የሚያካትት ለመሆኑ አጠያያቂ ነው::

በአዲስ ኪዳን ዘመን የወጣ ስያሜ ከሆነ ደግሞ በግልጽ ለአብ ÷ ለሥላሴ ብሎም ከስላሴ (ከአብ÷ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ) ረቂቅ አካላት ለአንዱ ወይም «ፍጹም አምላክነትን» ለመግለጽ የታቀደ መሆኑን በአሁኑ ወቅትም በዚህ እግዚአብሔር በሚለው ስም ያለውን አጠቃቀም በመመርመር መረዳት ይቻላል:: እንግዲህ "ቃልም እግዚአብሔር ነበረ::" ማለት አካላዊ ቃል በዘላለማዊ ግንኙነቱ ፍጹም አምላክ (ከአብ የማያንስ ነገር ግን እኩል መለኮት) ነበር ማለት ነው::

ይህ የአካላዊ ቃልን ፍጹም አምላክነት በግጻዊ መለኮት ለማስረዳት በርካታ ማብራሪዎች ቢኖሩም እያንዳንዱ ምሳሌያዊ አገባብ ወይም ማብራሪያ ግን ያለ እንከን አይደለም:: ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ ምድራዊ ማብራሪያ ከአእምሮ በላይ የሆነውን እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መግለጥ ባለመቻሉ ነው:: እዚህ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተርዮ እግዚአብሔር እንደሚያይ÷ እንደሚሰማና እጁም ከማዳን እንዳላጠረች ይገልጽልናል:: ይህ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሁለት አይኖች÷ ሁለት ጆሮዎችና ሁለት እጆች አሉት ማለት እንዳይደለ የሚያመላክተን እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ ስለ ሚያስተምረን ነው::

በዚህ መንገድ እግዚአብሔር በሰው ቋንቋና ባህል ራሱን ለሰው መግለጹ በራሱ ከመገለጽ የሚያልፈውን የእርሱን ማንነት ውሱን በሆነ መገለጫ ለሰው ግልጽ ሊሆንና ሰው ባለው የአካሉ ክፍል÷ ጠቀሜታውን ባጣጣመው ነገር ለማስረዳት የተደረገ ነው:: በግጻዌ መለኮት ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ከሚሰጡ ማብራሪያዎች አንዱና በተሻለ መልኩ ይህን የወልድን (የአካላዊ ቃልን) ፍጹም አምላክ መሆን የሚያብራራ ÷ ከረቂቅ አካልነት እንዲሁም ከግብርም አንጻር ያለውን ልዩነት የሚያሳየን የሚከተለው ማብራርያ ነው:-


የእግዚአብሔር አንድም ሦስትምነት (Triunity) ማብራሪያ: -




እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው ማብራሪያ መሠረት የእግዚአብሔር ልጅ (ወልድ) በግጻዌ መለኮት አቻ አምላክ ይኸውም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮት እኩል ወይም ያው እግዚአብሔር ነው:: ነገር ግን በአብ ዘንድ የራሱ ረቂቅ አካል እንደሆነና በዚህም ረገድ ወልድ ማለት አብ እንዳይደለ ማስተዋል ያሻል:: ስለዚህ አካላዊ ቃል (ወልድ) ከአብ ጋር አቻ መለኮት (ፍጹም አምላክ) ነው:: የአብ÷ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሦስትነት የየራሳቸው ረቂቅ አካላት የመሆንና የግብር ልዩነት እንጂ የመለኮት መለያየት ወይም መበላለጥ አይደለም::

እዚህ ላይ ደግሞ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን መስተጋብር (Interpersonal Relationship) ለማስገንዘብ የሚከተለውን ማብራሪያ መመልከት ይጠቅማል:-

የእግዚብሔር አንድም ሦስትምነት (Tri-une God)




ከላይ በሠፈረው መግለጫ መሠረት አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እንዳለ÷ ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ እንዳለ÷ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ እንዳለ ያመለክተናል::

### 1.1.6. አካላዊ ቃል በመልዕክተኛ አምሳያ (በአርአያ መልአክ) ተገልጧልን?

ኢትዮጵያውያን የሥነ መለኮት ሰዎች የአካላዊ ቃልን በመልአክ አምሳያ መገለጽ እንደሚቀበሉ መናገር የማይቻል ይመስላል:: እንዲያውም የመላዕክትን አምልኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮት እንደሆነ ለማስተማር በሌሎች የሥነ መለኮት መምህራን ዘንድ የወልድ ቅድመ ትሥጉት አካል በመልዕክተኛ አምሳያ መገለጥን (Theophany) እንደሚያመለክቱ የሚናገሩባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ፍጡራን መላዕክትን አመላካች ያደርጓቸዋል:: ይህ የአካላዊ ቃል የመልዕክተኛነት ግብር አካላዊ ቃል ከአብ እኩል÷ ዘላለማዊ የአብ የባሕርይ ልጅ ማለትም ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ከዘላለም በግጻዌ መለኮት ባለው ግንኙነት ለአባቱ ይላክ (መልዕክተኛ ሆኖ) ወደ ምድር ይመጣ እንደነበረ ያመለክተናል የሚለውን የሥነ መለኮት አቅጣጫ በሚከተሉቱ መምህራን በኩል የሚስተጋባ ነው::

ይህንን ሀሳብ ስናነሳ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነና ከመላእክትም ሆነ ከሰው ልጆች የተለየ ምልአተ ህልውና (ረቂቅ አካል) እንዳለው መረዳት እንችላለን:: "ረቂቅ አካል" ነው ከሚለው ትምህርት አንጻር የአካላዊ ቃል ወደ ምድር መምጣት በቅድመ ትሥጉት አካል እንዴት ሊሆን እንደሚችል የሚያጠያይቅ ነው:: የድኅረ ትሥጉት አካል

ክርስቶስ ሲናገር እርሱን ማየት አብን ማየት እንደሆነ ገልጿል (ዮሐ14:9)። ዮሐንስም በሰጠው ምስክርነት እግዚአብሔርን አይቶ የሚያውቅ እንደሌለ አንጸባርቋል (ዮሐ1:18)። *ታዲያ* በቅድመ ትሥጉት ቃልን አይቶ የሚያውቅ አለ ማለት ነውን? አካላዊ ቃል የሚታይ ከሆነስ በምን አይነት መልክ? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው።

አካላዊ ቃል (እግዚአብሔር ወልድ) በብሉይ ኪዳን ዘመን በመልእክተኛ ነት ይገለጽ ነበር የሚለው አመለካከት አንዱ የሥነ መለኮት ሰዎች የሚከራከሩበት ነጥብ ነው። የአካላዊ ቃልን በመልዕክተኛ አምሳያ ወደ ምድር መምጣት የሚያምኑቱ በግጻዊ መለኮት ያለው የግብር ልዩነት በትሥጉት አካል መንሥኤ ሳይሆን ዘላለማዊ መሆኑን መረዳት እንደሚያሻ ያስተጋባሉ። የትሥጉት አካል ክርስቶስ ከአብ ተልኮ መምጣቱን እንደሚጠቅስ ሁሉ የአብ የላኪነት ግብርና የአከላዊ ቃል (የወልድ) የመልእክተኛነት ግብር በብሉይ ኪዳንም በስፋት እንደተጠቀሰም ያመላክታሉ። ምናልባት ይህ አባባል ብሉይ ኪዳን በአብ÷ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን መለኮታዊ ግንኙነት ፍንትው አድርጎ ይገልጻል ማለት ነውን? የሚል ጥያቄን ሳይቀሰቅስብን አይቀርም። ምንም እንኳን በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር አንድም ሦስትምነት (Tri–unity) በአጠቃላይ መልኩ ቢጠቀስም በአርአያ መልአክ የተገለጸውን አካል ማንነት ሲገልጽ ራሱ "ያህዌ" አነባበቡ እስከ ዛሬም በትክክል የማይታወቅና አናባቢዎች ከሌሉት Y H W H (የ - ሐ - ወ - ሐ) ከሚሉት አማርኛ ፊደላት ተመሳሳይ ድምጽ በሚሰጡ የእብራይስጥ ፊደላት ተጽፎ እንደነበረ መረዳት ይቻላል።

በመልእክተኛነት (በአርአያ መልአክ) የተገለጸው አካል ማንነት ራሱ እግዚአብሔር «ያህዌ» መሆኑን የሚያመላክቱና ያ መልእክተኛ (መልአክ) አምልኮን እንደተቀበለ የሚገልጹ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ለአብነት ያህል ስንመለከት:– በዘፍ 16:7-14 ባለው ለሦራ አገልጋይ ለአጋር የተገለጸውን መልእክተኛ (መልአክ) እርሷ ራሷ ስታስረዳ «ኤልሮኢ» ማለቷ ያያትን ያየችው የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ በመገለጹ እንደሆነ ገልጻለች። በሌላ በኩል በዘፍ 31:11-13 ባለው ክፍል ደግሞ ለያዕቆብ የተገለጸው መልእክተኛ (መልአክ) ስለት የተሳልክልኝ አምላክ ነኝ በማለት ስለ ራሱ ተናግሯል። በዘጻ 3:14 ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር መልአክ (መልእክተኛ) በሚነድ ቁጥቋጦ መካከል እንደታየው እና ሙሴ ማን ነህ ብሎ ሲጠይቀው *ያህዌህ* «ያለና የሚኖር....» ነኝ እንዳለው እንመለከታለን። በዘጻ 33 ላይ እንዲሁ ስንመለከት «ያህዌ» ህዝቡ አንገተ ደንዳና በመሆኑ ምክንያት በመቆጣቱ ከፍጡራን መላእክት አንዱን እንደሚልክ እንጂ ራሱ (በአርአያ መልአክ) አብሯቸው እንደማይወጣ ተናግሯል።

እንግዲህ እነዚህን የሚመስሉ በግልጽ በአርአያ መልአክ የተገለጠ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን የሚያመላክት ክፍልን በመጥቀስ የመላእክትን አምልኮ ማስተናገድ ከትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽንሰ ሃሳብ የራቀ ከመሆኑም በላይ በብሉይ ኪዳን በመልእክተኛ አምሳያ የተገለጸውንና ከአብ በዘላለም ግንኙነቱ የመልእክተኛነትን ግብር ግብሩ ያደረገውን አካላዊ ቃል (ወልደ እግዚአብሔር) ማንነት የሚቃረን አስተሳሰብ እንደሆነ ይናገራሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ልንመለከት የሚገባን በእነዚህ ክፍሎች የምናገኘው መልእክተኛ (መልአክ) እንደ ፍጡር መላእክት ምናልባትም በኢሳ 6 ላይ እንደምናገኛቸው እንደ ሱራፌል ባለ ስድስት ክንፍ እንደሆነ አመላካች ጽንሰ ሀሳብ አለመኖሩን ነው:: በተጨማሪም ወልድ በአርአያ መልእክ በተገለጸባቸው ክፍሎች አምልኮ መቀበሉን እንመለከታለን::

## 1.2 ድኅረ ትሥጉት (ድኅረ ሥጋ መሆን)

በሥነ መለኮቱ አለም ክርስቶስ ማን እንደሆነ በሚደረገው የእውነት ፍለጋ ቅድመ ሥጋ መሆን ብቻ ሳይሆን ድኅረ ሥጋ መሆን በጥልቀትና በስፋት መዳሰስ ያለበትና በክርስቶስ በኩል ለሰው ዘር ለተደረገውም ታላቅ የማዳን ሥራም መሰረት ነው:: ስለዚህም ክርስቶስን በትክክል ከማወቅ ውጪ የድነትን ጽንሰ ሀሳብ ሙሉ ለሙሉ መረዳት አይቻልም::

ቅድመ አለም ራሱ እግዚአብሔር የሆነውና ከእግዚአብሔር ሦስቱ ረቂቅ አካላትነት (persons) አንዱ አካላዊ ቃል (ወልድ) የሰውን ልጆች ለማዳን ወደ ምድር የመጣበትን አመጣጥ፥ ከዚያ በኋላ የእርሱን ማንነት መቃኘትም ያሻል:: በግእዙ ትሥጉት (ሥጋ መሆን) የአካላዊ ቃል ሰውን ለማዳን ወደምድር መምጣትን ለማመልከት ከምንጠቀምባቸው አገላለጾች አንዱ ነው:: በዚህ አገላለጽ ምንነት ዙሪያ በጥልቀት ለመመልከት ከመሞከራችን በፊት የአካላዊ ቃል (የወልድ) ሰውን ላማዳን ወደምድር መምጣትና ከድንግል ማርያም መወለድ በግልጽ የሰፈረበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል «ቃልም ሥጋ ሆነ» (ዮሐ 1:14) ማለት ምን ማለት ነው? ቃል ሥጋ ለበሰን? ወይስ ሰው ሆነ?

### 1.2.1. «ቃልም ሥጋ ሆነ»:- ሥጋ ለበሰ? ወይስ ሰው ሆነ?

ሐዋርያው ዮሐንስ ከአካላዊ ቃል በግሪኩ አጠራር (ሎጎስ) ዘላለማዊ የግጻዌ መለኮት ግንኙነት በመነሳት ወደ ማዳን ሥራው አመጣጡ ያመራል:: ሰውን ለማዳን የመጣበትን አመጣጥ ሲገልጽም «.... ቃልም ሥጋ ሆነ» ይላል:: እዚህ ላይ በሥነ መለኮቱ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሞላበት ምርመራን የሚሻ ጽንሰ ሀሳብ እንዳለው ማስተዋል

ያስፈልጋል:: በተለምዶ የምንጠቀምበት «ሥጋ መልበስ» የሚለውን ሀሳብ ስንገመግመው የአገላለጽ ድክመቱ ቃል (ሎጎስ) ቁሳዊ ያልሆነውን የሰው ክፍል ሲይዝ ቁሳዊ አካሉ ደግሞ ቃል እንደ ልብስ የተጎናጸፈው የሰው ሥጋ እንደሆነ አመላካች ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ የክርስቶስ አካል (person) የማን ነው? የሰው ወይስ የቃል (የሎጎስ)? ለመሆኑ «ቃልም ሥጋ ሆነ» ማለት «ሥጋ ለበሰ» ወይስ «ሰው ሆነ» ማለት ነው?

የቃልን ሥጋ መልበስ የሚያስተጋባው ሀሳብ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ እንደሆነ ከማመልከት ይልቅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ የሰውን ሥጋ የሚታየው ቁሳዊ አካሉ አድርጎ እንደመጣ ወደ ማመልከት ፈቀቅ ያለ ሀሳብ ነው:: ይህንን ሃሳብ በተሟላ መልኩ የክርስቶስን ሰው መሆን በምንናነሳበት ክፍል ውስጥ እንመለከተዋለን:: በሌላ በኩል ደግሞ «ቃልም ሥጋ ሆነ» ማለት ሰው ሆነ ማለት ከሆነም የሚያስነሳው ጥያቄ አለ:: ለመሆኑ ቃል ሰው ሆነ ማለትስ የሚቻለው እንዴት ነው? ሥጋ፥ መንፈስና ነፍስ ያለው መሆኑን ለማመልከት ወይስ አምላክነቱን ትቶ ሰው ብቻ ሆኖ መምጣትን? ወይስ ደግሞ አምላክ ሲሆን ሳለ ሰው መሆንንም መጨመርን? ታዲያ ረቂቅ አካልነቱ (person) የማን ነው? የቃል (የሎጎስ)?፥ የሰው? ወይስ የቃልም የሰውም? ወይስ የቃል-የሰው ጥምረት? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ከመነሳታችን በፊት «ቃልም ሥጋ ሆነ» ተብሎ የተነገረለት አካል የተጠራባቸውን ስሞች አስቀድሞ ከትርጉማቸው አንጻር መመልከት አስፈላጊ ነው::

### 1.2.2. ስመ ሥጋዌ (የቃል ሥጋ መሆን) ስሞቹ:-

ስም የማንነት መገለጫ ሆኖ ያገለግላል:: ሥጋ የሆነው አካላዊ ቃልም ቅድመ አለም ከነበረው መጠሪያ ውጪ በአዲስና በበርካታ ስሞች ተገልጿል:: እነዚህን የትሥጉት ስሞች አንድ በአንድ ትርጉማቸውን መመልከት አስፈላጊ ነው:: ስድስት የትሥጉት አካል ስሞችን ከመገለጫ ግብራቸው አንጻር በሚከተሉት ሦስት ነጥቦች ስር እንመለከታቸዋለን:: እነርሱም:- *የአዳኝነት፥ የሹመቱ* እና *የማንነቱ መገለጫ* ስሞች ናቸው::

#### 1.2.2.1. የአዳኝነት ስሞቹ:-

##### ሀ. ኢየሱስ

በማቴ 1:21 እንደተጠቀሰው በጌታ መልአክ አማካይነት ለድንግል ማርያም ብስራት ሲደርሳት ለተወለደው ሕጻን የተሠጠ ስም ነው::

የዚህ ስም አወጣጥንና የተሰጠበትን ምክንያት ስንመለከት ህዝቡን ከኃጢአታቸው ከማዳኑ ጋር የተያያዘ እንደሆነ እንረዳለን:: በህዝቡ ዘንድ በወቅቱ የሚታወቅበትና የሚጠራበት ስም በመሆኑም የግል መጠርያውና መታወቂያስ ስሙ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: ይህ ከስመ ሥጋዊ ወይም ከትሥጉት ስሞቹ የአዳኝነት ስሙ ነው:: በተለይ በወንጌላት ውስጥ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት ከመሞቱ በፊት በህዝብ ዘንድ የሚታወቅበትና የሚጠራበት ሥም ነበር:: የዚህን መጽሐፍ ሥነ ጽሑፍ በማረም ካገለገሉኝ ወንድሞች አንዱ "ዛሬስ ኢየሱስ ተብሎ አይጠራምን? ስለምን 'ነበረ' ትላለህ?" የሚል አስተያየቱን ሰጠኝ:: የሚገርመው ግን የሥነ ጽሑፍ ችግር ያለበት ሳይሆን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምሬዎች ዘንድ የመሲህነት ተግባሩ ከመገለጡ በፊት "ኢየሱስ" በሚል ስም መጠራቱ፥ ይህንን ስም ከትንሳኤው በኋላ ባብዛኛው ያለመጠቀሙና ደቀመዛሙርቱም በዚህ ስም አዘውትረው ያልጠሩበት መሆኑ እንዲሁም ከወንጌላት ውጪ በስፋት አለመጠቀሱ ትኩረት ይሰጥበታል::

በዚህም ምክንያት ጸሐፊያኑ በወንጌላት ውስጥ በተገለጠና ያደረጋቸውን ነገሮች ለመጀመሪያዎቹ ተቀባዮች ሲያስተላልፉ በህዝብ ዘንድ ይታወቅበት በነበረው የግል መጠሪያ ስሙ እንደተረኩት እንጂ ከትንሳኤውም በኋላ "ኢየሱስ" ተብሎ መጠራቱ አግባብ እንዳይደለ ይናገራሉ:: ስለዚህም የአለም ሁሉ አዳኝ መሆኑን አበክሮ ለመግለጽ 'መድኃኔዓለም' የሚልን ስም ይጠቀማሉ:: ከዚህ በተጨማሪ 'ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ' ብሎ መጥራቱ የማዳን ስራውን አጠናቅቆ በአብ ቀኝ ለተቀመጠው ጌታ ተገቢ መገለጫው እንደሆነ አለያ ግን 'ኢየሱስ' ብሎ መጥራቱ ቤዛነቱን የማያካትት ስያሜን መጠቀም እንደሆነ በመምሬዎች ዘንድ ይንጸባረቃል::

## ለ. አማኑኤል

በማቴ 1:23 መሰረት ከትሥጉት ስሞቹ ውስጥ ሌላው ስሙ «አማኑኤል» የሚል ነው:: ይህንን ስም በመጠሪያነት እንደተጠቀመበት አመላካች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ባይኖርም በነቢዩ በኢሳይያስ አስቀድሞ የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን እንመለከታለን (ኢሳ 7:14 ከማቴ 1:23 ጋር ይነጻጸር):: አማኑኤል የሚለው ስም ትርጉም በግልጽ እንደተጠቀሰው «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» የሚል ነው::

ከዚህ የተነሳ ይህ ስም የሚገልጸው የአካላዊ ቃልን ሥጋ መሆንና በሰዎች መካከል ማደር በመሆኑ የትሥጉት ስሙ ነው:: አማኑኤል የሚለው ስሙ አካላዊ ቃል እንዴት ሥጋ እንደሆነ ስናወሳ ፍጹም

አምላክ የሆነው አካላዊ ቃል (ወልድ) ሰውንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ (ለማገናኘት) መካከለኛ (ብቸኛ) ሆኖ የመጣበትን አመጣጥ የሚተርክ ስያሜ ነው:: ይህ ስም በሃገራችን *የተዋሀደ ስሙ* መሆኑን በመግለጽ *ሥጋ* መሆን ሰው መሆንን እንደሚያመለክት ይናገራል (1ጢሞ 2:5÷ እብ 12:24):: ሆኖም ግን ይህ ስያሜ «አማኑኤል» ከዮሐ 1:14 ባልተለየ የአካላዊ ቃልን *ሥጋ* መሆን አመላካች በመሆኑም የአካላዊ ቃል *ሥጋ* መሆን የማለትን ምንነት በጥልቀት መመርመር ያስችል ዘንድ ለቀጣይ የጽሑፍ ክፍላችን ማቆየቱ የተሻለ ነው:: ሌላውና ስለ ስሞቹ ስናነሳ በአጽንዖት ልንመለከታቸው የሚገቡን የትሥጉት ስሞቹ ክፍል የሚሆኑት *የሹመት* ወይም *የማእረግ* ስሞቹ ብለን ልንጠራቸው የምንችላቸው ናቸው::

### 1.2.2.2. የሹመት ስሞቹ:-

### *ሀ.* ክርስቶስ

በብሉይ ኪዳን ለተለያዩ አገልግሎቶች ሰዎች ይሾሙ ነበር፤ ይህ ሹመት ደግሞ ለክህነት (ዘፀ 39:30 ÷ 40:12-16) ÷ ለነቢይነት (1ኛነገ 19:16) እና ለንግስና (1ኛ ሳሙ 10:1፤11:15፤16:1-3 1ነገ 1:1:30-40፤2ነገ 9:3) ነበር::

*ታዲያ የአካላዊ ቃል ሥጋ መሆን የሹመት ስም* የሆነው «ክርስቶስ» የሚለው ስያሜ ከድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደልን ወልድ የትስጉት አካል በእብራይስጥ መሲህ÷ በአማርኛ የተቀባ (የተሾመ)÷ በግሪኩ ክርስቶስ ተብሏል:: ይህ ስም መቀባቱን ማለትም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይኸውም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለመግባትና የመዋጀትንና የማስታረቅን ተግባር ለመፈጸም መሾሙን ገላጭ ነው (ሉቃ 1:35፤ማቴ 3:16፤16:16):: ይህ ስም በተለይ በመልእክታት ውስጥ ከትንሳኤ በኋላ ያለውን የኢየሱስን ማንነት የሚገልጥ ሆኖ በስፋት ተጠቅሷል:: አንዳንዶች እንደሚሉት ኢየሱስ የተባለ ሰው ሲጠመቅ በእርሱ ላይ ክርስቶስ ስለወረደበት የተሰጠው ስም አይደለም:: በስሙ ረገድ ያለ የመረዳት መዛባት ከአስተምህሮት ጥመትም ሆነ ከግንዛቤ ጉድለት ሊከሰት ይችላል:: በአንድ ወቅት ለአዲስ አማኞች የሚሰጥ የክትትል ትምህርትን ሳስተምር ለተማሪዎቼ አንድ ጥያቄ አቀረብኩ:: ጥያቄው:- "የኢየሱስ አባት ማን ነው?" የሚል ነበር:: ከአንድ ተማሪዬ የተሰጠኝ ምላሽ አስደነገጠኝ:: መልሱ "ክርስቶስ ነው!" የሚል ስለነበር ነው:: በአዲስ ኪዳን በተለይ በሐዋርያት ሥራና በመልእክታት ውስጥ ከትንሳኤ በኋላ ኢየሱስና ክርስቶስ የሚሉት ሁለቱ ስሞቹ በጥምረት ይገኛሉ:: ከዚህም የተነሳ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ወይም "ክርስቶስ ኢየሱስ" በመባል ተጠርቷል::

ይህ የሁለት ስሞች ጥምረት የእርሱና የአባቱ ስም በኢትዮጵያ ባህል መሠረት ለመጠሪያነት እንደምንገለገልበት ያለ ሳይሆን ኢየሱስ እርሱ የመሲህነት ግብሩን በመፈጸሙ ክርስቶስ እንደሆነ አመላካች ስያሜ ነው ።

### ለ. ጌታ

ከማርያም በሥጋ የተወለደልን እግዚአብሔር ወልድ ስልጣነ መለኮቱ በእግዚአብሔር መልክ መኖሩን ሳይለቅ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን እኩልነት (አቻ መሆን) ተነጠቅሁ ብሎ ሳይቆጥር ሥጋ ሆነ። ይህ ደግሞ ፍጥረታዊው ሰው አዳም አነሰኝ ብሎ የናቀውን በምስሉ እንደ ሰው በመገኘትና የበደሉን ካሳ በማቅረብ ዳግማዊ አዳምነቱን ያስመሰከረበት ነው። እንግዲህ ሰውን ከማዳን ተልእኮው አንጻር በባህርዩ የሁሉ ገዢ የመሆን ስልጣኑን እንደ መቀማት ባለመቁጠር አዳም በምድር ሁሉ ላይ ተሹሞ ሳለ በሠይጣን ያስወሰደውን ገዢነት አስመለሰ (ዘፍ 1:28፤መዝ 8:1-9፤እብ 2:6-9)። ጌታ የሚለው ስያሜ የክርስቶስን ከአብ ጋር አቻ ንግሥና ያለው መሆን አመላካች በመሆኑ በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ ነበር (ሮሜ 10:9፤1ቆሮ 12:3፤ፊል 2:11)። ይህ ስያሜ የክርስቶስ *የማእረግ ስሙ* ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህም የተነሳ የትሥጉት አካልን ማንነት ለማመልከት የሹመት (የማዕረግ) ስሞቹን ከግል መጠሪያ ስሙ ጋር በማጣመር መጠቀሙ ማለትም «ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ብሎ መጥራቱ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥበታል። ሆኖም የግል መጠሪያ ስሙን ማለትም ኢየሱስ የሚለውን ስያሜ በቅድመ ትንሣኤ የወንጌል ትረካ ሂደት መጠቀም የተለመደ ነው።

ሌላውና ወደ ቀጣዩ ነጥባችን የሚያመራን በትሥጉት ያለው ዘላለማዊው አካላዊ ቃል ራሱ ከማናቸውም ስሞቹ በላይ ስለ ራሱ ይገልጽባቸው የነበሩ የትሥጉት ስያሜዎች አሉ። እነዚህን ስሞች በህዝብ ዘንድ በመጠሪያነት የተገለገለባቸው ሳይሆኑ እርሱ ማንነቱን ያንጸባረቀባቸው ናቸው።

### 1.2.2.3. የማንነቱ መገለጫ ስሞቹ:-

### ሀ. የሰው ልጅ

አንዳንድ ጊዜ ስለ ወልድ በሥጋ ወደ ምድር መምጣት ያልተስተዋሉ ስህተቶች ሲሰነዘሩ ይታያል። ለመሆኑ ትሥጉት (የቃል ሥጋ መሆን) ሥጋ የሆነውን አካላዊ ቃል የሰው ልጅ

የሚያሰኘው ነውን? አኳኋኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው እንዴት ነው?

ለዚህ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያሳየን ከድንግል ማርያም በመወለድ ነው:: ቅድመ አለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው አካላዊ ቃል ድህረ አለም ደግሞ ከማርያም ተወልዷል (ማቴ 1:25፤ ሉቃ 2:6-7):: መጽሐፍ ቅዱስ የአካላዊ ቃል ሥጋ መሆንን ሲያብራራልን ማርያም እንደጸነሰችና እንደወለደችም ያመለክተናል:: ከዚህም በመነሳት እርሱ ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ይገልጽልናል (1ጢሞ 2:5፤ ሐዋ 2:22፤ ሮሜ 5:15፤ 17፤19 1ቆሮ 15:21፤47-49፤ 1ጢሞ 3:16፤ ገላ 4:4):: ከዚህ በተጨማሪ ኢየሱስ ራሱ ስለ ራሱ ሰው መሆን ተናግሯል (ማቴ 4:4፤ ሉቃ 24:39)::

ኢየሱስ ራሱን የሰው ልጅ በማለት ይጠራነበር (ዮሐ 6:62፤8:28):: ሆኖም ግን ይህ አጠራሩ በነቢዩ በዳንኤል የተነገረውንና የሚጠበቀውን ተስፋ አመላካች መሆኑን በማጣቀስ ሰው ሆኖ ስለ መጣ የወጣለት ስም ባይሆንም «የሰው ልጅ» በሚል መጠሪያ አስቀድሞ ስለ እርሱ እንደተነገረ መረዳት ይቻላል::

### ለ. የእግዚአብሔር ልጅ

በቅድመ ትሥጉት ስለ አካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለትም ወልድ መባል ተገልጿል መዝ (110):3 :: በድኅረ ትሥጉትም ስለ አካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ልጅነት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: ከማርያም በመወለድ ሰው የሆነው አካላዊ ቃል በትሥጉት የግል መጠሪያው:- "ኢየሱስ" ለእናቱ ለማርያም መልአኩ ሲያበስራት ከእርሷ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚባል ተናግሮአል (ሉቃ 1:35):: የኢየሱስ ደቀመዛሙርትም የእርሱን የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ተናግረዋል (ዮሐ 1:34፤ማቴ 16:16):: ኢየሱስም ስለ ራሱ ሲናገር የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ገልጿል:: አዳማጮቹም ይህን አባባሉን እግዚአብሔር ነኝ ከማለት ፈጽሞ ያልተለየ እንደሆነ ተገንዝበው ተቃውመውት ነበር (ዮሐ 5:18-24፤10:31-42):: ሆኖም ይህ ስም በሕዝብ ዘንድ የሚጠራበት ወይም የሚታወቅበት መለያው አልነበረም::

### 1.2.3. ክርስቶስ ፍጹም አምላክ (ራሱ እግዚአብሔር) ነውን?

በቅድመ ትሥጉት የወልድ ፍጹም አምላክነትን በተመለከተ በሰፊው ለማየት ችለናል:: ሆኖም ግን በቅድመ ትሥጉት ብቻ ሳይሆን በድህረ ትሥጉትም ከማሪያም የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ (ወልድ) ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን በጥንቃቄና በመጽሐፍ

ቅዱስ ማስረጃ መግለጽ አስፈላጊ ነው። አርዮስ ከቅድመ ትሥጉት ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት ወልድ የአብ ፍጹም ፍጥረት (የተከበረ አማልክት) እንደሆነ ያምን ነበር። አርዮስ በድኅረ ትሥጉት ሥጋ የሆነው ይህ የአብ ፍጹም የፍጥረት አካል ነው ብሎም ያምን ነበር።

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት አኳያ የክርስቶስን አምላክነት አበክሮ ለመናገር በሉቃስ 1:43 ላይ "... የጌታዬ እናት ..." የሚለውን ቃል በመመርኮዝ ለማርያም "የእግዚአብሔር እናት" በግሪኩ *ቲዮቶከስ* የሚልን ስያሜ ተሰጥቷት ነበር። ይህ ስያሜ በእስክንድርያ ባህል አስቀድሞ በ325 ዓ/ም በአንጾኪያ በተደረገው ጉባዔ አርዮስን በመቃወም በተግባር ላይ የዋለ ሲሆን ንስጥሮስ ይህንን ስያሜ በመቃወም የክርስቶስ እናት *(ክርስቶቶከስ)* መባል እንዳለባት በመግለጹ የክርስቶስን አምላክነት ከማደጎ ልጅ ጽንሰ ሃሳብ ለመከላከል በ 431 ዓ.ም በኤፌሶን በተደረገው ጉባዔም እንደገና ማጽኛ ተሰጥቶበታል።[7]

ለአርዮስ የድኅረ ትሥጉት አካል የሆነው ክርስቶስ በቅድመ ትሥጉት የአካላዊ ቃል አምላክነት ላይ እንዳለው እምነት ፍጹም መለኮት ሳይሆን (ራሱ እግዚአብሔር) ሳይሆን የተፈጠረ አምላክነት ነው። የአርዮስን አሰር (ፈለግ) ተከታዮች ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አላስተማረም÷ ደቀመዛሙርቱም ቢሆኑ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ግልጽ መረዳት አልነበራቸውም፤ ነገር ግን እንደ አይሁድ ራባይ (መምህር) ነበር የተከተሉት።" ብለው ሲናገሩ ይደመጣሉ። ለመሆኑ የኢየሱስ ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው እንዴት ነው?

### 1.2.3.1. ስለክርስቶስ አምላክነት ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች

በድኅረ ትሥጉት ስሞች የተገለጠው አካል ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን በቀጥተኛ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል። ነገር ግን የክርስቶስን ፍጹም አምላክ መሆን የማይቀበሉ የአርዮስ ተከታዮች እነዚህን ግልጽና ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ባብዛኛው አከራካሪ በሆነ መንገድ እንደተጠቀሰ ይናገራሉ። ነገር ግን ቢያንስ ስምንት የሚሆኑ ጥቅሶች የክርስቶስን መለኮትነት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የሚያመለክቱ መሆኑን በማስረጃነት መጥቀስ ይቻላል (ሮሜ 9:5፤ እብ 1:8፤ ዮሐ 1:1-2፤18፤ ዮሐ 20:28 ቲቶ 2:13፤ 2ጴጥ 1:1 እና ሐዋ 20:28)። ሆኖም እነዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ማስረጃዎች *New World Translation of the Holy Scriptures* እ.ኤ.አ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥር ወር 1961 በመቀጠልም እንደገና ታርሞ በ1970 በታተመው የአርዮስን

አሳብ በተከተለ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ የክርስቶስን ፍጹም እግዚአብሔር መሆን የሚያመለክቱትን እነዚህን ክፍሎች ከዮሐ 20:28 በስተቀር የትርጉም ልዩነት በማስጠት ግልጽ የሆነ ክህደትን አንጸባርቀዋል::

ከዚህም የተነሳ እነዚህ ክፍሎች አወዛጋቢነት አላቸው የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ:: ለመሆኑ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች እነዚህ አወዛጋቢ ብለው የፈረጇቸው ክፍሎች ብቻ ናቸውን? ኢየሱስ ራሱ ስለማንነቱ ሲገልጥ "እኔ እግዚብሔር ነኝ! ብሎ አልተናገረም÷ እውነተኛ አምላክ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ከማለት አይመለስም ነበር!" ለሚሉ የመከራከሪያ ነጥቦች ኢየሱስ የእርሱን ፍጹም አምላክነት ከማስተጋባቱ በላቀ መንገድ ከአብ የተላከበትን ተልእኮ በመወጣቱ (በግብሩ) እንዲገለጥ ወይም (ከአንደበት ይልቅ በስራ ራሱን መግለጥን) ይመርጥ እንደነበረ ተናግሯል (ዮሐ10:37-38)::

በዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ እንኳ "እኔና አብ አንድ ነን::" በማለቱ (ዮሐ 10:30)÷ አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩት እንደተነሱና የሚወግሩበትን ምክንያት ሲጠይቃቸውም በቁ.33 ላይ አይሁድ "ስለ መልካም ስራ አንወግርህም÷ ስለስድብ አንተም ሰው ስትሆን *ራስህን አምላክ ስለማድረግህ* ነው እንጂ ብለው መለሱለት" ይላል:: እንግዲህ አይሁድ እኔና አብ አንድ ነን ማለቱ እኔ ራሴ እውነተኛ አምላክ ከአብ ጋር እኩል መለኮት ነኝ ወይም እኔ እግዚአብሔር ነኝ ማለቱ እንደሆነ ተረድተው በድንጋይ ሊወግሩት እንደተነሱ አመላካች ክፍል መሆኑን እንረዳለን:: ለመሆኑ ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት ያልተረዳ ነበርን? ስለ ማንነቱ ሲናገር ምን አለ?

### 1.2.3.2 ኢየሱስ ስለ ራሱ ምን ይላል?

ኢየሱስ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ!" ብሎ በግልጽ አልተናገረም ለሚሉት መልሳችን «አዎን» የሚል አይደለም፤ ምክንያቱም የእርሱንና የአብን አንድነት መናገሩ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንደሚያመለክት አይሁድ ተረድተው ላደረጉበት ተቃውሞ ይቅርታ ያልጠየቀ በመሆኑ ነው:: ኢየሱስ ራሱ ፍጽም አምላክ (እግዚአብሔር) መሆኑን መናገሩ ባይሆንማ ኖሮ ንሰሃ ሳይገባ ትክክለኛ መሆኑን አበክሮ በመግለጽ መግፋቱና እንዲያውም ከአንደበት ይልቅ ስራዬ ይግለጠኝ የሚል ሆኖ መገኘቱ በራሱ ከእርሱ የማይጠበቅ በሆነ ነበር (ዮሐ 10:37-38):: ከዚህም በተጨማሪ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረባቸውን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስንቃኝ ለሰው ፈጽሞ ተገቢ ያልሆኑ መገለጫዎችን በመጠቀምና ከእግዚአብሔር የማያንስ መሆኑን

በመጥቀስ የፍጹም አምላክነት ይገባኛልን ወይም መብቱ እንደሆነ የሚያመለክቱ በርካታ ክፍሎችን እንመለከታለን:: ከእነዚህ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ከሚያስረዱ መግለጫች ውስጥ የሚከተሉት ይገኘ ብታል:-

1. ለሥራው የሚልካቸው መላዕክት እንዳሉት ተናግሯል:: እነዚህም መላዕክት የእግዚአብሔር መላእክት እንደሆኑ መረዳት ይቻላል (ማቴ 13:41፤ ሉቃ 2:8:9፤ 15:10) ::
2. ኃጢአተኞችን ይቅር የማለት ሥልጣን እንዳለው ተናግሯል (ማር 2:5):: በዚሁ ክፍል ላይ የሕግ መምህራን በእግዚአብሔር ላይ ስድብን መናገር ነው ያሉት ክርስቶስ ኃጢአትን የማስተሰረይ ስልጣን ያለው (ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ስለ ገለጠ ነው::)
3. ኢየሱስ የሰንበትን ትርጉም እንደገና የመስጠት መብት እንዳለው አስገንዝቧል (ማር 2:27-28)::
4. ኢየሱስ በዓለም ላይ እንደሚፈርድ ተናግሯል (ማቴ 25:31-46) ::
5. ኢየሱስ እርሱ እና አብ አንድ እንደሆኑ ገልጧል (ዮሐ 10:30) ::
6. ኢየሱስ እርሱን ማወቅ አብን ማወቅ እንደሆነ ተናግሯል(ዮሐ14:7-9)::
7. ኢየሱስ ከሠማይ የወረደ እርሱ ብቻ እንደሆነ ወደ ሰማይም የወጣ እርሱ ብቻ እንደሆነ ገልጿል (ዮሐ 3:13)::
8. ኢየሱስ ዘለዓለማዊ እንደሆነ ገልጧል (ዮሐ 8:58)::
9. ኢየሱስ የሚወደው ቢኖር ቃሉን እንደሚጠብቅ እርሱ እና አብ በአንድነት በአማኙ ዘንድ እንደሚኖሩ ገልጿል (ዮሐ 14:23)::
10. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ ትክክል መሆኑን ገልጿል (ማቴ 26:63)::
11. ኢየሱስ «ጌታዬ አምላኬም» ብሎ ቶማስ ሲጠራው ተቃውሞ አለማድረጉን አምላክ መሆን እንደተቀበለው ያረጋግጣል (ዮሐ 20:28)::
12. ኢየሱስ የተናገራቸው ቃሎች ከቃለ እግዚአብሔር (ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍት) ጋር በእኩል ደረጃ እንዳሉ አረጋግጧል (ማቴ 5:21-22 ፤27-28) ::
13. ኢየሱስ በሕይወትና በሞት ላይ ስልጣን ያለው /ዮሐ 5:21/ ÷ እንደ ያህዌ ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን ተናግሯል /መዝ (119)/
14. ኢየሱስ እንደ አብ ዘወትር በሥራ ላይ እንዳለ ተናግሯል /ዮሐ 5:2-18/:: ይህን አባባሉንም ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ (ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንደሆነ) እንደተናገረው አይሁዶች እንደተገነዘቡት እርሱም እንዳላመቻመቸ ቁ18 ላይ እንረዳለን::

15. ኢየሱስ ሁሉን የሚችል እንደሆነ ተናግሯል /ማቴ 28:18፤ ራእ 1:8/
16. ኢየሱስ ሁሉን የሚያውቅ እንደሆነ ተናግሯል/ማር 2:8 ዮሐ 1:48/
17. ኢየሱ በሁሉ ቦታ የሚገኝ እንደሆነ ተናግሯል /ማቴ 18:20፤ ማቴ 28:20፤ ኤፌ 1:23/::

ስለሆነ ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ካመለከተባቸው ሀሳቦች በተጨማሪ ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ማን ብለው አውቀውት ነበር? ለዚህ ጥያቄ መልሱን ለመስጠት ጌታን ያጋፉት ከነበሩ ከአያሌ ሰዎች÷ከሰባ ሁለት ደቀመዛሙርቱ÷አስራ ሁለቱ ሐዋርያት÷ ከሦስቱ ማለትም (የጴጥሮስ÷ ያዕቆብና የዮሐንስ) ከእነዚህ ሁሉ ለጌታ የበለጠ የተለየ ቅርበት ያለውና የልብ ወዳጅ እንደሆነ ጌታ ራሱ እንኳን የመሰከረለት «ጌታ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር» በመባል የተጠቀሰው ሐዋርያ ጌታን ማን ብሎ አውቆት ነበር?

### 1.2.3.3. የዮሐንስ (ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር) ምስክርነት

ጌታ ኢየሱስን ከተከተሉት በሙሉ "ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር" በማለት ስለ ራሱ የሚናገረው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው:: ዮሐንስ በጌታ እራት ስርአት ወቅት ሐዋርያው ጴጥሮስ እንኳን ጌታ የተናገረው ስለ ማን እንደሆነ እንዲነግራቸው የማለደውና ለጌታ ደረት የተጠጋ እንደሆነ የሚነገርለት ሐዋርያ ነው (ዮሐ 13:23-27):: ይህ ለጌታ ከሁሉ የቀረበ ሐዋርያ ስለ ጌታ ያለውን ግንዛቤ መረዳት መቻል የእርሱን ምስክርነት ከማንም በላይ ተቀባይነት ያሰጠዋል:: ለዚህም ታላቅ የሆነው ምክንያት ጌታ ራሱን በጥልቀት (በተለይ) ይገልጥላቸው ከነበሩት ከሦስቱ ሐዋርያት ውስጥ መሆኑና ከቡድኑም በተለየ መንገድ እንኳ ስለ ጌታ የሚገባው ያለው ወይም የሚያውቅ በመሆኑ ነው::

ታዲያ ይህ ደቀመዝሙር ስለ ጌታ በጻፈው ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌላውያን ማለትም ተመሳሳይ አቀራረብ ካላቸው:- ከማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ በተለየ መንገድ ከአካላዊ ቃል ዘላለማዊነትና በግጻዌ መለኮት ካለው ግንኙነት ይጀምራል:: የሌሎቹን ወንጌላት መግቢያ ሀሳብ ስንመለከት ግን ድኅረ አለም ከድንግል ማሪያም ከመወለዱ የምስራች በቀጥታ የሚጀምሩ ናቸው:: ታዲያ ይህ ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር በማለት ስለ ራሱ በመናገር በወንጌሉ ውስጥ የገለጠው ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ያለውን ምስክርነት

ከክርስቶስ ዘላለማዊ ማንነቱ  በመነሳት በዮሐ 1:1 ላይ መተረክ ይጀምራል::

ዮሐንስ በወንጌሉ መግቢያ ላይ ከቅድመ ትሥጉት ሀሳብ ይጀምራል:: የወንጌሉ ተቀባዮች እንዲሆኑ የሚነገርላቸውን አይሁድንም ሆነ አህዛብን በአንድነት በሚያግባባ የመነሻ ሀሳብ ላይ ያነጣጥራል:: ይህም ሀሳብ ስለ አካላዊ ቃል ወይም በግሪክ ቋንቋ ስለ «ሎጎስ» ነው:: ስለ አካላዊ ቃል ማንነት ለማስረዳት ሲነሳም የቃልን አካላዊነት ያልተረዱትን ተደራስያኑን ከጅማሬው ሳያስበረግግ እያግባባና እያሳመነ ማስረዳት ተያይዞታል:: ወንጌሉ የሚጀመረው "በመጀመሪያው ቃል ነበረ::" በማለት ነው:: ለመሆኑ ዮሐንስ በዚህ መግቢያ ወንጌሉን መጻፍ የጀመረው ለምንድር ነው?

ዮሐንስ «በመጀመሪያው» በማለት የወንጌሉን መግቢያ ማስፈሩ የመጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ማለትም የኦሪት ዘፍጥረትን መግቢያ እንድናስብ ያደርገናል:: በዘፍ 1:1 ላይ በመጀመሪያ በማለት እግዚአብሔር ከጊዜ በፊት ሰማይንና ምድርን መፍጠሩን ያመለክተናል:: ሙሴ በዘፍጥረት መጽሐፍ የአሮጌውን ፍጥረት መጀመሪያ ሲያስተዋውቅ ጊዜ ከመቆጠሩ በፊት የአለምን መፈጠር "በመጀመሪያ..." ብሎ መናገሩ የአሮጌውን ፍጥረት ጅማሬ ቢያሳይም ጅማሬ የሌለውን የአካላዊ ቃልን ዘላለማዊ ህላዌ ለማመልከት ዮሐንስ  ተመሳሳይ አገላለጥ  ተጠቅሟል:: ሆኖም ግን ይህ "በመጀመሪያው..." የሚለው ሃሳብ በዮሐንስ አገላለጥ ውስጥ ቅድመ አለም ማለትም አለም ከመፈጠሩ፤ ዘመን ከመቆጠሩ በፊት ይኸውም ከዘላለም የሚል ነው::

ዮሐንስ በመቀጠል የገለጸው «ቃል» (ሎጎስ) በማለት ነው:: ስለ ቃል (ሎጎስ) በአይሁድም ሆነ በግሪኮች (አህዛብ) ዘንድ የተደረሰበት መረዳት ነበረ:: ስለዚህም ዮሐንስ በወንጌሉ ስለ አካላዊ ቃል (ሎጎስ) መናገሩ የሁለቱንም ቡድኖች ቀልብ የሚስብ ነው:: ስለ «ቃል» (ሎጎስ) በአይሁድ ዘንድ የነበረው እምነት አንድ አምላክ የሁሉ ነገር ምንጭ እንደሆነ ቃል (ሎጎስ) ብጹእ ህላዌ ያለው፤ ነገር ግን እንደ ፍጡር አካል ጥገኛ እንደሆነ ነው:: በግሪክ ፍልስፍና ደግሞ "ቃል" (ሎጎስ) ሀሳብ ወይም ምክንያት ወይም ደግሞ ከሰው አንደበት የሚወጣና የሰውን ሀሳብ የሚገልጽ ማለትም ንግግር የሚል ትርጉም ነበረው:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በስድስተኛው ምእተ አመት የነበረው ሔራክልተስ የተባለ የግሪክ ፈላስፋ አባባል ቃል (ሎጎስ) ዘላለማዊ ነው:: ሁሉም ነገር በዚህ ቃል (ሎጎስ) ተገኝቷል:: እርሱ ከሁሉ የላቀ እውነታ አንዳንድ ጊዜ እንደ እሳት÷ አንዳንድ ጊዜ እንደ እግዚአብሔር÷ አንዳንዴ ደግሞ እንደ ቃል (ሎጎስ) እንደሆነ ያምን ነበር::

እንግዲህ በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ የሆነውን ፈቃድ የሚያስፈጽም (Efective Agent) እንደሆነ እንመለከታለን:: በመዝ (33):6 "በእግዚአብሔር ቃል ሠማዮች ጸኑ ሰራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ...." ይላል:: በዚህም የእግዚአብሔር ቃል መለኮታዊ ድርጊትን እንደሚፈጽም ያስረዳናል:: ከዚህ በመነሳት አይሁድ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች እንደጸኑ ÷ ግሪኮች (አህዛብ) ደግሞ ቃል ምክንያታዊ የሆነ ህግ እንደሆነ ሁለቱም የተፈጥሮ ህጎችን ቢገልጹም ሁለቱም ይህ ቃል የሁሉ ነገር መጀመሪያ እንደሆነ ይስማማሉ::

በመቀጠል ዮሐንስ የተጠቀመበት ሀሳብ «... ነበረ» የሚል ነው:: በመጀመሪያ ከሚለው አጠቃቀሙ በተጨማሪ «...ነበረ» ማለቱ ዘላለማዊነቱን እንጂ በጊዜ ውስጥ ቀዳሚ መሆኑን አያመለክትም:: ለዚህም ዋናው ምክንያት ቅድመ አለም የጊዜ ስሌት አለመኖሩ ነው ታዲያ ዮሐንስ ቅድመ አለም ማለትም "በመጀመሪያው ... ነበረ::" በማለት የገለጸው አይሁድም ሆኑ አህዛብ (ግሪኮች) በመስማማት ዘላማዊነቱን የሚመሰክሩለት ቃል (ሌጎስ) ነው::

ዮሐንስ "ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ::" በማለት ቃል ከእግዚአብሔር የተለየና በእርሱ ያለ መሆኑን አመላክቷል:: ይኸውም ቃል ከአብ ጋር ስላለው ግንኙነት ሲያመለክት በራሱ ልዩ አካል በግጻዊ መለኮት መኖሩን ይገልጻል:: እስከዚህ ነጥብ ድረስ አይሁድም ሆነ አህዛብ ትኩረት ሰጥተውትና በተመስጦ የሚከታተሉት በእነርሱም ዘንድ ያለውን አመለካከት የሚያስተጋባ በመሆኑ ነው:: ለዚህም ምክኒያቱ ዮሐንስ በቃል መሰረታዊ ሀሳብ ላይ ባለው ታሪካዊ ደሃራ ላይ ተመስርቶ ስለ ነበረ ነው::

ነገር ግን ዮሐንስ ቃል (ሎጎስ) ምክንያታዊ ህግ ሳይሆን ህያው ማንነት ያለው ወይም ረቂቅ አካልና የህይወት ምንጭ መሆኑን ÷ ማንነት ሳይኖረው በምሳሌ 8 ላይ ጥበብ ራሷን በገለጸችበት ማንነት ባለው መልክ (personification) ሳይሆን ማንነት ያለው (ረቂቅ አካል) ወይም (Person) እና ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ÷ የመለኮት መበላለጥ በሌለበት መንገድ «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» በማለት ገልጾታል:: ይህ አባባሉ ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ አስደንጋጭነቱ የማይካድ ነው:: ለዚህም ዋናው ምክንያት በእነርሱ ዘንድ ረቂቅ አካል (person) መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ባለመሆኑና "ማን" የሚባል ሳይሆን "ምን" የሚባል ተደርጎ ይቆጠር ስለ ነበር ነው:: ዮሐንስ ግን "ማን" የሚባል ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያለማወላዳት ገልጾታል:: በዚህም ዮሐንስ

የ«ቃል»ን አካላዊነት በመጥቀስ «አካላዊ ቃል» መሆኑን ዝርው (አካል አልባ) ቃል እንዳይደለ ተርኮታል::

በመቀጠልም ዮሐንስ "ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ::"(ቁ2) በማለት ከላይ የተጠቀሰውን እውነታ ያጠነካክረዋል:: በዚህም የአካላዊ ቃልን ዘላለማዊነትና ከአብ ጋር ያለውን የግጻዌ መለኮት ግንኙነት አበክሮ ገልጿል:: በቁ.3 ላይ ደግሞ:- "ሁሉ በእርሱ ሆነ ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም::" በማለት በቃልና በእግዚአብሔር አብ መካከል ከነበረው ግንኙነት፤ በቃልና በተፈጥሮ መካከል ወዳለው ግንኙነት ያመራል:: በዚህም ያለ ቃል የሆነ (ህልውናን ያገኘ) እንደሌለ በማለት እስከ ቁ.13 ድረስ ይህ አካላዊ ቃል ወደ ምድር መምጣቱን፥ አመጣጡም የሰውን ልጆች ወገኖቹ አድርጎ እንደሆነ፤ ነገር ግን ወገኖቼ ያላቸው ደግሞ እንዳልተቀበሉት ወይም እንዳላመኑበት፥ በእርሱ ላመኑቱም በእምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ልጅነትን ስልጣን እርሱ ራሱ እንደሰጣቸው ገልጿል::

በቁ.14 ላይ ደግሞ ቃል ወደ ምድር በመምጣት በሰዎች መካከል የተገኘበትን መንገድ ሲገልጽ «ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ ....» በማለት ወደ ዋናው የትሥጉት (ሥጋ መሆን) ሀሳብ ሲያመራ በአይሁድም ሆነ በአህዛብ ዘንድ አካላዊ ቃል መሆኑን ላልተረዱለትም ቃል ራሱ ሥጋ ሆኖ ወደ ምድር መምጣቱን ያወሳል:: እዚህ ጋ ዮሐንስ የተጠቀመበት አገላለጽ "ቃል ሥጋ ሆነ::" ሲል ቃል ሥጋ ለበሰ? ወይስ ቃል ሰው ሆነ ማለቱ ይሆንን? አሁንም የዚህን ሀሳብ ትክክለኛ ትርጉም ለመግለጽ የታሪካዊ ሥነ ክርስቶስ ጥናት የተሻለና ተገቢ ስፍራው ስለሆነ በዚህ ሀሳብ ዙሪያ የተካሄዱ የቤተክርስቲያን አባቶች ጉባዔዎችና አስተምህሮቶቻቸውን በሚያነጻጽረው በዚህ መጽሐፍ ክፍል ውስጥ ለማብራራት እሞክራለሁ::

ዮሐንስ በወንጌሉ ታላቅ ስፍራ የሰጠው ነገር ቢኖር የአካላዊ ቃል የትሥጉት መጠሪያው ኢየሱስ የሚለውን ስም በመጠቀም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ነው:: ይህንንም ከአይሁድ ለሚደርስበት ተቃውሞም ማለትም:- "ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር ስላስተካከልክ በድንጋይ እንወግርሀለን::" ብለው ሲነሱበት እንዳላመቻቸ በመመስከር ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነና በመለኮት እኩል መሆኑን አበክሮ ገልጿል /ዮሐ 5፡18-19፤10፡30-38/::

ከሐዋርያው ዮሐንስ በተጨማሪም ወንጌላዊው ማቴዎስ ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያቱን:- «....... እናንተስ እኔን ማን ትሉኛላችሁ?» ብሎ

ሲጠይቃቸው ሐዋርያው ጴጥሮስ፡- "አንተ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ።" ብሎ እንደመለሰለት ጠቅሷል (ማቴ 16:16)። ከዚህም የምንረዳው ሐዋርያው ጴጥሮስም ስለ ኢየሱስ ያለው መረዳት እንደ አንድ ረቢ (መምህር) ሳይሆን እንዲያውም የእግዚአብሔር ልጅ በማለት መመስከሩን ነው። የሁሉንም የጌታ ተከታዮችን ምስክርነት በዚህ ጽሁፍ ማካተት አስቸጋሪ በመሆኑ ሌላ አንድ ምስክርነት ብቻ በመቀበል ነገር በሁለት ምስክር እንዲጸና ማድረጉ የተሻለ ነው።

### 1.2.3.4. የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ እና የሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነቶች፡-

ከሐዋርያው ዮሐንስ ምስክርነት በመቀጠል የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊን መግቢያ መቃኘቱ አስፈላጊ ነው። ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የተረዳውን መቃኘቱ በቂ ቢሆንም መረዳታችንን ለማዳበር ይህንን የዕብራውያን መልእክት 1:1-3 ላይ ያለውን ክፍል አንድ በአንድ እንመለከታለን።

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ በመልእክቱ መግቢያ ላይ የክርስቶስን አምላክነት አበክሮ ያስገነዝባል። ለዚህም ገና በመጀመሪያው ቁጥር ላይ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የነበረው መገለጥ አድጎ ሙሉ እና ፍጻሜ ያገኘ እንደሆነና በዘመኑ መጨረሻ በልጁ በኩል እንደተናገረ ይገልጻል። በዚህ አገላለጹ ስለ ልጁ (ወልድ) ማንነት በቁ.2 እና 3 ላይ *ሰባት* ታላላቅ ገላጭ ሀሳቦችን በመጠቀም ይተርካል። እነዚህ ሰባት የልጁን ማንነት ያንጸባረቀባቸው ቃላት፡-

1. ...*ሁሉን ወራሽ ባደረገው* ... *ሥጋ* የሆነው አካላዊ ቃል (ክርስቶስ) የማዳንን ስራ በመፈጸም በብኩርና ደረጃ ላይ ሆኖ ሁሉን ወራሽ እንደሆነ የሚያመለክት ነው።
2. ... *አለማትን በፈጠረበት*... በዚህ አገላለጹ ከሐዋርያው ዮሐንስ እና ጳውሎስ ጋር በመስማማት እግዚአብሔር አለምን ሲፈጥር ሁሉን በ*ቃል* እንደፈጠረ ያመለክታል (ከዮሐ 1:3 እና ቆላ 1:16 ጋር ይነጻጸር)።
3. ...*እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና*... የፀሐይን ነጸብራቅ ከፀሐይ ለይተን እንደማናየው የልጁ ነጸብራቅ ከመለኮት ነጸብራቅ የሚለይ እንዳይደለ የሚገልጸው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።
4. ...*የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ*... ኢየሱስ የአብ የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ በመሆን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጥ እንደሆነ አሁንም ከዮሐንስና ከጳውሎስ ጋር በመስማማት ያብራራል (ዮሐ 14:9፤ ቆላ 1:15)። እዚህ ነጥብ ላይ ቅድመ አለም *ቃል* ከአብ መውጣቱ ወልድ እንዳሰኘውና ወልድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለመመልከት መሞከሬ ይታወሳል። ሆኖም ግን *ቃል* የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን

ቅድመ ዓለም ከአባቱ (ከአብ) መወለዱን እንጂ የዚህን አይነት ያለ እናት የሆነ ልጅነት ምንነት ግልጽ አልተደረገም።

በምድራችን የምናውቀው ከወንድና ከሴት በሩካቤ ዘበሥጋ በሚደረግ ግንኙነት አባትነትና እናትነት ላይ የተመሰረተ ልጅነት አለ። ከዚህም በተጨማሪ በጉዲፈቻ በሥጋ ያልወለዱትን ልጅ ለማሳደግ እናትና አባት ለመሆን ቃል ገብቶ በመውሰድ ላይ የተመሰረተ ልጅነትም አለ። የአካላዊ ቃል የአብ ልጅ መሆን ግን ከዘላለም ከአብ በመውጣቱና የአብ ትክክለኛ የባሕርይ ምሳሌ በመሆኑ ነው። ስለዚህም ይህንን አይነት ልጅነት *የባሕርይ ልጅ* ብለን ልንጠራው እንችላለን። ለማብራራት ያህል ለምሳሌ በግ የሚወልደው በግን እንጂ ፍየልን እንዳልሆነ፥ ሰውም ሰው እንጂ ጥጃን እንደማይወልድ ሁሉም ፍጥረት የባሕርዩን እንደሚወልድ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት የእግዚአብሔር ትክክለኛ ባሕርይ ያለው (የባሕርይ ልጅ) ማለት ነው። ስለዚህ ባሕርይ የትክክለኛ ማንነት መገለጫ ነው። ድኅረ ትሥጉት ክርስቶስም እንዲሁ የአብ የባህርዩ ምሳሌ ነው ሲል የባህርይ ልጅ ማለትም የአብ ባሕርይ የእርሱ ባህርይ የሆነና እርሱን ማየት የማይታየውን አብን መገንዘብ የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ መሆኑን አመላካች ነው (ከዮሐ 14:8-11 ጋር ይነጻጸር)።

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ በመቀጠል የሚያነሳው ነጥብ ከዘላለማዊው ማንነቱ፤ የማዳን ስራውን ለመፈጸም ወደሚያስችለውና በትሥጉት አካል ወደ ፈጸመው የወልድ ሚና ያመራል። ይኸውም:-
5\. *...ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ...* ኢየሱስ በቅድመ ትሥጉት አካል በእርሱ የተፈጠሩትን ሁሉ በአንድነት የሚደግፍና በፍጥረታት ላይ ታላቅ ሚና እንዳለው አመላካች ሃሳብ ነው። በዚህም በሥልጣን ከአብ ጋር እኩል መሆኑን ያመለክታል። በመቀጠልም በትሥጉት አካል የፈጸመውን ሲያነሳ:-
6\. *...ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ...* በሚለው ሀሳብ ደግሞ ሥርየትን ማስገኘት የሚችል ማንም ባለመኖሩ እና እርሱ ግን ከማንነቱ የተነሳ በራሱ የሰዎችን ሐጢአት ለማንጻት ብቃት ያለው መሆኑን አመላካች ነው። ከዚህም የተነሳ ልጁ ትሥጉት (ሥጋ የሆነበትን) በማንም መከናወን የማይችል የሥርየትን ጽንሰ ሃሳብ ይገልጻል። ይህ ደግሞ በተለይ የትሥጉት አካልን ማንነት ከግብሩ አንጻር ስንቃኝ የምናተኩርበት ይሆናል።
7\. *...በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀምጦ...* በዚህም ሃሳብ የድነትን ሥራ በመፈጸም በክብር ከአብ ጋር ባለው እኩል ንጉስነት ስፍራ እንዳለ ያመለክታል።

ከላይ የተጠቀሱት ሰባት ነጥቦች እያንዳንዳቸው የትሥጉት አካል በክርስቶስ፣ ራሱ እግዚአብሔር መሆን እና የመለኮት መበላለጥ ያለመኖር ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው:: በመቀጠል የዕብራውያን ጸሐፊ ልጁን (ወልድን) ከመላእክት ጋር በማነጻጸር ማንነቱን ያስረዳል:: ይህ ምናልባት በአይሁድ አማኞች ዘንድ በዘመናችን ራሳቸውን "የይሆዋ ምስክሮች" ብለው እንደሚጠሩት ሰዎች:- "ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል ነበር!" በማለት እንደሚሰብኩት ያለ እና ስለ ልጁ በተሳሳተ አመለካከት ከእግዚአብሔር የሚያንስ ደግሞም እንደ መልአክ ያለ እንደሆነ የተከሰተን የአመለካከት ውዥምብር ለማረም የተደረገ ማነጻጸሪያ ሳይሆን አይቀርም:: በማነጻጸሪያውም ወልድ የእግዚአብሔር ልጅነቱ የተለየ ስፍራ እንደሚያሰጠው እንዲያውም መላእክት ለእርሱ የሚሰግዱለት አምላክ እና ከእግዚአብሔር ጋር አቻ ንጉስ መሆኑን እንዲሁም ጌታ እንዲሁም ከጥንት አለማትን የፈጠረ መሆኑን በመጥቀስ ልጁ ከመላእክ በኩር (የላቀ) እንደሆነ ያብራራል:: በዚሁ መንገድ ከሙሴም ከካህናትም ጋር በማነጻጸር ልጁ (ወልድ) ከሁሉ በላይ የላቀ እንደሆነ በማተት ይህ ደግሞ እንደ ፍጡር ሰው ወይም ከመላእክት አንዱ ሳይሆን የሁሉ ጌታና ራሱ እግዚአብሔርነቱን ያስረዳናል::

እንግዲህ ለተጨማሪ ድጋፍ ሐዋርያው ጳውሎስ በፊል2:6 ላይ ያለውን *...በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም...* በማለት መግለጹን በመንተራስ አንዳንዶች መለኮትነቱን እርግፍ አድርጎ በሰማይ ትቶ ሰው ብቻ ሆኖ ወደ ምድር መጥቷል በማለት የትሥጉት አካል ክርስቶስ አምላክ አልነበረም ለማለት ሲሞክሩ ይደመጣሉ:: ጳውሎስ በዚህ ክፍልም ላይ *በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ* ማለቱ ራሱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ሰው መሆኑን ማለትም እግዚአብሔርነቱን በሠማይ ሳይተው ሰው እንደሆነ በዚህም የመለኮት ባህርዩን ሳይለቅ ለትስብእት (ለሰው) ያሉትን ግብሮች መፈጸም የሚያስችሉትን ባህርየ ትስብእት እንደወሰደ አመላካች ነው:: ስለዚህ ጳውሎስም በዚሁ የትስጉት አካል ክርስቶስ አምላክ ሲሆን (በእግዚአብሔር መልክ ሳለ) ለድነት ግብሩ ሲል ሰው እንደሆነ እንጂ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን አልካደም::

### 1.2.3.5. ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን የካዱ ታሪካዊ ኑፋቄዎች:-

ቤተክርስቲያን ገና ከጅማሬዋ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ትክክለኛውን መረዳት በአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተርዕዮ ላይ ተመስርታ ለማርቀቅ በጀመረችበት ወቅት ኑፋቄዎች ተከስተዋል:: የክርስቶስን

ፍጹም አምላክነት በመካድ የተንጸባረቁ ታሪካዊ ኑፋቄዎች ሁለት ናቸው:: እነዚህ ሁለት ኑፋቄዎች ኢየሱስ ማን እንደሆነና ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የተሳሳቱ አመለካከቶች ናቸው::

## ሀ. ኢቦናዊነት

የመጀመሪያው ቡድን ኢቦናዊነት የተሰኘ ሲሆን በክርስቶስ አምላክነት ዙሪያ የነበረውን አሳቤ ሲሰነዝር እውነተኛ አምላክ ወይም በእርሱነቱ እግዚአብሔርን እግዚአብሔር የሚያሰኘው ማንነት የሚይዝ አምላክ እንዳይደለ ገለጿል:: ይህ ኢቦናዊነት የሚለው ስያሜ ከይሁዲነት እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘና በመጀመሪያ ለሁሉም ክርስቲያኖች በመቀጠልም ለአይሁድ ክርስቲያኖች መጠሪያ የነበረ ÷ በኋላም ለአይሁድ የመናፍቃን ቡድን በመጠሪያነት አገልግሏል::

ይህ የመናፍቅነት ትምህርት በእግዚአብሔር አንድነት (Monotheism) ላይ የጠነከረ እምነት የነበረው ሲሆን የክርስቶስን ከድንግል መወለድ በመካድ ኢየሱስ የዮሴፍ ህጋዊ ልጅ ማለትም ዮሴፍ በሩካቤ ዘበስጋ ከማርያም የወለደው ነው ብሎ ያስተምር ነበር:: ስለ ኢየሱስ የሚያስተምሩትን ስንቃኝ ኢየሱስ ጻድቅና ጠቢብ የሆነ ተራ ሰው ነበር፤ነገር ግን በተጠመቀበት ወቅት ክርስቶስ በእርግብ አምሳል በእርሱ ላይ ወረደ ከዚያም እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል ታላላቅ ነገሮችን ፈጽሞ ልክ ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት ክርስቶስ ከእርሱ ተለይቶ ሄዷል ብለው እንደሚያምኑ መረዳት ይቻላል::

ለዚህ ኑፋቄ መሠረታዊ ምክንያት የሚሆነው በአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻህፍት ያለማመናቸው በመሆኑ በተለይ ደግሞ የኢየሱስን ዘላለማዊነት ከድንግል መወለዱንና የነበረውን የላቀ ደረጃ የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንም ይክዳሉ:: ይህ የመናፍቅነት ቡድን በ2ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የተነሳና የክርስቶስን ፍጹም እውነተኛ አምላክነት የካደ ነው::

## ለ. አርዮሳዊነት

አርዮሳዊነትን የተመለከቱ አንዳንድ አሳቤዎችን ቃል በግጻዌ መለኮት ባለው ግንኙነት በቅድመ ትሥጉት ዙሪያ ስንነጋገር አንስተናል:: የዚህን ታሪካዊ ኑፋቄ ምንነትና የስህተቱን መሠረት በዚህም ርእስ ስር ማንሳቱ ተገቢ እንደሆነ አስባለሁ::

አርዮስ በተባለ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ በነበረ ሰው በ4ኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ የመናፍቅነት ትምህርት ነው:: ከኢቦናዊነት ኑፋቄ በጠለቀና በተደራጀ መንገድ በተከታታይ የሥነ

መለኮት ነጸብራቅ ሂደት በመከሰቱ ለቤተክርስቲያን ታላቅ ተግዳሮት ነበር:: ይሄ ኑፋቄ ምንም እንኳ በ325 እና ከዚያም በተከታታይ በተደረጉ የኒቅያ ጉባኤና ሌሎች ጉባዔዎች በቤተክርስቲያን አባቶች የተወገዘ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ በተለያየ መልኩ የሚከሰት በመሆኑ በዘመናችን ራሳቸውን "የይሆዋ ምስክሮች" በማለት የሚጠራ ቡድን የዚህ ኑፋቄ ተከታዮች አርዮሳውያን ናቸው::

እንደ አርዮሳዊያን ትምህርት እግዚአብሔር ብቻ (ይህን ሲሉ አብ ብቻ) ያልተፈጠረና ዘላለማዊ ነው:: ሌሎች በሙሉ ግን የተፈጠሩ ናቸው :: እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ብቸኛ ምንጭ ነው:: እርሱ ብቻ የመለኮትነት ባህርይ አለው:: እርሱ ማንነቱን ለማንም አያጋራም÷ እርሱነቱን ከማንም ጋር አይካፈልም:: እርሱነቱን ለሌላ የሚያጋራ ከሆነ የሚከፋፈልና የሚለወጥ ስለሚሆን እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም:: ሌላ መለኮታዊ አካል ከእርሱ ጋር የሚጋራ ከሆነ የመለኮት ሁለትነትና መባዛት እንደሚኖር መናገር በተቻለ ነበር:: ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ማንነት በመጋራት ከአብ መውጣት አይችልም:: ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌሎች በሙሉ ከሚታየው የተፈጠሩ ናቸው:: ከዚህም የተነሳ አርዮሳውያን የክርስቶስን ለአብ የግብር ቅደም ተከተል (Functional Subordination) አመላካች ክፍሎችን በመጥቀስ ከአብ የሚያንስ አምላክ እንደሆነ ለመናገር ደፍረዋል:: ስለዚህም ድኅረ ትሥጉት አካል ክርስቶስም የአብ የመጀመሪያና ታላቅ ፍጥረት ሆኖ እንደተፈጠረ ነገር ግን እርሱ ራሱ ህላዌ እንዳልነበረው ይናገራሉ::

በአጠቃላይ አርዮሳዊያን የኢየሱስን ፍጹም አምላክነት የተሟላ መሆን ይክዳሉ:: ከዚህም የተነሳ ኢየሱስ አምላክ ግን ከአብ ያነሰ ሆኖ የሚመለክ ያደርጉታል:: ይህ ከሆነ በአምላክ አንድ ብቻ መሆን ያምናሉ ማለት ያስችላልን? ኢየሱስንና አብን የተለያየ ደረጃ ያላቸው መለኮቶች በማድረግና በማመናቸው የብዙ አማልክት አምልኮ (Polytheism) ያላቸው አያስኛቸውምን?

ከዚህም የተነሳ አርዮሳውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ስብሳብ ላይ እንጂ በሥነ መለኮታዊም ሆነ የፍልስፍናዊ መርህን በተከተለ መንገድ ክፍሎቹን አልተመለከቷቸውም ለማለት ያስችላል:: ስለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ከአጠቃላይና ከቅርብ አውዳቸው ውጪ በመፍታት እንዲሁም ወልድን እግዚአብሔር በሚያሰኘው (እርሱነቱ) እና በግብር÷ በረቂቅ አካልነትና በስም ረገድ የተነገሩ ክፍሎችን ባለማስተዋል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል:: በድኅረ ትሥጉት

አካል በክርስቶስ አምላክነት ላይ በተዛባ ትርጉም የሚፈቷቸው ክፍሎችን ስንቃኝ:-

1. ኢየሱስ ፍጡር እንደሆነ ለማመልከት የሚሞክሩባቸው ክፍሎች (ሐዋ 2:36፤ሮሜ 8:29፤ቆላ 1:15፤እብ 3:2)
2. አብ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ የሚያመለክት የኢየሱስ ጸሎት (ዮሐ 17:3)
3. ለኢየሱስ ፍጹምነት የማያላብሱ ማለትም ድካምን፥ መከራንና አላዋቂነትን (የማያውቀው ነገር ያለው መሆኑን) የሚያሳይ ጥቅስ (ማር 13:32) ይገኙባቸዋል::

ከላይ የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአጭሩ አንድ በአንድ መመልከት አስፈላጊ ነው:: ለዚህም በመጀመሪያ ነጥብ ስር ኢየሱስን ፍጡር ሰው ለማለት የሚጠቅሱት (ሐዋ 2:36) "ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም አደረገው::" የሚለውን ሀሳብ በመውሰድ ኢየሱስ ጌታም ክርስቶስም አልነበረም ይላሉ:: ነገር ግን አብ በጸጋ እንዳደረገው አመላካች አድርጎ መውሰድ ትክክለኛ አይደለም:: በዚህ ክፍል አውድ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሐዋርያው ጴጥሮስ ለእስራኤላውያን ሲናገር እነርሱ የሰቀሉት ኢየሱስ ከግብሩ ወይም ሰዎችን ለማዳን ካደረገው የተነሳ በማእረግ ወይም በሹመት ስፍራ መቀመጡንና እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ እንዳደረገው አመላካች እንጂ ፍጡር እንደ ነበረ የሚያመለክት ክፍል አይደለም:: ከመሲህነት ግብሩ የተነሳ የላቀ መሆኑን ከሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት *...ምላስም ሁሉ ይንበረከክ እና ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ እግዚአብሔር ከስም ሁሉ በላይ ስም እንደ ሰጠው* አመላካች እንጂ በማንነቱ ያነሰ የነበረውን የደረጃ እድገት መስጠትን በፍጹም አያመለክትም ከፊል 2:9-11 ጋር ይነጻጸር::

ሌላው ደግሞ በሮሜ 8:29 እና በቆላ 1:15 የልጁን (የወልድን) በኩር መሆን የሚያመለክትን ሀሳብ በመጠቀም ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር ከሆነ ለምን በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር በሌላ በኩል ደግሞ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ይለዋል? የሚል ነው:: በዚህ ክፍል ልጁ የአብ ፍጡር ነው የሚል ሀሳብን በፍጹም አናገኝም:: ክርስቶስን ከሌሎች (ፍጥረታት) ካነጻጸርነው በኩር የሚያገኛቸው እድሎች ባለቤት የሚያደርገው የተለየ ልጅነት ያለውና ሁሉ በእርሱ የተፈጠሩ መሆኑን አመልካች ነው:: ይህ አይነቱ ክርስቶስን ከፍጥረታት የማነጻጸርና የእርሱን በኩርነት (ከትርጉም አንጻር የላቀ መሆን የሚልን ሀሳብ የያዘውን ቃል) መጠቀሙ በዕብራውያን መልእክትም ውስጥ እርሱ ከመላእክት፥

ከሙሴ÷ ከካህናት በኩር (የላቀ) መሆኑን ለመግለጽ የተጠቀመበት መንገድ መሆኑን አስቀድሞ ለመግለጽ እንደሞከረኩት ነው::

ይህ የትሥጉት አካል ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሲሆን ሳለ የሰው ልጅ ሆኖ በመምጣቱ ወንድሞቹ እንሆን ዘንድ የተገባን እንደሆንን የሚያስረዳ ክፍል ነው:: በዚህም ረገድ እርሱ በአመኑቱ መካከል ያለው ብኩርና ከሁሉ የላቀን ስፍራ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ በመያዙ ነው የሚል ሆኖ እናገኘዋለን:: ስለዚህም በኩር የሚለው ቃል የመጀመሪያ ከማለት በተጨማሪ የላቀ (outstanding) ማለት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የወልድን አምላክነት መካድ ሳይሆን የትሥጉት አካል ክርስቶስን አምላክ–ሰው በመሆኑ ላመኑቱ ያለውን ወንድምነትና በዚህ ወንድምነቱ ያለውን የላቀ ደረጃ አመላካች ነው::

ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች በሁለተኛ ደረጃ የሰፈረው በዮሐ 17:3 *...እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን...* የሚለውን ጥቅስ በመውሰድ አርዮሳውያን ኢየሱስ ወደ አብ ሲጸልይ አብ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ በመጥቀስ እርሱ ራሱ ግን እውነተኛ አምላክ እንዳልሆነ መስክሯል የሚልን አፈታት በመፍታት የተሳሳተ ድምዳሜና ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱሱ ሀሳብ የተቃረነ አመለካከትን ይሰነዝራሉ:: በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ የአብን አምላክነት ከራሱ ጋር አላነጻጸረም:: ስለዚህም በዚህ ክፍል ላይ የተናገረበትን ሀሳብ ስንመለከት ከግብር እንጂ ከማንነት አንጻር ያልተናገረው መሆኑን ማስተዋል ይቻላል::

በመቀጠልም ኢየሱስ አብ የላከው እንደሆነና አብ ላኪ ሲሆን እርሱ ደግሞ ተላኪ መሆኑን አመላክቷል:: ይህንን አይነት አገላለጽ ከዚህ ክፍል አስቀድሞ በዮሐ 10:29 ላይ *የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል* ሲል በግብር ቅደም ተከተል (Functional Subordination) አንጻር እንጂ በማንነቱ ወይም በአምላክነቱማ ከዚሁ ቁጥር ቀጥሎ ባለው ላይ *እኔና አብ አንድ ነን* በማለት አይሁድ *...ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር ስላስተካከልክ በድንጋይ እንወግርሀለን* እንዲሉት ድንጋይ እንዳነሱበት እንመለከታለን:: በዮሐ 17:3 ላይ ኢየሱስ የአብን እውነተኛ አምላክነት ሲናገር ከራሱ ጋር አነጻጽሮ ሳይሆን በአጠቃላይ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ትኩረት የሰጠበትን ከአብ ተልኮ መጥቶ የተላከበትን ስራ ከመፈጸሙ አንጻር የግብር ቅደም ተከተሉን የገለጸበት ነው::

በሦስተኛው ነጥብ ስር አርዮሳውያን ያቀረቡትን ጥቅስ ስንቃኝ ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽዓቱ ቀን ሲናገር ልጁም (ወልድም) እንኳን

እንደማያውቅ መናገሩን በማውሳት በተጨማሪም መድከም፥ መራብና መጠማት እንዲሁም መከራ መቀበሉን በማስታከክ ፍጹም አምላክ አይደለም ይላሉ (ማር 13፡32)።

ይህ የክርስቶስን ማንነት ካለማስተዋልና የትሥጉትን ጽንሰ ሀሳብ በጥልቀት ካለመረዳት የመነጨ ነው። የወልድን በትሥጉት አካል በሥጋ ባሕርይ ይኸውም ለመለኮት ባህርይ የማይገባውን መከራ መቀበል ፥ መሞት እንዲሁም የምጽዓትን ቀን አላውቅም ማለቱን እንመለከታለን። ለዚህ ጥያቄ የተሟላ ምላሽን መስጠት ይቻል ዘንድ የአምላክ ሰው ባሕርያትን ግንኙነት በምንመለከትበት ክፍል መረዳቱ የተሻለ ስለሚሆን ለዚያ ተገቢ ርእስ አቆየዋለሁ። በአጠቃላይ ግን እነዚህ እንደ መራብ፥ መጠማት፥ መሞትና የምጽዓትን ቀን አለማወቅ በፍጹም ከክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ያለ መሆን ጋር የተገናኙ ሀሳቦች አለመሆናቸውን ማስተዋል ያሻል።

### 1.2.4. ክርስቶስ ፍጹም ሰው ነውን?

በድኅረ ትሥጉት ማለትም ወልድ (አካላዊ ቃል) ሥጋ ከሆነ በኋላ ባለው አካል በክርስቶስ ማንነት ዙርያ የትሥጉትን አካል ፍጹም ሰው መሆን መብራራት ያለበት ነጥብ ነው። ይህንም ስል መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል በግልጽ ከሚናገራቸው ሁለተኛው ሀሳብ ሰዎችን በማዳን እቅድ ሥጋ ሆኖ መምጣቱ ነው (ዮሐ 1፡14)። ቃል ሥጋ ሆነ ማለት ምን ማለት ነው? ሥጋ ለበሰ? ወይስ ሰው ሆነ? ለዚህ ጥያቄ ምላሽን ለማፈላለግ ተገቢው ርዕሳችን የክርስቶስ ሰው ሆኖ መምጣትን የምናነሳበት ይህ ነጥብ ነው።

የቃል ሥጋ መሆን የድኅረ ትሥጉት አካልን ሰው ያሰኘው ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም ደግሞ ክርስቶስ አንድ ተፈጥሮአዊ ሰው ያለውን ሥጋ፥ መንፈስ (ነፍስ) የነበረው እንደሆነ እንመለከታለን። ይህ ክርስቶስ ሰው እንደሆነ የምንመለከትበት ሀሳብ ደግሞ አስቀድመን በስፋት ከተመለከትነው ከፍጹም አምላክነት ጋር አይቃረንምን? የሚልን ጥያቄ ይቀሰቅሳል፤ ይህንን ነጥብ በአምላክ ሰው ባሕርያት ህብረት ዙሪያ የምናነሳው ሲሆን የቃል ሥጋ መሆን (ትሥጉት) ማንነት ከቃል ሰው መሆን ግንዛቤ ጋር ስላለው እሳቤ ማውሳቱ አስፈላጊ ነው። የትሥጉት አካል ክርስቶስ ሰው ነው ለማለት የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወረሰ ቃል አለን። ይህም ቃል «ትሥብእት» የሚባል ሲሆን ትርጓሜውም ሰብ (ሰው) መሆን ማለት ነው።

እንደ አለቃ ኪዳነወልድ መዝገበ ቃላት አፈታት "ሰብ" ማለት ሠባት ማለት ሲሆን ይኸውም የሰውን ሠባትነት አመላካች ነው:: አክሲማረስ እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረባቸውን ሠባት ነገሮች ሲጠቅስ:- ከአራቱ ባህርያተ ሥጋ:- መሬት÷ ውሃ÷ እሳት እና ንፋስ እንዲሁም ከሦስቱ ግብራተ ነፍስ:- የማትበላና የማትጠጣ÷ የማታንቀላፋ ብሎም የማትሞት እንደሆነ ይገልጻል::[8] በአጠቃላይ እነዚህ ሰባት ነገሮች በሰው ሥጋና ነፍስ ውስጥ ይገኛሉ:: ስለዚህም ሰው ሰባት ነው የሚልን ጽንሰ ሀሳብ በማያያዝ «ሰብ» የሚለው ቃል ለፍጥረታዊው ሰው ይነገራል:: እንግዲህ የትሥጉት አካል ክርስቶስም ፍጹም ሰው እንደሆነና በሰው ውስጥ የሚገኙ ሰባት ነገሮች ያሉት ሙሉ ሰውነቱን ለማመልከት *ትስብእት* የሚለው ቃል ሙሉ ትርጉሙን የሚገልጽ ነው::

እንግዲህ ስለ ክርስቶስ ስንናገር የቃላት መረጣ ወሳኝነት ካልተስተዋለ ኑፋቄያዊ እሳቤ ሰዎችን ከማስፈረጅ ለመጠንቀቅ ይረዳናል:: የክርቶስን ማንነት በማስተማር መስክ ከገጠመኝ አንዱን ማካፈሌ የቃላት አጠቃቀምን ወሳኝነት የሚገልጥ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ:: በአንድወቅት በዚህ ነጥብ ላይ በትምህርት ሂደት አንድ ተማሪዬ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ የመጣ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ እንደሚያምንና ሥጋው የሰው ሥጋ ከመሆኑም በላይ መለኮትነቱ የማይታየው ማንነቱ (person) እንደሆነ መናገር ጀመረ:: በዚህ ወቅት ይህ ተማሪዬ ሥጋ ለበሰ የሚለውን ቃል በተለምዶ ከነበረው አጠቃቀም ወጣ ባለ መንገድ እንደተረዳውና ለዚህም መረዳቱ የጥሬ ቃል ትርጉሙ እንደሆነ በማስተዋል «ለመሆኑ ክርስቶስ ሰው እንደሆነ ታምናለህን?» ብዬ ጠየቅሁት:: እርሱም ሥጋው የሰው እንደሆነ እንጂ እርሱነቱ (የማይታየው ክፍሉ ነፍሱ÷ መንፈሱ) የሰው እንደሆነ ማመን እንደሚያዳግተው መናገር ጀመረ::

ከዚህ ተማሪዬ የተረዳሁት ክርስቶስ 50% እግዚአብሔር÷ 50% ሰው በመሆኑ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በማለት ለማስረዳት የነበረውን ሙከራ ነው:: በጣም የገረመኝ የክርስቶስን ሥጋ የሰው እንደሆነ መናገርም ሆነ ነፍሱን (መንፈሱን) የአምላክ አድርጎ ማሰብ በራሱ የክርስቶስን ማንነት ሙሉ ለሙሉ አለመረዳትን ከማንጸባረቁም በላይ ቀጥለን እንደምንመለከተው በታሪካዊ ኑፋቄነት ከተወገዙ አስተምህሮቶች አንዱ ነው:: ከታሪካዊ ሥነ መለኮት መማር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው::

ስለዚህ በዚህ ዋና ርእስ ማጠቃለያ ላይ በጥልቀት ስለምንቃኝ በተገቢው ስፍራ ከታሪክ እንማርበታለን:: በዚህ ስለክርስቶስ በተማሪዬ አማካኝነት በተሰነዘረው እሳቤ ላይ በአጭሩ ምላሽን

ለመስጠት መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ስለ ሙሉ (ፍጹም) እግዚአብሔር መሆኑ እንደሚያነሳው ሁሉ ፍጹም ሰው ስለመሆኑም ያስረዳናል:: ምንም እንኳ ሥጋው የሰው ሥጋ ነው የሚለውን አመለካከት አምላክ ሥጋ የለውም ከሚለው እውነታ አንጻር የተናገረው ቢሆንም አሁንም ይህንን እሳቤ ስህተት የሚያደርገው ምክኒያት በአምላክነቱና በሰው መሆኑ መካከል ያለውን ግንኙነት ለምንቃኝበት ርእስ ማቆየት አስፈላጊ ነው:: በዚህ ርእስ ስር ግን የክርስቶስን የትስብእት አካልነት ለመዳሰስ አስቀድመን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው መሆኑ የሚናገረውን መመልከት አስፈላጊ ነው::

### 1.2..4.1. ክርስቶስ ሰው መሆኑን የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች:-

ስለ ትሥጉት አካል ክርስቶስ ስናስብ በመጀመሪያ ፍጹም ሰው መሆኑን የምንመለከተው እንደ ሰው መወለዱና የሰው ተክለ ሰውነት እንዳለው ነው (ሉቃ 2:1-52):: አካላዊ ቃል በሰብአዊ አካል መወለዱ እንደማንኛውም ሰው በአጭር ቁመትና በጠባብ ደረት የተወሰነ እንዲሆን አድርጎትም ነበር:: ሰው በመሆኑም ተርቧል፥ ተጠምቷል፥ ደክሞታልም (ማቴ 4:2፤ዮሐ 19:28፤ ዮሐ 4:6):: ከዚህም በተጨማሪ ሰው ስለሆነ ሞትን ሞቷል:: በኢየሱስ ላይ ስለሆነበት ነገር ሁሉ ዮሐንስ እውነታውን ሲገልጥ ሰው መስሎ መገኘት ሳይሆን ሰው መሆን እንደሆነ ያስረዳናል (1ዮሐ 1:1) ::

ጌታ ኢየሱስ ራሱ ሰው መሆኑን ሲገልጽ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል» ማለቱና ሌሎች የኢየሱስን ሰው መሆን መመስከራቸውንም እንመለከታለን (ማቴ 4:4፤ ሐዋ 2:22፤ ሮሜ 5:15 ፤17፤19፤ 1ቆሮ 15:21፤47–49፤1ጢሞ 3:16፤ ዮሐ1:14፤ ገላ 4:4):: ይህ የክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆን ከትንሳኤውም በኋላ ማረጋገጫ የተሰጠበት ነው (ሉቃ 24:39)::

### 1.2.4.2 ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት፤ ግን ሰው ነውን?

ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን ስናነሳ እንግዲያው ሰው ሆኖአል ካልን ከኃጢአት ባሕርይ ውርስ አንጻርስ ከእናቱ ወደ እርሱ የተላለፈ ኃጢአት የለምን? የሚል ጥያቄ ይነሳል:: ይህ ጥያቄ ደግሞ ስለ ኢየሱስ እናት ስለ ማሪያም ማንነት እንድናስብ ያደርገናል:: ስለዚህም የኢየሱስ ኃጢአት አልባነት ከእናቱ ከማሪያም፥ ከአጸናነሱ ወይስ ደግሞ ከእርሱ ማንነት አንጻር ሊሆን እንደቻለ የተለያዩ እሳቤዎችን መዳሰስ አስፈላጊ ነው::

አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባቶች በተለይ በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ካላቸው የጽሑፍ ማስረጃዎች እንደምናገኘው ከሆነ ኃጢአት በወንድ ዘር አማካኝነት እንደሚወረስና ኢየሱስ ግን ከሥጋ ፈቃድ ሳይሆን ድኅረ አለም ያለ አባት ከእናት ብቻ በመወለዱ የኃጢአት ውርስ እንደሌለበት ይናገራሉ::[9] ይህ በፍልስፍና ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ለኢየሱስ ኃጢአት አልባነት በመንስዔነት የሚያቀርበው ከወንድ ፈቃድ ያለመገኘቱን ነው:: ሆኖም ይህን የኃጢአት ውርስ በወንድ ዘር ይተላለፋል የሚል እሳቤ በመጽሐፍ ቅዱስ መደገፍ የሚቻል አይመስለኝም::

በሌላ በኩል ደግሞ ከኢየሱስ እናት ከማርያም ማንነት ጋርም በማያያዝ ምላሽ ለመስጠት የሚጥሩም አሉ:: እነዚህን በሁለት ቡድን መክፈል ይቻላል:- አንደኛው ቡድን ማርያም የውርስ ኃጢአት ነበረባት እንጂ በራሷ (በሐልዮ÷ በነቢብ እና በገቢር) ማለትም:- ከአስተሳሰብ÷ ከድርጊትም ሆነ ከአንደበት ኃጢአት ፍጹም ነጻ ነበረች ምክንያቱም የእግዚአብሔር እናት እንድትሆን አስቀድሞ ተወስኗልና ሲል ሁለተኛው ቡድን ደግሞ ማርያም በውርስም ሆነ በራሷ የፈጸመችው ኃጢአት የሌለባት እንደነበረች ይናገራል:: ስለዚህም ወደ ጽንሱ ወደ ኢየሱስ የተላለፈና የተወረሰ ኃጢአት አልነበረም ይላሉ::[10] እነዚህን አመለከከቶች ስንቃኛቸው ለመጀመሪያው እሳቤ ከአዳም ኃጢአት ነጻ ካልነበረች እንግዲህ ክርስቶስ ከውርስ ኃጢአት ነጻ ነበረን? እንዴት? ካልነበረ ደግሞ ሰዎች አልዳኑም ማለት ነዋ? ለሚሉ ጥያቄዎች መንፈስ ቅዱስ ሲጸልላት ኃጢአት ከእርሷ ወደ ክርስቶስ እንዳይተላለፍ ማድረጉንና የክርስቶስ ሞት ለእርሷም የተከፈለ ዋጋና የተቤዠችበት እንደሆነ ይናገራሉ::

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ ከውርስም ሆነ ከግብር ኃጢአት ነጻ ካልሆኑት የሰው ዘር ሳትሆን የመላእክት ወገን ነበረችን? የመንፈስ ቅዱስ እርሷን የመጸለሉ ሚስጥር ምንድር ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ማርያም ከሰማይ የወረዱ የመላእክት ዘር ሳትሆን ከኢያቄምና ከሐና (ከሁለት ባለትዳር ሰዎች) በሩካቤ ዘበሥጋ የተወለደች እንደሆነች ይናገራሉ:: በመቀጠልም በሉቃ 1:35 መሠረት የመንፈስ ቅዱስ መጸለል (መጋረድ) የውርስም ሆነ የግብር ኃጢአት ስለነበረባት ሳይሆን የብስራቱን ቃል እንድትቀበልና የክርስቶስ ማደሪያ ለመሆን የተዘጋጀች እንድትሆን ለማድረግ ነበር በማለት ምላሻቸውን ያንጸባርቃሉ:: ይህ ከሆነ ደግሞ ማርያም የአዳም ዘር ናት ማለት ያስችለናልን? ለሚለው ጥያቄ አሁንም ምላሽ የሰጠ አይደለም::

ስለዚህም የክርስቶስ ኃጢአት አልባነት ከምን የተነሳ እንደሆነ አያመላክተንም::

በዚህ ሃሳብ ዙርያ ልናስበው የሚገባን አንድ መሠረታዊ ነገር ቢኖር በሥነ መለኮቱ አለም በ "ውርስ ኃጢአት" ረገድ የሚንጸባረቁ ሁለት የተለያዩ አመለካከቶች አሉ:- አንደኛው የበደል ውርስ ሲሆን በአዳም ኃጢአት የሰው ዘር በሙሉ በደለኛ ሆኖ በተጠያቂነት ስር እንዳለ ያመለክታል:: ሁለተኛው ደግሞ የኃጢአት ባሕርይ ውርስ ይኸውም:- የሰው ዘር የሆነ ሁሉ ኃጢአትን አለመስራት እንደማይችል የሚያመለክት ነው:: በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምሬዎች "በጥንተ አብሶ" ማለትም የአዳም በደል በሰው ዘር ላይ መወረስ እንደሚያምኑ መረዳት ይቻላል:: ለዚህ እሳቤም በመሰረትነት ከሚጠቀሱ ክፍሎች መካከል "ዳዊት እናቴ በኃጢአት ወለደችኝ::" (መዝ 51:5) ማለቱ የሚጠቀስ ነው:: ይህም ደግሞ ሰዎች ሁሉ በአዳም በደል ተጠያቂዎች እንደሆኑ አመላካች ነው:: ለአብነት ያህል በብሉይ ኪዳን በስፋት የተንጸባረቀ የአባቶችን በደል በልጆች ላይ የመምጣቱ ነገር ከአዳምም በኋላ በደል በዘር እንደሚወረስ የተንጸባረቀባቸው የመጽሐፍ ክፍሎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠባቸው መሆኑ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የህጻናት ጥምቀትን ከድነት አስተምህሮ ጋር ማቆራኘ ታቸው የበደልን ውርስ ከማስወገድ አኳያ የሚታይ ነው:: ካገላበጥኳቸው በኢትዮጵያውያን መምሬዎች የተጻፉ መጻሕፍት ለመረዳት እንደቻልኩት የሰው ልጆች የበደል ውርስ እስከ ክርስቶስ የመስቀል ሞት ድረስ እንደ ነገሠና በመስቀሉ ሥርየት ካሣ እንደተከፈለበት እንደሚያምኑ ተመልክቻለሁ::

የኃጢአት ባሕርይ ውርስን በተመለከተ ማንኛውም ሰው በግል ህይወቱ በተለያየ መንገድ ኃጢአትን ከመፈጸም ነጻ እንዳይደለ የሚያመለክት ነው:: እንግዲህ ከክርስቶስ የመስቀል ሞት በኋላ ያሉ ሰዎች የኃጢአተኝነት ባሕርይን እንጂ የአዳም የበደለኝነት ውርሳቸው (ጥንተ አብሷቸው) በክርስቶስ ሞት ዋጋ የተከፈለበት እንደሆነ አመላካች ነው:: ቢሆንም ግን ጥምቀት ኃብተ መንፈስ ቅዱስን እንደሚያሰጥ ስለሚታሰብ ህጻናት ለድነታቸው መጠመቅ እንዳለባቸው ይታመናል:: ይህንን ነጥብ በተለይ በድነት ጉዳይ ላይ ሰፋ አድርጎ መመልከት የተሻለ ነው::

ወደ ተነሳሁበት ሃሳብ ልመለስና ማርያምም እንኳ ከክርስቶስ ሞት በፊት የነበረች በመሆኗ ከአዳም በደል ውርስ ነጻ እንዳልነበረች የሚያመላክቱ እንደ ሠይፈ ሥላሴ ያሉ ኢትዮጵያውያን መምሬዎች እንዲህ ይላሉ:-

አንዳንዶች እመቤታችን እድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም፤ ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘ ች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላዕክት ወገን አይደለችምና፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገርና የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም::[11]

በማለት የአዳም ጠባይዕ ወይም የጥንተ አብሶ (የአዳም በደል) ወራሽ እንደነበረች የሚያመለክትን ሃሳብ ይገልጻል:: በዚህም የበደል ውርስ ከክርስቶስ የመስቀል ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ላሉቱ ካሣ የተሰጠበት መሆኑን ያመለክታል::

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥነ መለኮት መምሬዎች የውርስ ኃጥአት ሁለቱም ማለትም:- የበደልና የኃጢአት ባሕርይ ውርስ ማለት ቢሆንም ወደ ሰው ዘር በሙሉ የተወረሰው በደለኝነት (ተጠያቂነት) ሳይሆን ከኃጢአት ነጻ መሆን የማያስችል ባሕርይ ብቻ ነው የሚሉ የሥነ መለኮት ሰዎችም አሉ:: ይህ ደግሞ በውርስ ኃጢአት ምክንያት ማንም ሰው ያለ ኃጢአት መሆን አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነው:: ከዚህም በመነሳት በክርስቶስ ኃጢአት አልባነት ረገድ ከተሰነዘሩት አንደኛው አሳቤ ለማሪያም የበደለኝነት ውርስ (ጥንተ አብሶ) የነበረባት መሆንና የክርስቶስ ሞት ለሰው ዘር በሙሉ ሥርየት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ለማርያም አስፈላጊነቱንም ያሳያል:: የኃጢአት ባሕርይ ውርስን በተመለከተ ግን ማርያም ፈጽሞ ነጻ እንደነበረች ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው የእግዚአብሔር እናት እንድትሆን አስቀድሞ እንደተወሰነች የሚናገር ነው::

ሁለተኛው እሳቤ ማርያምን ሰው ግን ደግሞ በኃጢአት ረገድ ከበደል ውርሱም ሆነ ከኃጢአት ባሕርይ ውርስ ነጻ እንደነበረች የሚናገር ቢሆንም እርሷን ከአዳም ዘርነት ልዩ የሚያደርጋት ምን እንደሆነ አለመግለጽ አሁን ምላሹን መሰረት አልባ ያደርገዋል:: ስለዚህ ሁለቱም እሳቤዎች የተሟላ ምላሽ እንዳላቸው መቁጠር ፈጽሞ አስቸጋሪ ነው:: ይህ ደግሞ ከማርያም የተወለደውን ኢየሱስን ከውርስ ኃጢአት ባሻገር በራሱ ኃጢአት ማድረግ ያልቻለ? ወይስ ኃጢአት አለማድረግ የቻለ? ነበር ወደሚል ጥያቄ እንድናመራም ያደርገናል::

### 1.2.4.3 ክርስቶስ ኃጢአት ማድረግ አይችልም? ወይስ ኃጢአት አለማድረግ ችሏል?

እንግዲህ ክርስቶስ ሰው ነው ስንል ሰው ሆኖ ያለ ኃጢአት ያለ ማንም በምድር ላይ እንደሌለ ቃለ እግዚአብሔር በሮሜ መልእክት ውስጥ አበክሮ ይገልጽልናል (ሮሜ 3:23):: ታዲያ ክርስቶስ ሰው ነው ካልን እንዴት ያለ ኃጢአት (ኃጢአት የሌለበት) ነው ማለት እንችላለን? የሚለው በብዙዎች አእምሮ የሚጉላላ ጥያቄ ነው:: ከላይ በጠቀስኩት መሠረት እናቱ ማርያም ያለ ኃጢአት እንደነበረች ከሚገልጸው ከሁለተኛው ሀሳብ በመነሳት እርሱም ያለ ኃጢአት መሆን ቻለን? ወይስ ደግሞ ሌላ ስለ እርሱ ስናነሳ መዘንጋት የሌለብን ምስጢር ይኖራል ብሎ ማሰብ አስፈላጊ ይሆንን?

በዘመናችን ራሳቸውን «የይሆዋ ምስክሮች» በማለት የሚጠሩ አርዮሳውያን ክርስቶስ ኃጢአት አልባ የሆነው በፍጥረቱ ቅድመ ውድቀት የአዳምን ባሕርይ በመያዙና እንደ አዳም ለኃጢአት ሳይሸነፍ ጨክኖ እግዚአብሔርን በማክበሩ እንደሆነ ይናገራሉ:: ስለዚህም በእነርሱ እሳቤ ክርስቶስ *ኃጢአት አለማድረግ ችሏል* የሚለውን አመለካከት የሚደግፍ ነው:: በዚህም ክርስቶስ ከቅድመ ውድቀት ከአዳም ባሕርይ ጋር በማስተካከል እኩል ይመዝኑታል::[12] ለመሆኑ ክርስቶስ ሰው ነው ስንል ቅድመ ውድቀት የሆነን ሰው አይነት ማለት ነውን?

በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስን ሰው መሆን ለማስረዳት ከኃጢአት አንጻር ስንመለከት የኃጢአት ባሕርይ ከሌለው እንዴት ሰው ልንለው እንችላለን? የሚልን ጥያቄ ይቀሰቅሳል:: ለዚህም "ክርስቶስ ኃጢአት መስራት አይችልም ነበር" የሚለውን አመለካከት ተቀባይነት የሚጋፋ በዕብ4:15 መሰረት ኢየሱስ ... *ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደኛ የተፈተነ...* የሚለው ቃል ደግሞ መፈተኑ የሚያመለክተው ምንድር ነው ? የሚልን ጥያቄ ያስከትላል::

አንዳንድ የሥነ መለኮት ሰዎች:- "ኢየሱስ የተፈተነው ኃጢአት መስራት አለመቻሉን ለማሳየት ሳይሆን ኃጢአት የሌለበት መሆኑን ለማስረገጥ ነበረ::" ይላሉ:: ኃጢአት የሌለበት መሆን ደግሞ ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱት በሁለቱም መንገዶች ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛነት ቢኖረውም ስለ ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆን በእንዲህ አይነት አወዛጋቢ ሂደት ውስጥ የሚጥለን ስለ እርሱ ሁለት ባሕርያት ግንኙነት ባለን ግንዛቤ ላይ የሚመሠረት ነው:: ስለዚህ ለዚህም ጥያቄ ተገቢ መልስን ለማግኘት በኢትዮጵያውያን የሥነ መለኮት መምሬዎች ዘንድ ስለ ክርስቶስ የአምላክነትና የሰውነት ባሕርያት ግንኙነትን ያለውን

ግንዛቤ መያዝ ስለሚያሻ ከሁለቱ ባሕርያት ግንኙነት አንጻር በምናነሳው ርዕስ ስር ምላሽ እንደሚያገኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

### 1.2.4.4. ክርስቶስ ከማርያም ሥጋ እና ነፍስ ነስቷልን (ወስዷልን)?

ሌላውና መሰረታዊ የሆነው ነገር ክርስቶስ ሰው ነው ካልን እንደ ማንኛውም ሰው በአጸናነስ ሂደት ከእናቱ ዘር እንቁላል የሚወሰድ ተክለ ሰውነት አለውን? የሚል ነው። በዚህ ረገድ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ሰው የሚመስል ሳይሆን ሰው እንደሆነ ያመለክተናል። ይህም ማለት ከማርያም ተጸንሷል ተወልዶማል። እንግዲህ የክርስቶስን ማንነት ልዩ የሚያደርገው ከወንድ ፈቃድ አለመወለዱ ነው። በአካላዊ ቃል ከድንግል መጸነስ ሂደትም የመንፈስ ቅዱስን ሚና እንደ ወንድ ዘር የማርያምን የዘር እንቁላል ማልማት ነው ብሎ ማሰብ ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃን ማቅረብ የሚያስችለን አይደለም። ስለዚህም ከማሪያም ሲጸነስ ከመንፈስ ቅዱስ መጸነሱ መንፈስ ቅዱስን የአባትነት ድርሻ አያሰጠውም። ነገር ግን ጽንሱ በሩካቤ ዘበሥጋ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልጅ (ወልድ) ከማሪያም ተጸንሶ ሰው እንዲሆን ማድረጉን አመላካች ነው። ክርስቶስ ምንም እንኳ ከወንድ ዘር ባይጸነስም የሰው ተክለ ሰውነት አለው። በዚህም የሰውን ባሕርይና ተክለ ሰውነት ከማሪያም ተጸንሶ በመወለዱ ተጋርቷል ወይም ነስቷል።

ከነፍስ ነፍስን መንሳት የሚለውን እሳቤ ስንመለከተው ከሰው የተወለዱ ሁሉ የሰው ነፍስ እንዳላቸው ሁሉ እርሱም ነፍስ እንዳለው አመላካች እንጂ በማንኛውም ሰው አጸናነስ ሂደት ነፍስ ከወላጅ የምትነሳ እንደሆነች ማሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይመስለኝም። ይህ ከሆነማ የወላጅ ነፍስ ለልጅ እየተቀረሰች እንደመውሰድ ያለ አመለካከት ውስጥ ከትቶን ከወላጆቻችን ተክለ ሰውነትና ሰብአዊ ባህርይን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም እንወስዳለን ማለትን ያስከትላል። ለዚህ አንድ የጥንት በኢትዮጵያዊ የእምነት አባት የተጻፈው መጽሐፍ የሥጋ ባሕርይ ከአባትና ከእናት እንደሚገኝና ረቂቅ ነፍስ ግን ልክ ብላጺ የተባለውን ድንጋይ ከብረት ጋር ባጋጩት ጊዜ እሳት እንደሚፈጠር እንዲሁም በሩካቤ ዘበሥጋ ሂደት የምትገኝ መሆኗን ይገልጻል።[13] በዚህ አገላለጽ ነፍስ በወንድና በሴት ሩካቤ ሥጋ ሂደት በሚኖረው የወንድ ዘር የሴትን የዘር (እንቁላል) በሚሰብርበት ጊዜ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ የምትገኝ እንጂ ከእናት ወይም ከአባት የምትነሳ (የምትወስድ) አይደለችም ማለት ነው።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን ከማርያም መጸነስና መወለድ ሲገልጽ በግልጽ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቷል አይለንም:: ሆኖም ግን ከወንድ ዘር እንዳልተወለደ በግልጽ ስለሚያስረዳ ሰው ከመሆን የሚጎድለው ነገር እንዳለ አያመለክተንም:: በተክለ ሰውነት÷ በባሕርይ ሆነ በነፍስ ከሰው የወሰደው ነገር፤ ግን እርሱን ሰው ብቻ ያላሰኘው ሰብአዊ ነገሮቹ ምሉእ ነበሩ:: ስለዚህ በዚህም ሀሳብ ዙሪያ የመለኮት ሰው ሆኖ በምድር መገኘት (ትስብእት) የክርስቶስን ፍጹም ሰው መሆንን ሲያስረዳን ከሰው ምንም የማይጎድለው መሆኑን ያመለክተናል::

እንደ አምላክነቱ ሁሉ በሰው የመሆኑ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ የተነሱ ታሪካዊ ኑፋቄች አሉ:: እነዚህ ኑፋቄዎች የክርስቶስን ሰው ሆኖ መምጣት ሳይሆን ሰው መስሎ መምጣትን የሚናገሩና ሙሉ ለሙሉ ሰው መሆኑን የሚክዱ ናቸው :: በዚሁ ነጥብ ላይ እንዳለን የታሪካዊ የሥነ መለኮት ኑፋቄዎችን ምንነት በጥልቀት መመልከት አስፈላጊ ነው::

### 1.2.4.5. የክርስቶስን ሰው መሆን የካዱ ታሪከዊ ኑፋቄች:-

ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው የክርስቶስን አምላክነት ብቻ ሳይሆን ሰው መሆኑንም ያልተቀበሉ የስህተት ትምህርቶች ተነስተው ነበር:: ከእነዚህ የስህተት ትምህትቶች ውስጥ ሁለቱን መቃኘት አስፈላጊ ነው:: ይኸውም:-

#### ሀ. ዶስቲስቶች

ዶስቲስቶች በመባል የሚጠሩት ቡድኖች ኢየሱስ ሰው የሚመስል ብቻ ነበረ እንጂ ቁስ አካልን ይዞ አልመጣም ብለው ያምናሉ:: ክርስቶስ በማርያም ውስጥ አልፎ እንደመጣ እንጂ ከእርሷ እንደተወለደ አያምኑም:: ማርያም መጠቀሚያ ሆነች እንጂ ምንም ድርሻ አልነበራትም ስለዚህም ልክ ውሀ በቧንቧ ውስጥ እንደሚያልፍ ነገር ግን ቧንቧው ከማስተላለፊያነት ባሻገር ለውሀው ምንም እንደማይጨምርለት ማርያም ለኢየሱስ እንዲሁ ናት ብለው ያምናሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በምሳሌ ለማስረዳት ቲማቲም በቅርጫት እንዲያዝ እና ቅርጫቱ ለቲማቲሙ ከመያዣነት ባሻገር ምንም ማእድን እንደማያስተላልፍለት ኢየሱስ በማርያም አልፎ መጥቷል እንጂ ከእርስዋ ምንም አልወሰደም ይላሉ:: ይህ ደግሞ በዘመናችን የማህጸን ኪራይ በመባል ከሚታወቀውና መውለድ በማትችል መሃን ሴት ማህጸን ውስጥ የሌላ ወንድና ሴት ዘርን በማልማት ከሚኖረው

የእትብት ግንኙነት እንኳን በራቀ መልኩ ከማርያም ወደ ኢየሱስ ያለፈ ነገር እንደሌለ እንደሚያምኑ አመላካች ነው::


ዶስቲስቶች ስያሜያቸውን ያገኙት ከግሪኩ ትርጓሜው «መስሎ መገኘት» ከተሰኘ ቃል ነው:: ኢየሱስ ሰው የሚመስል ብቻ ነበረ እንጂ ቁሳዊ አካልን ይዞ አልመጣም÷ ቁስ አካል በሙሉ እርኩስ ሲሆን እርሱ ግን ፍጹምና ቅዱስ ነው÷ ከሁሉ የላቀ አምላክ ስለሆነና ከርኩስ ቁስ አካል ጋር ህብረት መፍጠር ስለማይችል ኢየሱስ ሰው ሆኖ አልመጣም ሰው መስሎ እንጂ የሚል ትምህርት አላቸው:: ይህ ትምህርታቸው ደግሞ ሐዋርያው ዮሐንስ በተለይ በመልዕክቱ ውስጥ በሰፊው ምላሽ የሰጠበት *የኖስቲኮች* አሳቤ ማለትም የኢየሱስን በሥጋ መምጣት የሚቃወም አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው:: ዶስቲስቶች *የኢየሱስን ሰው መሆን እውነተኛነት የሚክዱ* ናቸው::

## ለ. አፖሎኒያሪስቶች

*አፖሎንያሪስቶች* ደግሞ *የክርስቶስን ሰው መሆን የሚቀንስ* ትምህርት አላቸው:: ኢየሱስ ሰው ሆኖ ሳለ የሰውን ባሕርይ በሙሉ ግን አልያዘም ነበር ብለው ያስተምራሉ:: በዚህ መሠረት ክርስቶስ ሰው የመሆን ዋና ባሕርያትን ማለትም (ሰብዓዊ ፈቃድ÷ ምክንያት እና አስተሳሰብ) ረገድ የሚጎድለው ስለነበረው እርሱ ፍጹም (ምሉዕ) ሰው ነው ማለት የሚያዳግት ነው ብለው ያምናሉ::

*አፖሎሪያሪስቶች* ይህን ስያሜ ያገኙት እ.ኤ.አ. በ361 ዓ.ም የሎዶቅያ ጳጳስ ከነበረና *አፖሎናሪየስ* ከተባለው ሰው ስም ነው:: *አፖሎናሪየስ* የክርስቶስ አካል የሰው ሰውነት ÷ የመለኮት አእምሮና መንፈስ ያለው ነው ብሎ ያስተምር ነበር:: ይሁንና ይህ የአፖሎናርየስ ትምህርት ከ362ዓ.ም. ጀምሮ ከእስክንድርያ ጉባኤ ተቃውሞ ሲገጥመው ቆይቶ በቆስጠንጢኖስ ጉባኤ እ.ኤ.አ በ381 ዓ.ም. የተወገዘ ትምህርት ነው:: በአጠቃላይ በአፖሎሪስቶች ትምህርት *የክርስቶስን ሰው መሆን የተሟላ አይደለም* ብለው ያምናሉ:: ስለዚህም ክርስቶስ 50% ሰው ማለትም በቁሳዊ አካሉ ÷ 50% እግዚአብሔር ማለትም በማይታየው በነፍሱ (መንፈሱ) በማለት የሁለቱ ያልተሟላ ማንነት ድምር (ጥምረት) እንደሆነ ይናገራሉ::

ይህን በመግለጫ ለማስረዳት ክርስቶስ:-




(ሰ.ባ) 50 % (መ.ባ) 50 % እግዚአብሔር ምሉዕ ሰው ያልሆነ
በተክለ ሰውነቱ (አካሉ) በነፍሱ (መንፈሱ) (ሰው መሆኑ ያልተሟ

1.2.5. አምላክነት እና ትስብእት (ሰው መሆን) በክርስቶስ ውስጥ ያላቸው ግንኙነት:-

ባለፉት ተከታታይ ርእሶች የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ወይም ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን በሰፊት ተመልክተናል:: በመቀጠልም የአካላዊ ቃልን ሥጋ መሆን በማንሳት አካላዊ ቃል ሰውን ለማዳን ከማሪያም በመወለድ ፍጹም ሰው ስለ መሆኑ በጥልቀት ተመልክተናል:: እንግዲህ አምላክነቱንና ሰው መሆኑን ከተመለከትን እነዚህ ሁለቱ የአምላክና የሰው ባህርያት ያላቸውን ግንኙነት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል:: ክርስቶስ አምላክ ነው!÷ ክርስቶስ ሰው ነው! ስንል ክርስቶስ ሁለት ማለትም አንዱ አምላክነት በሠማይ ዙፋን÷ ሌላው ሰው የሆነው በምድር ለሰዎች ኃጢአት የሞተው ማለት ነውን? አለያም አምላክ ነው÷ ሰው ነው ማለት እንዴት ሊሆን ይችላል? ከሁሉ አስቀድሞ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው::


1.2.5.1. ክርስቶስ በአካል ስንት ነው?

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት እንደምንረዳው ንስጥሮስ የተባለ የቁስጠንጥንያ የቤተክርስቲያን አባት እ.ኤ.አ. በ 428 ዓ.ም ለማሪያም «ማህደረ መለኮት» ማለትም በግሪኩ ቲዮቶኮስ ለሚለው ስያሜ ተስማሚነት በመጠንቀቅ ሲያስብ እንዲህ አለ:- "እግዚአብሔር እናት ሊኖረው አይችልም:: የሥላሴ አባላትን ማስገኘት የሚችል ፍጥረት ደግሞ የለም:: ስለዚህ ማርያም የእግዚአብሔር ማደርያ አልነበረችም÷

እርሷ ለእግዚአብሔር መጠቀሚያ የሚሆን ሰው ማደሪያ ሆናለች!" ብሏል::[14]

ከዚህ ከንስጥሮስ አባባል ንስጥሮሳዊነት የተሰኘ የታወቀው የስህተት ትምህርት መነጨ:: ይህ የስህተት ትምህርት የክርስቶስን አምላክነትና ሰው መሆኑን ለሁለት በመክፈል ክርስቶስ ሁለት እንደሆነ የሚያስተምር ነው:: መለኮትነቱን ሳይቃወም በሁለቱ ባሕርያት (ሰብአዊ እና መለኮታዊ) መካከል ያለው ጥምረት የፈቃድ ብቻ እንደሆነ ያምናል:: ምንም እንኳን ክርስቶስን ሁለትነት ያለው እንደሆነ ቢያመለክትም ይህ አባባሉ ለመለኮታዊ ባሕርይ ሰባዊ ግብርን ማለትም:- እንደመከራ መቀበል ያለውን ድርጊት ካለመቀበል የተነሳ በምድር ከድንግል የተወለደው የእግዚአብሔር መጠቀሚያ የሚሆን ሰው ማለቱ ክርስቶስ ሁለት ነው ለሚል ትምህርት መሠረት ሆኗል::

ይህ የመናፍቅነት ትምህርት እ.ኤ.አ. በ 431 ዓ.ም በኤፌሶን በተደረገው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባዔ ተወግዟል:: ይህ የኤፌሶኑ ጉባኤ በእስክንድርያው ፓትሪያርክ በቅዱስ ቄርሎስ የተመራ ነበረ:: ንስጥሮስ ከጉባኤው ወገዛ በኋላ የይቅርታ ደብዳቤ እንደጻፈ ቢታመንም ይህን አመለካከት ይዘው የተራመዱ ክርስቶስ ሁለት አካል አለው ወደሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቴ በምትለው በቅዱስ ቄርሎስ መሪነት የተከሄደው ይኸው ጉባዔ ንስጥሮስ የክርስቶስን ሁለት ባሕርያት በመነጣጠሉ የማይከፋፈልና የማይለያይ በወንጌላት የተገለጸው አንድ ክርስቶስን አላንጸባረቀም የሚል ወገዛ ከማሳለፉ አልታቀበም ነበር:: በአጠቃላይ ይህ ንስጥሮሳዊነት ክርስቶስ ሁለት አካል (persons) ነው ይላል:: ይህንን በመግለጫ ለማስረዳት ካስፈለገ የክርስቶስ አንዱ አካል በመለኮትነት ባሕርይ በሰማይ÷ ሌላውና ሁለተኛው አካል በሰብአዊ ባሕርይ በምድር ነበር ይላል:: ይህንን ኑፋቄ በሚከተለው ማብራሪያ ተመልከቱት:-




ክርስቶስ ቁ 1
በሰማይ

ክርስቶስ ቁ 2
በምድር

ይህ በንስጥሮስ የተሰነዘረው አሳቤ በታሪካዊ ሥነ መለኮት ውስጥ በግልጽ ለተቀመጠው የክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን ግንኙነት እንደ መፍትሄ የቀረበ ነበር:: ሆኖም ግን ክርስቶስ አንድ እንጂ ሁለት እንዳይደለ የሚያመለክቱ በርከታ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች መመልከት አስፈላጊ ነው:-

1 ክርስቶስ ሁለትነት (Dual personality) እንዳለው የሚያመለክት ምንም የመጽሐፍ መረጃ አለመኖሩ::

2 ሁለቱም የክርስቶስ ባህርያት ማለትም ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰው መሆኑ በአንድ ባለቤት (subject) መገለጻቸው (ዮሐ 1:14፣ ገላ 4:4፣ 1ጢሞ 3:16)::

በክርስቶስ ሥራ ላይ ማለትም በግልጽ የመለኮት ወይም የሰው ግብር መሆኑን ሳይጠቁም የአንድ ጥምር ባለቤት (unfied subject) የሚያመለክቱ ክፍሎች መኖራቸው (ኤፌ 2:16-18፣ 1ዮሐ 2:1-2):: እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ ቢናገርም እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም ከመግለጽ ስለማይመለስ ይህ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ የሆነው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመውን ግብር በአንድ አካል (person) ይገልጽልናል (1ዮሐ 4:2 ከ4:15 እና 5:5ጋር ይነጻጸር)::

በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንዱ ባሕርይ ግብራት መጠሪያነት የተገለጹ ቢሆኑም አንድ አካል መሆኑን ማመላከታቸው:-

ሀ) በመለኮት መጠሪያ ሳለ በሰው ግብር (በግብረ ትሥብእት) የተገለጠባቸው ክፍሎች (1ቆሮ 2:8፣ ሐዋ 20:28፣ ቆላ 1:13-14፣ ሮሜ 9:5፣ ሉቃ 1:43፣ 2:11)::

ለ) በሰው መጠሪያ ሳለ በመለኮት ግብር (በግብረ መለኮት) የተገለጠባቸው ክፍሎች (ዮሐ 3:13፣ 6:62፣ ማቴ 12:8፣ 9:6፣16:፣ 24:29–31፣ 25:31–34፣ 63–65፣ ሐዋ 7:57):: በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ መጠሪያ ሳለው መለኮታዊ ግብርን የሚፈጽም የአካላዊ ቃል የትሥጉት አካል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንንሚያስተምር መረዳት እንችላለን::

እንግዲህ ከእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች በመነሳት ክርስቶስ አንድ እንጂ ሁለት እንዳይደለ መናገር የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር አንዱ ክርስቶስ *በመለኮት መጠሪያ ሳለ በሰው ግብር፥ በሰው መጠሪያ ሳለ በመለኮት ግብር* መገለጹ በተጨማሪም የአካላዊ ቃል ሰው መሆን

ይኸውም «ቃልም ሥጋ ሆነ» የሚለውን ሃሳብ ራሱ «ቃል» እግዚአብሔር ሲሆን ሳለ ሰው እንደሆነና ክርስቶስ አንድ መሆኑን አበክሮ የሚገልጽ ነው:: ሆኖም ግን እነዚህ ሁለት ባሕርያት (የአምላክነት እና የሰው) በአንዱ ክርስቶስ ውስጥ ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው? ኢየሱስ ሁለቱንም ባሕርያት ያሉት ሆኖ በማፈራረቅ ይጠቀምባቸዋልን? አለያም ምን ጊዜ እና እንዴት የሰው ባሕርይን÷ መቼ ደግሞ የመለኮት ባሕርይን ይጠቀም ነበር?

አንዳንዶች ኢየሱስ ከመስቀል ሞቱ በፊት በሰው ባሕርይ÷ ከትንሣኤው ጀምሮ ደግሞ በአምላክነት ባሕርዩ እንደተገለጠ ይናገራሉ:: ሌሎች ደግሞ ኢየሱስ የሁለት ባሕርያት በአንድ አካል ውስጥ እንደሆነ ይናገራሉ:: አሁንም አንዳንዶች ከሁለት ባሕርያት አንድ አካል እንደሆነ ያስተምራሉ:: ለመሆኑ የሁለቱ ባሕርያት (የአምላክነት እና የሰው) ግንኙነት በአንድ አካል ውስጥ የተገለጸው እንዴት ነው?

### 1.2.5.2. ክርስቶስ የአምላክ እና የሰው «ተዋሕዶ» (አምላክ–ሰው)?

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት እንደምንረዳው የክርስቶስን አምላክነት በመቃወም የጀመረው ኑፋቄ÷ ሰው እንደሆነ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትም ላይ ተከስቶ ነበር:: በሁለቱም አቅጣጫ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በመመርመር ቅዱሳን አባቶች ወገዛን ያሳለፉና ለአቃቤ መሠረተ እምነት ገድላቸውን ያበረከቱ ሲሆን ይህ የኑፋቄ ይዘት በቀጣይነት የሁለቱ ባሕርያትን ግንኙነት በተመለከተ ምንም አይነት ህብረት የሌላቸውና እንዲያውም ክርስቶስ ራሱ እንኳ ሁለት አካል እንደሆነ በንስጥሮስ አማካኝነት ከተሰነዘረው እሳቤ ንስጥሮሳዊነት የተባለ የኑፋቄ ትምህርት እንደተነሳ ለመግለጽ ሞክሬአለሁ::

ይህ የክርስቶስ አንድ አካል መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት የተደገፈ ሲሆን ያው አንዱ አካል ያለው ባሕርይን በተመለከተ አሁንም ከታሪካዊ ሥነ መለኮት ረገድ ቀጣይ የቤተክርስቲያን አባቶች የውይይት አጀንዳ ሆኗል:: በመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ላይ በተደረገ ውይይትና ክርክርም ቅዱስ ቄርሎስ እ.ኤ.አ. 412 ዓ.ም. ጀምሮ ቴዎፍሎስን በመተካት የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ፓትሪያርክ በነበረበት ዘመን የሁለቱ ባሕርያትን ግንኙነት ከቅዱስ ቄርሎስ ሃሳብ ጋር በመስማማት ቃላት ሳይሆኑ ቃላቱ ያቀፏቸው ትርጉሞች ላይ የማተኮርን መርህ በመከተል ስለ *የእግዚአብሔር ቃል ትሥጉትነት አንድ ባሕርይ እና የእግዚአብሔር ቃል አንድ አካል በ (ከ) ሁለት ባሕርያት ይናገራል*::[15]

ይህ አስተምህሮተ ክርስቶስ እ.ኤ.አ. ከ433 ዓ.ም. ጀምሮ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን አባቶች የእምነት መግለጫ ነበር::

በኢትዮጵያውያን መምሬዎችም ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደሆነና በሰውነቱ (የትስብእት አካል) የባሕርይ አምላክ ወይም የአብ የባሕርይ ልጅ እንደሆነ÷ ከአባቱ ጋር እኩል በመሆን መለኮታዊ ግብርን እንደፈጸመ አፈሊቃውንት አክሊሉ ካስፈሩት መጥቀስ ይቻላል::[16]

በቅዱስ ቄርሎስ የእምነት መግለጫ የክርስቶስ አንድ አካል መሆን በአንድ ባሕርይነቱ ከመጠቀሱም በላይ ይህ አንድ ባሕርይ ከመለኮት ወደ ሰው ከሰው ወደ መለኮት ባህርይ መወራረስ የሌለበት መሆኑን ነው:: የዚህ አገላለጽ ትክክለኛ ግንዛቤን በቀላሉ ማግኘት አስቸጋሪ ነው:: ሆኖም ግን የቅዱስ ቄርሎስ መሠረተ እምነት የእግዚአብሔር ልጅ በድንግል ማህጸን የሰው ልጅ ሆኖ መወለድ አንድ እንጂ ሁለት እንደማያሰኘውና የትሥጉት አካል ያደረጋቸው ማናቸውም ግብራት የአንዱ የክርስቶስ ግብር መሆናቸውን አበክሮ የሚገልጽ ነበር:: ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ አምላክ–ሰው ማለትም መለኮት ሲሆን ሰው እንደሆነ እንጂ መንታነት እንዳለው የሚያመለክቱ አስተምህሮዎችን ትቃወማለች:: የእስክንድርያም ቤተክርስቲያን በዚህ በ ቅዱስ ቄርሎስ ዘመን በጸደቀው የእምነት መግለጫ ስትመራ ከቆየች በኋላ ቅዱስ ቄርሎስ በሞት በመለየቱ በእርሱ ምትክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ መንበሩን ተረክቧል::

እንግዲህ ይህ የቅዱስ ቄርሎስ የእምነት መግለጫ በኢትዮጵያም ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘና ከቤተክርስቲያን ታሪክ አንጻርም ኢትዮጵያ በወቅቱ የዚህ *የአሃዱ ባሕርይ* (አንድ ባሕርይ) ባህል ተከታይ እንደ ሆነች ይታመናል:: በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ያላትን ቤተክርስቲያንን ታሪክና አስተምህሮት ከምድራችን የወንጌል ብስራት አንጻር መመልከቱ የተዋሕዶ ትምህርት ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር ያለውን ትስስርና በቤተክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ በአገር ውስጥ የተካሄዱ ውይይቶችን እንዲሁም አገር በቀል ሥነ ክርስቶስ መጎልበትን መቃኘት አስፈላጊ ነው::

### 1.2.5.3. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የታሪክ አሰሳ እና የተዋሕዶ አስተምህሮቷ

በኢትዮጵያ ምድር ከክርስትና ብስራት አስቀድሞ የአረማዊነት መስፋፋት በከፍተኛ ደረጃ እንደነበረ ታሪክ ያመለክተናል:: ወደ ኢትዮጵያ ምድር በመጀመርያ እንደገቡ የሚነገርላቸው ከኖህ ልጆች የካም ልጅ የኩሽ ዘሮች እንደሆኑ ይነገራል:: በዚህ በነገደ ኩሽ ትኩረት መሰረት ደግሞ በምድር ተንቀሳቃሽ የሆኑ ፍጥረታት ይመለኩ እንደነበረ የሚያመለክቱ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ:: እነዚህም የአምልኮ ሥርዓቶች ከፋርስ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ እንደማይቀሩ ይገመታል::

በኢትዮጵያ ምድር የእባብ አምልኮ የተለመደ እንደነበረ የሥነ ቅርስ ባለ ሞያዎች በአክሱም ምድር ያገኟቸውን ማስረጃዎች ዋቢ በማድረግ ይጠቅሳሉ:: በጮራመጽሔት እንደተገለጸው ደግሞ በቤት እንስሳት÷ በአራዊት÷ በአእዋፍ÷ በኮረብታ÷ በሐይቅ÷ በወራጅ ውሀ÷ በሚሳቡ ፍጥረታት (የእባብ አይነቶች) ÷ በዛፎች÷ በድንጋዮች የማምለክ ልምድ የነገደ ካም ዝርያዎች ትውፊት ነበር[17] በማለት በኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የነበረውን አምልኮ ይጠቅሳል::

በሌላ አቅጣጫ የብዙ አማልክት አምልኮን (Polytheism) በቀይ ባህር በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ነጋዴች የተለያዩ የሰማይ÷ የምድርና የባህር አማልክትን አስተዋውቀዋል:: በመቀጠልም በጮራ መጽሔት መሠረት ደግሞ የጸሐይ÷ የጨረቃ÷ የከዋክብት አምልኮ ከነገደ ሴም ዝርያዎች ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሳባውያን ትውፊት (ውርስ) ነበረ የሚል ትረካ ይቀርባል:: ይህም አይነት አምልኮ በደቡብ አረቢያ ከተገኘ ው የአምልኮት ቅርስ ጋር ስለሚመሳሰል ሳባውያን እንደ ፊደላቸው ሁሉ ስርአተ አምልኮአቸውን ይዘው ገብተው ነበረ ቢባል ያስኬዳል:: ይህ እንግዲህ እንደ ስልጣኔ እንቅስቃሴ የተቆጠረና ሰዎች ከከበቧቸው ፍጥረታት ወደ ታላላቅ ግኡዛን አይኖቻቸውን በማቅናት ለአምልኮ የላቀ ነገርን መፈለጋቸውን አመላካች ነው::[18]

ከዚህ ከአረማዊነት ጎን ለጎን ይሁዲነት በኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና ታሪክ የጎላ ስፍራ ነበረው:: ንግስተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ንጉስ ሰሎሞንን መጎብኘቷና ጸንሳ መምጣቷ ከዚያም ሚኒሊክን መውለዷ ይነገራል:: ሚኒሊክ ሲያድግ አባቱን ሰሎሞንን ለመጎብኘት ኢየሩሳሌም እንደሄደም ይተረካል:: ከዚያም ከሌዊ ነገድ ብዙ እስራኤላውያንንና የቃል ኪዳን ታቦት ይዞ እንደመጣና ይሁዲነት በኢትዮጵያ የመስፋፋቱ ትውፊት አለ::[19]

ቅድመ ክርስትና ኢትዮጵያ ይህንን የሚመስል ታሪክ የነበራት ሲሆን ክርስትና በኢትዮጵያ የመበሰሩን ጉዳይ በተመለከተ አራት የተለያዩ አመለካከቶች ይሰነዘራሉ:- የመጀመሪያው በሐዋ 8:26-40 መሰረት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በኩል የሚል ሲሆን ይህ ጃንደረባ ከፊልጶስ ወንጌልን ሰምቶ ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት እንደሰበከ ይነገራል:: ሁለተኛው በበዓለ ጴንጠቆስጤ በተገኙ ኢትዮጵያውያን በኩል እንደገባም የሚናገሩ አሉ:: እንደ ጆን ክርሶስቶም ያሉ የታሪክ ተመራማርያን በሐዋ 2 መሠረት ለበአሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን የሰሙትን የወንጌል የምስራች ይዘው በመመለስ እንደ ሰበኩ ይናገራሉ:: ሦስተኛው ሐዋርያው ማቴዎስ ወንጌልን ለኢትዮጵያ እንዲያደርስ ዕጣ ወጥቶለት

እንደ ነበርና እርሱም መጥቶ ስለ ወንጌል መስዋእት እንደሆነ የሚነገር ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግን ወንጌልን ያለ ደም ማፍሰስ እንደተቀበለች ታምናለች:: ሌላውና አራተኛው አመለካከት በፍሬምናጦስ በኩል የሚል ሲሆን ከዚያ በፊት ግን በኢትዮጵያ ምድር የሮም ነጋዴዎች የጸሎት ቤቶች እንደነበሯቸው፥ በግልም ያመልኩ እንደ ነበር የሚያመላክተው ነው::

የጢሮስ ፈላስፋ እንደሆነ የሚነገርለት መሮጼዎስ ከሁለት ዘመዶቹ ከፍሬምንጦስና ከኤዲስዮስ ጋር ህንድን ለመጎብኘት በጉዞ ላይ እንዳለ ቀለብ ያልቅባቸውና በአፍሪካ ወደብ ላይ ያርፋሉ:: ሕዝቡ በዚያን ወቅት ለሮም ዜጎች ከፍተኛ ጥላቻ ስለነበራቸው በመርከቧ ውስጥ ያሉትን በሙሉ ገድለው ፍሬመንጦስንና ኤዲስዮስን ብቻ ያተርፏቸዋል:: በመቀጠልም ወደ ንጉሡ ያመጧቸዋል:: ኤዲስዮስን ጠጅ አሳላፊ፥ ፍሬምናጦስን ጸንደረባና ጸሐፊ አድርጎ እያገለገሉት ሳለ ንጉሡ ይሞታል::

ይህ ንጉሥ ከመሞቱ በፊት ወደ ሃገራቸው መሄድ ከፈለጉ እንዲሄዱ ፈቅዶላቸው ነበር:: ነገር ግን ንግስቲቱ ልጇ እስኪያድግ ድረስ ሕዝብን በመምራት ረገድ እንዲያግዟት ለመነቻቸው:: ልጇ አድጎ ሃገር ለመምራት በቻለበት ወቅት ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ለመኑት:: ኤዲስዮስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ ሄዶ ፍሬምናጦስ ግን ወደ እስክንድርያ በመሄድ ለአዲሱ ፓትርያርክ ለአትናቴዎስ ጉዳዩን ሁሉ ተረከለት:: በአክሱም እያደገ ያለውን ክርስትናን የበለጠ ለማስፋፋት ጳጳስ እንዲሾም ጠየቀው:: የቀሳውስቱን ጉባዔ ከሰበሰበ በኋላ ፓትርያርኩ ፍሬምናጦስ ራሱን ለአክሱም ጳጳስ አድርጎ ሾመው::

ክርስትና የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ መገለጽ በሀገራችን ታሪክ ከፍተኛና የጎላ ድርሻ ነበረው:: ኢትዮጵያውያን ለፍሬምናጦስ ያላቸው አቀባበል ባወጡለት ስም የተንጸባረቀ ነበር:: ፍሬምናጦስን አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (የሰላም አባትና ብርሃንን ገላጭ) ብለው ስም አውጥተውለት ነበር:: በ356 ዓ ም የአክሱም ገዢዎች የነበሩ ዒዛናና ሳይዘናስ ከተጠመቁ በኋላ ስማቸው አብርሃ (አብርሆት ሰጪ) እና አጽብሃ (ንጋት ሰጪ) መባላቸው እንመለከታለን:: ኢትዮጵያ የአርዮስ ትምህርት የተወገዘበት እ ኤ አ በ325 ዓ/ም የተካሄደውን የኒቂያ ጉባዔ ባትካፈልም ከአትናቴዎስ ጋር የኒቅያን ጉባኤ ውሳኔ ተቀብላለች::

እ ኤ አ ከ 350-650 ዓ/ም የክርስትና መስፋፋት በኢትዮጵያ እንዴት እንደ ነበር ስንመለከት:- ቅዱስ ፍሬምናጦስ በግብጻዊው ሚናስ እንደተተካና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የግብፅ (የእስክንድርያ) መሪነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ እንደተንጸባረቁ እንመለከታለን::

እ.ኤ.አ. በ 480 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ የመጡና በንጉሥ እልዓሜዳ አቀባበል የተደረገላቸው ዘጠኙ ቅዱሳን በመባል የሚታወቁ እንደነበሩ ይታመናል:: ከዘጠኙ ቅዱሳን ውስጥ በጣም ታዋቂዎቹ:- ዘሚካኤል (አረጋዊ)÷ ጰንጠሌዎን÷ አፍጼ እና ገሪማ ወይም ይሳቅ ይባላሉ:: እነርሱም ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡና የአንድ አስተምህሮት ተከታዮች ነበሩ:: ከዚህ የተለየ አስተምህሮታቸው የተነሳ ከሃገራቸው ሳይሰደዱ እንደማይቀር ይታመናል:: ከዚህም የተነሳ ሁሉም የኬልቄዶኑ ጉባኤ ውሳኔን የሚቃወሙ እንደሆኑ ይነገራል:: በአክሱም የሕዝቡን ቋንቋ አጥንተው ከሕዝቡ ባህልም ጋር ራሳቸውን አስተዋውቀዋል:: በመቀጠልም ወደ ተለያየ ስፍራ በመሄድ ገዳማትን መመስረት ጀመሩ:: አባ ጰንጠሌዎንና አባ ሊቃኖስ ብቻ አክሱም አካባቢ ሲቀሩ ሌሎቹ ራቅ ያሉ ስፍራዎች ሄደው የባዕድ አምልኮ ያለባቸውን ቦታዎች መድረስ ጀመሩ:: ዘሚካኤል (አረጋዊ) ወደ ደብረ ዳሞ በመሄድ የእባብ አምልኮን በማጥፋት ገዳም ተከሉ:: የዘጠኙ ቅዱሳን ስም እና ክብረ በዓላቸው እንደሚከተለው ነው[20]:-

1. ዘሚካኤል ወይም አረጋዊ ——————— ጥቅምት 14
2. ጰንጠሌዮን ——————————— ጥቅምት 6
3. ገሪማ ወይም ይስሐቅ ——————— ሰኔ 17
4. አፍጼ ———————————————ግንቦት 29
5. ጉባ ———————————————ግንቦት 29
6. አሌፍ ———————————————መጋቢት 11
7. ይምዓታ ——————————————ጥቅምት 28
8. ሊቃኖስ ——————————————ሕዳር 28
9. ጽሕማ ——————————————ጥር 16

ዘጠኙ ቅዱሳን መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ በመተርጎም ታላቅ አስተዋፅዖ ነበራቸው:: አዳዲስ ቃላትን (ለምሳሌ:- ሃይማኖት÷ ቄስ÷ ጣዖት ወዘተ ያሉትን) አስተዋውቀዋል÷ መጽሐፍ ቅዱስን በግዕዝ ቋንቋ ተርጉመዋል:: እያንዳንዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ቢያንስ አንዱን ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍትን መተርጎማቸው ይታመናል:: በቅዱስ ቄርሎስ ስም የአስተምህሮት እውነታዎችን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቀኖናን ተርጉመዋል:: የገዳም ህግጋትን የሚያንጸባርቁ ጽሑፎችንም ተርጉመዋል÷ የቅዱስ እንጦንስ የሕይወት ታሪክ የሆነውንና በቅዱስ አትናቴዎስ የተጻፈውን መጽሐፍም ተርጉመዋል:: እነዚህ መጻሕፍት ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አስተምህሮት የተመሠረተባቸው መጻሕፍት ናቸው::

አስቀድሞ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እ.ኤ.አ በ 433 ዓ.ም የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ በነበረው በቅዱስ ቄርሎስ አማካኝነት የጸደቀው የአሃዱ ባሕርይ ባህል ተከታይ

እንደሆነችና ቅዱስ ቄርሎስ በኢትዮጵያ አስተምህሮተ ክርስቶስ ውስጥ ታላቅ ስፍራ እንዳለው ይታመናል:: ከዚህም የተነሳ ቅዱስ ቄርሎስ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር ያለው ትስስር ከታሪክ እንደምንረዳው ከፍሬምናጦስ (አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን) እና ከዘጠኙ ቅዱሳን የአሃዱ ባሕርይ ባህል ተከታይነት የተነሳ ነው::

እነዚህ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መመሥረት ታላቅ አስተዋጽያ የነበራቸው የእምነት አርበኞች ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር ከነበራቸው ትስስር የተነሳ የእስክንድርያ አባቶች ያወገዟቸውን እያወገዙ የሚጓዙ ለመሆናቸው አጠያያቂነት የለውም:: ስለዚህም እ.ኤ.አ. በ 432 የኤፌሶኑን ጉባዔ የመራው ቅዱስ ቄርሎስ በ 444 ዓ.ም በሞት ከተለየ በኋላ ፓትሪያርክ የነበረው ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እጅግ የሚከበር ሲሆን በምሥራቃውያን (የሮም ካቶሊክና የሮም ኦርቶዶክስ) የኬልቄዶን ጉባዔ ተከታዮች ዘንድ ግን ዲዮስቆሮስ ከቅዱስ ቄርሎሰ ትምህርት በመሳት ወደ ኑፋቄ እንዳመራ ይነገራል::

ስለዚህም ናሁአዳም ለማቅረብ እንደሞከረው:-

> ይልቁንም በኬልቄዶኑ ጉባዔ ድል የእኛ ነው ያሉቱ የሁለት ባሕርያት ባህል ተከታዮች የተንጣለለ ሰፊ ግዛትን በነበረው በሮም መንግስት ድጋፍ ከዚህ ተመለስ ያልተባለ የበላይነትን በግድ ለማሳወቅ ተግተው ተንቀሳቀሱ:: የእስክንድርያስ ቤተክርስቲያን አባት የሆነውን ሊቀ ጳጳሳት ዲዮስቆሮስን ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ገና በክርክሩ መግቢያ ላይ ጉባዔው አወገዘው:: ይኸው ጉባዔ የውግዘቱን ምክንያት ለእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ማስረዳት አልቻለም÷ ቤተክርስቲያን የጉባዔውን የውግዘት ውሳኔ መቀበል አለመቀኗንም ለማወቅ ጥረት አላደረገም÷ ውግዘቱን የምትቀበል ከሆነ ሌላ አስተዳዳሪ አባት እንድትመርጥ አላሳበም:: ጉባኤው ከአንዱ የግፍ ስራ ወደ ባሰ የግፍ ስራ ተሸጋገረ:: የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የምታከብረውን ዲዮስቆሮስን በመንግስት ስልጣን ተጠቅሞ በደሴተ ጋግራ አሳሰረው:: ጥርሱ እስኪሰበር ድረስ አስደበደበው÷ በዚህም አልተገታም ያለ ምእመናት ፈቃድና ምርጫ የሁለት ባሕርያትን ባህል ያስፋፋልኛል ያለውን ፕሮቴሪዮስ የተባለውን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት እንዲሆን ሰየመ:: እስክንድርያውያን አንቀበልም ሲሉ በመንግስት ጦር አሳጅቦ በዲዩስቆሮስ መንበር እንዲቀመጥ አደረገ:: ዳሩግን ምእመናት አበክረው በመቃወማቸው የተነሳው ብጥብጥ መካከል አዲሱ ተሻሚ ሞተና ምእመናት ራሳቸው የመረጡትን ጢሞቴዎስን በመንበሩ ተኩ::[21] በማለት አስፍሯል::

ምሥራቃውያን ሆነው የኬልቄዶን ባህል ማለትም እ.ኤ.አ. በ 451 ዓ.ም የተካሄደውን ጉባዔ ውሳኔ የተቀበሉና ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉት የሚሉቱ (የሮም ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ግሪክ÷ የራሽያ÷ ቆጵሮስ÷ ቁስጥንጥንያ÷ ሩማንያ÷ ሐንጋሪ እና ሰርቢያ በተጨማሪም የግብፅ የሮም ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት÷ የሶርያ÷ የሊባኖስ÷ የአሜሪካ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በሲና በረሃ የሚገኘው የቅዱስ ካትሪን ገዳም ያሉቱ) ስለ ዲዮስቆሮስ የሚያሰፍሩትም ደግሞ ዲዮስቆሮስ የአውጣኬ ደጋፊ ሆኖ እንደነበር የሚገልጽ ነው::[22] እንግዲህ እውነቱን ለታሪክ እንተወውና ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ አንጻር የአንድ ባሕርይ ባህል ከቅዱስ ቄርሎስ ወይስ ከአውጣኬ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ መቃኘትና መተማመኛ መያዝ አስፈላጊ ነው::

በኢትዮጵያ ምድር ከ4ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እንደሆነ መታመኑን በተለይም እ ኤ አ በ 480 የዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት ለአሃዱ ባሕርይ ባህል መጎልበት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደነበረው ግልጽ ነው:: ዶናልድ ክረሜይ በተሰኙ የታሪክ ምሁር አገላለጽ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተዋሕዶ አስተምሮትን በአጼ ዘረ ያእቆብ (ከ1434-1468) ዘመን እንደገና እንዳጸናች በመግለጽ ይህ አስተምሮት ከአውጣኬ መለኮት ሰብአዊነት የዋጠበት አንድ ባሕርይ ባህል የተለየ መሆኑን አስረድተዋል::[23] እንደ ተስፋእግዚ አባባልም ኢትዮጵያ ከሶርያና ከግብጽ በመጡ ሁለት መነኮሳት እ.ኤ.አ .ከ1435-1468 በነገሰው በበእደ ማርያም ዘመን የተዋሕዶ አስተምሮትን እንደገና አጽንታለች::[24]

በአጠቃላይ ከታሪክ ለመረዳት እንደሚቻለው እስከ 1604 የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአሃዱ ባሕርይ ባህልን ያለ ምንም ለውጥ የተቀበለች መሆኗን ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል:: ምንም እንኳን ይህን የአሃዱ ባሕርይ ባህል የታሪክ ጸሐፊዎች ተዋሕዶ ብለው ቢገልጹትም በስያሜ ላይ ግን አወዛጋቢ ነገሮች አሉ::

በኢትዮጵያ ምድር ገዳማት የሥነ መለኮት ትምህርትና አገር በቀል ሥነ መለኮት መፍለቂያ ስፍራ እንደነበሩ ይታመናል:: በአመሠራረታቸው ጥንታዊነት እንዳላቸው የሚነገርላቸው ሦስት ገዳማት:– ደብረ ሊባኖስ እ.ኤ.አ.በ 1312 በቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ÷ ደብረወርቅ እ.ኤ.አ በ 1333 በቅዱስ እዮስታቴዎስ እንዲሁም ደብረ ቢዘን በቅዱስ ኢዮስታቴዎስ የተተከሉ ነበሩ:: እነዚህ ገዳማት የሚገኙ -ት በቅደም ተከተላቸው በሸዋ÷ በጎጃምና በኤርትራ (በቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት) ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪ «ቅብዓት» በመባል የሚታወቅ ቡድን (ቤተ–ኢዮስቴዎስ) ለመባሉ በኢዮስቴዎስ በተመሠረተው ገዳም መምሬዎች ዘንድ መገኘቱ÷ የተዋሕዶ እምነትም

(ቤተ–ተክለሃይማኖት) ለመሰኘቱ በተክለ ሃይማኖት በተመሠረተው በደብረ ሊባኖስ ገዳም መምሬዎች ዘንድ መፍለቁ ይነገራል:: በሂደት ምናልባትም እሳቸው ራሳቸው የካቶሊክ ኃይማኖት ወይም የኬልቄዶን ባህል ተከታይ እንደሆኑ በሚነገርላቸው በአጼ ሱሲኒዮስ ዘመን (1607-32) የአስተምህሮት ጅማሬው እንደሆነ የሚነገርለት አዲስ ትምህርት በደብረሊባኖስ ሊቃውንት ዘንድ በ 1763 ዓ.ም ተከሰተ:: ይህ ቡድን ስያሜው የፀጋ ልጅ ወይም «ሦስት ልደት» የሚባል ነው::

እነዚህ በተለይ በደብረ ሊባኖስ ገዳም መምሬዎች ዘንድ የነበሩ የተዋሕዶና የፀጋ ልጅ ቡድኖች ሁለቱም ቤተ–ተክለሃይማኖት እንደሆኑ የሚናገሩ ናቸው:: እንደ አድማሡ አባባል የፀጋ ልጅ ቡድን የማይገባው ቤተ–ተክለ ኃይማኖትነት የተቀበለው ሙዋሊም ጴጥሮስ ኩሪንቺ የተባለ ካቶሊካዊ ሰው ወልድ በቅብዓት የፀጋ ልጅ ሆነ የሚልን ትምህርት እንዲያስተጋባ አስተምሮት ስለ ነበረ ነው እንጂ የቅዱስ ተክለ ኃይማኖት አስተምህሮ አልነበረም በማለት ይከራከራሉ:: በመቀጠልም የዚህ የፀጋ ልጅ ትምህርት ምንጩ ካቶሊክ እንጂ የፕሮቴስታንቱ ፒተር ኃይሊንግ እንዳይደለ ሲገልጹ የፕሮቴስታንቶች ሚስዮንማ "እመን ብቻ ትድናለህ!" የሚልን ስብከት እንደ ባንድራ ከማንገብ ውጪ ለፀጋ ልጅ ትምህርት መንስዔ አይደሉም የሚልን ሃሳብ አንጸባርቀዋል::[25]

ሆኖም በተለይ «ተዋሕዶ» የሚለውን ስያሜ በመጠቀም ቀዳሚ በመሆን ረገድ ውዝግብ አለ:: ከዚህም ባሻገር ሁለቱም «ተዋሕዶ» ስያሜአቸው እንደሆነ የሚናገሩ ሲሆን አስተምህሮታቸውን በተዋሕዶ ስም ለማስተጋባት በሚያደረጉት ሙከራም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተዋሕዶ አስተምህሮት በሁለቱ አመለካከቶች ልዩነት ምክንያት ጥርት ብሎ እንደማይታወቅ ብዙዎች ሲናገሩ ይስተዋላል:: ከዚህ የፀጋ ልጅ የተዋሕዶ ስያሜ ይገባኛል ባይነት የተነሳ አንዳንዶችም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ የኬልቄዶን ባህል የምትለየው በምን እንደሆነ ግራ መጋባት ውስጥ ናቸው:: ለዚህም የካቶሊኩ ዶ/ር አባ አየለ ተክለ ኃይማኖትም የተዋሕዶ አስተምህሮ ከኬልቄዶን ጉባዔ ውሳኔ ልዩነቱ የቃላት አጠቃቀም ብቻ እንደሆነ ላቀረቡት ክርክርና የማቀራረቢያ ሃሳብ ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ *መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና* በተባለው መጽሐፋቸው የኬልቄዶኑ ውሳኔ ከንስጥሮስም ሆነ ከአውጣኬ ያልተለየ ኑፋቄ እንደሆነና የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም አበክራ እንደምታወግዘው ገልጸዋል::[26] ዶ/ር አባ እ ኤ አ በ 1982 ባሳተሙት *The Ethiopian Church and Its Christological Doctrine* በተባለው መጽሐፋቸው አንዳንዶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአውጣኬን አሃዱ ባሕርይ (Eutyches'Monopysitism) እንደምታምን ሲያስረዱ ሌሎች ይህን ኑፋቄ የሚያስዝብ አይነት

እምነት እንዳላት ሲናገሩ ይደመጣል፥ ሌሎች በጣም ጥቂቶችም ከኢትዮጵያውያን ጥንታዊ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንደሆነ ይናገራሉ በማለት የተለያዩ አመለካከቶችን ሰንዝረዋል።[27] አባ አየለ የዛሬዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአውጣኬን አሃዱ ባሕርይ ፈለግ የምትከተል እንዳይደለችና የኬልቄዶን ጉባዔን ውሳኔ ካልተቀበሉቱ አብያተ ክርስቲያናት (Non-Chalcedonian Churches) እንደምትመደብም ገልጸዋል።[28]

እንግዲህ ከኢትዮጵያ ነገስታት ውስጥ አጼ ሱሲንዮስ (1607–1632 ዓ/ም) የካቶሊክን እምነት እንደተቀበሉ ከሚያመለክተን የታሪክ ማስረጃ ውጪ ከሳቸው ዘመን መንግስት በፊት የሁለት ባሕርይ ባህል በኢትዮጵያ ምድር ተከስቶ የማይታወቅ መሆኑ ግልጽ ነው። በ1603/04 ዓ/ም በአጼ ሱሲንዮስ አባት በንጉስ ዘድንግል ዘመን የጀመረው የነገረ ክርስቶስ ውዝግብ ንጉስ ፋሲል በ1633 ዓ/ም የካቶሊክ ሚስዮናውያንን ከአገር በማባረር ተደምድሟል።[29] ሆኖም የሁለት ባሕርይ ባህል ተከታይ የሆነው የፀጋ ልጅ ቡድን በአጼ ቴድሮስ ዘመነ መንግስት አቡነ ሠላማ ሦስተኛ ንጉሱን ለንግስና ለመቀባታቸው እንደ ወሮታ አድርገው ንጉሱ በፀጋ ልጅ ቡድን አጠራር «ካራ» በተባለው ቡድን "ተዋሕዶ" የሚል ስያሜያቸውን በኃይል እንዳስነጠቋቸው እንዲያውም፡– "ይህንን የንጉሡን እምነት ያልተቀበለ ከፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቆረጥ!" የሚል ትዕዛዝም ወጥቶ እንደ ነበርም የሚናገሩ አሉ።[30]

ከላይ በተሰነዘሩት የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ በመመሥረት የትኛው አስተምህሮት በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ያለው እንደሆነ ስንቃኝ በመጀመሪያ «የአሃዱ ባሕርይ» ባህልን ተከትሎ ያለምንም ለውጥ ከክርስትና ጅማሬ አንስቶ ለበርካታ አመታት የተገኘው ቡድን ጥንታዊነት እዳለው ግልጽ ነው። በተጨማሪም ይህ የአሃዱ ባሕርይ ባህል የሚከተል (በአሁኑ ወቅት በስልጣን ላይ ያለውንና ተዋሕዶ በመባል የሚታወቀውን ቡድን) በኃይል ስማችንን በመንጠቁ ምክንያት «ካራ» እንደተባለ የሚገልጸው የፀጋ ልጅ ቡድን ተከታዮች የሚያቀርቡት ክስ አጸፌታው ደግሞ የተዋሕዶ ባህል ተከታዮች በፀጋ ልጅ ቡድን ካራ የሚል ስያሜ እንዴት እንደተሰጣቸው ሲናገሩ በቦሩ ሜዳው ክርክር ድልን በመቀዳጀታቸው እንደሆነ መግለጣቸው የተሻለ መከራከሪያ ሳይሆን አይቀርም።

በእነዚህ በሦስቱ ቡድኖች ማለትም በቅብዓት፥ በተዋሕዶ እና በፀጋ ልጅ መካከል በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት በ1870 ዓ.ም «ቦሩሜዳ» በመባል በሚጠራ ስፍራ በተደረገ ክርክር የፀጋ ልጅ በመባል የሚታወቀው ቡድን ተወግዟል። «የተዋሕዶ» ባህል ኦፌሴላዊ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የእምነት መግለጫ ሆኗል:: የቅብአት ቡድንም ከተዋሕዶ ቡድን ስር የተለየ አመለካከቱን ሳያስተጋባ እንዲንቀሳቀስ የተተወ ቡድን ሆኗል:: ከዚህ የተነሳ በተለይ በተዋሕዶ ስም የሚጻፉ ጽሑፎች ስማችንን የተነጠቅንና የጥንቱ ተዋሕዶ ነን በሚሉ በፀጋ ልጅ ቡድን ወይም ደግሞ እነርሱ "ካራ" ብለው በሚጠሩቸው ኦፊሴላዊ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሊጻፉ ስለሚችሉ የተዋሕዶ ምስጢር በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግልጽ እንዳይደለ መቁጠር ትክክል አይመስለኝም:: ከአስተምህሮት እሳቤያቸው አንጻር የፀጋ ልጅ ቡድን *ተዋሕዶ በተዐቅቦ* የሚለውን ትምህርት ሲያስተጋባ እነርሱ ካራ ብለው የሚጠሩት የተዋሕዶ ቡድን እሳቤ የሁለቱን ባሕርያት ያለመደባለቅና ያለመለወጥ÷ላይለያዩና በተናጥል ላይገለጹ መጠመራቸውን በመግለጽ የአሃዱ ባሕርይ ባህልን የሚያንጸባርቅ ነው:: (ለተጨማሪ ማብራርያ በመጽሐፉ ማጠቃለያ የተገለጸውን ደጋፊ ማብራሪያ ቁ 1 ተመልከቱ)::

እንደ ተስፋግዚ እምነት:- "በየትኛውም ጉባዔም ሆነ የንጉስ ትእዛዝ ኦፊሴላዊ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ በቦሩ ሜዳው ጉባዔ ወቅትም ውሳኔ አልተሰጠበትም:: ሆኖም ግን በሰላማዊ መንገድ ከአጼ ሚኒሊክ 2ኛ ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን» በመባል ትጠራለች በማለት ሲያሠፍር [31] ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ ደግሞ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን "የቅብዓት" እና "የፀጋ ልጅ" ቡድኖችን በኢየሱስ መጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ በመውረዱ አምላክ (እግዚአብሔር) እንደሆነ ማመናቸው የማደጎ ልጅነትን የሚቀበሉ (Adoptionist) መሆናቸውን በመጥቀስ ቤተክርስቲያን ልዩ የሆነውን «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን» የሚል መጠሪያን እንደያዘች ገልጸዋል::[32]

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ እምነት በአሃዱ ባሕርይ ባህል ላይ የተመሠረተና ይህም የአሃዱ ባሕርይ ባህል በቅዱስ ቄርሎስ (የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ) መሪነት ከተደረገው የ 433 ዓ.ም የጉባዔ ውሳኔ ጋር አንድ እንደሆነ÷ እንዲሁም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባቶች መካከል ከተደረገ ከቦሩ ሜዳው ጉባዔ በኋላ አገር በቀል በሆነ መንገድ የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት የተብራራበት እንደሆነ የተቆጠረበት እምነት ተዋሕዶ እንደተባለ መረዳት ይቻላል:: ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የተዋሕዶ አስተምህሮት በትክክል የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት እንደነበረና የቅዱስ ቄርሎስ ተከታይ ዲዮስቆሮስም ለዚሁ እምነት መሰዋቱን በመግለጽ እምነታቸው ተዋሕዶ እንደ ሆነም አብራርተዋል:- «....ኢትዮጵያም ለአንድ ባሕርይ ባህለ ሃይማኖት ለተሰዋው ለዲዮቆሮስ ትምህርት ታማኝ በነበረችው በእስክንድርያ ሊቀ ጵጵስና ስር ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በሚል እምነት

የጸናች ነበረችና...»[33] በማለት ዲዮቆሮስም ሆነ ከእርሱ አስቀድሞ ቅዱስ ቄርሎስ *የተዋሕዶ* እምነት ባህል ተከታዮች እንደነበሩ ይገልጻሉ።

እንግዲህ ለአስተምህሮቱ በስያሜነት የተሰጠው "ተዋሕዶ" የሚለው መጠሪያ ከቦሩ ሜዳው አገር በቀል ውይይት በኋላ ሊሆን ቢችልም፥ የአስተምህሮቱ ጥንታዊነት ግን ከቅዱስ ቄርሎስ ጋር የተቆራኘ ነው ማለት ያስችላል። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ቄርሎስን አሃዱ ባሕርይ ባህል የምታብራራበት መንገድም ሙሉ ለሙሉ ከአውጣኬ ኑፋቄ የተለየ ነው።

1.2.5.4. ክርስቶስ የአምላክ እና የሰው ባሕርያት ድብልቅ?

በቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ ስለ ክርስቶስ አምላክነትና ሰው መሆን ብቻ ሳይሆን የእርሱን ማንነት በተመለከተ በተደረጉ ጉባዔዎች ከተንጸባረቁ አሳሳች አመለካከቶች ውስጥ በሁለቱ ባሕርያት ግንኙነት ረገድ ለየብቻቸው የራሳቸው አካል እንዳላቸው በንስጥሮስ ከተሰነዘረው አመለካከት ከመነጨው ኑፋቄ በተቃራኒ መንገድ አውጣኬ የሚባል አንድ በእድሜው የገፉ ሰው ክርስቶስ ከሁለት ባሕርያት (መለኮትና ሰብአዊነት) ድብልቅና መለኮት ሰብአዊነትን የዋጠበት አንድ ባሕርይ ያለው እንደሆነ ገልጿል። በዚህ አውጣኬያዊነት በመባል የሚታወቅና ከቅዱስ ቄርሎስ በተለየ መንገድ በሁለቱ ባሕርያት መደባለቅ የሚያምን ቡድን ተከስቷል። ይህ ኑፋቄ በክርስቶስ አካል መለኮትነት ያየለበትና ሰብአዊነቱ በመለኮትነቱ የተዋጠ እንደሆነ ያስተምራል።

ከአውጣኬ አስቀድሞ በቅዱስ ቄርሎስ አማካኝነት የተደረሰበት የቤተክርስቲያን አባቶች የእምነት መግለጫ:- ክርስቶስ አንድ አካል፥አንድ ባሕርይ ሲሆን ከመለኮትነቱ ወደ ሰባዊነቱ እንዲሁም በተገላቢጦሹ የተቀየጠ ነገር የለውም የሚል ነበረ። ይህ እ.ኤ.አ. ከ 433 ዓ.ም. ጀምሮ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን አባቶች ስለ ክርስቶስ የነበራቸው እምነት ነው። ይህ የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት ቤተክርስቲያን ለሁለት በተከፈለችበት ወቅት የእስክንድርያው ቤተክርስቲያን መሪነት የተቀበሉ የምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት ማለትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ጨምሮ የእምነት መግለጫቸው ነበር።

የአውጣኬ ትምህርት ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው በማለቱ በመሠረታዊ የቃላት አጠቃቀሙ ከቅዱስ ቄርሎስ አባባል ጋር የሚስማማ ቢሆንም ከቅዱስ ቄርሎስ የአንድ አካል፥አንድ ባሕርይ እሳቤ ያፈነገጠና ኢየሱስን የሁለት ባሕርያት ቅይጥ ስለሆነ ከሰውም ከእግዚአብሔርም የተለየ መለኮትነት ያደላበት ሰው የሚያስብለው

ነው:: እንግዲህ አውጣኬ ከንስጥሮስ በተቃራኒ ሁለቱን ባሕርያት በተናጥል ከመመልከት መቀየጡ ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ አንጻር የሚያስወግዘው ሆኗል:: መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ የአምላክና የሰው ድብልቅ ሳይሆን ሁለቱ ባሕርያት ያላቸው አንድነት ከንስጥሮስ ትምህርት በተቃራኒ "የማይከፋፈልና የማይለያይ" እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ከአውጣኬም ትምህርት በተቃራኒ "የማይቀላቀልና የማይለወጥ" መሆኑን ያስረዳናል::

የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት በመከተል የአንድ አካል አንድ ባሕርይን አስተምህሮት የሚቀበሉቱ የተዋሕዶ መምሬዎች አውጣኬያውያን የኢየሱስን መወለድ÷ ማደግ÷ መራብ÷ መጠማት÷ መሞትና ከሞት መነሳት የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚመለከቱባቸውን መንገዶች ጥያቄ ውስጥ ይጥሏቸዋል:: ለዚህም ዋና ምክንያቱ ኢየሱስ አምላክነቱ ሰብአዊ ባሕርዩን እንደዋጠው በመናገራቸው እርሱ መለኮት ብቻ ከሆነ ለመለኮት የማይገቡ ግብራትን እንዴት ሊፈጽም ይችላል ከሚል አመለካከት በመነጨ ነው:: ስለዚህ ቱሳሔ (ለውጥ ማምጣቱ) የራስን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በመተው ሌላውን ሆኖ ወደ መገኘት የሚያመራ በመሆኑ ተቀባይነት አልተሰጠውም:: በሌላ በኩል ደግሞ ቱሳሔ (ቅይጥ ባሕርይ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮች ሲቀላቀሉ (ሲደባለቁ) የሚመጣው ሦስተኛው ባሕርይን የሚያመለክት ነው:: ይህን የአውጣኬን ትምህርት በባሕርያት ውላጤ ብቻ ሳይሆን የባሕርይ ውላጤ በአካሉ ላይም የሚንጸባረቅ መሆኑን በማስተዋል ክርስቶስ የአምላክና የሰው ቅይጥ (ዲቃላ?) ባሕርይ ያለው መሆኑን የሚያንጸባርቅ ነው:: እንግዲህ ስለ ክርስቶስ አካል ከተነሳ የክርስቶስ አካል ከሁለቱ ባሕርያት የየትኛው አካል ነው? ለሚል ጥያቄ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነው::

### 1.2.5.5. የክርስቶስ አካል የ«ሰው»? የ«ቃል»? የ«ተዋሕዶ» ወይስ የሁለቱም ባሕርያት?

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት መገንዘብ እንደሚቻለው የክርስቶስ ማንነት በባሕርዩ መሠረትነት ላይ የሚፈረጅ ነው:: የክርስቶስ ባሕርይ ሰባዊ ባሕርይ ብቻ ነው ለሚሉ ለኢቦናዊቶች ክርስቶስ በሰው ብቻ ነው÷ በክርስቶስ ውስጥ መለኮታዊ ባሕርይ ሰባዊነቱን የዋጠበት አሃዱ ባሕርይ ነው በሚሉቱ ለአውጣኬያውያን ክርስቶስ አምላክ ብቻ ነው ማለት ያስችላል:: በተዋሕዶ ለሚያምኑቱ ደግሞ የክርስቶስ አካል የአምላክ – ሰው ተዋሕዶ አካል መሆኑ ግልጽ ነው::

እዚህ ላይ ተዋሕዶ የሚለውን ቃል ትክክለኛ ትርጓሜ መገንዘብ ያሻል:: እንደጮራ መጽሔት ቁ 10 ገጽ 28 ገለጻ ዛሬም ምስጢረ

ሥጋዊ የሚነገረው «ተዋሕዶ» በሚለው ቃል ነው:: የግእዙ ግስ *ዋሐደ* በአማርኛ አንድ አደረገ አንድ ሆነ ተዋሀደ ከማለት ይነሳና ተዋሕዶ መዋሐድ በአንድ መሆን ማለትን ያስከትላል::[34] በአሁኑ ወቅት ይህ ከግእዝ የተወረሰው ቃል ፍታቴ መዛባት ለትርጉሙ መዛባት አይነተኛ ምክንያት ሆኖ መደባለቅ÷ መዋዋጥ÷ መጠፋፋት የሚሉ የግእዙን ቱሳሔ ወይም ቱስሀትና ውሳጤ ትርጉም እየያዘ መምጣቱ የተዋሕዶን ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት አዳጋች እየሆነ ነው::

እንግዲህ የሁለቱ ባሕርያት አንድነት «በተዋሕዶ» በሚለው ቃል ምንጭ መሠረት አንድ መሆንን አመላካች እንጂ አንድ ለመሆን ባለው ሂደት ለውጥ ማስከተልን አያስተናግድም:: ስለዚህ ይህ አንድነት ላይነጣጠል÷ ላይቀየጥ የተደረገ ጥምረትን አመላካች ነው:: የክርስቶስን አካል የዚህ የሁለት ባሕርያት አንድነት (ጥምረት) አካል አምላክ–ሰው (God – man) ያሰኘዋል::

በአገር በቀል ሥነ መለኮት በ 1870 ዓ.ም በቦሩሜዳ በተደረገው የሦስቱ የአስተምሮተ ክርስቶስ ጎራዎች ማለትም:– በቅብዓት÷ ተዋሕዶ (ካራ) እና ሦስት ልደት (የፀጋ ልጅ) ቡድኖች መካከል በተንጸባረቁ ውይይቶች ቅብዓቶች የክርስቶስ ሥጋ በቅብዓት የባሕርይ አምለክ ሆነ የሚለውን እሳቤ ሲሰነዝሩ÷ የተዋሕዶ (ካራ) ቡድን የክርስቶስ ሥጋ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ሆነ የሚል አስተምህሮትን አንጸባርቀዋል:: የሦስት ልደት (የፀጋ ልጅ) ቡድን ደግሞ ከክርስቶስ ሥጋ ወደ መለኮትነቱ እንዲሁም በተገላቢጦሹ የተላለፉ ነገሮች አሉ የሚል እሳቤን አንጸባርቀዋል::

ከዚህ የተነሳ የተዋሕዶ ሚስጥር:– "ዳሩ ግን ከሔዋን ዘር ከተወለዱት ሁሉ ንጹህና ቅዱስ የሆነ ሊገኝ ባለመቻሉ (ኢዮ 14:4፤15፤14-16) እግዚአብሔር ወልድ ሊነሳው ያለውን ሥጋ ነፍስና መንፈስን በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል በመክፈል የተከፈለውንም በማንጻትና በመቀደስ በማዋሐድም ተጸነሰና ተወለደ::"[35] በማለት በድንግል ማህጸን የመንፈስ ቅዱስ ሚና ተዋሕዶን መተግበር እንደሆነ ገልጿል:: ይህም ማለት የክርስቶስ ሥጋው÷ ነፍስና መንፈሱ የተዋሕዶ ሥጋ÷ነፍስና መንፈስ ነው:: ከዚህም የተነሳ የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሥጋ በተዋሕዶ የባሕርይ አምላክ ሆነ ትላለች:: ይሁንና ይህ የተዋሕዶ አካል የቃል የሆነው የሥጋ÷ የሥጋ የሆነው የቃል የሆነበት ነው::

ከዚህ ለየት ያለው አስተምህሮት ደግሞ የሦስት ልደት ቡድን አስተምህሮት ነው:: በሦስት ልደት ቡድን እሳቤ መሠረት *ተዋሕዶ በተዐቅቦ* ተቀባይነት አለው:: ተዋሕዶ በተዐቅቦን ለማብራራት:–

"አንድነታቸውም በመንታነትና በክፍፍሎሽ መታወቅን መኖርና መስራትን ከሚያጠፋላቸው በስተቀር ተክለ ሰብእናቸውን (እኔነታቸውን) በመጨፍለቅ በአንድ ማምረቻ ውስጥ ተሰርተው የመጡ ቀድሞ ከነበራቸው የተለወጠ ባሕርይ ልዩ አካል ያለው ባለ ልዩ ህላዌ አያደርጋቸውም:: እንደዚሁም በመለኮትና በትስብእት ተዋሕዶ መጨፈላለቅና መዋዋጥ መጠፋፋትም እንዳይኖር የሚጠብቅ በአንቀጸ ተዋሕዶ ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው ቃል *«ተዐቅቦ ወይም ተዓቅቦ»* የሚለው ነው::"[36] በማለት ተዓቅቦን ለማብራራት በተደረገው ጥረት ሁለቱ ባሕርያት አንድነታቸው ከላይ በተገለጸው መሠረት ሆኖ በአንዱ ክርስቶስ ውስጥ "በመገናዘብ" መገኘታቸው እንደሆነ ይገልጻሉ:: በዚህም *ሥጋ* መለኮታዊ ባሕርይን እንዲሁም መለኮት ሰብአዊ ባሕርይን ገንዘቤ ብሎ ይጠቀምበታል የሚል እሳቤን ያንጸባርቃሉ::[37]

እንግዲህ የሁለቱን ባሕርያት ግንኙነት በተዓቅቦ መከላከልና አንዱ የሌላውን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ መጠቀም ከ«ካራ» የተዋሕዶ እሳቤ በተለየ *መንገድ የቃል* የሆነው *የሥጋ*÷*የሥጋ* የሆነው *የቃል* <u>እንደ</u> ገንዘብ የሆነበት (ገንዘቤ ነው ብሎ የሚጠቀምበት) አንድነት ነው:: በ«ካራ» የተዋሕዶ እምነት *ቃል* <u>*ሥጋ* *መሆኑን*</u> እንጂ *ቃል* *የሥጋ* ባሕርይን እንደ ገንዘቡ ማድረጉ አይነገርም:: ስለዚህም *የሥጋ* የሆነው *የቃል* *መሆኑን* ለማመልከት የክርስቶስ ደም የእግዚአብሔር ደም እንደሆነ÷ *የቃል* የሆነው *የሥጋ* *መሆኑንም* ለማመልከት ተዋሕዶተ አካል ክርስቶስ ዛሬም ከአብ እኩል የሚመለክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርልናል (ሐዋ 20:28 ፊል 2:10):: ለዚህም አሁን ለክርስቶስ ስንሰግድ ለአምላክነቱ እንጂ ለሠውነቱ አንሰግድም በማለት መነጣጠል እንደሌለ ግልጽ ነው::

ከእነዚህ አስተምሮቶች በተጨማሪ በታሪካዊ *ሥነ* መለኮት የሁለት ባሕርያት በአንድ አካል የየራሳቸውን ልዩ የሆነ መገኘት ሳይለቁ በተዓምር እንዳሉ የተሰነዘረ ሌላ አስተምሮት አለ:: የፀጋ ልጅ ቡድን ከዚህ የኬልቄዶን ጉባዔ ውሳኔ እንደሚለይ ሲጠቅስ ኬልቄዶናውያን የክርስቶስን *ሥራ* ለሁለቱ ባሕርያት በመከፋፈል ይናገራሉ እኛ ግን በእርሱ የተሠራው በሙሉ የአንዱ አካል *ሥራዎች* እንደሆኑ እናምናለን ይላሉ:: ለዚህም ለአብነት ያህል ኬልቄዶን በመስቀል የሞተው የክርስቶስ *ሥጋው* ነው ስትል የፀጋ ልጅ ደግሞ ገንዘቡ ባደረገው በ*ሥጋ* ባሕርይ ነው ይላሉ:: የተዋሕዶ ሊቃውንት ደግሞ መለኮት ከ*ሥጋ* ጋር ተዋሕዶ ስላለ በ*ሥጋ* ጠባይዕ (ባሕርይ ግብር) ሞተ እንጂ *ሥጋ* ብቻ ሞቶ አለምን እንዴት ያድናል ይላሉ:: ይህንን ሃሳብ በጥልቀት በክርስቶስ ግብር ላይ በምንነጋገርበት ርዕስ እንመለከታለን::

ይህ ደግሞ የተዋሕዶን ትምህርት በሁለት የተለያዩ ጎራዎች አሳቤ መሠረት የመመልከታችንን አስፈላጊነት ያጠናክረዋል። ይኸውም በቅዱስ ቄርሎስ የአሃዱ ባሕርይ ባህል መሠረት የተሰነዘረውን የእምነት መግለጫ ትክክለኛ መረዳት ፍለጋ የሚቀሰቅስ ነው። ለመሆኑ የቅዱስ ቄርሎስ የእምነት አቋም አሃዱ ባሕርይ ባህል ተዋሕዶን ወይስ ተዋሕዶ በተዓቅቦን ይደግፋል? ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት በፊት ሁለቱን አስትምህሮቶች ከማብራሪያቸው ጋር በማጣቀስ ማነጻጸር አስፈላጊ ነው።

### 1.2.5.6. የቅዱስ ቄርሎስ ምሥጢረ ሥጋዌ:- «ተዋሕዶ» ወይስ «ተዋሕዶ በተዓቅቦ»?

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የአሃዱ ባሕርይ ባህልን ለመግለጽ ተዋሕዶ የሚለውን ቃል ትጠቀማለች። እንደ ናሁ አዳም አገላለጽ ይህ ስያሜ የቤተክርስቲያኒቱ መጠሪያ የሆነው በኤፌሶኑ የምሥጢረ ሥጋዌው ጉባዔ ነው። ናሁ አዳም ቤተክርስቲያኒቱ "ኦርቶዶክስ" የምሥጢረ ሥጋዌ የእምነት መግለጫዋ "ተዋሕዶ" ስለ መሰኘቱ ሲናገር ጥንታውያን አባቶች በኒቅያ ጉባዔ ውሳኔ ተገልጦ በተተረጎመው ንጹህ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተችውን የጸናችና የቀናች ርትእት ሐይማኖትን (ኦርቶዶክስን) በሌላ ሳይበርዙና ሳያጎድሉ በመያዛቸው ራሳቸውን "ኦርቶዶክሳውያን" ስመ ሃይማኖታቸውንም "ኦርቶዶክስ" እንዳሰኙ ሁሉ በኋላም በኤፌሶኑ ጉባዔ ለምሥጢረ ሥጋዌ ተስማሚ መግለጫ ሆኖ የጸደቀውን ተዋሕዶን በአጽንዖትና በአንክሮ በመቀበላቸውና በመስበካቸው ቀድሞ በነበረው ኦርቶዶክስ በሚለው ስማቸው ላይ ተዋሕዶ ተጨምሮበት ስመ ሐይማኖታቸውን 'ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ' አሰኝተው አቆይተዋል።"[38]

ምንም እንኳን የቅዱስ ቄርሎስ ምሥጢር ሥጋዌ ተዋሕዶ እንደሆነ ቢጠቀስም በሀገር በቀል ሥነ መለኮት ሂደት በ 1870 ዓ.ም በቦሩ ሜዳ በተደረገው ጉባዔ የተዋሕዶን አስተምህሮት ለማስረዳት እንደሞከሩ የሚነገርላቸው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በኦፊሴላው መንገድ የምትወክለው ተዋሕዶና ሦስት ልደት ወይም የፀጋ ልጅ በመባል የሚጠሩቱ *ተዋሕዶ-በተዐቅቦ* ብለን ልንጠራው የምንችለውንም አስተምሮት አንጸባርቀዋል። የእነዚህ ሁለት አመለካከት መምሬዎች የተዋሕዶን ምሥጢር ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው ማብራሪያዎች አሏቸው።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ኦፊሴላዊ የተዋሕዶ መምሬዎች የተዋሕዶን ምሥጢር ለማብራራት ከሚጠቀሙባቸው ማብራሪያች ውስጥ ሦስቱን መመልከት አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያውን ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ እንዲህ ይላሉ:- "ነገር ግን የአምላካችን

ተዋሕዶ የዓይንን÷ ከብርሃን÷ የቃልን ከመላስ፤ የእሳትን ከብረት፤ ያለመደባለቅና ያለመለያየት መዋሐድ መርምረህ በዚሁ እመን ተረዳ እንጂ፤ ተዋሕዶውን ከውሃና ከዘይት÷ ከወሃና ከወተት እንዳታስተካክለው እንዳታስመስለው እንዳታቀላቅለው እወቅ ተጠንቀቅ::"[39] ስለዚህ ተዋሕዶን በተገቢው መንገድ ሊገልጹ ከማይችሉ መግለጫዎች ለመረዳት መሞከር 'ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ!' እንዲሉ ያለ ነው::

እንደ ቀሲስ ከፍያለው መራሂ አገላለጽ ደግሞ:- የቃል ሥጋ መሆን ተዋሕዶ ልክ ብረት ከእሳት÷ አይን ከብርሃን እንዲሁም ሃር ከወርቅ ጋር እንዳለው ጥምረት ነው የሚልን ሀሳብ በማንጸባረቅ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ድንግል ማርያም የመልአኩ ገብርኤል ብስራት ሲደርሳት በቤተመቅደስ ሃርና ወርቅን እያስማማች ትፈትል እንደነበርና ይህም የተዋሕዶን ምስጢር ገላጭነቱ ይታመንበታል:: በመቀጠልም ቀሲስ ከፍያለው ተዋሕዶን ሲያብራሩ የመለኮት ባሕርይ ምልዓቱን ሳይለቅቅ ውስንና የሚጨበጥ ሆኖ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ:: በዚህ አንድነት የመለኮት ባሕርይ ለሥጋ÷ የሥጋም ባሕርይ ለመለኮት ሆኗል::[40]

ሌላው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቅ የሆኑት መላከ ገነት አፈወርቅ ደግሞ የተዋሕዶ ምስጢር ልክ ምግብን ከተመገብን በኋላ ከሰውነታችን እንደሚዋሐድ ነው:: ምግብ ከተፈጨ በኋላ ከሰውነት ውስጥ ነጥለን እንደማናወጣውና በምግብነት እንደማንጠራው ያለ ነው::[41] በማለት ሲገልጹ ሠይፈ ስላሴ የተባሉ መምህር ደግሞ ነፍስና ሥጋ በአንድነት ሰው እንደሚባል በማብራሪያነት ይጠቀማሉ::[42]

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱትን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ኦፊሴላዊ መምሬዎች ማብራሪያ ስንቃኛቸው ተዋሕዶን አጠንክረው ይገልጻሉ:: ተዋሕዶ መቀላቀል÷ መደባለቅ÷ መለየትና መለወጥን የማያስተናግድ ጥምረት ነው:: ብረት እሳት ውስጥ ገብቶ ከወጣ በኋላ የጋለ ብረት እንጂ ብረትና እሳት ተብሎ እንደማይጠራ (የእያንዳንዱ ባሕርይ በተናጥል እንደማይጠቀስ) የቃልና የሥጋም ተዋሕዶ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ-ሰው እንጂ አምላክም ሰውም በማሰኘት ሁለት ባሕርያት አያደርገውም:: እንዲሁ ሃሩን ከወርቁ በመነጠል ይሄ የሃሩ ይሄ ደግሞ የወርቁ ማለት እንደማይቻለን አንዱ የሌላውን ውበትም ሆነ ጥንካሬ እንደሚያሳይ ወይም ደግሞ ምግብ በሰውነት ውስጥ ከተፈጨ በኋላ ነጥሎ ይሄ ምግቡ ነው ተብሎ እንደማይነጠል ያለን አንድነት (መዋሐድ) አመላካች ነው::

ከላይ በተዘረዘሩት ማብራሪያዎች ተዋሕዶን መግለጽ ምናልባት ይህ አሃዱ ባሕርይ ሁለቱ ባሕርያት የየራሳቸውን ጠባያት በመልቀቃቸው ነውን? የሚል ጥያቄን ያነሳሳል:: ሠይፈ ሥላሴ ይህን የተዋሕዶን ምስጢር በነፍስና በሥጋ አንድነት ሲገልጹ :- "ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ÷ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ በተዋሕዶው ፍልጠት÷ ቡአዲ ውላጤና ሚጠት የለበትም በተዋሕዶው እንደ ነፍስና ሥጋ ነው:: ሥጋ ግዘፉን ሳይለቅ ነፍስም ርቀትዋን ሳትለቅ ተዋሕደው አንድ ሰው እንዲባል ቃል ርቀቱን ትቶ ሳይገዝፍ ምልዓቱንና ስፋቱንም ትቶ ሳይወሰን ትስብእትም ግዘፉን ምልዓቱንና ስፋቱንም ትቶ ሳይወሰን ትስብእትም ግዘፉን ለቆ ሳይረቅ ሳይዋጥና ውሱንነቱንም ለቆ ምሉዕና ስፉሕ ሳይሆን ነው::"[43] የነፍስና የሥጋ አንድነት የየራሳቸውን መለያ ጸባያት (Attributes) ሳይለቁ ሰው እንደሚያሰኙ «ቃል» (Logos) የራሱን መለያ ጸባይ (Attribute) ሳይለቅ ትስብእት (ሰው) ተክለ ሰውነቱን ሳይለቅ ክርስቶስ ሆነ ሥጋ በተዋሕዶ መለኮት የሆነው የራሱ የሆኑ ነገሮቹን (properties) ሳይለቅ ነው በማለት ያብራራዋል::

*የተዋሕዶ በተዓቅቦ ሊቃውንት* ደግሞ ስለ ተዋሕዶም ሆነ ስለተዓቅቦ ሲናገሩ የሚሰጧቸው ማብራሪያዎች ለየት ያሉ ናቸው :: ለዚህ የተዋሕዶ ምስጢር በምሳሌነት የሚጠቀሙባቸው አራት ማብራሪያዎ-ች:- የባልና የሚስት÷ የምዕመናን÷ የምዕመናንና የክርስቶስ እንዲሁም የሥላሴ አንድነትን ነው::

የባልና የሚስትን ተዋሕዶ በመጥቀስ ምሥጢረ ሥጋዌን ሲገልጹ:- "ባልናሚስት እያዳንዳቸው እኔ የማለት መብታቸው (ፔርሶናሊቴያቸው) እንደተጠበቀ÷ ባል ወንድ የተሰኘበት አካሉና ባሕርዩ÷ ያለና የጸና መሆኑ ሳይሻርበት÷ ሚስትም ሴት የተሰኘችበት አካሏና ባሕርይዋ እንደተጠበቀላት÷ ሁለቱ ያለመጠፋፋት÷ ያለመዋዋጥ ህገ ተዐቅቦ በመካከላቸው ሆኖ ተዋሐዱ"[44] በማለት ተዐቅቦ በተዋሕዶ ትርጉም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያመጣ ማብራሪያን ይጠቀማሉ::

ሌላውና ሁለተኛውን ምሳሌ ማለትም የምእመናን አንድ መሆን የሚያመለክተውንም ሲያብራሩ:- «ምእመናን....÷ የተለያየ የአገልግሎት ስጦታ ቢሰጣቸው የራስ በራስ መዋሐድ (ተዋሕዶ) አላቸው:: ተዋሕዶአቸውም በአንድ አካል እንደተገጣጠሙ እንደተዋደዱና እንደተጠቃለሉ ብልቶች ይመስላል ተብሎ ተነግሮአል:: የምእመናን ተዋሕዶ (አንድ መሆን) ምሥጢር መቀላቀል÷ መዋዋጥ÷ መጠፋፋትና መቀላቀል የሌለበት የጽንአተ ባሕርይና የጽንአተ አካል አቋማቸው የእኔነት መብታቸው የእያንዳንዳቸውም ግዴታና ሀላፊነት እንደተጠበቀ

(ህገ ተዓቅቦ እንደጸና) መሆኑን አንዘነጋም 1ቆሮ 12:12-13፤ ገላ 3:26-28፤ ሮሜ 14:12፤ 15:5-6 በማለት በተለያዩ አካላት እንደ ብልት አንድ አካልነት ምሳሌ በተጠቀሰውና ከምሳሌያዊ አንድነት ባሻገር እውነታዊ የተከለ ሰውነት አንድነትን የማያመለክት መግለጫን ለትሥጉት አካል ተዋሕዶ በምሳሌነት ለመጠቀም መሞከሩ ተዓቅቦን በማጉላት ከምሳሌያዊ መግለጫነት የማይዘልል አንድነትን የሚገልጽ ነው።

በሦስተኛው ምሳሌ ደግሞ የምእመናንና የክርስቶስ አንድ መሆንን በመጠቀም ሲያብራራ «ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና እያንዳንዱ ምእመን ተክለ ስብእናቸው ግላዊ ባሕርያቸው እንደጸና ህገ ተዓቅቦ ሳይፈርስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተዋሐዱ ማለታችን ነው።...... (ህገ ተዓቅቦ ከተዋሕዶ ጋር አለ) ይላሉ። በአራተኛው ምሳሌ ደግሞ የሥላሴን አንድ መሆን በማንሳት የተዋሕዶን ምስጢር ሲገልጹ «...የሥላሴ ጽንአተ አካል የያንዳንዳቸው አካላዊ ግብርና ስም እያንዳንዳቸው ባሕርያዊ ኩነትና ስም ሳይፋለስ እንደተጠበቀ (በህገ ተአቅቦ) በመለኮት የተዋሐዱ ናቸው።[45] በማለት አንቀጸ ተዋሕዶ ምን ጊዜም በምሥጢረ ሥላሴም ሆነ በምሥጢረ ሥጋዌ ከህገ ተዓቅቦ ተለይቶ እንደማይነገር ይገልጻሉ። በዚህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነትና የተሟላ ሰብእነት የተዋሐዱበት ወልድ ዋሕድ (አንድያ ልጅ) ነው በማለት ያስረዳሉ።

ከላይ በተገለጹ ምሳሌዎች የተንጸባረቀውን ምሳሌያዊ አንድነትና ልዩነት በመጠቀም የተዋሕዶን ምስጢር ከመግለጽ ባሻገር ተዋሕዶው ያለ ተዐቅቦ እንዳይደለ ለመግለጽም «መለኮትና ትስብእት ሳይለያዩ÷ ሳይከፋፈሉ÷ ሳይደባለቁ÷ ሳይለዋወጡ (ሳይጠፋፉ) በተዐቅቦ ተዋሐዱ (አንድ ሆኑ) እንላለን። በምሥጢረ ሥጋዌ የአንቀጸ ተዋሕዶ አስፈላጊነት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይን÷ አንድ አካልን÷ አንድ ህላዌን ለማስገኘት ሲሆን የህገ ተዐቅቦም አስፈላጊነት የሁለቱ አንድ መሆን መጠፋፋትንና መዋዋጥን አለማስከተሉን ለማመልከት ነው።"[46] በማለት የአሃዱ ባሕርይ ባህል ተከታይነትን በማንጸባረቅ በተዓቅቦ ግን ከአውጣኬ አሰር ለመራቅ በሚል ሰበብ ተዋሕዶውን ምሳሌያዊ ብቻ የሚያደርግ አስተምህሮ ተከታይ አመላካች እሳቤን ያንጸባርቃል።

እንደ ተስፋግዚም አገላለጽ አንቀጸ ተዐቅቦ የሁለት ባሕርያትን መገኘ ት አመላካች እንደሆነ የመረዳትን አስፈላጊነት ያጠናክራል።[47] ከዚህም በመነሳት *የተዋሕዶ በተዐቅቦ* እምነት ተዋሕዶን በምሳሌያዊነት በመጠቀም አሃዱ ባሕርይን ቢቀበልም ተዐቅቦ እስካለ ድረስ ግን ከምሳሌነት ያለፈ እውነታዊ የተዋሕዶ ምስጢር የተገለጸበት ሊሆን አይችልም። ለመሆኑ የትሥጉት አካል ተዋሕዶ ምሳሌያዊ ወይስ እውነታ? ለዚህ የተዋሕዶ ምሥጢር መሠረት ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱና ዋነኛው ዮሐ1:14 ላይ የምናገኘው ክፍል

ያለማወላዳት «ቃልም ሥጋ ሆነ» በማለት በምሳሌያዊነቱ ሳይሆን በእውነታዊነት ይገልጸዋል::

እንግዲህ የቅዱስ ቄርሎስ «አሃዱ ባሕርይ» አስተምህሮት «ተዋሕዶ» ወይስ «ተዋሕዶ በተዓቅቦ»? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማፈላለግ ስንጥር የቅዱስ ቄርሎስ አሃዱ ባሕርይ ባህል የሁለቱ ባሕርያትን አንድነትና ክርስቶስ ራሱ አንድ መሆኑን ያንጸባርቀበት ነው::[48] እንዲያውም አስቀድሜ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ቅዱስ ቄርሎስ የቅዱስ አትናቴስን መርህ በመከተል ሥነ መለኮታዊ ውዝግቦች በቃላት ላይ ሳይሆን ሥረው ቃሉ ባካተተው ትርጉም ላይ እንደሆነ ያምን ነበር:: ስለዚህም ቅዱስ ቄርሎስ በግሪኩ «ፊስስ» የሚል ቃል በአማርኛው «ባሕርይ» ከግሪኩ «ሃይፓስታሲስ» ወይም አካል እና ህላዌ ከሚሉት ቃላት ጋር በእኩልነት ያሰፍራቸዋል::[49]

ይህን የአሃዱ ባሕርይ ትምህርትን የትኛው ማለትም *የተዋሕዶ* ወይስ *የተዋሕዶ በተዓቅቦ* ማብራሪያ በትክክል እንደሚገልጸው ለመዳኘት መሠረታዊው ነገር ቅዱስ ቄርሎስ ተዋሕዶን ምሳሌያዊ ወይስ እውነታዊ አድርጎ እንደተናገረበት መረዳቱ አስፈላጊ ነው:: በፀጋ ልጅ አስተምህሮ ተዐቅቦ የሁለት ባሕርያትን በተናጥል መገኘት አንጸባራቂ ነው:: የተዋሕዶ ለቃውንት ግን ተዓቅቦ ውላጤ እንደሌለ አመላካች ነው ይላሉ::

ከዚህ ሌላ ሁለቱ ባሕርያት በአንድ አካል የየራሳቸውን ልዩ የሆነ መገኘት ሳይለቁ እንዳሉ የሚያምንና የኬልቄዶን ጉባዔ ውሳኔ እንደሆነ የሚነገርለት ሌላ አስተምሮት አለ:: የተዋሕዶ ሊቃውንት ይህንን አስተምህሮት ከንስጥሮስ ባልተለየ መንገድ ክርስቶስ አምላክም ሰውም እንደሆነ የሚገልጽ ስለ ሆነ ያወግዙታል:: ለመሆኑ ክርስቶስ አምላክም ሰውም ነውን?

### 1.2.5.7. በአንድ ጊዜ ክርስቶስ አምላክም ሰውም (አምላክ እና ሰው)?

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት እንደምንረዳው እ.ኤ.አ. በ 440 ዓ.ም ታላቁ ሊዮ በመባል የሚታወቀው በሮም የመጀመሪያ ጳጳስ ሆነ:: ይህ ሰው በምእራቡ አለም የሮምን ቤተክርስቲያን የበላይነት ያስፋፋ÷ በአምስተኛም ክፍለ ዘመን በአስተምህሮተ ክርስቶስ ረገድ የተካሄዱ ውዝግቦችና ክርክሮችን የመራና የክርቶስን አምላክነት በሰብአዊነቱ ላይ ያለውን ተጽእኖ የተመለከቱ እሳቤዎችን አጽንቶ የተፋለመ ሰው ነበር:: እ.ኤ.አ. በ 449 ዓ.ም በኤፌሶን በተደረገው *የሽፍቶች ጉባዔ* ተብሎ በተሰየመው በክርስቶስ ማንነት ላይ በተካሄደው ውይይት ቢነቀፍም ከሁለት አመታት በኋላ እ.ኤ.አ. በ 451 ዓ.ም የኬልቄዶን ጉባዔ በክርስቶስ

ማንነት ላይ ላሳለፈው ትርጓሜ የእርሱ እሳቤ ዋና ምንጭ ሆኖ ነበር:: ሊዩ:- "ክርስቶስ የፍጹም ሰው ባሕርይና የፍጹም አምላክ ባሕርይ አለው፤ ነገር ግን የተለያየ አካላዊ ማንነት የለውም" ብሏል::[50]

ከዚህ ከሊዩ እሳቤ የመነጨ የ 451 ዓ.ም ኬልቄዶን ጉባዔ አገላለጽ በክርስቶስ ሁለቱ ባሕርያት በአንድ አካል እንዳሉ÷ እያንዳንዱ ባሕርይ ከሌላው ልዩ ሆኖ ሳለ አንዱን ከሌላው መነጠል የማይቻል እንደሆነ ያስገነዝባል:: አፈ ሊቃውንት አክሊሉ ገብረ ክርስቶስ ስለ ኬልቄዶን እሳቤ ሲገልጹ:- "የኬልቄዶን ጉባዔ የመለኮትነትና የሰው ባሕርያት በሁለት ሁኔታና ሁለትነትን በሚንጸባርቅበት አደረጃጀት እንዳሉ ያምናል::" በሚል ሀረግ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ስለ ኬልቄዶን ያለትን መረዳት ጠቅሰዋል::[51]

ይህ ደግሞ ከተዋሕዶ አስተምህሮት የክርስቶስ አንድ ባሕርይ የሁለት ባሕርያት ጥምረት እንደሆነ ከሚገልጸው በእጅጉ የተለየ ነው:: የኬልቄዶን ጉባዔ ክርስቶስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ የመለኮትና የሰው ግብራት እንዳሉት መግለጹ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያጣበትን ምክንያት ሊቀ ጠበብት አያሌው ሲያስረዱ "እና" የምትለው አያያዥ ቃል አንድነቱን መንታ የምታደርግ በመሆኗ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ (እግዚአብሔር) "ቃልም ሥጋ ሆነ::" በሚለው የወንጌል ቃል መሠረት መጠራት አለበት ይላሉ::[52] እንደ አድማሱም አገላለጽ ወንጌል ቃል ሥጋ ሆነ እንጂ ቃል ሥጋ ነው እንደማይል ሁሉ መንታነትን የሚያንጸባርቅ ቃል በማስወገድ አንዱ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ወይም ፍጹሙ አምላክ በክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑ በሌላ አገላለጽ አምላክ-ሰው በማለት ጥንቃቄ የሞላበት አገላለጽን መጠቀም ያስፈልጋል::[53]

የተዋሕዶ ሊቅ አያሌው ታምሩ የመከራከሪያ ነጥብ *የአሃዱ ባሕርይን* (የአንድ ባሕርይን) ባህል በተደጋጋሚ ጥያቄዎች በማስረዳት *የኪልቱ ባሕርያት* (የሁለት ባሕርያት) ባህልን ውግዘት ያንጸባርቃሉ:: ለዚህም የሚከተሉትን አራት ጥያቄዎች ያቀርባሉ:-(1) የሰው ባሕርይ አካል የለውም እንላለንን? (2) የእግዚአብሔርስ ባሕርይ? የእግዚአብሔር ባሕርይ አካል የለውም እንላለንን? (3) የሰው ባሕርይ እና የመለኮት ባሕርይ በማለት የምንነጣጥል ከሆነ ሁለት አካላት እንዳሉ ማስረጃ አይሆንምን? (4) ከዚህ የተነሳ በሁለቱ ባሕርያት መገኘት ካመንን እንዴት የሁለት አካላት መገኘትን መካድ እንችላለን? የትኛውስ አካል ጠፍቷል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ የሁለት ባሕርያት ባህል ተከታዮችን ከንስጥሮስ ያልተለየ እሳቤ እንዳላቸው ያወግዛሉ::[54] እንደ ሊቀ ጠበብት አያሌው የመከራከሪያ ነጥብ ከሆነ የሁለት ባሕርያት አማኞች ከቅዱስ ስላሴ ጋር የሚመለክ አራተኛ አካልን ይጨምራሉ:: ስለዚህም ቅዱስ

ሥላሴን ይከዳሉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል:: አሊያ ግን ባሕርይ የአካል መሠረት ነውና ሁለት ባሕርያት የሚሉቱ በአንድ ባሕርይ ባህል ማመን አለባቸው::

ከዚህም በተጨማሪ የሁለት ባሕርያት በአንድ አካል ውስጥ መገኘት የባሕርያቱን አካል የማን ያሰኘዋል? ለሚለው ጥያቄ የካቶሊኩ ጳጳስ ሊዮ የክርስቶስ አካሉ የቃል (ሎጎስ)፥ ሰብአዊ ባሕርዩ አካል አልባ መሆኑን እንደሚያምን በመጥቀስ ይህንን አባባል ከአውጣኬያዊነት ማለትም መለኮትነት ሰብአዊነትን የዋጠበት አካል ፈጽሞ የማይለይ በመሆኑ ውግዘቱን በሌላም አቅጣጫ ያጠናክራሉ::[55] ለዚህ በመሠረታዊነት የሚጠቅሱትም በድነት ግብር ረገድ የአካሉ ማንነትን ወሳኝነት በመጥቀስ ኬልቄዶናውያን የክርስቶስን ሞት ከንቱ የሚያደርግ አስተምህሮት እንዳላቸውም ይገልጻሉ::

ከታሪካዊ ሥነ መለኮት አንጻር ከተመለከትነው ይህ የኬልቄዶን አስተምህሮት ለቤተክርስቲያን መከፈል ታላቅ ምክንያት ሆኗል:: ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው ከቅዱስ ቄርሎስ የአሃዱ ባሕርይ አስተምህሮት የተለየ መሆኑና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መወገዙ ነበር:: ሆኖም ግን የኬልቄዶትን ውሳኔ የተቀበሉት በሮም መንበረ ፓትሪያርክ ስር መስፋፋት ሲቀጥሉ ለቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት የታዘዙቱ በእስክንድሪያ ቤተክርስቲያን ስር ቀጥለዋል:: እንደ እስክንድርያ ቤተክርስቲያን 117ኛው ጳጳስ ሽኖውዳ አባባል የሶርያ፥ የአርሜንያ፥ የኢትዮጵያና የህንድ አብያተ ክርስቲያናት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋም የሚጋሩ ሲሆኑ ኬልቄዶናዊ ያይደሉ አብያተ ክርስቲያናት በመባል ይታወቃሉ:: ሆኖም የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን "አሃዱ ባሕርይ" በማለቷ ምክንያት 'ሞኖ ፋይዛይት' ተብላ መጠራቷንም ገልጸዋል::[56] በዚህም ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ:- የኬልቄዶን ተከታዮች ምዕራባውያን፥ በእስክንድርያ የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት ስር ያሉቱ ምሥራቃውያን በመባል ተለያይተዋል:: እንግዲህ በምሥራቃውያን እምነት ምዕራባውያን ሁለት ባሕርያት በማለታቸው ከንስጥሮሳዊነት ባልተለየ መንገድ ሁለት ክርስቶስ፥ ከአውጣኬያውያን ባልተለየ መንገድ መለኮት አካሉ የሆነ ክርስቶስን ያምናሉ::

የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሳሉ የኬልቄዶንን አሰር በተከተሉቱ እንደ ግሪክ፥ የራሽያ፥ ቆጵሮስ፥ ቁስጥንጥንያ፥ ሩማንያ፥ ሐንጋሪና ሰርቢያ በተጨማሪም የግብፅ የሮም ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፥ የሶርያ፥ የሊባኖስ፥ የአሜሪካ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በሲና በረሃ የሚገኘው የቅዱስ ካትሪን ገዳም[57] ባሉቱ አመለካከት ደግሞ የቅዱስ ቄርሎስ ተከታዮችን ከአውጣኬ

አስተምህሮት ባልተለየ መንገድ ይቆጠራሉ:: ከታሪክም እንደምንረዳው በሂደት በበእደ ማርያም ዘመነ መንግስት (1468-1478) በወቅቱ የአውጣኬን አስር እንደተከተሉ ከሚነገርባቸው የሶርያና የግብጽ ቤተክርስቲያናት ሁለት መነኮሳት አማካኝነት የአውጣኬ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ገብቶ እንደነበረ ቢተረክም በኢትዮጵያ ምድር ፈጽሞ ተቀባይነት አግኝቶ እንደማያውቅ ይታመናል:: ስለዚህም ኢትዮጵያ ኬልቄዶናዊ ካይደለው የቅ/ቄርሎስ የእምነት መግለጫ ጋር የተጣበቀች ሆናለች:: ስለ ተለያየ ታሪካዊ የነገረ-ክርስቶስ ገለጻዎች ይህንን ያህል መቃኘት ከቻልን እነዚህን ሥነ መለኮታዊ እሳቤዎች ማነጻጸር ለማጠቃለያ ሀሳብነት የሚረዳን ከመሆኑ በላይ ጥንፍፍ ያለ መረዳትን ለመጨበጥ ያስችለናል::

### 1.2.5.8. የአርዮስ÷ የቅዱስ ቄርሎስ÷ የአውጣኬ÷ የኬልቄዶን እና የተዋሕዶ አስተምህሮቶች ንጽጽር:-

ክርስቶስ ማን ነው? (Ontological Christology) በተሰኘው ክፍል ክርስቶስን ለመረዳት በሚያስችልና በታሪካዊ ሥነ መለኮት እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሚደረግ ጥናታዊ ምርምር ላይ የተለያዩ በክርስቶስ ላይ የተሰነዘሩ እሳቤዎችን ለመዳሰስ ሞክረናል:: ለዚህ የታሪካዊ ሥነ መለኮት አሰሳ በዋና ምክንያት የምንይዘው የታሪክ ትምህርትን መቅሰም ሳይሆን ከታሪክ የምንማራቸውን ስህተቶች በማጤን የስህተት ግልባጭ ላለመፈጸምና በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ላይ ለምናደርገው ጥናት አብርሆትን ለማግኘት ስንል ነው:: የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የየትኛውም ባህል ደጋፊነት ላይ ተመሥርቶ ጥናት ማድረግ በመሠረትነት ለያዙት ባህል አድልዎ ማድረግን ስለሚያስከትል በማነጻጸር እና በትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ አፈታት ላይ በመታገዝ አስተምህሮቱ የተመሠረተባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መመልከት አስፈላጊ እንደሆነ ያምንበታል:: ከዚህም በተጨማሪ ሥነ ክርስቶስን በሁለት በመክፈል የክርስቶስ ማንነት (Ontological Christology) እና የክርስቶስ ግብራት (Functional Christology) በማለት ማጥናቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቢሆንም ግብሩን ከክርስቶስ ማንነት መነጠል ባለመቻሉ ስለ ማንነቱ ያለን መረዳት በቀጥታ ከግብሩ ጋር ግንኙነት እንዳለው በማስተዋል መመልከት ያሻል::

እንግዲህ በታሪካዊ ሥነ መለኮት መጎልበት ዙሪያ ቤተክርስቲያን በበጎም ሆነ በክፉ ጎናቸው በታሪክ የምትጠቅሳቸውን አበቶችና በአሁኑ ወቅት በሁለት ታላላቅ ጎራዎች በመክፈል ምእራብና ምሥራቅ (የካቶሊክና የሮም ኦርቶዶክስ÷ የኦርየንታል ኦርቶዶክስ) አብያተክርስቲያናት ነገረ-ክርስቶስን ማነጻጸራችን እንዲሁም ከእነርሱ መማራችን አስፈላጊ ነው:: በተለይም ደግሞ በወንጌል አውዳዊ መሆን

የሚገኙ ታላላቅ ጠቀሜታዎች ባለቤት በመሆን የአድነኖትን የምሥራች በአገር በቀል ሥነ ክርስቶስ በኢትዮጵያ ምድር ለማወጅ እንዲቻል የተለያዩ አስተምህሮች ባለቤቶችንና አሳቤዎቻቸውን ማነጻጸሩ ጠቃሚ ነው:: በሀገራችን በኢትዮጵያ ክርስትና ረጅም እድሜ ቢኖረውም በታሪክ ሂደት የተፈጠረው የቤተክርስቲያን መከፋፈል ወገንተኝነት በመፍጠርና ልዩነትን በማስፋፋት ባመጣው ጦስ አንዱ ሌላውን በማውገዝ ከመሠረታዊው የክርስቶስ ግብር የራቀና ግላዊነት የሞላበት ድምዳሜ ላይ መድረስን አስከትሏል::

ናሁ አዳም ከትንሣኤ መጽሔት ነሐሴ 30/1963ዓ.ም የተጻፈን ሀሳብ በመጥቀስ የቤተክርስቲያን መከፋፈልን ሲገልጽ:- " ይሁንና ይቺ አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ 451 ዓ.ም በጉባዔ ኬልቄዶን ላይ በደረሰባት ኃይማኖት ለበስ የስልጣን ሽሚያ ጦርነት ከምንጊዜም የከፋ እድል ገጥሟት ከሁለት ተከፈለች:: ልጆችዋም አውጣኬያውያንና ንስጥሮሳውያን መባባል ጀመሩ «ጠላት ይቀባል ጥላት» እንደተባለው ሁሉ አንዱ ክፍል ሌላውን ጥላት መቀባት ጀመረ ጠቡ ተካሮ እርስበርስ መወጋገዝ እግዚአብሔርን እንደማገልገል ተቆጠረ::"[58] በማለት ለቤተክርስቲያን መከፈል የስልጣን ሽሚያን በምክንያት ይጠቅሳል:: ይህ ከሆነ ደግሞ ታሪክን አጥርቶ ካለማየት የተነሳ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርገውን ውግዘት ለማጫፈር ከመሮጥ ማነጻጸርና ነፃ ሆኖ መገምገም አስፈላጊ ነው::

እንግዲህ ወደ ንጽጽሩ ሂደት ስናመራ እ.ኤ.አ. በ 325 ዓ.ም በኒቅያ የቤተክርስቲያን ጉባዔ በክርስቶስ እውነተኛ አምላክነት ላይ ባደረገው ክህደት ከተወገዘውና በአሁኑ ወቅት በምድራችን ራሳቸውን የይሆዋ ምስክሮች በማለት ከሚጠሩ ተከታዮች ትምህርት እንነሳ:: አርዮስ በወልድ ላይ ያቀረበው መከራከሪያ በቅድመ ትሥጉት ቃል (ወልድ) የአብ ፍጡርና በመለኮትነቱ ከአብ ያነሰ መሆኑን በመግለጽ ነው:: ለዚህ መከራከሪያው ያቀረባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ደግሞ በጤናማ የሥነ አፈታት ድምዳሜዎች ላይ የተደረሰባቸው አይደሉም:: ለዚህም በዋቤነት ምሳ 8:22 ላይ ያለውን ክፍል ምንም እንኳን አውዳዊ ሀሳቡ በአዲስ ኪዳን ብርሃን የ«ቃልን» ማንነት አመላካች እንደሆነ ድምዳሜ ላይ መድረስ ቢቻልም እንኳን የቃላት ጥናት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ከዚህ በተጨማሪም ግልጽ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአሻሚነት የሚገኙትን ክፍሎች እንዲገዛቸው በማድረግ መተርጎም በሥነ አፈታት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው መገንዘብ መሠረታዊ ነገር ነው:: ሌላውና ሦስተኛው ነገር ደግሞ ከአውድ ውጪ ለመፍታት የተሞከሩ ክፍሎችን የሚመለከት ነው:: ጥቅሶችን በጭቆ ከአውዳቸው ውጪ ለቅድመ ግምታዊ እሳቤ ተስማሚ አድርጎ መውሰድ ታሪክ ምህረት የማያደርግለት ስህተት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ በግብራት

ክርስቶስ (Functional Christology) የምንመለከተው በድኅረ ትስብእት ያሉ ግብራት የተገለጹበትን ሀሳቦች ከክርስቶስ ማንነት ጋር በማቀላቀል የሚፈጸሙ ስህተቶችን የሚመለከት ይሆናል።

የቅዱስ ቄርሎስን አሃዱ ባሕርይ ባህልን ከአውጣኬ አስተምህሮት መቀየጥ ታላቅ ስህተትና በተለይ የወገኑለትን እሳቤ ተቀባይነት ለማስጠት ከሚደረግ ጥረት የመነጨ ነው። የኪለቱ ባሕርያት ደጋፊዎች አሃዱ ባሕርይ የሚልን በሙሉ አውጣኬያውያን በማለት ለአስተምህሮታቸው ወገዛን ሲያጸድቁ መገኘታቸው ትክክል አይመስለኝም። ከቅዱስ ቄርሎስ ነገረ-ክርስቶስ መቅሰም የሚቻሉ እውነታዎች የተዳፈኑ ቢመስሉም ታሪክ ራሱን የሚደግምበትና የነገረ መለኮት ሰዎች አይኖቻቸውን ወደዚህ ጥንታዊነት ወዳለው የአባቶች ትምህርት የሚያቀኑበት እንዲሁም ለበርካታ ምላሽ ያጡ ጥያቄዎች ያለውን ጠቀሜታ የሚያስተውሉበት ጊዜ ሩቅ አይመስለኝም።

እንግዲህ ከቅዱስ ቄርሎስ በኋላ አውጣኬ ይህንኑ 'አሃዱ ባሕርይ' የሚለውን ቃል ተጠቅሞ መለኮትነት ሰብአዊ ባሕርይን የዋጠበት አንድ ባሕርይ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱን የቅዱስ ቄርሎስን መርህ የተከተለች የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአጽንኦት የምታወግዘው ነው። ስለዚህም የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት በፍጹም ከአውጣኬ ጋር ሊነጻጸር አይገባውም። ምክንያቱም "ከአብ አካል በአካል÷ ከአብ ባሕርይ በባሕርይ በራሱ ልዩ አካል «ሎጎስ» የሰውን አካልና ባሕርይ ተጋርቶ ከማሪያም ተወልዷል።"[59] የሚለው የተዋሕዶ እምነት የቅዱስ ቄርሎስን አሃዱ ባሕርይ ባህል አንጸባራቂነቱ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይታመንበታል።

ሆኖም አንዳንዶች ቅዱስ ቄርሎስን የተረዱበትን መንገድ ሲገልጹ ከዚህ አባባል የሚቃረን ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይኸውም "የሁለቱ ባሕርያት አንድ መሆን ቃል የወሰደው የሰው ባሕርይ አካል አልባ ነው።" ብሎ እንደሚያምን የሚያመለክቱ ጸሐፊዎች ናቸው።[60] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ የሆኑት አያሌው ግን ይህ የሮም ጳጳስ የነበረው የሊዮ አባባል እንደሆነና የክርስቶስ አካሉ የቃል ብቻ ነው ማለት የ«ቃል» አካል ከአብና መንፈስ ቅዱስ እኩል መለኮት ስለሆነና የመለኮት ሁለትነት ስለሌለ አካሉ የቃል የሆነ ኢየሱስ ሞተ ማለት በአጠቃላይ የአብና መንፈስ ቅዱስ ህላዌም አምላክነት በመሞቱ ምክንያት ሞቶ ነበር የሚል ድምዳሜ ላይ እንደሚያደርስ ይገልጻሉ።[61] ከዚህም በመነሳት ይህ እሳቤ የቅዱስ ቄርሎስ እሳቤ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ የቅዱስ ቄርሎስ አስተምህሮት ከተዋሕዶ አስተምህሮት ጋር ያለውን መወዳደት ቄርሎስም ሆነ አውጣኬ ሁለቱም "አሃዱ ባሕርይ"

የሚል ቃል በመጠቀማቸው ብቻ ሳይሆን በትርጉም ደረጃ የቅዱስ ቄርሎስ እምነት ከአውጣኬ አሰር የራቀና የተለየ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ቄርሎስን ትምህርት በትክክል እንደተከተለች የሚታምን ሲሆን ለዚህም በእምነት መግለጫዋ አገር በቀል ማብራሪያዎች በመስጠት ለማስገንዘብ ትጥራለች፡፡ ከዚህም በመነሳት የተዋሕዶ ምሥጢር (*miaphysis*) ማለትም የሁለት ባሕርያት ጥምረትን እንጂ (*monophysis*) በውላጤ ሁለቱ አንድ የሆኑበት አይደለም፡፡ እንግዲህ የኢትዮጵያ መምሬዎች የቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት የተዋሕዶ ትምህርት ሲሆን የአውጣኬ ትምህርት ደግሞ በውላጠ. የሚያምነው የአንድ ባሕርይ ትምህርት ነው፡፡ ሊዮ በመባል የሚታወቀው የሮም ጳጳስ እሳቤና በኬልቄዶን ጉባኤ የጸደቀው አስተምህሮት ደግሞ በኢትዮጵያ ፍልስፍናና አመክንዮት ጥያቄ ውስጥ የወደቀው የሁለት ባሕርያት በየራሳቸው በአንድ አካል መገኘትን ምናልባትም በተአምራት ለመደገፍ የሚጥር ይመስላል፡፡ እነዚህን የማንነት ግንዛቤዎች በይበልጥ ለመረዳት የአካልን ግብር ለመገንዘብ በሚያስችሉ ሀሳቦች ላይ መነጋገር አስፈላጊ ነው፡፡

## II የክርስቶስ ግብራት ምን ምን ናቸው?
### (Functional Christology)

ወልድ ከሥላሴ አንዱ ረቂቅ አካል ሆኖ ሳለ የሰውን ልጆች ከኃጢአት ለማዳን ከነበረው ዐላማ የተነሳ ሰው ሆኖ በምድር ተመላልሷል:: የትሥጉት አካል የሆነው የክርስቶስን ግብር ለመረዳት ስለ ክርስቶስ ማንነት አስቀድመን በተነጋገርንባቸው መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ላይ ወደ ትክክለኛ መረዳት መምጣት አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም የክርስቶስን ግብር በትክክል መረዳት ስለ እርሱ ማንነት ባለ ግንዛቤ ላይ የሚመሠረት በመሆኑ ነው:: እንግዲህ «ክርስቶስ» የሚለው ስያሜ አካላዊ ቃል በትሥጉት አካል አምላክነቱ ሳይቀነስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር የመጣበትን ማንነቱን ከሚገልጹ ስሞቹ አንዱ ነው:: አምላክ አምላክነቱን ሳይለቅ ሰው የሆነው ከመለኮታዊ መንስዔ የተነሳ መሆኑን መገንዘብ ያሻል:: አካላዊ ቃል ከሁሉ በላይ የሆነ ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ሳለ ሰው መሆን በፈለገ ጊዜ የሚከለክለው አንድም የበላይ አልነበረበትም:: ሆኖም ግን ያለ ምንም ተልእኮ እንዲያው ሥልጣኑን ለማሳየት ያክል ሰው አልሆነም:: ከዚህም በመነሳት አካላዊ ቃል አምላክ ሲሆን ሰው የሆነበት ዐላማን ምንነት አስቀድሞ መቃኘት አስፈላጊ ነው::

### 2.1. ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያደረገው ምንድር ነው?

የሰው ዘር በአዳም ውድቀት ምክንያት በኃጢአት ተጽዕኖ ውስጥ ወድቋል:: ከዚህም የተነሳ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጥል ነግሷል:: ሰውንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ብቁ አካል በምድር ላይ ፈጽሞ አልተገኘም:: በተጨማሪም ሰው በኃጢአተኝነቱ የሚገባውን ቅጣት ይኸውም ለሠይጣንና ለመላእክቱ የተዘጋጀውን /የገሀነመ እሳት ፍርድ/ ሊቀበል ፍርደኛ ሆኗል:: በመሆኑም የሰው አእምሮ÷ ፈቃድና ስሜት በተጽእኖ ስር ሆኗል (ኤር 17:9፤ ዘፍ 6:5፤ ማቴ 15:18-19፤ ሮሜ 7:5፤23):: ታዲያ ሰውንና እግዚአብሔርን ማን ያስታርቅ?

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት በምድራችንና ከባህላችን አንጻር የምናከናውነው በአንድ ልምምድ ላይ የተመሠረተ ጥያቄን ማንሳቱ አስፈላጊ ነው:: በባለትዳሮች መካከል ግጭት /አለመግባባት ወይም ጥል/ ሲከሰት ትክክለኛ አስታራቂ /ሽማግሌ/ የሚሆኑ እነማን ናቸው? ጎረቤት÷ ጓደኞች÷ የአካባቢ ሽማግሌዎች?÷ የሚስት ዘመዶች?÷ የባል ዘመዶች? ወይስ ማን? በእኔ አመለካከት ለዚህ ጥያቄ ልንሰጥ የምንችለው ትክክለኛው ምላሽ በባህላችን እጅግ ውጤታማ የሆነው

ከባልም ከሚስትም ወገኖች በእኩል ቁጥር በተውጣጡ ሽምግሌዎች እየተከናወነ ያለበት መንገድ ብቻ ነው።

ባሳለፍኳት ጥቂት የህይወት ዘመኔ በርካታ የሽምግልና ሂደት ተሞክሮዎች አሉኝ። ከዚህ ውስጥ ለሦስት አመታት ያሳለፍኩበት ከአንድ የማስታረቅ /ሽምግልና/ ሂደት ተሞክሮ የተማርኩትን ማካፈሉ አስፈላጊ ይመስለኛል። በሁለት ክርስቲያን ቤተሠቦች በወጣት ልጆቻቸው ምክንያት በተፈጠረ መተሳሰፍ ከፍተኛ ጥላቻ ተፈጥሮ የማስታረቅ ሂደት ውስጥ ገባሁ። ከሁለቱም ቤተሠቦች ጋር በጌታ ካለኝ አገልግሎት እንጂ በስጋ ዝምድና የለኝም። ሆኖም በሁለቱም ቤተሠቦች ፈቃድ የማስታረቁን ሂደት ከሌሎች ክርስቲያን ወገኖች ጋር ስንገፋበት ከቆየን በኋላ አንዳንዶች የጉዳዩ መካረር በጎላ ቁጥር ራሳቸውን ማግለል ጀመሩ። እኔም ሦስተኛውን አመት በሽምግልና ሂደቱ ከገፋሁና ፍርድ ቤት የደረሰበት አካሄድ እግዚአብሔር የሌለበት መሆኑን ሳስተውል ከቆየሁ በኋላ ውስጤ ከፉኛ ማዘን ጀመረ። እንዲያውም መጨረሻው ላይ በሥጋ ዘመድ ለሆኑ ሰዎች ሽምግልና ትኩረት በመሠጠቱና ነገሩን መቋጨት ባለመቻላችን ከጸሎት ያለፈ ምንም አይነት ጥረትን ላለማድረግ በመወሰን ከሽምግልናው ራሴን ለማግለል እስከማሰብ ደረስኩ።

ነገሩ የሁለቱንም ቤተሠቦች የስጋ ዘመዶችን ባካተተ የሽማግሌ ቡድን መዳኘት ሲጀመር ወዲያው እልባት አገኘ። እኔም ለሁለቱም ቤተሠብ የስጋ ዝምድና ሳይኖረኝ በወንጌል አገልጋይነቴ እነዚህን ሁለት ቤተሠብ ለማስታረቅ መሞከሬ ከተዛቢነት ያላለፈ እንዲያውም ትዕግስቴ የተፈተሸበት እንደነበረ አስተዋልኩ። ለጉዳዩ ፈጣንና የማያወላዳ እልባት በማሠጠት የፍርድ ቤቱን ክስ ለማቋረጥ እጅግ የታመነበት መንገድ ከሁለቱም ወገኖች የተውጣጡ ሽማግሌዎች መገኘ ታቸው እንደሆነም አስተዋልኩ።

በዚህ ምድር በሁለት ሰዎች መካከል ለሚፈጠር ጥል ትክክለኛው አስታራቂ የሁለቱን ወገን ያካተተ የሽማግሌ ቡድን እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ለተፈጠረውም ጥል መፍትሔው በባህላችን የምናገኘው ብቸኛና ውጤታማ መንገድ አምላክ–ሰው መሆን እንዳለበት ያስገነዝበናል። መቼም እግዚአብሔርንና ሰውን ለማስታረቅ አንዳንዶች መላእክት ጥሩ ሽማግሌ ናቸው ሲሉ ይደመጣሉ። መላእክት በፍጥረታቸው የሰው ወገን ካለመሆናቸውም በላይ የእግዚአብሔርም ወገን ባለመሆናቸው የራሳቸው ፍጥረት ያላቸው ናቸው። ከዚህም የተነሳ ምናልባት የጠቡን መካረር ታግሰው እንዳይዘልቁ የሚያደርጋቸው ትእግስቱም ሆነ የሚጠበቀውን መስዋእት መክፈል የሚያስችል ማንነትም የላቸውም። ስለዚህ በጠብ መሀል

እግር ጥሎት ለማስታረቅ እንደገባ ሽማግሌ ነገሩም ሲካረር "እኔ እናንተ መካከል ምን ዶለኝ!" ብሎ እንደሚሄዱ ናቸው።

አንዳንዶች ደግሞ ቅድስት ማርያምና ቅዱሳንን መካከለኛ ለማድረግ ያስባሉ። የእኔ የሽምግልና ሂደት በሁለቱም ወገኖች ትኩረት እንዲነፈገው የሚያስደርግ የወገን /የዘር/ መዋጮ የሌለበት የአንድ መንፈሳዊ ሰው ጣልቃ ገብነት እንደመሠለ እነርሱም ቅዱሳን ሠዎች እንጂ አምላክነት የሌላቸው በመሆኑ እንዲሁም የሚከፈለውንም መሥዋእትነት ለመክፈል የሚያስችል ማንነት ስለሌላቸው ትክክለኛ ሽማግሌ ሊሆኑ አይችሉም።

ሌሎች እግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የሌለው ስለሆነ እንግዲያው እርሱ ራሱ ይታረቀን እንጂ ማን ይሽመግለናል የሚለው ምላሽ ትክክለኛ ሳይመስላቸው አይቀርም። ሆኖም ጥሉ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር ባሕርዩን መቃረን ባለመቻሉ እርሱ ራሱ የማስታረቅ መሥዋእት አይሆንም። ስለዚህም ምንም እንኳን ለጥል መወገድ መለኮታዊ መንስዔ ቢኖርም ትክክለኛ እርቅን ለማውረድና ለእርቁ የሚያስፈልገውን መሥዋእት ለመክፈል የሚችል በሠማይም ሆነ በምድር የተገኘው *አንድ ብቻ* ነው። እርሱም አካላዊ ቃል አምላክ ሲሆን ሳለ ሰው ሆኖ በመምጣት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተፈጠረው ጥል ትክክለኛ አስታራቂ ወይም ሽማግሌ መሆኑ ነው። ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያደረገው ታላቅ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ብቁ መስዋእት ሆኖ በመገኘቱ ነው። ለመሆኑ ክርስቶስ ለሰዎች መስዋእት የሆነው እንዴት ነው?

### 2.1.1 መስቀሉ እና ሥርየት

#### ሀ. መስቀሉ

በአገራችን የመስቀል ምንነት በተለይ የሚዘከረው ከመስቀል በዓል አከባበር አንጻር በሚወሳ ሃይማኖታዊ እሳቤ መሠረት ተደርጎ ከሚቆጠር ትውፊት አንጻር ነው። ይህም ታሪክ እንደሚያመለክተው፡-

አይሁድ በክርስቶስ ላይ ያላቸውን ጥላቻ የተሰቀበለትን መስቀል በቆሻሻ ክምር ሠ ሥቅበር መግለጻቸው፥ የኢትዮጵያ ንግሥት እንደሆነች የሚነገርላት "ንግስት እሌኒ" መስቀሉ የተቀበረበትን ስፍራ በማፈላለግ ስትጨነቅ ከከረመች በኋላ በአካባቢው ላይ ደመራ ተክላ እንዳበራች፥ በመለኮታዊ ምሪትም የደመራው ጭስ መስቀሉ የተቀበረበት ትክክለኛ ስፍራን በማመልከቱ ቦታው እንዲቆፈር በማድረግ የክርስቶስን መስቀል ከቆሻሻ ክምር ስር እንዳወጣች የሚነገር ትውፊት አለ።

ከዚህም የተነሳ በኢትዮጵያ የመስቀል በዓል ብዙዎች በተለያየ መንገድ በመስቀል ስያሜነት በተለየ የክብረ በዓል ስሜት ውስጥ የሚገቡበት ወቅት ነው:: መስቀል ላንዳንዶች የባሕላዊ ዘፈኖችና ጭፋሮዎች ጥም መርኪያ ሲሆን ለሌሎች ከጎመን እስከ ሥጋ ክትፎ አገላብጦ በመብላት ደስ የሚሰኙበት ነው:: መስቀል ላንዳንዶች ችቦ ለኩሶ «የጎመን ምንቸት ውጣ! የገንፎ ምንቸት ግባ!» በማለት ችጋርን አባረው ጥጋብን በምኞት የሚያስገቡበት ሲሆን ለሌሎች ደግሞ ለትዳር የሚሆኑ ልጃገረዶችን የሚመርጡበት /የሚያጩበት/ "ሙየት"ንና ምርቃትን ከወላጆቻቸው ለመቀበል ወደየትውልድ ሃገራቸው የሚገቡበት ነው:: መስቀል ላንዳንዶች ተዓምራትን በማድረግ ስለ ራሱ ያረጋገጠ ሆኖም ከቆሻሻ ውስጥ ተቆፍሮ የወጣ ክርስቶስ የተሰቀለበት እንጨት ተገኝቶ ግማሹ ክፍሉ (ግማደ መስቀሉ) በኢትዮጵያውያን እጅ በነዋየ ቅዱስነት የገባበት ታላቅ ምስጢር ሲሆን ለሌሎች ደግሞ የክረምት ማለፍና የበጋ መምጣት «የኢዮ አበባዬ! መስከረም ጠባዬ!» የወቅት መለወጥ የምስራች ነው::

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ስለ "መስቀል" ሳይሆን ስለ መስቀሉ ሥራ ይገዳቸው ነበር:: ስለ መስቀሉ ሲያስቡ እንደ ኢትዮጵያውያን:- የጎመን ክትፎ÷ የእጮኛ መረጣ÷ የጎመን ምንቸት ወጥቶ የገንፎ ምንቸት መግባቱ (የብልጽግና ዘመን ምኞት) ወይም ደግሞ መንፈሳዊ ለማድረግ በትንቢት እይታ ግማደ መስቀሉ ከቆሻሻ ስር ወጥቶ ለኢትዮጵያውያን የአምልኮ ምንጭ መሆኑ አልታያቸውም ነበር::

አራቱ ወንጌላውያን ከራሱ ከክርስቶስ አንደበት እንደወጡ በገለጿቸው ሠባት ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ የተናገራቸውን በመጠቀም መስቀሉን ከሦስት የተለያየ አቅጣጫ እንደተመለከቱት መረዳት ይቻላል:: በዚህም መሠረት ለአራቱም ወንጌላውያን መስቀሉ የወንጌል ከፍተኛ ደረጃ /climax/ ነው:: እዚህ ላይ ሰው በሕይወቱ መጨረሻ የሚናገራቸው ነገሮች ቃል በቃል ሊዘነጉ የማይችሉ ደግሞም እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ ሁሉ የክርስቶስ ከመስቀል ሞቱ (ነፍሱን ከመተው) በፊት የተናገራቸው እነዚህ ሰባት ቃሎቹ የመስቀሉን ምስጢር አበክረው የሚገልጹ በመሆናቸው ከአማኞች ህሊና መጥፋት የሌለባቸው ናቸው::

# ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ የተናገራቸው ሰባት ቃላት በአራቱ ወንጌላውያን እይታ:-

ማቴዎስና ማርቆስ ✝ ዮሐንስ

ሉቃስ

እነዚህ ሰባት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ከተናገራቸው ቃላት ሁለቱን ማቴዎስና ማርቆስ ሲጋሩ÷ ሁለቱን ሉቃስ÷ ሦስቱን ደግሞ ዮሐንስ ጠቅሰዋቸዋል:: እነዚህ ሦስቱ የመስቀሉ ሚስጥራት መስቀሉን ከተለያየ እይታ የሚያስቃኙ ናቸው::

1. ለማቴዎስና ለማርቆስ *መስቀሉ የጣር ስፍራ* ነው /ማቴ 27:46፤50፤ማር 15:34፤37/::

በኢትዮጵያውያን ዘንድ የስቅለት ሳምንት "ሰሞነ ህማማት" በመባል የሚታወቅና የክርስቶስ መከራ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ጎልቶ የሚነገርበት የሚታሰብበትም ወቅት ነው:: እንደ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን መስቀሉን ማዶ ሆነን አሻቅበን ስንመለከት ጌታ ስለ እኛ የተቀበለውን ታላቅ ሥቃይ እያሰብን በእንባ የምንሞላ ብዙዎች ነን:: በዚያው መጠን የሚታዘንለት /የሚለቀስለት/ ሳይሆን ለእኛ ያዘነልንን ጌታን የምናመልክ መሆናችንን ስናስብ የተደባለቀ ስሜት አለን::

ክርስቶስ በመስቀል ስለ እኛ የመሞቱን ምስጢር ስናስብ የመስቀል ሞት ፍርድን ከሌሎች አይነት ፍርዶች ልዩ የሚያደርገው ምን እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል:: ለመሆኑ ከፍርድ አይነቶች ሁሉ የትኛው ፍርድ ከባድ ነው? በልጅነት ዘመኖቼ ከሰማኋቸው ዜናዎች የማልረሳውና የመጨረሻ ዘግናኝ ፍርድ ብዬ አቆጥራቸው ከነበሩ ፍርዶች አንዱን ልግለጽ:: በፈረንጆቹ አገር ነው:- አንዲት ልእልት በቁንጅና ውድድር ሪኮርድ ነበራት:: እናም ሪኮርዷ እንዳይሰበርባት ስትል በአገሪቱ የነበሩትን ቆንጆ የተባሉትን በርካታ ልጃገረዶችን በስውር አስገደለች:: በኋላም ይህ ወንጀሏ ስለተደረሰባት በፍርድ ቤት የተወሰነባት ቅጣት በሕይወት ሳለች ግንብ ተገንብቶባት እግንቡ መካከል እንድትቀር ማድረግ ነበር:: መቼም የዚህችን ሰው ስቃይ ስናስብ ቅጣቱን የመጨረሻ ዘግናኝ ሳንለው

አንቀርም። ታዲያ የክርስቶስን ሞት ከዚህ ዘግናኝ ፍርድ ልዩ የሚያደርገው ምንድር ነው?

የክርስቶስ ሞት የመስቀል ሞት መሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን "በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት የተረገመ ነው።" የሚለውን እርግማን በንፁሑ በክርስቶስ ላይ ተፈጻሚ የሚያደርግና የእርጉም ሰው ሞት እንደ ሞተ የሚያመለክት ነው (ዘዳ 21:23፤ ገላ 3:13)። በሮማውያን ዘንድ ደግሞ ለዜጎቻቸው ፈጽሞ የተከለከለና ከሮም ዜግነት ውጭ ሆነው የመጨረሻ ከባድ ጥፋት በፈጸሙት ላይ የሚተገበር ቅጣት ነው። ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሰው የመስቀል ሞት ቅጣት ነፍስ ከሥጋ ቶሎ እንዳትለይ በማድረግና ሥቃይን በማራዘም ፍርደኛ ውን ለተራዘመ ጣር የሚዳርግ በመሆኑ ነው። ደም ከሰውነት ቀስ በቀስ እየተንጠባጠበ አልቆ እስትንፋስም ቶሎ እንዳታቋርጥ በማድረግ ስቃይን አራዛሚ ቅጣት ከመሆኑም የተነሳ እንደ አይሁድ ህግ ፀሐይ ሳትጠልቅ ሬሳው ወደ መቃብር መውረድ ስለነበረበት በስቅላት የተቀጣውን ሰው ቋንጃ በመስበር ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ነፍሱ እንድትወጣ ማድረግ ያስፈልግ ነበር።

የክርስቶስ ሞት የመስቀል ሞት መሆኑ በሌላ በኩል እርቃን በአደባባይ ያስገለጠ ቅጣት እንደሆነ ከሚነገረው አንጻር «ከአይሁዳውያን ይልቅ ሰዓሊያን ለክርስቶስ ያዝኑለታል!» የሚለው አባባል አንድ ምስክር ነው። አይሁድ ኢየሱስን ሲሰቅሉት በአንዳንድ የስቅለት ሥዕል ላይ እንደምናየው ግልድም የተገለደመለት አልነበረም፤ ነገር ግን እርቃኑን ሰቅለውታል። ይህም የክርስቶስን ሞት ልዩ ያደርገዋል። እንግዲህ ማቴዎስም ሆነ ማርቆስ የክርስቶስን መስቀል ሲዘግቡና በመስቀሉ ላይ ሳለ ከተናገራቸው ሁለቱን ሲገልጹልን *መስቀሉ የጣር ሥፍራ* እንደሆነ ያመላክቱናል።

2. ለሉቃስ መስቀሉ ***የፍቅር ሥፍራ*** ነው /ሉቃ 23:34፤43/

ከእኛ የሆነ የሚወደድ ነገር ለሌለንና ጽድቃችን የመርገም ጨርቅ ለሆነ፥ ተወደን ሳለን ለፍቅር ምላሻችን የሚስምን መንከስ ለሆነና በክርስቶስ ቁስል ጠጠር መጨመርን ተግባራችን ላደረግን ለሰው ልጆች መስቀሉ የፍቅር ሥፍራ መሆኑ መወደዳችን "ለምን?" እና "ከምን የተነሳ?" እንደሆነ እንድናስብ ያደርገናል። ስለዚህም በአንዳንዶች ዘንድ የምትክነት ሞት ጥያቄ ውስጥ ወድቋል። ምንም እንኳ ይህ ከመስቀሉ የፈለቀው ፍቅር ያልተለመደና እንግዳ ቢሆንም እንግዳነቱ እንደ ሰው ስናስበው እንጂ ከወደደን ከእግዚአብሔር አንጻር ካስተዋልነው የፍቅሩን ወደር የለሽነት የሚያስገነዝብ ነው። የምትክነት ሞት በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት የተገለጸ ሐሳብ ስለሆነም ሌላን "ሰው ተክቶ ሞትን መሞት

የሚችል የለም!" የሚለው የአንዳንዶች አባባል ተቀባይነት የለውም (ኤፌ 5:2፤ 1ኛቆሮ 15:3፤ ሮሜ 5:8 ወዘተ)::

ሉቃስ የክርስቶስ መስቀል ፍቅር የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆኖ ለእኛ የምትክነት ሞት ጽዋን እንዲጎነጭ ማድረጉን የሚያበስርበት የመስቀሉን ቃል የሚያሳስበው ነው:: ይህንን ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ይቅርታ በደሉን ስለመተውና በምትክነት መስዋእት በመሆን በደለኛውን ነፃ ስለማድረግ የክርስቶስ ግብር ሳስብ በአንድ ወቅት በድራማ መልክ የቀረበና የተመለከትኩትን ትዝ ያሰኘኛል::

አንድ ወጣት እመንገድ ላይ ሲጓዝ በአጋጣሚ በተፈጠረ ጠብ ሰው ይገድላል:: አገዳደሉም ተናዶ ሳለ በእጁ የገባውን ድንጋይ በመጠቀም የሟችን ጭንቅላት በመምታቱ ስለነበረ ልብሱ ላይ ደም ይረጫል:: የመታው ሰው መሞቱን ሲያስተውል እየሮጠ ወደ ቤቱ ይሸሻል:: በዚህ ወቅት እቤት እንደገባ በጣም የሚወደው ወንድሙ ያገኘውና ምን እንዳጋጠመውና ልብሱ ለምን በደም እንደተበከለ ይጠይቀዋል:: ገዳይም ከሰው እንደተጣላ፥ በድንጋይም ስለ መታው ሰውየው እንደሞተ፥ ፖሊስም ሲያባርረው እየሮጠ እንዳመለጠ ይነግረዋል:: ወንድምየውም በጣም ይወደው ነበርና የእርሱን በደም የተለወሰ ጃኬት አስወልቆ የራሱን ጃኬት በማልበስ በደም የተበከለውን ጃኬት ይለብሳል:: በዚህ ላይ እንዳለ በድንገት በር ይበረገዳል:: በርጋጁ ፖሊስ ነበር:: ወዲያውም በደም የተበከለ ጃኬት ለብሶ የተገኘውን ያለምንም ጥያቄ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይወስደውና በፍርድ ቤት ቀጠሮ እለት ለፍረድ ይቀርባል:: የወንጀለኛው ወንድም በደም የተበከለውን ጃኬት በመልበሱ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ተጠያቂና ወንጀሉ የነፍስ ግድያ በመሆኑ በወንድሙ ምትክ በስቅላት እንዲቀጣ ይደረጋል::

ከዚህ ድራማ እንዳስተዋልኩትና መጽሐፍ ቅዱስም በግልጽ እንደሚያመለክተው ስለ ቸር ሰው እንኳ ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል (ሮሜ 5:7):: ክርስቶስ ግን ስለ እኛ ስለ ኃጢአተኞች መሞቱን ይገልጻል (ሮሜ 5:8):: ይህ ማለት ደግሞ ኃጢአት ያላወቀው እርሱ ኃጢአት ሆኖ እንደሞተልን የሚያመላክት ነው (ኤፌ 2)::

አዎን! ለሉቃስ መስቀሉ የፍቅር ሰፍራ እንደሆነ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ከተናገራቸው ሰባት ቃላት ውስጥ ሁለቱ:- ለኃጢአተኞች ይቅርታ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽነት የታወጀባቸው ናቸው:: ስለዚህም በኢትዮጵያ ባብዛኛው ስለ መስቀሉ የጣር ስፍራነት ጎልቶ ከሚታይበት እይታ ባሻገር የመስቀሉን ምስጢራት አመጣጥና

እንደ ሉቃስም እመስቀሉ ስር በመግባት ከመስቀሉ የፈለቀውን ፍቅር ማስተዋል አስፈላጊ ነው፡፡

3. ለዮሐንስ *መስቀሉ የድል ሥፍራ* ነው/ዮሐ 19:26፤28፤30/፡፡

በቁጥር 26 ላይ «... እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት፡፡ ከዚህ በኋላ ደቀመዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው፡፡» ሊዮን ሞሪስ የተባሉ የሥነመለኮት ሰው በማብራሪያቸው፡- «ይህ አባባል ጌታ ይወደው የነበረው ደቀመዝሙር የኢየሱስን ስፍራ ይዞ የማርያም መከታና ጧሪ እንዲሆን አመልካች ሲሆን አሁን የክርስቶስ የማዳን ተልእኮ ማብቃቱን ያበስራል፡፡»[62] በማለት ያስረዳሉ፡፡

በቁጥር 28 ላይ፡- «የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ ተጠማሁ አለ፡፡» የሚለውም ሐሳብ የመጽሐፉ ቃል ፍጻሜ ማግኘቱን አብሳሪ ነው፡፡ በቁጥር 30 ላይ፡- «ተፈጸመ» የሚለው ቃል ደግሞ እንደ ሊዩን ሞሪስ አባባል፡- «ኢየሱስ በከንፈሮቹ ድል የሞላበት ጩኸትን አስተጋብቷል፡፡ ይህ የሽንፈት ሲቃ አልነበረም፤ ትህትና የሞላበት የሰቆቃ መገለጫም በመሆን ተሸናፊነትን አያንጸባርቅም፡፡ ሊፈጽመው የመጣውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቁን የሚያበስር የድል ብስራት ነበር፡፡[63] እንግዲህ አራቱ ወንጌላውያን ለመስቀሉ ያላቸው እይታ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ በተናገራቸው ሰባት ቃላት ውስጥ መስቀሉን ከሦስት የተለያዩ አቅጣጫዎች የማየት አስፈላጊነትን ያበስሩናል፡፡ በሀገራችን በኢትዮጵያ ባብዛኛው ሰዎች "ለመስቀል" እንጂ በመስቀሉ ለተሰራው ስራ ትኩረት በመንፈጋቸው ከምልክትነት ያለፈ ትርጉም እስከማይኖረው ድረስ የመስቀሉ ስራ እየተቀበረ ነው፡፡

ለዚህም ለአብነት ያህል የምጠቀሰው በክርስትና ስም በሚጠሩ የአምልኮ ቦታዎች የመስቀል ምልክትነት ከፍተኛ ስፍራ የተሰጠው ቢሆንም እንኳ በአመታዊ ክብረ በዓላት ጊዜ በተለየለት የመስቀል በዓል በባህላዊ ልምዶች ተሸፍኖ እንዲያውም ለባእድ አምልኮ እንኳ በር የከፈተና ያልተዋጀ ልምምድ በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር የመስቀል ምልክት በአንገት ላይ የሚንጠለጠል ጌጥና ክርስቲያን የመሆን መለያ ተደርጎ የመቁጠር፥ ወደየደብሩ አቅጣጫ ፊትን አዙሮ ማማተቢያ እንዲሁም እንደ መስቀሉ ቅርጽ አይነት የትግሬ፥ የጎንደር፥ የጎጃም እየተባለ የቅርጹ ውበት የሚደነቅበትና በምልክትነት ብሔሮችን የሚያስተዋውቅ የቱሪስቶች መስህብ ሆኗል፡፡

ይህንን ሳስብ ከአራት አመት በፊት በአዲስ አበባ ውስጥ በታክሲ እየተጓዝኩ ሳለሁ ያስገረመኝን ነገር መጥቀስ አስፈላጊ መስሎ ታይቶኛል፡፡ ከቄራ ወደ ፒያሳ በመጓዝ ላይ እንዳለሁ ድንገት የታክሲውን ረዳት ስመለከተው የሙስሊም ቆብ አድርጓል፥ ተለቅ ያለ የእንጨት መስቀል

በክር አንገቱ ላይ አስሮ ደረቱ ላይ ከሸሚዙ በውጭ በኩል በግልጽ ስፍራ አንጠልጥሏል፥ ደግሞም በካሴት ከወንጌላውያን ቤተክርስቲያን አባላት የአንዷ እህት ዝማሬ ነበርና በልዩ ሁኔታ ምናልባትም ባላጋንን እያመለከ አቀላጥፎ ይዘምራል:: እኔም በመደነቅ ማንነቱን ስጠይቀው ወቅቱ የሙስሊም ፆም የተያዘበት ነበረና ያደረገውን ቆብ እየነካ በምልክት ምላሽ ሰጠኝ:: እዚህ ላይ ለማስተዋል የሞከርኩት የውጫዊ ምልክት ምንም ፋይዳ እንደሌለውና የእውነተኛ ማንነት መገለጫ ሊሆን እንደማይችል ነው::

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን በክርስቶስ መስቀል ከተከናወነው ታላቅ ምስጢር ይልቅ የምልክት አፍቃሪያን በመሆን ላይ ያለን ትኩረትም ለመስቀሉ ሥራ መቃለል አይነተኛ ምክንያት ነው:: ነገር ግን መስቀሉን ለሰው ልጆች ታላቅ ዋጋ የተከፈለበት፥ ፍቅር የተላለፈበትና ድል የታወጀበት እንደሆነ በማስተዋል ዘወትር ልንኖርበት የሚገባንን ታላቅ እውነት ቸል ካለ ህይወት ልንርቅ ይገባል::

## ለ. ሥርየት

ቁርዓን አምስት ጊዜ በመደጋገም የሚናገርበት ነገር ቢኖር *የሌላውን ኃጢአት መሸከም የምትችል ነፍስ እንደሌለች ነው::* ከዚህም የምንገነዘበው እስልምና የሚሰብከው እያንዳንዱ ሰው የስራውን ፍሬ እንደሚያጭድ ነው:: ስለዚህም አንዳንዶች:- «የመርየምን ልጅ አልገደሉትም፥ አልሰቀሉትም፤ ነገር ግን እንደገደሉት አሠቡ እንጂ» በማለት እንዲያውም በመቀጠል ሲናገሩ በነቢይ ኣላህ ኢሳ ፈንታ እጣ በማውጣትና ኣላህ ልጁን ለመታደግ ባደረገው ጥረት ወይ የአስቆሮቱ ይሁዳን ወይም ደግሞ የቀሬናው ስምዖን በእርሱ ፈንታ እንዲሞት አድርጓል በማለት ይተርካሉ:: በ19ኛው ክፍለ ዘመን አህመዳውያን በመባል የሚጠሩ የሐይማኖት ቡድኖች ከክርስቲያን ሊበራል ጽንሰ ሀሳብ በመውሰድ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ልቡን ነስቶ (Faint) አድርጎ፤ መቃብር ውስጥ ሲገባ ግን አንሰራርቷል:: ከዚያም ወደ ህንድ ተጉዞ አስተምሯል በመጨረሻም እዚያው ሞቷል በማለት እነርሱም በካሽሚር ያለው የእርሱ መቃብር ጠባቂዎች እንደሆኑ ይናገራሉ::[64]

ይህንን የካሽሚሮችን አባባል ሳስብ በቅርቡ በአካል የማላውቀውና በስልክ ተገናኝተን አስደናቂ የክርስትናን ምስጢር ገላጭ ሃሳብን ያጫወተኝ ሰው ትዝ ይለኛል:: ይህ ወንድም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ሲናገር:– "የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ውበቱ ባዶነቱ ነው!!" አለኝ:: በእርግጥም ካሽሚሮች የሚጠብቁት መቃብር የኢየሱስ ሳይሆን በምትክነት መሞት የማይችል ተፈጥሮአዊው ሰው ነው::

የኢየሱስ ሞቱም ሆነ ትንሳኤው የምትክነት ሞትና የትንሳኤም በኩር በመሆኑ ሥርየትን ዐላማው ያደረገ ነበረ።

እንግዲህ ክርስትና መስቀሉን እስካልተረዳን ክርስቶስን እንዳልተረዳን ያመለክተናል። ስለ ክርስቶስ መስቀልም ስናነሳ፡- እኛን ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብ÷ ስለ ኃጢአታችን÷ ሞታችንን ድል ለመንሳት ወዘተ ክርስቶስ እንደሞተ በግልጽ ያስገነዝበናል። በሥነ መለኮቱ ዓለም ለክርስቶስ የመስቀል ሞት በዐላማነት ከሚጠቀሱ ነጥቦች አንዳንዶቹን እንመለከታለን። ከእነዚህም ውስጥ በኃጢአት ላይ በተወሰደው እርምጃ *ለእግዚአብሔር እርካታን ማስገኘት* የሚለው የመጀመሪያው ነው። በዚህ በምትክነት እርካታ ማስገኘት ላይ አሊስተር ሐርዲ የተባሉ በኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ የእፅዋት ተመራማሪ ፕሮፌሰር በ 1965 ዓ.ም ባወጡት «መለኮታዊው ነበልባል» (*The Divine Flame*) በተሰኘው ጽሑፍ፡- «እኔ እጠራጠራለሁ! ደግሞም እግዚአብሔር ኢየሱስን ዘግናኝና ጭካኔ በሞላበት መንገድ መስዋእት በማድረጉ እንዲሁም ስቃዩ በጠናበት አካል ሞት ቁጣዬ ይበርዳል እንደማይል እርግጠኛነት ይሰማኛል... የክርስቶስ ሞት ለዓለም ኃጢአት የተፈጸመ የመስዋእት ሞት መሆኑን ወይም እግዚአብሔር በልጁ ራሱን ለእኛ መቤዠት ብሎ አሰቃይቷል የሚለውን አባባል መቀበል አልችልም!» በማለት እንዲውም፡- «ኢየሱስ እንኳን በዚህ ዘመን በምድር በሥጋ ቢኖር ክርስቲያን ይሆናል ብዬ አላምንም። ... ለእኔ ይህ ኢየሱስ ካስተማረው ሐይማኖት የተለየ ሐይማኖት ነው።» ብለዋል።[65]

በሌላ በኩል ደግሞ መስቀሉን *ለሠይጣን እርካታ ማስገኛ* አድርገው በመቁጠር የዲያብሎስ ምንዳ እንደሆነ የሚሰነዝር አስተምህሮም አለ። ይህ በጥንታዊቱ የግሪክ አባቶች ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት የተቸረው ነበር። በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ እንዲሰቀል ያደረገው ሠይጣን ነው የሚል እምነት ነበረ። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መስቀሉ ለሠይጣን ስልጣን መገፈፍ እንደሆነ ያበስራሉ። ከውድቀት ጀምሮ የሰው ዘር ለኃጢአትና ለበደል ብቻ ሳይሆን ለዲያብሎስም የተገዛ እንደነበር ያመለክታሉ። ሠይጣን የኃጢአትና የሞት ጌታ እንደሆነ ይታሰብ ስለነበረ ኢየሱስ ሰዎችን ነፃ ለማውጣት እንደመጣ ይታመናል።

ስለዚህ፡- "እኛን ከሠይጣን ባርነት ነፃ ለማውጣት የክርስቶስ ደም ለሠይጣን ካሳ ተከፍሏል። ነገር ግን ሠይጣን የክርስቶስን ደም ካሳ አግኝቶ እኛን ከባርነት ከለቀቀን በኋላ ክርስቶስ ከሞት በመነሳቱ ተታልሏል።" የሚል አመለካከት ይሰነዘራል።[66] ይህንን እምነት ለመሰንዘር ኦርጂን የመጀመሪያው ሰው ነበር።

የዚህን አስተምህሮ ችግር ስንቃኝ፡- ለሠይጣን ካለው ሃይል በላይ መስጠቱ÷ መስቀሉን ሠይጣን በግዞት ስር ላዋላቸው የካሳ ክፍያ

በመጠየቁ የተሠጠው እንደሆነ መቆጠሩና በኃጢአተኛው የሰው ዘር ላይ ያለውን ስልጣን ከኃጢአት ነፃ በሆነው በክርስቶስ ላይ እንዳለው መቆጠሩ በጥንቃቄ መታየት ይገባቸዋል (እብ 2:14)::

በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስ ሞት *ለህግ እርካታን ማስገኘት* እንደሆነ በተለይ የጥንት የላቲን አባቶች አመለካከት እንደነበረ ይታመናል:: ኃጢአት ህግ አልባነት ነው (1ኛዮሐ3:4):: ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ህግ ማጣጣልና አለመታዘዝ ነው:: ኃጢአተኞች ህግን የመተላለፋቸውን ቅጣት መቀበል አለባቸው:: ነገር ግን የህግ ፍርደኛ የሆኑበትን የቅጣታቸውን ክፍያ ክርስቶስ ከፍሎታል:: ስለዚህ ህግ ተክሷል፤ በትንቢተ ዳንኤል ምእራፍ 6 ላይ ንጉሡ እንደ ህጉ ሳይሆን በተገቢው መንገድ ፍርደኛ ያደረገንን ህግ የሚጠይቀውን ዋጋ ከፍሎ እኛን ከህግ እርግማን ዋጀን (ገላ3:10 ÷ 13)::

ሌላው የሥርየት ጽንሰ ሀሳብ ደግሞ *ለተነካው የእግዚአብሔር ክብር የሚሆን እርካታን ማስገኘት* ነው:: ይህ የካንቲቡሪው አንስላም በመባል የሚታወቀውና በ11ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ አመለካከት ነው:: በዚህም የመስቀል ዐላማ የተነካውን የእግዚአብሔርን ክብር ማርካት በመሆኑ ሠይጣን ድል የተነሳ እንጂ እግዚአብሔርን ባለ እዳ አድርጎ ካሳ የሚሻ አይደለም:: ይልቁንም እርሱ ቅጣት የሚጠብቀው ነበር:: ስለዚህም አብ ምህረትንና ፀጋን አበዛልን÷ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ አረካልን መንፈስ ቅዱስ ሙት ለሆነው ማንነታችን ህይወትን በመዝራት በእውነተኛና በህያው እምነት ድነትን እንድናገኝ አደረገን::

እንግዲህ የክርስቶስ የመስቀሉ ዐላማ ማእከሉ *የምትክነት ቅጣት መቀበል* ነው:: ይህም ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷል (ኤፌ 5:2፤ ዕብ 9:6-15፤ ኢሳ 53፤ ሮሜ 5:8)÷ ደግሞም የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ ኃጢአታችንን ተሸክሞ ቅጣታችንን ተቀብሏል (ሮሜ 3:25፤ ዕብ 2:17፤ 1ኛዮሐ 4:10) ማለት ነው:: ምንም እንኳን ከላይ የተገለጹ ነጥቦች የእግዚአብሔር እውነት ያለባቸው ቢሆኑም ይህ የምትክነት ቅጣት ግን ከሁሉም በላይ የሥርየትን መሠረታዊ ትርጉም ይዟል::

### 2.1.2. የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ሞት ነውን?

በዘመናችን አንዳንድ የኃይማኖት ቡድኖች የክርስትናን እምነት ለማጣጣል ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች አንዱ በክርስቶስ ሞት ላይ ያነጣጠረ ነው:: ጥያቄውም "የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ሞት ነውን?" የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ በሚሰነዘረው ምላሽ ላይ ተከታታይ ጥያቄዎችን ያነሳሉ:: መቼም በትክክል የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ «አዎን!» የሚል ነው:: የተከራካሪዎች ቀጣይ ጥያቄ ደግሞ:- "እግዚአብሔር ይሞታልን?" ወይም "ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ

የማይሞት መሆኑ ነው ትሉ የለምን?" ሲሉ በሌላው በኩል ደግሞ "የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ሞት ከሆነ ክርስቶስ ሞቶ በመቃብር ባደረባቸው ሦስት ቀናት ዓለምን ይገዛት የነበረው ማን ነው?" የሚሉ ናቸው።

ለእነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ የክርስቶስን ማንነት ኢትዮጵያውያን መምሬዎች ከሚመለከቱባቸውና ከሚረዱባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ ግንዛቤን ማጤን ያሻል። "ተዋሕዶ" የክርስቶስ አካል የትሥጉት አካል ነው። ክርስቶስ አምላክ-ሰው ነው። ስለዚህም የሰባዊና የመለኮታዊ ባሕርያት ጥምረት በአንዱ አካል የሚገኝበት በመሆኑ *አምላክ በሥጋ ሞተ! እንጂ የክርስቶስ ሥጋው ሞተ፥ አምላክነቱ ግን አልሞተም በማለት የሚነጣጥል እሳቤ ተቀባይነት የለውም*። ለዚህም ዋና ምክንያቱ የክርስቶስን ሞት ከሌላ የሰው ባሕርይ ብቻ ካለው (ሰው ብቻ ከሆነ) አካል ልዩ የሚያደርገው አምላክ *በሥጋ* የመሞቱ ምስጢር ነው (ጴጥ 3:18)። በዚህ ክፍል ውስጥ ክርስቶስ በሥጋ እንደ ሞተና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሙታን እንደተነሳ የሚያመላክትን ሃሳብ እናገኛለን። እንግዲህ የቃላት ጫወታ ያይደለ ታላቅ ትኩረትን የሚሻው ነገር፦ በሥጋ ሞተ ማለት ሥጋው ሞተ ማለት ሳይሆን አምላክ በሥጋ ሆኖ (በትሥጉት አካል) መሞቱን ነው። ይህም ማለት አምላክ በራሱ ባሕርይ አይሞትም፤ ነገር ግን በተዋሕዶ (በጥምረት) የራሱ ባደረገው በሥጋ መሞቱን አመላካች ነው። የትሥጉት አካል ሞት የአምላክ (የእግዚአብሔር) በሥጋ መሞት እንጂ በመለኮት ባሕርይ መሞትን ወይም ደግሞ የሚሞት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ መለኮትነት የነበረው መሆንን አያመላክትም። ስለዚህም ከታሪካዊ ሥነ መለኮት እንደምንረዳው ከእነ ቅዱስ ቄርሎስ በፊት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አባት የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ፦ "አምላክ መሆኑን ሳይለቅ፥ ቀድሞ ያልሆነውን ሰው ሆነ።" (He became what He was not, He continued to be what He was) ብሏል።[67]

ይህንን ነጥብ በጥንቃቄ ስንቃኘው ክርስቶስ በሥጋ ጸባይ ማለትም በሚሞተው የሰው ባሕርይ ግብር ሞተ ቢባልም፤ በማይሞተው በአምላክ ባሕርዩ ግብሩ ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አቻ ንጉሥ ነበር። ይህ ደግሞ የባሕርይ መንታነትን ሳይሆን የሁለቱ ባሕርያት ተዋሕዶ (ጥምረት) ሚስጥር ከመረዳት አንጻር ብሩህ ሆኖ የሚታይ ነው። በተዋሕዶ የማይሞተው በሚሞተው መሞት ሲችል፥ የማይመለከውም በሚመለከው መመለክን ተላብሷል። ለዚህም ከተዋሕዶ ምስጢር ማብራሪያዎች አንዱን እንመልከት፦ ቁራጭ ብረትን በሚንበለበል እሳት ውስጥ ጨምረን በማውጣት በመዶሻ ብንመታው የመታነው "የጋለውን ብረት" እንጂ ብረቱን ብቻ ነው

ማለት እንደማንችል ሁሉ በትሥጉት አካል በክርስቶስም ላይ የሆነው ሁሉ በአምላክ–ሰው ላይ የተፈጸመ እንጂ በሥጋው ላይ ነው አይባልም:: ይህንንም ስንል የተራበው÷ የተጠማው÷ መከራን የተቀበለው÷ የተሰቀለው÷ የሞተውና የተቀበረው አምላክ–ሰው የሆነው ክርስቶስ እንጂ ሰባዊ ባሕርዩ ብቻ አልነበረም::

የሁለቱ ባሕርያት ጥምረት በአንዱ በክርስቶስ ውስጥ:– ያለመነጣጠልና ያለመለያየት ነበሩ:: ቁራጩ ብረት የሚመታ ባሕርይ ሲኖረው የሚንበለበለው እሳት ግን በባሕርዩ አይመታም:: የማይመታው በሚመታው የተመታው በተዋሕዶ እሳቱ ከብረቱ ጋር በመጠመሩ ነው:: እንዲሁም የማይሞተው አምላክ የሞተው ከሚሞተው የሰው ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ (ተጠምሮ) ስለ ነበረ ነው:: ይህ ደግሞ የጋለው ብረት የእሳትን ጸባይ (የባሕርይን ግብር) እንዳልለቀቀ ሲነካ በማቃጠል እንደሚያረጋግጥልን÷ ነገር ግን እሳቱን በተናጥል እንደማናገኘው ሁሉ ተዋሕዶ ሁለቱን ባሕርያት ባተናጥል መገኘት ሳይሆን ባሕርያቱ ያላቸውን ጠባይ (character and characterstics) እንዳልለቀቁ የሚያስገነዝብ ነው:: ይህንን ሃሳብ እየተጠቀምንበት ባለው ማብራሪያ ከተመለከትነው በጋለው ብረት ውስጥ የምናገኘው የሚንበለበውን እሳት ባሕርይ ሳይሆን የማቃጠል ጠባዩን ነው:: ስለዚህም የባሕርይንና የጠባይን ልዩነት በጥንቃቄ ማስተዋል ያሻል::

ሊቀ ጠበብት አያሌው ታምሩ:– "ኢትዮጵያስ፤ ባሕርይ÷ ምን ግዜም ቢሆን ረቂቅ፤ ለሕሊና እንጂ ለዓይንና ለእጅ የማይመች፤ መሆኑን አካል እንደ ባሕርዩ ሁኔታ በግዘፍ ሆነ በርቀት ባሕርዩን እየገለጠ ለዓይንና ለእጅ በመመቸቱ ባሕርይ ምን እንደሆነ ÷ ለሚመረምር ሁሉ መምህር ሆኖ መኖሩን ታውቃለች ታስተምራለች:– … ጠባይዕ የሚለው ቃል ምን ግዜም ቢሆን እርሱ ባያውቀው ነው እንጂ የባሕርይ ግብርን ከማመልከት በስተቀር ባሕርይን ለማመልከት አይገባም፤ ሲነገርም፤ በሞያው ከሆነ ለፈጣሪም ሆነ ለፍጡር ይነገራል::" በማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥነ መለኮት ሰውና የኬልቄዶን ተከታይ የሆነው ዶ/ር አየለ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለነበረው የተሳሳተ አመለካከት ምላሽ ሰጥተውበታል::[68]

ከዚህ ከላይ ከተጠቀሰው ትርጉም በመነሳት ባሕርይና ጠባይዕ በአሁኑ ወቅት በተለምዶ የትርጉም ለውጥ ያመጣውና በዘመናችን በማስታወቂያ በተደጋጋሚ እንደምንሰማው:– "የኤድስ ሰለባ ላለመሆን የባሕርይ ለውጥ አምጣ!" እንደሚባለው ያለ አይደለም:: ሰው ለውጥ ማምጣት የሚችለው የባሕርይ ሳይሆን የጠባይዕ ነው:: ጠባይዕ ደግሞ

የባሕርይ ግብር ነው እንጂ ራሱ ባሕርይ አይደለም። ስለዚህም ሰው ባሕርዩን ለውጦ ሰው መሆኑን ትቶ ምን መሆን ይችላል? በዚህ ዘመን "ባሕርይህን ለውጥ!" በማለት ሰው ሊለውጥ የማይችለውን ባሕርዩን ለመለወጥ በሚያደርገው ትግል ተሸናፊ በመሆኑ ቀሳፊ በሽታው እድል ፈንታ ማግኘቱ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። ስለዚህም ሰው ሊለውጠው ከሚችለው ከባሕርዩ ግብር አንጻር "ጠባይህን ለውጥ!" በሚለው ትክክለኛ አገላለጹ መጠቀም ያስፈልጋል። የክርስቶስንም ሞት ስንናገር የሥጋ ባሕርይ ሞት ሳይሆን በተዋሕዶ የአምላክ በሥጋ ጠባይዕ (በሥጋ ባሕርይ ግብር) ሞት እንጂ ከተዋሕዶ በኋላ ባሕርያትን መነጣጠል አይቻልም።

እንግዲህ አምላክ በሥጋ መሞት የቻለው ደም የሌለው ረቂቁ አካላዊ ቃል አካል የሰውን ደም የራሱ (የእግዚአብሔር) ደም አድርጎ ነው (ሐዋ 20:28)። በክርስቶስ አምላክ በሥጋ ሞተ እንጂ በራሱ የአምላክ ባሕርይ ግብር ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዓለምን ይገዛ ነበር። አምላክ በአምላክ ባሕርዩ ሞተ ማለትማ በእርግጥም በባሕርዩ መፋለስ ገጥሞታል፥ ዓለምንም ለሦስት ቀናት በዑደት መርቷታል! የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መላምት ውስጥ ይከትታል። ከዚህም በተጨማሪ የሞተው ሥጋው (ሰባዊ ባሕርይ) ነው ማለትም የክርስቶስን ሞት የሰው ሞት ብቻ ስለሚያስኘው ከእነ ሙሴ ሞት ያልተለየ ያደርገዋል። ስለዚህም ከሥርየትም አንጻር የሰዎችን ኃጢአት ለማስተሰረይ ብቁነቱን ጥያቄ ዉስጥ ይጥላል። ኢትዮጵያውያን መምሬዎች የክርስቶስን ሞት የአምላክ በሥጋ መሞት እንጂ የመለኮት ወይም የሥጋ ባሕርይ በተናጥል መሞት እንዳይደለ ሁለቱ ባሕርያት ከተዋሕዶ በኋላ በተናጥል መገኘት የማይችሉበት ጥምረት ስላላቸው በ"ተዋሕዶ" ያምናሉ። የክርስቶስን ሞትም የአምላክ በሥጋ (በሰብአዊ ባሕርይ ግብር) ሞት እንጂ አምላክ (በአምላክ ባሕርይ ግብር) ሞት እንዳሌለበት ጥንቃቄ በሞላበት መንገድ መረዳት እንደሚያስፈልግ አበክረው ይገልጻሉ።

ስለዚህም በክርስቶስ አምላክ በሥጋ ባሕርይ ግብር ሲሞት በአምላክነት ባሕርይ ግብር ደግሞ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው አቻ ንግሥና በሠማይ ዙፋኑ ላይ ሆኖ ዓለምን ይገዛ ነበር። ይህ አምላክ በትሥጉት አካል በክርስቶስ ያለውን አቻ ንግሥና በተመለከተ በሞቱ ብቻ ሳይሆን በምድር ከመወለዱ እስከ መስቀል ሞቱ ድረስ ያሳለፈበት ማናቸውም ነገሮች በሥጋ ባሕርይ ግብር እንደ ሰው በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ያሳለፈበት ሲሆን ሳለ እንደ እግዚአብሔርነቱ ከአብ ጋር ባለው አቻ ንግሥና በሠማይ ዙፋን ላይ ሆኖ ዓለምን ይገዛ እንደ ነበረ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።

## 2.2. የክርስቶስ አገልግሎቶች:-

በብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሳን አባቶች ለተለዩበት አገልግሎት ለምሳሌ:- እንደ ክህነትና ንግሥና ላሉ አገልግሎቶች ይቀቡ ነበር:: ስለ ጌታ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ (የተቀባ) መሆን ስናነሳ ለምን ተግባር እንደተቀባ መጠየቅ አለብን:: የኢየሱስ መቀባት በኢትዮጵያ መምሬዎች ዘንድ ከተለያየ አቅጣጫ ግንዛቤ ተችሮታል::

በኢየሱስ መቀባት ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች:- (ኢሳ 61:1፤መዝ 2:2 (44):8፤ ዳን 9:25፤ዕብ 1:9፤ማቴ 3:16) ሲሆኑ በእነዚህ ክፍሎች ላይ ኢትዮጵያውያን መምሬዎች የተለያዩ ድምዳሜዎች ላይ ደርሰዋል:: ስለ ክርስቶስ መቀባት በደብረ ሊባኖስ ገዳም የተገኘውና «የፀጋ ልጅ» በመባል የሚታወቀው የሥነ መለኮት ቡድን መምሬዎች:- "አብ ቀቢ÷ ወልድ ቅብ÷ መንፈስ ቅዱስ ቅብዓት" በማለት ሥጋ በተዋሕዶ ከበረ ወይም ከቃል ጋር በመዋሐዱ ከበረ÷ ክርስቶስ በተዋሕዶ የባሕርይ ልጅ ነው የሚል አስተምህሮ አላቸው:: በመቀጠልም በተዋሕዶ ወልድ ዋሕድ÷ በቅብዓት መሲሕ ሆነ ይላሉ:: ክርስቶስ ሦስት ልደት አለው:- 1ኛ ከአብ:- ከዘለዓለም 2ኛ ከድንግል:- በጊዜ ስሌት ውስጥ በሥጋ መወለዱ 3ኛ ከመንፈስ ቅዱስ ቅብዓት መወለዱ:: በማለት የቅብዓት አስፈላጊነቱ የኢየሱስን መሲህ መሆንና ሦስተኛ ልደት ማግኘቱ የተረጋገጠለት በመሆኑ ነው በማለት ይገልጻሉ:: ቅብዓት በመባል የሚታወቀውና የጎጃሜዎች የባሕል መግለጫ እንደሆነ የሚነገርለት አስተምህሮት ደግሞ:- «ከመለኮት ጋር መዋሐዱ ለትሥብእት እንደ ቅብዓት ሆነለት በቅብዓት የባሕርይ ልጅ ሆነ:: ተዋሕዶ የተፈጸመው በቅብዓት ነው:: ክርስቶስ የአምላክ የባሕርይ ልጅ የሆነው በቅብዓት ነው:: ክርስቶስ ሁለት ልደት ብቻ አለው:- 1ኛ ከእግዚአብሔር አብ እምቅድመ ዓለም ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ ድኅረ አለም ከድንግል ማሪያም ያለ አባት መወለዱ:: በማለት ሁለተኛውና ቅብዓት በመባል የሚታወቀው ቡድን አስተምህሮቱን ይገልጻል::»[69]

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ሁለት በቅብዓት ላይ የተሠነዘሩ የሥነ መለኮት እሳቤዎች በማደጎ ልጅ (Adoptionist) አስተምህሮት በኑፋቄ ውስጥ መውደቅ በመግለጽ የተዋሕዶ መምሬዎች ደግሞ ግንቦት 18 ቀን ወር 1870 ዓ.ም. ወሎ ውስጥ ቦሩ ሜዳ በተባለ ሥፍራ በተደረገ ክርክር ክርስቶስ ሁለት ልደት እንዳለው አስረድተዋል:: ክርስቶስ የባሕርይ ልጅ÷ በሰውነቱም አምላክ ነው:: በማለት በዮሐንስ 4ኛ እና በዳግማዊ ምኒሊክ በተጠራው ጉባዔ ፊት ገልጸዋል::[70] ክርስቶስ ሁለት ልደት በተዋሕዶ የከበረ ነው:: ወልድ በራሱ ልዩ አካል ቅብ ነው:: በሰውነቱም የባሕርይ አምላክ ነው:: በማለት የ"ሦስት ልደት" ቡድን

በተጨማሪ ነቢያት እንኳ ስለ ክርስቶስ የነቢይነት አገልግሎት የተናገሩለት እንደሆነም ያስረዳናል (ሐዋ 3:24)።

እንግዲህ ስለ ክርስቶስ ነቢይነት ስናነሳ በአንዳንዶች ዘንድ እንደተለመደው ሰው ብቻ ሳሉ የነብይነትን አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር ማነጻጸር የተሳሳተ ከመሆኑም በላይ የክርስቶስን ማንነት ካለማስተዋል የሚመነጭ ሚዛን የሳተ ድምዳሜ ነው። ከዚህም በመነሳት በክርስቶስ የተገለጸው እውነት ከማንም ከምንም በላይ እንደሆነ ማስተዋልና የአስተርእዮ ቁንጮነቱ ስለ ነቢይነቱም ነቢያት የተናገሩለት እንዲሁም እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ ራሱን ለሰዎች ያስተዋወቀበት አስርተዕዮ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

## 2.2.2. ክህነት

በብሉይ ኪዳን ሁለት አይነት የክህነት አገልግሎትን እንመለከታለን። የመጀመሪያውና በጥልቀት ልንረዳው በቂ መረጃ የሌለን የመልከ ጼዴቅ ክህነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሌዊ ነገድ የክህነት አገልግሎት ነው። የክርስቶስ የክህነት አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ነው (መዝ(110):4፤ ዘካ6:13)። በዚህም የመልከ ጼዴቅ ክህነት ወደ ክርስቶስ የሚያመለክት እንደሆነ እንረዳለን (ዕብ 5:6)። የክርስቶስ ግብር የሊቀ ክህነት አገልግሎት ነው (ዕብ 8:1-2፤ 9:11-14፤ 10:11-14)። እንግዲህ የክርስቶስ ክህነት እንደ መልከ ጼዴቅ እንጂ እንደ ሌዊ ያለ ክህነት ካይደለ በልዩነት ከሚነሱ ነገሮች የሌዊ ነገድ ካህናት የሆኑቱ ዘላለማዊ እንዳይደሉና በየጊዜው መስዋዕትን ማቅረብም ይጠበቅባቸው እንደ ነበር ማስተዋል ያሻል (ዕብ 7:11፤20-25)። ክርስቶስ ግን በገዛ ደሙ የክህነት አገልግሎት ያለው ነው (ዕብ 9:6-14)። እንግዲህ ከክህነት ሚናዎች ውስጥ መስዋዕት ማቅረብ፥ ሥርየትን ማሰጠትና ማማለድ በቀደምትነት የሚጠቀሱ ቢሆኑም የማማለድ ሚናን በተመለከተ በኢትዮጵያውያን መምሬዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ ስለ ክርስቶስ ማንነት ባለው የአስተምህሮ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ነው። ለመሆኑ የክርስቶስ አማላጅነት በኢትዮጵያውያን እይታ ምን ይመስላል?

### 2.2.2.1. ክርስቶስ አማላጅ ነውን?

ከሁሉ አስቀድሞ "ማማለድ" የሚለው ቃል ፍቺ በትክክል መቀመጥ ይኖርበታል። አንዳንድ የኃይማኖት አባቶች ማማለድ ለሚለው ሥረው ቃሉ "ማለዳ" የሚለው ቃል እንደሆነና በማለዳ ገስግሶ ፍርደኛውን ነፃ ማውጣትን የሚያመለክት ቃል መሆኑን ይናገራሉ (መጠይቅ አቶ ጸጋዬ)። ከዚህም በመነሳት በአሁኑ ወቅት ያለው የቃሉ አጠቃቀም የትርጉም ለውጥ እንዳመጣ ያስገነዝባሉ። በአሁኑ ወቅት የማማለድ

በተከታታይ ጥያቄዎች ለማጎልበትና የክርስቶስን የፀጋ ልጅነት ለመግለጽ የሞከረባቸውን መንገዶች ይቃወማሉ:: የሦስት ልደት ቡድን ተከታታይ ጥያቄዎችም:- 1) እግዚአብሔር አዳምን ሕያው ነፍስ ያለው አድርጎ ሲፈጥረውና በመንፈስ ቅዱስ ሲያከብረው የፀጋ ልጅ አላደረገውምን? 2) አዳም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሱ ይህ የፀጋ ልጅነቱ በውድቀት ተጽዕኖ ውስጥ አልወደቀምን? በማለት ለሁለቱ ጥያቄዎች ከተዋሕዶ ሊቃውንት የተሰነዘረውን አዎንታ በመጠቀም ሦስተኛውን ጥያቄ ጠይቀዋል:: 3) አዳም የእግዚአብሔርን ህግ ጠብቆ ቢሆን ኖሮ የእኛ በኩር ይሆን ነበር÷ አይሆንም ነበርን? ለሚለው የመከራከሪያ ጥያቄያቸው የተዋሕዶ ሊቃውንት በመወከል የቀረቡት መላከ ብርሃን ይህ «...ቢሆን ኖሮ...ይሆን ነበር::» የሚል አጠቃቀም በመከራከሪያነት ማስፈር እንደማይገባ በነገሥታቱ ፊት በማቅረብ በሦስት ልደት ቡድን ላይ አስቀውባቸዋል::[71]

በዚህ ክርክር ውጤት ላይ በመንተራስ ጉባዔው የሚከተለውን የእምነት አንቀጽ አውጥቷል:- «ክርስቶስ ሁለት ልደት አለው:: በተዋሕዶ ከብሯል:: በሥጋው የባሕርይ አምላክ ነው:: በሰውነቱ እንደ አብና መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ከዚህም የተነሳ እውቀትን ገላጭም ነው:: ወልድ በራሱ ልዩ አካል ቅብ ነው:: ይኸውም «ወልድ ቅብ» ማለት ነው::[72]

ከላይ ከተዘረዘሩት ሥነ መለኮታዊ እሳቤዎች በመነሳት የክርስቶስ መቀባት በኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ መምህራን ዘንድ እንደ ብሉይ ኪዳን አባቶች በተለያዩ አገልግሎቶች ከመለየት አንጻር ሳይሆን ከትሥጉት አካል ማንነት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ነጥብ ነው:: ከዚህም የተነሳ የትሥጉት አካል ክርስቶስ በሥጋው የባሕርይ አምላክ የሆነው በመልአኩ ብስራት ወቅት ሁለቱ ባሕርያት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ÷ አንድ አካል በመሆናቸውና ቅብዓቱ የክርስቶስን ስብእና ከአዳም መተላለፍ ውድቀት ማንጻቱን አመላካች ነው:: ይኸውም «ሥጋ በተዋሕዶ ከበረ» ማለት ነው:: ስለዚህ የክርስቶስን አገልገሎቶች በመንፈስ ቅዱስ ከመቀባቱ ጋር በማያያዝ ሳይሆን ራሱ ቅብዓት÷ ቅብ እና ቀቢ ስለሆነ ከግብረ ትሥብእት አንጻር አምላክ ሰው ሆኖ ሰዎችን ከአብ ጋር ለማስታረቅ የፈጸማቸውን ግብራት አመላካች ነው:: በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በቅዱሳን አባቶች የተጠቀመባቸው ሦስት የተለያዩ አገልግሎቶችን ክርስቶስ እንደያዘ ተመላክቷል:: እነዚህ ሦስት አገልግሎቶች:-ገላጭነት(Revealing)÷ገዥነት(Ruling) እና አስታራቂነት (Reconciling) ናቸው:: እነዚህ የአገልግሎት ቢሮዎች (Offices) የክርስቶስ ተልእኮን የሚያስፈጽሙ እንደሆኑ ማስተዋል ተገቢ ነው::

### 2.2.1. ነቢይነት (ገላጭነት)

#### 2.2.1.1. ክርስቶስ ነቢይ-አምላክ ነውን?

በዘዳግም 18:15-19 እግዚአብሔር እንደ ሙሴ ያለ ነብይን እንደሚያስነሳ በገባው ተስፋ መሠረት በሐዋ 3:22-23 ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ተብሎ ትንቢት የተነገረለት እንደሆነ ፍጻሜውን አመላክቷል:: ከዚህም በተጨማሪ በሉቃ 13:33 ላይ ኢየሱስ ራሱ ነቢይ እንደሆነ ገልጿል:: ሌሎች ኢየሱስ ነቢይ እንደሆነ የሰጡትን ምስክርነቶች በሉቃ 24:19 እና ማቴ 21:11 ላይ እንመለከታለን:: እንግዲህ የነቢይን ማንነት ለመገንዘብ አስቀድሞ ተግባሩን ማጤን ያሻል:: ነቢይ ማለት ከእግዚአብሔር መልእክትን ተቀብሎ ለሕዝብ የሚያስተላልፍ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ነቢይ በመሆኑ ከአብ የሰማውን ያንኑ አስተላልፎልናል:: እንዲያውም የዕብራውያን ጸሐፊ መልእክቱን ሲጀምር እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ በውድ ልጁ መናገሩን ይገልጻል (ዕብ 1:1):: የኢየሱስ የነቢይነት አገልግሎት እርሱ በአብ÷ አብም በእርሱ በመሆኑ የእግዚአብሔር ምሉዕ መገለጥ ሆኖ እግዚአብሔርን በማስተዋወቁ (በመተረኩ) ነው::

እንግዲህ ምንም እንኳ በኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ ሊቃውንት ዘንድ ቅብዓት ከአገልግሎት ወይም ከግብር (Function) ጋር ሳይሆን ከማንነት (Person) ጋር በተያያዘ የሚነሳ ቢሆንም የክርስቶስ ገላጭነት ወይም ደግሞ የነቢይነት ሚና አምላክ ሰው ሆኖ በሰዎች መካከል በማደር የማይታየውን ባሕርዩን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት የገለጸበት አስተርእዮ ነው (ዕብ 1:1):: ይህ ደግሞ የክርስቶስ ነቢይነት እንደሌሎች ቀዳሚ÷ ታላላቅና ደቂቅ ነብያት ያለ ነውን? የሚልን ጥያቄ ይቀሰቅስብናል::

#### 2.2.1.2. የክርስቶስ ነብይነት ልዩነቱ ምንድር ነው?

ክርስቶስ በማንነቱ ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ሳለ ሰው የሆነ አንድ ባሕርይ አንድ አካል እንደሆነ ኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ መምህራን አጽንተው ይናገራሉ::: ለቀደሙት አባቶች እግዚአብሔር በብዙ አይነትና በብዙ ጎዳና በነቢያት ሲናገር እነዚህ ነብያት ሰዎች ብቻ የነበሩና ከእግዚአብሔር የገለጾላቸውን በድንግዝግዝ የተመለከቷቸውን እነዚያኑ ለሕዝቡ በማስተላለፋቸወ የነብይነት አገልግሎት ውስጥ ነበሩ:: ክርስቶስ በማንነቱ አምላክ-ሰው በተዋሕዶ ሲሆን መልእክቶቹ እንደ ቀደሙት ነቢያት ምሉዕነት የሚጎድለው አልነበረም:: በእርሱ በኩል የመጣውን መልዕክት አለመቀበል ፍጻሜው ጥፋት እንደሆነም እንመለከታለን (ዘዳ 18:15፤18፤19 ከሐዋ 3:22-23):: ከዚህም

አገልግሎት ያለው የትርጉም አጠቃቀም ስለ ሌላ ሰው መለመን (መጸለይ) ሲሆን አማላጅ ማለት ደግሞ "በራሱ ማድረግ የማይችል ለምኖ የሚያስደረግ ማለት ነው::" ማማለድ በመሠረተ ሃሳቡ መስዋዕትን ማቅረብ÷ ሥርየትን ማስጠት÷ የምስራች ማወጅና ከእግዚአብሔር ግንኙነትን ማስፈጠር ነበር:: እንግዲህ ኢትዮጵያውያን መምሬዎች ክርስቶስ ከመስቀል ሞቱ በፊት በግብረ ትሥብእት ማልዷል ማለትም በአሁኑ ወቅት ባለው የማማለድ ትርጉም ጸልዮአል (ስለ ሰዎች ለምኗል)፤ ነገር ግን ከትንሣኤው በኋላ አይለምንም ምክንያቱም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ለተፈጠረው ጥል የማስታረቅን ሥራ በግብረ ትስብእት በማጠናቃቁ ነው:: እንደ መላከ ገነት አፈወርቅ አገላለጽ:- «የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ በሥጋ በምድር ሲመላለስ አማልዷል:: ይህን የማማለድ (የመለመን) አገልግሎቱን በምድር በሥጋ ሳለ አጠናቋል:: ከአብ ቀኝ ከተቀመጠበት ተነስቶ እንደገና እንዴት ይጸልያል? ያኔም እንኳን መለኮት በሥጋ አማልዷል:: ሥጋ በመለኮት ለጸሎት መልስ ሰጥቷል::» (ቃለ መጠይቅ:- መላከ ገነት አፈወርቅ÷ ህዳር 12 1993)

በሌላ በኩል ደግሞ የጥንቱ ተዋሕዶ እንደሆነ የይገባኛል ጥያቄ ያለውና የሦስት ልደት በመባል ከሚታወቀው ቡድን እምነት አቶ ጸጋዬ ደምሴ ሲገልጹ:- ዮሐንስ አፈወርቅ:- "ገንዘቦቹ ሳደረገን ለእኛ ይማልድልናል::" ይላል በማለት የማማለድን ትርጉም «መሃከል መግባት» ወይም «የእርስ በእርስ ግንኙነትን ማስፈጠር» በሚለው አገላለጽ መገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ:: ከዚህ በተጨማሪ:-" በፍጹም ሰውነቱ ስለ እኛ ይማልዳል (ይለምናል)÷ በፍጹም አምላክነቱ ደግሞ መልስ ይሠጣል::"[73] በማለት የሁለት ባሕርያትን በተናጥል በተግባር መገለጽ የሚያስተጋባ አመለካከት የተንጸባረቀበት ምላሽን ይሰነዝራሉ::

በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ መምሬዎች ዘንድ የክርስቶስ የምልጃ አገልግሎት ስለ ማማለድ በአሁኑ ወቅት ካለው የመለመን ትርጉም አንጻር ከትንሣኤው በፊት በግብረ ትስብእት ፍጻሜን ያገኘ በመሆኑ ባጠናቀቀው የማማለድ ግብር አሁን ስለ እኛ በአብ ፊት የሚታይልን መሆኑን ይገልጻሉ:: ይህም ክርስቶስ ከትንሣኤው በፊትና ከትንሣኤው በኋላ ያሉት አገልግሎቶች የተለያዩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህም "ክርስቶስ ከዕርገቱ በኋላ ስለ ሰዎች ይለምናል::" የሚለው አባባል ተቀባይነት የለውም:: ይህ ደግሞ ለአንዳንዶች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ አምላክ ብቻ እንደሆነ እንደምታምን አድርገው በተሳሳተ መንገድ ለመገንዘባቸው በምክንያትነት የሚጠቀስ ነው:: ኢትዮጵያውያን መምሬዎች ክርስቶስ ከትንሣኤው በፊት ባብዛኛው በግብረ ትሥብዕት÷

ከትንሣኤው በኋላ ደግሞ የማዳን ስራውን በማጠቃለሉ በግብረ መለኮት እንዳለ እንጂ የትሥጉት አካል በትንሣኤ ምክንያት ለውጥ እንዳመጣ አታምንም:: ስለዚህም አሁንም ክርስቶስ አምላክ–ሰው በተዋሕዶ ብላ ታምናለች:: ይህንን የክርስቶስን የክህነት አገልግሎት በተመለከተ ክርስቶስ በሥጋ በምድር ሲመላለስ ባብዛኛው በግብረ ትሥብዕት÷ ከትንሣኤውም በኋላ ደግሞ በግብረ መለኮት እንዳለ እንጂ በትንሣኤው ምክንያት በተዋሕዶ አካሉ ላይ ለውጥ እንዳመጣ አይታመንም::

ከክርስቶስ የክህነት አገልግሎት ውስጥ የአስታራቂነት ተግባሩ በእግዚአብሔርና በሰው መሃል በመግባቱ ላይ የሚያተኩር ነው:: በሰዎች መካከል ለሚከሰቱ አለመግባባቶች መፍትሔ የሚያስገኙቱ ሰዎች ማንነት አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተከሰተ ጥልም የአስታራቂው ማንነት ወሳኝ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስረዳን ወልድ ሰው ሆኖ በመምጣት " ... በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ÷ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ..." ተብሏል /1ኛጢሞ 2:5/:: ይህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የመግባት ሚና በክህነት አገልግሎት ውስጥ የተካተተ ነው:: እንግዲህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ማማለድ ስለ ሰው ልጆች መለመን ይኸውም ማድረግ የማይችል ለምኖ የሚያስደርግ ከሚለው ትርጉሙ በተቃራኒ በተከናወነው የክርስቶስ የአድኅኖት ሥራ አማካኝነት ስለ ሰው ልጆች በአብ ፊት መታየትን በሚያካትት መልኩ ይታምንበታል:: ስለዚህም ከትንሣኤ በኋላ የክርስቶስ ክህነት በግብረ ትስብእት በተፈጸመ ሥራ ላይ እንጂ ገና ለአምላክ ሰው መሆን ባስፈለገበት ተልዕኮ በአሁኑም ወቅት ባልተጠናቀቀ የማስታረቅ ሥራ ላይ እንዳለ መቁጠር የተሳሳተ አመለካከት ነው የሚል ሃሳብን የሚያንጸባርቅ ነው::

### 2.2.2.2. የክርስቶስ ክህነት ያስገኘው ልዩነት ምንድር ነው?

የክርስቶስ ክህነት ከሌዊ የክህነት አገልግሎት በአይነቱ የተለየ የመሆኑን ያህል በውጤቱም እንዲሁ ልዩ ነው:: ለዚህ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ በሰፊው የክርስቶስን ክህነት ከሌዊ ክህነት በማነጻጸር የሚያትተውን መመልከት አስፈላጊ ነው:: የክርስቶስ ክህነት በራሱ (አምላክ–ሰው) በሆነው በእርሱ ደም የተፈጸመ የማማለድ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው:: በየጊዜው የመስዋዕት ደም ማቅረብ የሚያስፈልገው ሳይሆን አንድ ጊዜ ራሱን መስዋዕት አድርጎ በማቅረቡ ለዘላለም የሚሆን የማስታረቅ አገልግሎት መፈጸም ያስቻለው ነው:: ለዚህ ሁሉ ደግሞ የክርስቶስ ማንነት መሠረት ነው:: መስዋዕቱ የበግ ወይም የፍየል ደም መስዋዕት ወይም የሰውም የደም መስዋዕት (እንደ የአህዛብ አማልክት ለሆነው ለሞሌክ አምልኮ የሚደረገው አይነት)

ሳይሆን የአምላክ–ሰው ደም በመሆኑ በአብና በሰው መካከል ለመግባትና የእግዚአብሔርን ቁጣን ማብረድ የተቻለው ነው።

እንደ ሌዊ ነገድ የክህነት አገልግሎት የመስዋዕት ደም ፍጹም ሥርየትን ማምጣት የማይቻለው ነበር። እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ያለው የሊቀ ካህኑ የክርስቶስ ደም ግን የአምላክ–ሰው ደም በመሆኑ በላቀ መንገድ «በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አለ!» ያሰኘው የክርስትና ታላቅ ምሥጢር መሆኑን መረዳት ከሁሉ የሚበልጥ ነው (ዕብ 9:11-14)።

## 2.2.3. ንጉሥነት

### 2.2.3.1· ክርስቶስ በግጻዌ መለኮት አቻ ንጉሥ ነውን?

ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በግዳዌ መለኮት እኩል ንጉሥ ነው። ይህንን የክርስቶስ አቻ ንግሥና ኢትዮጵያውያን የሥነ መለኮት መምሬዎች የሚገልጹት በቅድመ ትሥጉት የአካላዊ ቃል ማንነት ላይ ብቻ ሳይሆን በድኅረ ትሥጉት አካል በሆነው በክርስቶስ ረገድም ነው። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚሉት ከሆነ ክርስቶስ በሥጋ በምድር ሲመላለስ ይቅርና በሞቱ እንኳን አቻ ንግሥናው የተገሠሠ አይደለም:- «ምንም እንኳን የክርስቶስ ነፍሱ ሲዖል ብትወርድ ሥጋው በመቃብር ቢያድር መለኮቱ ከሥጋ ጋር በመቃብር፥ ከነፍሱ ጋርም በሲዖል አድሯል እንዲሁም በዘባነ ኪሩብ በየማነ አብ ተቀምጦ ዓለምን ያስተዳድራል እንጂ ለቅጽበት ከነፍስም ከሥጋም አልተለየም።»[74]

እንደ መላከ ገነት አፍወርቅ አባባል:- «ክርስቶስ በዓለም ላይ ንጉሥ ነው። እርሱ ከእርገት በፊት ንጉሥ ነው፥ ከእርገት በኋላም ንጉሥ ነው። ሠይጣን የዚህ ዓለም ገዢ ነው ማለት በክርስቲያኖች ላይ ገዢ ነው ማለት አይደለም። ክርስቲያኖችን ድል ማድረግ አይችልም፤ ነገር ግን ይፈትናል። ስለዚህ የክርስቶስ ንግሥና በዓለም ላይ ቅድመና ድኅረ ትሥጉት ነው፡ ሆኖም ግን በቅድመ ትሥጉት ቃል፥ በድኅረ ትሥጉት ክርስቶስ እንደተባለና አቻ ንጉሥ እንደሆነ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታስተምራለች፡[75]፡

እንግዲህ የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን የክርስቶስን አቻ ንግሥና ስትገልጽ በዓለም ላይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን እኩል የሆነ ንጉሥነቱን በመለኮት ብቻ ሳይሆን በሥልጣንም፥ በኃይል፥ በአገዛዝ እኩል መሆኑን የሚያመላክት ነው። ከዚህ በዓለም ላይ ካለው የክርስቶስ ንግሥና በተጨማሪ በአማኞች ላይ ያለውን ንግሥናም

የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ታምናለች። እንደ መላከ ገነት አፍወርቅ አባባል፡- «ክርስቶስ የማይሞት ንጉሥ ነው። ይህም ማለት ሞቷል ደግሞም ከሞት ተነስቷል። ስለዚህም ለዘለዓለም ህያው ንጉሥ ነው። እርሱ በቅዱሳንና በመላዕክት ላይ ንጉሥ ነው። እኛ አመንንም አላመንንም እርሱ ከእርገቱ በፊትም ሆነ በኋላም ንጉሥ ነው።»[76]

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በሁለት አይነት የክርስቶስ ንግሥና ይኸውም በዓለም ላይ ባለው አቻ ንግሥናና በአማኞች ላይ ባለው ልዩ ንግሥና ታምናለች። በዚህም የክርስቶስ ንግሥና ዘላለማዊና የማይለወጥ መሆኑን አበክራ ትናገራለች። የክርስቶስ ልዩ ንግሥና ምንነት በብዙዎች ዘንድ ጥያቄ የሚቀሰቅስ ነው። ለመሆኑ ክርስቶስ ልዩ ንግሥና አለውን? መልሱ አዎን ከሆነ ስለዚህ ልዩ ንግሥና መረዳት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

### 2.2.3.2. ክርስቶስ ልዩ ንጉሥነትን ተቀብሏልን?

በኢትዮጵያውያን መምሬዎች ዘንድ የክርስቶስ ንግሥናን ልዩ የሚያሰኘው በአማኞች ላይ ያለውን ንግሥና በተመለከተ በሚሰነዘሩ ሃሳቦች ዙሪያ ነው። ይህ ንግሥናው በአማኞች (በኪዳን ህዝቡ) ላይ ያለው ንግሥና ነው። ክርስቶስ በግጻዌ መለኮት ካለው አቻ ንግሥና በተጨማሪ ያለውን ንግሥና ልዩነት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በኪዳን ህዝቡ ላይ ያለው ንግሥና ትንቢት የተነገረለት ከመሆኑም በላይ በፍጻሜውም ማመላከቻ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከመሲህነት ተልዕኮው የተነሳ ከፍ እንዳደረገው መመልከት ይቻላል (መዝ 2:6፤(45):6-7፤ ዕብ 1:8-9፤ ሚክ 5:2፤ ዘካ 6:13፤ ሉቃ 1:33፤ 19:27፤ ዮሐ 18:36-37፤ ሐዋ 2:30፤36)። እንደ አባ መልከ ጼዴቅ አገላለጽ ደግሞ የክርስቶስ ንግሥና በሞቱና ሲዖል በመውረዱም ተንጸባርቋል፡- «ክርስቶስ ሲዖል ሲወርድ ጨለማው በራ፤ እንደ ነቢይነቱና እንደ ሊቀ ካህንነቱ ሰበከላቸው፤ እንደ ንጉሥነቱ ደግሞ ምርኮን ማረከ ነፍሳትንም ከሲዖል ወደ ገነት አወጣ አሸጋገረ።»[77]

እንግዲህ ይህ የክርስቶስ ንግሥና በግጻዌ መለኮት ካለውና በዓለም ላይ እቅዱን ለማስፈጸም ከሚያስችለው ንግሥና ባሻገር በማዳን ስራው ረገድ ንጉሥ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህን ከክርስቶስ ግብር ጋር የተያያዘ ንግሥናውን በተመለከተ፡- «ንጉሥ የቃል ኪዳን ሕዝቡን ይጠብቃል፤ ይመግባል፤ ይገዛል፤ ያስተዳድራል። ይህም ሥራ ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጥቷል (ኢሳ 9:6-7፤ ኤር 25:5-6፤ ዮሐ 10:11-15፤27-30)።[78] በአጠቃላይ በአማኞች ላይ ያለው ንግሥና በግዳዌ መለኮት ከትሥጉት አካል የማዳን ተልዕኮን መወጣት አንጻር የተሰጠና ከግብሩ ጋርም የተያያዘ ነው።

## 2·3 የክርስቶስ ግብራት ደረጃዎች
(The stages of Christ's Functions)

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በአካላዊ ቃል ሰው ሆኖ ሰውን የማዳን ተልዕኮ ላይ የህማማቱንና ያለ ልክ ከፍ ከፍ የማለቱን ሂደት በተለያዩ እርከኖች (steps) ላይ በመመሥረት ታስረዳለች:: የሥነ መለኮት መምሬዎቿ በክርስቶስ ህማማት እርከኖች አፈጻጸም ወቅት መለኮት በሥጋ ማለትም ኢየሱስ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በግብረ ትስብእት መከራን እንደተቀበለ ሁሉ÷ ሥጋም በመለኮት ማለትም ሰው ሆኖ ሳለ በግብረ መለኮት የሚመለክ አምላክ እንደሆነ ይገልጻሉ:: ይህ ደግሞ የትሥጉት አካል ከትንሣኤው በፊትና ከትንሣኤው በኋላ ያለፈባቸውን እርከኖች (steps) እንዴትና ካሉት ከሁለቱ ግብራት በየትኛው ጸባይ (የባሕርይ ግብር) እንደነበረ በሚደረግ ገለጻ ላይ የሚካተት ነው:: ባብዛኛው በሌሎች ዘንድ ራሱን ዝቅ ማድረጉ (Humilation) በመባል የሚታወቀው ከሰው መሆን እስከ መቃብር የሚያደርሰውን ደረጃ የቃላት አገላለጽ የሚቃወሙ እንደ መላከ ገነት አፈወርቅ ያሉ ሊቃውንት "ወደ ቀደመው ክብሩ መመለሱ" የሚለውንም አጠቃቀም ይቃወማሉ:: ለዚህ አመለካከት መንጸባረቅ መንስዔው ደግሞ አካላዊ ቃል ሰው ሲሆን አምላክነቱን እርግፍ አድርጎ ትቷል የሚልን ኑፋቄ ከመስጋት ያለፈ ነው:: ስለዚህ ራሱን ዝቅ አደረገ ማለት አምላክነቱን ቀንሶ መጣ ከማለት ጋር እንዳያደናግር "ግብረት ትሥብዕት" ቢባል ወደ ቀድሞ ክብሩ መመለሱ የሚለውም አባባል "ግብረ መለኮት" ቢባል የሚል አቀራረብን ማስተዋል ችይለሁ::

### 2.3.1. ግብረ ትስብእት (Human Functions)

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሬዎች አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ ሰዎችን ለማዳን በግብረ ትስብእት ያደረጋቸው ነገሮች:- ትሥጉት÷ የመስቀል ሞቱ÷ መቀበሩና ወደ ሲዖል መውረዱ በተናጥል ለእነዚህ ምግባራት የሚገባ ባሕርዩ (ሰባዊ ባሕርዩ) የፈጸመው ሳይሆን በተዋሕዶ አካል ላይ የተፈጸመ ሆኖ ወደ አፈጻጸም የመጣው ግን በግብረ ትስብእት ነው ይላሉ:: ትሥጉት በሰፊው ለመግለጽ እንደተሞከረው የመለኮትና ሥጋ ተዋሕዶ (ጥምረት) እንጂ እንደ መልካም ጉርብትና ያለ ሽርክና አይደለም:: አባ መልከ ጼዴቅ እንዳስፈሩት:- «ወልድ ሰው ሆነ ስንል ህልውና ያለው የአብ ቃል ነው፤ ስለዚህ መለኮቱ ወይም አምላክነቱ ምንም ሕጸጽ ወይም ጉድለት የሌለበት ነው::»[79] ስለዚህ የትሥጉት አካል የፍጹም መለኮት ከሥጋ ጋር መዋሐድ (ላይነጠል መጣመር) ማለት ነው:: ይህ ደግሞ:- «በጸነሰች ጊዜ የአብ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ ነፍስንም ሥጋንም

ተዋሕዷል÷ ሥጋ በተዋሕዶተ መለኮት የጸና በመሆኑ አንዱ ከሌላው አልተለያዩም::[80]

ከግብር አንጻር፦ በአብ መላኩን÷ መከራን መቀበሉንና ከትንሣኤው በፊት የተናገራቸውን እንደ የምጽዓትን ቀንም አላውቅም ያለባቸውን ክፍሎች በመንተራስ «በማንነቱ ከአብ ያነሰ መለኮት ነበር!» የሚሉትን የአርዮሳውያንንም ትምህርት ከግጻዌ መለከከጽ የግብር ሦስትነትና የማዳን ተልእኮ አንጻር መመልከቱ አስፈላጊ ነው:: ስለዚህም የመለኮት መበላለጥን ሳይሆን ከትንሣኤው በፊት መለኮትነቱን ሳይለቅ ሰዎችን ለማዳን ከነበረው ተልእኮው አንጻር በተለይ በግብረ ትሥብእት መስዋዕት የመሆንንና የማስታረቅን ስራ እንደሰራልን የሚያስረዳ ነው:: ከዚህም የተነሳ ከግብር አንጻር የተነገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ማስተዋልና በጥንቃቄ መፍታት ያስፈልጋል:: እንደ በአብ መላኩ÷ መከራን መቀበሉ÷ በመስቀል መሞቱና የምጽዓትን ቀን አላውቅም ማለቱ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን እንደ መቀማት ካልቆጠረባቸው እንዲሁም በፈቃዱ በአብ የተላከበትን በማድረግና የአብን ፈቃድ በመፈጸም ያስከበረው መሆኑን ከማመልከት አንጻር እንጂ ከአብ ያነሰ መለኮት መሆኑን ከማመልከት አንጻር የተነገሩ እንዳይደሉ መረዳት ያሻል::

የክርስቶስን የመስቀል ሞት በተመለከተ:– «ክርስቶስ በሰው እግር ገብቶ መከራ መስቀልን በተቀበለ ግዜ÷ በኋላም ሙቶ በተቀበረ ግዜ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ መለኮት ከሥጋም ከነፍስም ከቶ አልተለየም::»[81] ይህ ደግም «.... የክርስቶስ ሥጋ ለሦስት ቀናት ያህል ለቅጽበትም እንኳን አልተለየውምና:: ነፍስ ተለየች ይባላል እንጂ በምንም መልክ መለኮት ከሥጋም ከነፍስም ተለየ አይባልም::...» የሚለውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው:: በክርስቶስ መቀበር ወቅትም መለኮት የተዋሐደው የክርስቶስ ሥጋ በመቃብር÷ መለኮት የተዋሐዳት የክርስቶስ ነፍስም ሲዖል ወርዶ እንደነበረ ያመላክታል:: በመቀጠልም «ሲዖልም የምንላት ነፍሳት ተግዘው የነበሩባት የመሬት ጥልቀት ናት:: .... ወደዚያም የግዞት ስፍራ የማንኛውም ሰው ነፍስ በአዳም በደል ምክንያት ለፍርድ ትወርድ ነበር ....» ይላሉ::[82]

ከላይ ከተገለጸው ሃሳብ በመነሳት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ በሞተበት ወቅት ሥጋው በመቃብር ሲያድር በአካለ ነፍስ ደግሞ ወደ ሲዖል እንደወረደ ለሚነገርለት ለክርስቶስ የተዋሕዶ ምስጢር ጠቀሜታን ሲያብራሩ:- «ወደ ሲዖል የወረደችው የክርስቶስ ነፍስ መለኮት ባይዋሃዳት ኑሮ ፩ኛ. በሲዖል ያሉትን ነፍሳት የማዳን ነፃም የማውጣት ኃይል አልነበራትም ነበር:: ፪ኛ እንደ ሌሎች የሩቅ ብእሲ

ነፍስ ከሆነች በዲያብሎስ ቁራኝነት ትያዝ ነበረች:: መለኮትን የተዋሐደችው ነፍስ ሲዖል በመውረዷ ግን ለነፍሳት ሁሉ መድኃኒት ሆነች::.... እንዲሁ የክርስቶስ ሥጋ መለኮት ያልተዋሃደው ቢሆን ኑሮ ሦስት ቀን በመቃብር ሲቆይ ይበሰብስ፤ይለወጥ ነበር:: የክርስቶስ አካል ግን መለኮት ያልተለየው በመሆኑ ሳይፈርስ ሳይበሰብስ ሳይለወጥም ቆይቶ በሃይል ለመነሳት ቻለ::[83]

እንግዲህ በእነዚህ በእርከን የተዋቀሩ የህማማት ነጥቦች ከትሥጉት እስከ የተዋሕዶተ ሥጋ በመቃብር÷ የተዋሕዶተ ነፍስ በሲዖል በማደር ሰውን በማዳን ሂደት በግብረ ትስብእት የተፈጸሙ ግብራትን እንመለከታለን:: አባ መልከ ጼዴቅ ተዋሕዶ የክርስቶስን ሥጋ በመቃብር እንዳይበሰብስ÷ የክርስቶስን ነፍስ በሲዖል በዲያብሎስ ቁራኛ ነት ስር እንዳይወድቅ የማድረግ ጠቀሜታ እንደነበረው ሲገልጹ መላከ ገነት አፈወርቅ ደግሞ:- «የተገረፈው ሥጋ ብቻ ቢሆን አያድነንም መለኮት በሥጋ በመገረፉ ያድናል:: ሥጋ በሥጋነቱ ቢሞት መዳን ባልቻልን÷ መነሳትም ባልቻልን! የሥጋ ባሕርይ በሥጋነቱ ቢሞት መዳን ባልቻልን ትንሣኤም እውን ባልሆነ:: አካላዊ ቃል ሥጋን ተዋሕዶ በሥጋ ባሕርይ /ከእኛ በነሳው ባሕርይ/ ግብር ሞተ:: መለኮት በሥጋ ሞተ÷ በራሱ ባሕርይ ግብር አልሞተም! ሥጋማ በራሱ ባሕርይ የታወቀለት ሟች ነው:: ለዚህም ከክርስቶስ ሞት በፊት በእነ ሙሴም ሞቷል::"[84]

ከላይ ከተገለጸው የመላከ ገነት አፍወርቅ አባባል እንደምንረዳው የክርስቶስ ሞት ሥርየትን ማስገኘት የቻለው የአምላክ በሥጋ ሞት በመሆኑ እንዲሁም ከሌሎች ሰው ብቻ ከሆኑ ቅዱሳንም ሞት ልዩ ስለሆነ ነው:: መላከ ገነት አፍወርቅም የክርስቶስን በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል መውረድ ከአዳም ጀምሮ እስከ እለተ አርብ ድረስ የሞቱትን ነፍሳት በሙሉ ከሲዖል ለማውጣት (ከጣዖት አምላኪዎች በስተቀር እንዲሁም ይሁዳን ምክንያቱም ከክርስቶስ መስቀልን በፊት ነፍሱ ያልወጣች በጻሕር የቆየ በመሆኑ) እንደሆነ ይናገራሉ::[85] ሆኖም ግን መለኮትነቱ በሥጋውም ሆነ በነፍሱ ላይ ካስገኘው ጥበቃ አኳያ የሚሉት አልነበረም::

እንግዲህ ከሥርየት አኳያ በመላከ ገነት አፍወርቅ በኩል የተሰነዘረው ነጥብ የክርስቶስን መስዋዕት መሆን ልዩና ተቀባይነት የሞላው የሚያሰኘው ከመሆኑም በላይ የክርስቶስን ማንነት ከግብራቱ ጋር የሚያስተሳስር ነው:: በሐዋ 20:28 መሠረትም የክርስቶስ ደም የእግዚአብሔር ደም መሆኑን ከሚያመለክተው ሃሳብ እንጻር ተክለ ሰውነታዊ የሆነውን ክፍሉ እንኳ መነጠል እስከማይቻል ድረስ የመለኮት በሥጋ (የአምላክ–ሰው) ተዋሕዶ አካል መሆኑን ያመለክተናል::

### 2.3.2. ግብረ መለኮት (Divine Functions)

በአንዳንዶች አመለካከት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መምሬዎች "ክርስቶስ እስከ መስቀል ሞቱ ድረስ ሰው መሆኑ እንደተንጸባረቀበት÷ ከትንሣኤው በኋላ ደግሞ አምላክ ብቻ እንደሆነ ያስተምራሉ!" የሚል አሳቤ እንዳለ ለመጥቀስ ሞክሬአለሁ፡፡ ሆኖም ግን የትሥጉት አካል ተዋሕዶ ዘላለማዊና ለለውጥም ያልተጋለጠ እንደሆነ ከሊቃውንት አንደበት እንዲሁም ጽሑፎች መረዳት እንችላለን፡፡

እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- "ትንሣኤው የነፍስና የሥጋ መዋሐድና በሕይወት ቆሞ መታየት ብቻ አልነበረም፤ የተነሣው አካል በመስቀል የተሰቀለውና የተቸነከረው ቢሆንም ያው አካል በተሐድሶ ተነሥቶአል፤ ...የክርስቶስ ትንሳኤ ከአልአዛርና ከሌሎችም ሰዎች ትንሣኤ የተለየ ነው፤ የእነዚያ ትንሣኤ በብሉይ ሥጋ ነው፤ ቆይተውም ሞተዋል፤ እርሱ ግን ዳግም ሞት የለበትም፤ (ራእ 1:18) ስለዚህም በኩረ ሙታን ይባላል ፤ (1ኛ ቆሮ 15:20፤ ቆላ 1:18)"[86]

መላከ ገነት አፈወርቅም:- " '... ያለ ልክ ከፍ አደረገው::' (ፊል 2:9) ማለቱ ትንሣኤው ተዋሕዶን እንዳላፋለሰና ሥጋ በመለኮት አምልኮ የተገባው እንደሆነ የሚገልጽ ነው::"[87] በማለት ትንሣኤው በትሥጉት አካል ላይ ለውጥ እንዳላመጣበት ያመላክታሉ:: ሆኖም ግን የትንሣኤውን አካል በተመለከተ ለአገላለጽ አስቸጋሪ የሆነውን ሃሳብ በክርስቶስ ማንነት ላይ ከተከናወነ ለውጥ አንጻር ሳይሆን ከግብር አንጻር ማስረዳት መቻል በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ የተለመደ ነው:: ከዚህም በመነሳት የትሥጉት አካል ከትንሣኤ በፊትና ከትንሣኤ በኋላ ለውጥ እንዳመጣ ሳይሆን ከትንሣኤ በፊት ባብዛኛው በግብረ ትስብእት፣ ከትንሣኤ በኋላ በግብረ መለኮት መገኘቱ ደግሞ ሰውን የማዳን ተልዕኮውን በማጠቃለሉ ምክንያት እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

ስለ ግብረ መለኮት ስናነሳ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ካደረጋቸው ነገሮች ሌላው ዕርገቱ ነው:: ካረገም በኋላ በአብ ቀኝ እንደተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል:: እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- ከዐረገም በኋላ «በአብ ቀኝ ተቀመጠ» (ኤፌ 1:20፤ዕብ 10:12) የሚለው አነጋገር ፊደል በፊደል የሚተረጎም ብቻ ሳይሆን ኃይልንና ሥልጣንን ክብርንም የሚያመለክት ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀኝና ግራ÷ ፊትና ኋላ የለምና፤ ስለዚህ ነቢረ የማን ክርስቶሳ ግብረ ትስብእትን ከፈጸመ በኋላ እንደገና የሰውነትን ሥራ የማይሠራ ነገር ግን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በክብር መለኮታዊ ሥራውን እየሠራ የሚኖር መሆኑን የሚያስረዳ ቃል ነው::"[88]

ከላይ ከተጠቀሰው የሠይፈ ሥላሴ አባባል የክርስቶስ ግብረ ትስብእት መለኮት በሥጋ ለሰዎች ድኅነት ሊፈጽም ያስቻለውን ነገሮች ሲያስረዳን ከትንሣኤውና ከእርገቱ በኋላ በአብ ቀኝ አንደ ተቀመጠ የሚያመለክተን ሃሳብ ደግሞ የማዳን ሥራውን በመፈጸሙ ምክንያት በግብረ መለኮት እንዳለ ነው:: ይህ ደግሞ ከትንሣኤው በፊትና በኋላ የትሥጉት አካል በግብረ ትስብእትና በግብረ መለኮት በየጊዜያቱ ቅደም ተከተል መገለጡን እንጂ በአካሉ ለውጥ እንዳመጣ አመላካች አይደለም:: ሌላ መነሳት ያለበት ነጥብ በአንዳንድ የሥነ መለኮት ሰዎች ዘንድ የሰው ልጆችን የማዳን ተልዕኮው ማጠቃለያ እንደሆነ የሚታመንበትና የመጨረሻ እርከን ተደርጎ የሚቆጠረው የዳግም ምፅዓቱ ጉዳይ ነው:: ለመሆኑ ዳግም ምፅዓቱ የማዳን ተልዕኮው የመጨረሻ እርከን ነውን?

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥነ መለኮት መምሬዎች ዘንድ የማዳን ሥራው የተጠናቀቀው በመስቀል ሞቶ በመቀበሩና በሲዖልም የተጋዙትን ነፃ በማውጣቱ ነው:: ከትንሣኤው በኋላ የቆየ ያልተጠናቀቀ የማዳን ሥራ እዳለው አይታመንም:: በዚህም ምክንያት ዳግም ምጽዓቱ ከማዳን ዐላማው ጋር ሳይሆን በክብር ተመልሶ ከመምጣት ጽንሰ ሃሳብ ጋር የተያያዘ ነው:: እንደ መልአከ ገነት አፈወርቅ አገላለጽ:- «ዳግም ምጽዓት ሰዎችን ከማዳን የእግዚአብሔር እቅድ ጋር የተያያዘ አይደለም:: ሰውን ለማዳንማ በግብረ ትስብእት የማይሞተው ሞቷል፤ በዚህም ከአብ ጋር አስታርቆናል:: ስራውን ካጠናቀቀም በኋላ የተረሳና የቀረ ሥራ እንዳለው ከአብ ቀኝ አይነሳም፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ሥራውን ጨርሷል ማለት ባንችልም ዳግም ሲመጣ የሚሰራው ሥራ እንዳለፈው አይደለም:- ጻድቃንንና ሃጢአንን ለመለየት ስለሚመጣ ዳግም ሥራው በግብረ ትስብእት አይደለም::[89]

እንግዲህ የትሥጉት አካል በሁለቱ ግብራት መገለጥ በተለያየ ጊዜ ማለትም ከትንሣኤ በፊትና በኋላ ክብሩን ከማጣትና መልሶ ከማግኘት አንጻር ሳይሆን ቃል ከሥጋ ጋር ስለተዋሐደ በሥጋው መከራና ሞት እንዳለበት፤ ከትንሣኤው በኋላ ግን ዳግም እንደማይሞት ለማንጸባረቅ ነው:: ስለዚህም «ራሱን ዝቅ ማድረግ» (Humiliation) የተሰኘው ደረጃ ስያሜም የማንነቱን መቀነስ አመላካች ስለሚመስል በግብረ ትስብእት መገለጹ ቢባል፥ «ወደ ቀደመው ክብሩ መመለሱ» የሚለውን በግብረ መለኮት መገለጹ ቢባል ተገቢ ትርጉሙን ያገኛል:: ይኸውም የትሥጉት አካል ክርስቶስ አምላክ ሲሆን ሳለ ሰው ሆኖ እንደመጣ እንጂ አምላክነቱን በሠማይ ትቶ ሰው ብቻ ሆኖ እንዳልመጣ ወይም ትሥብእት በአምላክነቱ ላይ ለውጥን እንዳላስከተለበት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ፥ በመለኮት፥ በፈቃድ፥ በሥልጣን አንድ እንደሆነ ለመግለጽ ነው::

## ማጠቃለያ

ነገረ-ክርስቶስ የክርስትና መሠረት በመሆኑ ክርስትናን ከሌሎች ኃይማኖቶች ልዩ የሚያደርገው አንኳር ትምህርት ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያቱ ጋር በምድር በተመላለሰበት ወቅት የማያምኑቱ ስለ እርሱ የነበራቸውን መረዳት ብቻ ሳይሆን ይከተሉት የነበሩት ራሳቸው ሐዋርያቱ ማን እንደሚሉት ሲጠይቅ ከጴጥሮስ የተሰነዘረው ምላሽ የእርሱን መሲህነትና የአብ የባሕርይ ልጅነቱን አመላካች መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን የአምላክ ሰው መሆን ምስጢር 'ሾላ በድፍን!' ተብሎ ያለ ምንም ጥያቄ የሚታለፍ አልነበረም። የክርስትና ተቃዋሚ ከሆኑት ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ዘንድ ጎልቶ የታየ የክርስቶስ ማንነት ጥያቄ ተስተውሏል። የክርስቶስ ምሉዕ አምላክነት ብቻ ሳይሆን ምሉዕ ሰው መሆኑም ክርክር ተነስቶበታል። ስለ ፍጹም አምላክነቱ ከቅድመ ትሥጉት ማንነቱ በመነሳት ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሲመሰክሩ (የባሕርይ ልጅነቱን) ለማስረዳታቸው አጠያያቂነት ባይኖረውም ስለ 'ጊዜ' ያለው ግንዛቤ በራሱ እንደ አርዮስ ላሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ውድቀት መንስዔ ሆኗል። እንግዲህ አርዮስ በዘላለም ውስጥ የጊዜ ጽንሰ ሃሳብ እንዳለና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ጊዜ መቆጠር እንደተጀመረ የነበረው እሳቤ ወልድ ቅድመ ዓለም በአብ እንደፈጠረ ማመኑ 'በመለኮትነቱ ፍጡር!' የሚል ድምዳሜ ላይ የመድረሱ መንስዔ ነው። ከዚህም ባሻገር አርዮስ ባብዛኛው ኢትዮጵያውያን መምሬዎች የማይስማሙበት የወልድ በአርአያ መልአክ መገለጥ የግጸዌ መለኮት የግብር ቅደም ተከተል (Functional Subordination) ዘላለማዊነትን እንጂ የማንነት (Ontology) መበላለጥን በፍጹም አመላካች እንዳይደለ ያለማስተዋል ይታይበታል።

በድኅረ ትሥጉት አካል ማንነት ዙሪያ የተነሱ ጥያቄዎች ለመግለጽ እንደሞከርኩት ከአካሉና ከግብሩ አንጻር የተነገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለይቶ ካለማተዋል የመነጩ ናቸው። በግብር ቅደም ተከተል ወልድ በአብ መላኩም ሆነ የአብ ግብር የሆነውን የምጽዓትን ቀን አለማወቁ የመለኮት መበላለጥን እንዳስከተለ መቁጠር አሁንም የክርስቶስን ማንነት በተገቢው መንገድ ካለማስተዋል የተከሰተ ነው። እንዲያውም የኤፌሶኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባዔ፦ 'ማርያም የእግዚአብሔር እናት!' ብሎ የእምነት አንቀጽን ያወጣበት ምክንያትም ከእርሷ የተወለደው የክርስቶስን ምሉዕ አምላክ (እግዚአብሔር) መሆን ለማስረዳት ታቅዶ እንደነበር ግልጽ ነው። ይህም ደግሞ በአብና በወልድ መካከል የመለኮት መበላለጥ እንደሌለ ከማሳየቱም በላይ

ምሉዕ አምላክ የሆነው አካላዊ ቃል ራሱ ከማሪያም እንደተወለደ የሚገልጽ ነው።

ከታሪካዊ ነገረ-ክርስቶስ በመነሳት ለማስረዳት እንደሞከርኩት ቤተ ክርስቲያን ገና ከምሥረታዋ ጀምሮ የነቢያትንና የሐዋርያትን ምስክርነት ከቅዱሳት መጻሕፍት በማጣቀስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ በጥልቀት ለመረዳት የሚያስችሉ ጉባዔዎችን አካሂዳለች። በድኅረ ትሥጉት ስለ ሰው መሆን ያለው አሳቤ በክርስቶስ ማንነት ላይ ተጽዕኖ እንዳመጣበት የመቁጠር ሁኔታም ተከስቷል። አንዳንዶች ሰው ብቻ ነበር ሲሉ ሌሎች ደግሞ በቁሳዊና ቁሳዊ ባልሆነው አካሉ መካከል በመለያየት ግማሽ እግዚአብሔር÷ ግማሽ ሰው ለማለት የመነሳታቸውም መንስዔ የአምላክ ሰው አኳኋንን ካለመረዳት የመነጨ ነው። ለዚህ ደግሞ የክርስቶስን ምሉዕ አምላክነት ብቻ ሳይሆን ምሉዕ ሰው መሆኑንም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ማስረዳቱ ስለ እርሱ አንድነት ሊኖር የሚችለውን ግንዛቤ በግራ መጋባት ውስጥ ይከተዋል። ከዚህም የተነሳ ስለ ክርስቶስ ማንነት ለሚነሱ የአመክንዮት ጥያቄዎች ከሐዋርያው ጴጥሮስ ምላሽ በጠለቀ መንገድ ወጥነት ያለው መረዳትን ይጠይቃል። ጴጥሮስ «ክርስቶስ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ» ያለው የትሥጉት አካል ራሱን «የሰው ልጅ» በማለት በስፋት ይናገር ነበር። እንግዲያው እርሱ፡- አምለክ? ሰው? አምላክ–ሰው? አምላክናሰው? የአምላክና ሰው ድብልቅ? ወይስ አምላክም ሰውም? ነው።

ኢትዮጵያን ከአፍሪካ አገሮች ልዩ የሚያደርጋት ለቅኝ ገዥዎች አለማጎብደዷ ብቻ ሳይሆን በዓለም የመጀመሪያይቱ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አባቶችን አሰር (ፈለግ) ተከትላ የራሷ የሆነ ነገረ-ክርስቶስን የምትረዳበት መንገድ ያላት በመሆኗ ነው። ከእስክንድርያዋ ቤተ ክርስቲያን መንበሯን ሮም ያደረገችውና የኬልቄዶንን አሰር የተከተለችው የምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ስትለይ÷ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን በመባል የምትታወቀውም (የግሪክ÷ የራሽያ ወ.ዘ.ተ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት) ከኬልቄዶን ጉባዔ ውሳኔ ጋር ሲስማሙ÷ ከጊዜ በኋላ የግብጽ ቤተ ክርስቲያንም የቄርሎስን ትምህርት ከመረዳት ተዘናግታ የአውጣኬን አሰር እንደከተለች ሲነገርባት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን የቅዱስ ቄርሎስን አባትነት ተቀብላ ክርስቶስን፡- "ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ÷ ከሁለት አካል አንድ አካል በተዋሕዶ (አምላክ–ሰው)" በማለት የሁለት ባሕርያት መልካም ጉርብትናንም ሆነ በመቀዋጥ ውላጤ (ለውጥ) ማምጣት የሚያስተጋባ ትምህርት አመክንዮታዊነት የሚጎድለው እንደሆነ ከመናገሯም በላይ የኃዋርያትም ሆነ የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያንም ትምህርት እንዳልነበረ ትናገራለች።

ይህ ስለ ክርስቶስ ማንነት ያላት አስተምህሮዋ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ እንደተፈጸመ ከሚገልጽልን የማዳን ግብር ጋር የሚስማማ፥ ስለ ክርስቶስ በየጊዜው ለሚነሱ ጥያቄዎች ማንነቱን ከግብሩ ጋር ያስተሳሰረ ወጥነት ያለውና የተሟላ ምላሽን ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ ነው:: በ5ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ለሁለት መከፈል ለእስልምና ኃይማኖት መስፋፋት በር ከፋች የነበረ ከመሆኑም በላይ እስከ ዛሬም አንድነቷ ባለመመለሱ የሰብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ላይ አሉ የማይባል ተጽዕኖ በማምጣት ላይ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ተሐድሶ ከምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን መነከሳት በመነሳቱና ወደ ኢትዮጵያም የነበረው አመጣጥ እስከ አሁንም ድረስ ተቃውሞ የበዛበት በመሆኑ የምዕራቧን ቤተ ክርስቲያን ነገረ-ክርስቶስ ሙሉ ለሙሉ መከተል በምድረ ኢትዮጵያ ያሉ የተሐድሶ ቤተ ክርስቲያናት ዘንድ ለሚሰነዘረው ተቃውሞ እንደ አጸፌታዊ ምላሽ የተቆጠረ ይመስላል::

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ነገረ-ክርስቶስ አባት እንደሆነ የሚነገርለት ቅዱስ ቄርሎስ በዓለም ደረጃ የሥነ መለኮት ሰዎች ትኩረት እየተቸረው ይገኛል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ቄርሎስን አውዳዊ በሆነ መንገድ ስትገልጸውም ከኢትዮጵያ ፍልስፍና አተዋወን ጋር በተጣጣመ መልኩ ነው:: ከዚህ በመነሳት ለምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ መነከሳቶቿ የመሆናቸውን ያህል ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶም እንደ ፒተር ሃይለንግ ተዋሕዶአዊ የተሐድሶ መሪዎች መሆናቸው አውዱን ያገናዘበና በመናፍቅነት ውግዘትም የማዳኑን ወንጌል ሩጫ የማያቅብ ነው:: በሮም መንበር ስር በፖለቲካዊ የበላይነት ተቀባይነቱን እንዳደራጀ የሚነገርለት አገር በቀል ያይደለና በኢትዮጵያውያን አመክንዮት ለመረዳት አዳጋች የሆነ፥ የእሳቤ ወጥነትም ሲጎድለው በተዓምር ላይ ከሚደገፍ ነው:: ከመሠረታዊ የእግዚአብሔር የአድኅኖት ስራ አንጻር በክርስቶስ ውስጥ የሁለት ባሕርያት የየራሳቸውን ሳይለቁ በተናጥል መገኘት የማዳን ስራንም የሥጋ ባሕርይ በተናጥል የፈጸመው እንደሆነ እንድናስብ ከመገፋፋቱም በላይ የአምላክ ሰው ሆኖ መምጣትን ታላቅ ተልዕኮ በወጥነት ለማስረዳት አዳጋች መሆኑን ማስተዋል ያሻል:: ከዚህም የተነሳ ወደ አገር በቀሉ ነገረ-ክርስቶስ ፊትን ዞር በማድረግ በእምነት የሚገኝ የድነትን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ለምድራችን በአውዳዊ መልኩ ማወጅ የሚመከር ብቻ ሳይሆን በውጤታማነቱም ወደር የሌለው ነው ለማለት እወዳለሁ::

ከዚህም በተጨማሪ ይህን አስደናቂና መሠረታዊ የድነት ትምህርት ለረጅም ዘመናት በምድራችን ይዛ ከሊቃውንት ጉባዔ ያልወጣ መረዳት ሆኖ እንዲቀር ያደረገችን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ማንነት ከግብሩ ጋር ባጣመረ መልኩ ለህዝባችን የማድረስን ታላቅ ተልዕኮ ትወጣ

ዘንድ ለአባቶቼ ለካህናት ለወንድሞቼም ለዲያቆናት እንዲሁም ለህዝበ ክርስቲያኑ በሙሉ ጥሪዬን ሳስተላልፍ በክቡር ልጁ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ህግ ስራ መገለጡን አጽንዖት ሰጥቶበት በስፋት የእግዚአብሔርን የምሥራች የሚያውጅልንን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የጻፈውን መልዕክት በማንበብ «እኔን ማን እንደሆንኩ ትሉኛችሁ?» በማለት ለሚጠይቀን ጌታ መድኃኔዓለም መሆኑን ብለን ስንመልስለት በአንደበት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ከእርሱ ውጪ መዳን እንደሌለ ማመን ያሻል! ታሪክ ተማሪዎች ብቻ ሳንሆን ከታሪክ በመማር በቤተ ክርስቲያን መከፈል ሠይጣን ብቻ እንዳተረፈ ተረድተን በወንጌል ከተሰበከውንና ለዓለምም ሁሉ የአድኅኖት ዜና ከሆነው ከጌታችንንና ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላን ትምክህት ከእኛ እናርቅ!!

## የምንጭ ማጣቀሻ /End Notes/

[1] Dr. Tim Dowley, *The History of Christianity*, Hong Kong, Lion Publishing, 1977, p.164-165).

[2] D. Guthrie & T.A. Motyer (Eds), *New Bible Commentary*, Grand Rapids, Inter-Varsity Press, 1970 p. 558)

[3] Dr. Tim Dowley, *The History of Christianity*, p.165-167.

[4] Dr. Tim Dowley, *The History of Christianity*, p.145.

[5] *ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልእኮ፥* **ገፅ 25**

[6] *መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት ÷* "ክርስትና በኢትዮጵያ" ቁ 12 ገጽ 20

[7] P. H. Lewis, "Theotokos" in S. B. Ferguson, D. F. Wright, J. I. Packer, *New Dictionary of Theology* England, InterVarsity Press, 1988, p. 415

[8] *መክብብ ግርማየሱስ(አራሚ)፥ የአክሲማረስ መጽሐፍ፥* አዲስ አባባ፥ ኢትዮጵያ ብራና መጽሐፍ ማይክሮ ፊልም ድርጅት፥ የካቲት 30 1980፥ ገፅ 152–153

[9] ብሔራዊ በተመዘክር እና ቅርሥ ጥበቃ፥ የመለያ ቁጥር 481፥ ገጽ 115 –121)::

[10] *ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሀዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልእኮ፥* ገጽ 29 እንዲሁም *ከየኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት፥ ...* ገጽ 53 ጋር ይነጻጸር::

[11] *ሠይፈ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልእኮ* አዲስ አበባ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ገጽ ፳፱

[12] Watch Tower Bible & Tract Socity, *በምድርላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፥* U.S.A, 1991, p.63).

[13] ብሔራዊ ቤተመዘክር እና ቅርሥ ጥበቃ፥ የመለያ ቁጥር 481 ÷ ገጽ 115 –121

[14] Milard J. *Erickson, Christian Theology*, Grand Rapids, Michigan, Baker Book House, 1985, p.727)

[15] G. D. Dragas, "Cyril of Alexanderia", in *New Dictionary of Theology*, p.185.)

[16] Tesafazghi Uqbit, *Current Christological Positions of E.O.C. Theologians*, Rome: Pontifica Institutum Studiorum Orientalium, 1973. , p. 153

[17] *መሠረት* ስበሐት ለአብ፥ *ጮራ መጽሔት፥* "ክርስትና በእትዮጵያ"፥ ቁ 4 ገፅ 11

[18] *መሠረት* ስብሐት ለአብ፥ ... ቁ 4 ገፅ 11

[19] *መሠረት* ስበሐት ለአብ፥ *ጮራ መጽሔት...* ቁ 4 ገጽ 12

[20] Sergaw Hable Sellassie, *Ancient and Medival Ethiopian History to 1270*, Addis Ababa, Haile Sellassie I University 1972, p.115)
[21]**መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት ቁ፤1 ገጽ 21**
[22] Tim Dowley, *The History of Christianity*, p.182
[23] Donald Crummey, *Priests and Politicians*, Oxford, Oxford Press, 1972, p. 15).
[24]Tesfazghi Uqbit, Current Christological Positions of E.O.C Theologians, p.55).
[25]Tesfagzhi p68–69
[26] **አያሌው ታምሩ መች ተለመደና ከተከሳ ዝምድና ... 1953 ገጽ 70)**
[27]Ayala T/Hymanote, The Ethiopian ..., Addis Ababa. Graphic Printers,1982, 83
[28] Ayala T/Hymanote, The Ethiopian ..., 49
[29] Tesfagzhi p58
[30] **ቃለ መጠይቅ :- አቶ ጸጋዬ ደምሴ፥ ሕዳር 7 1993**
[31] Tesfagzhi p 86
[32] Tesfagzhi, p82
[33] **መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት ቁ11 ገፅ22**
[34] **መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት ቁ10 ገፅ28**
[35] **መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ ቁ 10 ገፅ 27**
[36]**መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ ቁ 10 ገፅ 28**
[37] **ቃለ መጠይቅ፥ አቶ ጸጋዬ ደምሴ ፥ የጮራ መጽሔት ዋና አዘጋጅ፥ ሕዳር 7/1993**
[38]**መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት ቁ 10 ገጽ 3**
[39]**አያሌው ታምሩ፥ መች ተለመደና ... ፥ ገጽ 148**
[40] Kefyalew Merahi (Kessis), *The Contribution of the Orthodox Tewahido Church:* To the Ethiopian Civilization, Addis Ababa, Commercial Press, April 27, 1999, p.166 – 168
[41] **ቃለ መጠይቅ፥ ከመላከ ገነት አፈወርቅ፥ ጥቅምት 29 1993 በመኖሪያ ቤታቸው**
[42] ***ሠይፈ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ... ገጽ 25***
[43] ***ሠይፈ ሥላሴ የኢትዮጵያ ... ገጽ 25***
[44]**መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ ቁ10 ገጽ 29**
[45] **መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ ቁ10 ገጽ29-30**
[46] **መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ ቁ10 ገጽ 30**
[47] Tesagzhi, p.26
[48] Dr. Tim Dowley (Ed.), *The History of Christianity* p.82
[49] G.D. Dragas, "Cyril of Alexanderia, in "Sinclair b. Ferguson, David F. Wright, J.I. Packer (Eds), *New Dictionary of Theology,* 1988, p.185
[50] Dr. Tim. Dowley, *The History of Christianity*, p. 184)

[51]Tesfazghi, p.153
[52] Testazghi, p. 159
[53] Tesfagzhi, 162
[54] አያሌው ታምሩ:- መቼ ተጠለዩ እና ከተከላ ዝምድና ገጽ 75-76
[55]አያሌው ታምሩ÷ መች ተለመዩና... ገጽ 70
[56] H.H. Pop Shenouda III, *The Nature of Christ*, J.C Center, Dar El-Kawmia, 1997, 8
[57] H.H. Pop Shenouda III, *The Nature of Christ*, 9
[58]መሠረት ስብሐት ለአብ÷ ጮራ መጽሔት ቁ11 ገጽ 20
[59] ሊ. ጠ  አያለው ታምሩ:-  መች ... ገጽ115)
[60] Dr. Tim Dowley, *History of* Christianity p.182.
[61]ሊ. ጠ. አያሌው ታምሩ:- መች ተለመዩና ከተከላ... ገፅ 147
[62]Leon Morris, *The Gospel According to John*, Grand Rapids, WM B. EERDMANS Publishing Co., 1971, P.812)
[63] Leon Morrie, *The Gospel* ..... , p. 815
[64] John Stott, *The Cross of Christ*, England, Inter-Varsity Press, 1989, p.41)
[65] John Stott, *The Cross of Christ*, p. 111
[66]John Stott, *The Cross*..., p.113
[67] Paul e. little, *Know what you believe*, Singapore, SU Publishers, 1986, p.34)
[68]አያሌው ታምሩ:- መች ተለመዩና ... ÷ ገጽ 166)
[69]ሊ. ጠ. አያሌው ታምሩ:- መች ተለመዩና ከተከላ ዝምድና ገጽ 218
[70]Tesfagzhi, *Current Christological*..., p.83)
[71] Tesfazghi, p.83– 85
[72]Tesfagzhi, p. 95
[73]መጠይቅ:- አቶ ጸጋዬ ደምሴ ሕዳር 21 1993
[74]The E.O.T.C., Faith, Order of Worship... p57)
[75] መ ገ አፍወርቅ ቃለ መጠይቅ:- 10/11/92
[76] መ ገ አፍወርቅ ቃለ መጠይቅ:- 10/11/92
[77]አባ መልከ ጼዴቅ ትምህርተ ክርስትና ገፅ 57
[78]ጸጋዬ ደምሴ÷ ጮራ መጽሔት ቁ19 ገፅ 17
[79]አባ መልከጼዴቅ:- ትምህርተ ክርስትና 2ኛ መጻሐፍ 1984 ዓ.ም ገፅ 50
[80]አባ መልከ ጼዴቅ:- ትምህርተ ክርስትና ... ገጽ 58
[81]አባ መልከ ጼዴቅ:- ትምህርተ ክርስትና ... ገጽ 58
[82] አባ መልከ ጸዴቅ ገጽ 56 –57
[83]አባ መልከ ጼዴቅ:- ትምህርተ ክርስትና ገጽ 58
[84]ቃለ መጠይቅ:- መላከ ገነት አፈወርቅ 10/11/92
[85] መ ገ አፍወወርቅ:- መጠይቅ 10/1/92
[86]ሠይፈ ሥላሴ :- የኢ.ኦ.ተ. ቤተክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና .ገጽ ፳፯
[87] መ ገ አፍውርቅ:- መጠይቅ 10/11/92)
[88]ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ. ቤተክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖትና ...ገጽ 28
[89] መ ገ አፍወርቅ :- ቃለ መጠይቅ 10/11/92

መለኮት በሥጋ:- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሁለቱ ባሕርያት በተናጥል ላይጠሩ በተዋሕዶ አንድ መሆናቸውን፤ ነገር ግን መለኮት በሥጋ ጠባይዕ (የባሕርይ ግብር) መገለጡን ለማስረዳ ትጠቀምበታለች:: ኃዋርያው ጴጥሮስ '...በሥጋ ሞተ...' 1ኛ ጴጥ 3:18 ሲል የክርስቶስ ሥጋ ሞተ ሳይሆን አምላክ–ሰው የሆነው ክርስቶስ በሥጋ ጠባይዕ መሞቱን ያስረዳል:: ሥጋም በመለኮት ጠባይዕ እንዳለ ለማመልከት የምትጠቀምበት ቃልም '...ሰው አምላክ ሆነ!' የሚል ሲሆን አሁን ክርስቶስ በአብ ቀኝ ከማርያም በነሳው ሥጋ – ተዋሕዶተ አካሉ እንዳለ ለመግለጽ ትጠቀምበታለች::

መምሬ(Teacher):–ለሥነ መለኮት ትምህርት መምህርነት ለበቁ እና ደቀ መዛሙርት ለሚያፈሩ አስተማሪዎች የሚሰጥ ስያሜ ነው::

ስመ ሥጋዌ:- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አካላዊ ቃል ሰው ከመሆኑ በፊትና በኋላ የተለያዩ መጠሪያዎች እንዳሉት ስለምታምን፥ ሰው ከሆነ በኋላ የተጠራባቸው ስሞቹን ለማመልከትም ስመ ሥጋዌ በማለት ትለያቸዋለች::

ባሕርይ (Nature):–የማንኛውም አካል መሠረት ነው:: ሥረው ቃሉ 'ባሕር' ከሚለው ቃል የመነጨ ሲሆን ባሕር በውሃ ውስጥ ለሚኖሩ ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ምንጭ (መሠረት) እንደ መሆኑ "ባሕርይ" የአካል መሠረት ነው::

የባሕርይ ልጅ (Son of nature):- ቃል ለአብ ዘላለማዊ ልጅ መሆኑን የሚያመለክት መጠሪያ ሲሆን የአብ ትክክለኛ ባሕርይ ያለው መሆኑን የሚያመለክት ስያሜ ነው::

ተዋሕዶ:- (Composite Unity) :- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅ/ ቄርሎስን አስተምህሮ ዋቢ አድርጋ በክርስቶስ ውስጥ ሁለቱ ባሕርያት በተናጥል ላይገለጹ እና ላይደባለቁ እንደተጠመሩ አገር በቀል በሆኑ መግለጫዎች የምታስረዳው የእምነቷ መጠሪያ ነው:

ተዋሕዶ–በተዓቅቦ

(Composite Unity with Preservation):– በተዋሕዶ መምሬዎች ዘንድ በክርስቶስ ሁለቱ ባሕርያት ያለመደባለቅ፥ ያለመቀላቀል፥ ያለመከፋፈል እና ያለመለያየት (በጥምረት) እንዳለ ለማመልከት ሲሆን በ «ዐጋ ልጅ» አስተምህሮ ትኩረት የሚሠጥበት ደግሞ ተዓቅቦ በክርስቶስ አካል የሁለቱ ባሕርያቱን በተናጥል መገኘት የሚያመለክት ነው። ከዚህ ትኩረታቸው የተነሳ ለዐጋ ልጅ ቡድን መለያ እስከ መሆን ደርሷል።

ተፈጥሮ:– በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር የፈጣሪነት ሚና ካለመኖር ወደ መኖር የመጡ ፈጥረታትን ያመለክታል። ይህንን ቃል ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣቱን ለመግለጽ መጠቀም ትክክል አይደለም።

ትሥጉት:–(Incarnation):– የአካላዊ ቃል ሥጋ መሆንን የሚያመለክትና 'ቃልም ሥጋ ሆነ...።' የሚለው ጥቅስ አጠራር ነው።

ትስብእት:–(Perfect Man) :– የአካላዊ ቃል ሥጋ መሆን ፍጹም (ምሉዕ) ሰው መሆንን:– በአንድ ሰው ውስጥ የሚገኙ ሥጋ፥ መንፈስና ነፍስ ያለው መሆኑን ይገልጻል።

አሃዱ ባሕርይ(One nature) :– አንድ ባሕርይ ማለት ሲሆን በታሪካዊ ሥነ መለኮት ረገድ የተለያየ አተረጓጎም ይኑራቸው እንጂ ቅ/ቄርሎስም ሆነ አውጣኪ በክርስቶስ ውስጥ የሁለቱ ባሕርያትን ግንኙነት አንድ ባሕርይ ማምጣቱን የሚያመለክቱበት ነው።

አማላጅ:– በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን 'ማለዳ' ከሚለው ቃል የተገኘና አንድን ወንጀለኛ በማለዳ (ጎህ ሳይቀድ) ገስግሶ መታደግን ገላጭ ነው። ይህንን ተግባር ክርስቶስ የፈጸመው በግብረ ትሥጉት እስከ መስቀል ሞቱ በነበረው ተልዕኮው ሂደት እንደ ሆነ ይታመናል። በአሁኑ ወቅት የቃሉ ትርጉም በራሱ ማድረግ የማይችል፤ ነገር ግን ካለው ቀረቤታ አንጻር ለምኖ የሚያስደርግ ማለት ነው። ስለዚህም አማላጅ ቅዱሳን

እንጂ ክርስቶስ አይደለም የሚተለው ከሁለተኛው ወቅታዊ ትርጉሙ የተነሳ ነው።

አስተርዕዮ (Revelation)፦ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች የገለጠበት መንገድ ነው።

አካላዊ ቃል(Logos)፦ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቃል (Logos) ከሰው አንደበት እንደሚወጣና አካላዊነት እንደሌለው ቃል አለመሆኑን ለመግለጥ እንዲሁም አኗኗር ያለው መሆኑን ያስገነዝባል።

አካል (Person)፦ የባሕርይ መገለጫ ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር ስታስተምር ለአዕምሮ በሚመች (በሰው ሰውኛው አገላለጥ የተገለጠበትን መንገድ ለማሳየት ካልሆነ በቀር) እግዚአብሔር ቁሳዊ ተክለ ሰውነት የሌለው፤ ነገር ግን ረቂቅ ሕያውና ያልተፈጠረ አካል እንደሆነ ታስረዳለች። የሰውም አካል የሰው የባሕርዩ መገለጫ የሆነ ማንነቱ ነው። (በተጨማሪ ደጋፊ ማብራሪያ ቁ 2 ተመልከቱ)

አካል ዘእም አካል ፥
ባሕርይ ዘእም ባሕርይ፦ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በአብና በወልድ መካከል ያለውን ግንኙነት አካላዊ ቃል ከዘላለም ከአብ ባሕርይ በባሕርይ፥ ከአብ አካል በራሱ ልዩ አካል መውጣቱን የምታስረዳበት መንገድ ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፦ በኢትዮጵያውያን መምሬዎች ዘንድ በተደረጉ ጉባኤዎች የዳበረ አውዳዊና አገር በቀል ሥነ መለኮት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት። ሌሎች የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያናት የምዕራቡን (የኬልቄዶንን) ፈለግ የሚከተሉ፥ ግን አገር በቀል የሆነና የራሳችን የሚሉት ሥነ መለኮት የሌላቸው በመሆኑና የተካይ ሚስዮናውያኖቻቸውን ትምህርት ስለሚከተሉ የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን መሆናቸው እንጂ «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን ስያሜ መጠቀም ተገቢነት አይኖረውም።

ኦርቶዶክስ:- ለምሥራቋም ሆነ ለአርየንታል አብያተ ክርስቲያናት በጋራ የሚያገለግል ስም ሲሆን የግሪክኛው ትርጉሙ ቀና ወይም ቀጥተኛ ማለት ነው:: በኢትዮጵያ ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ስመ ኃይማኖቷ ኦርቶዶክስ÷ ነገረ ክርስቶሷ ተዋሕዶ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመባል ትታወቃለች:: ከአርየንታል ቤተ ክርስቲያናትም አንዷ ናት::

ጠባይዕ(Character):- እንደየአገባቡ ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር የምንጠቀምበት ሆኖ በየባሕርይ ግብርነቱ የሚጠቀስ ነው::

ግብር (Function):- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ሥራ በተመለከተ የምትገልጽበት ቃል ነው::

ግብረ መለኮት (Divine Function):- በክርስቶስ የመለኮታዊ ባሕርይ ግብር መለኮታዊ ጸባይዕ:- እንደ ከአብ ቀኝ መቀመጥና በአለም ላይ ገዢነት የአምላክ ግብሮች እንዳሉ ለመግለጽ ነው::

ግብረ ትስብእት (Human Function):-በክርስቶስ የሰብአዊ ባሕርይ ግብር የሰው ጸባይዕ:- እንደ መከራን መቀበል÷ ማማለድ÷ መሰቀልና መሞት ያሉ በሰው ህይወት የሚከናወኑ ድርጊቶችን እንዴት እንደፈጸመ የሚገልጽ ነው::

ግጻዌ መለኮት(God head):- በአብ÷ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለን ዘላለማዊ ግንኙነት የሚያመለክት ነው::


የፀጋ ልጅ (son of Grace) :- አማኞች በክርስቶስ የማዳን ሥራ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ያገኙትን ልጅነት የሚያመለክት ነው:: ሆኖም ክርስቶስም ይህንን አይነት ልጅነት በሥጋው ተቀብሏል የሚል ክርክር ያላቸው ቡድኖች «ሦስት ልደት» ወይም «የፀጋ ልጅ» በመባል ይታወቃሉ::

| ደጋፊ ማብራሪያ ቁ 1 | | | |
|---|---|---|---|
| | ተዋሕዶ/ካራ/ | ሦስት ልደት/የጸጋ ልጅ/ /ተዋሕዶ በተዐቅቦ/ | ቅብዓት |
| ደረጃው (Status) | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኦፊሴላዊ ኃይማኖት | ባብዛኛው በጎንደር መምሬዎች የሚደገፍና በውግዘት ስር የዋለ ቡድን ነው:: | ባብዛኛው በጎጃም መምሬዎች የሚደገፍ ቡድን ነው:: |
| ታዋቂ ሊቃውንት /መምሬዎች/ | ሊቀ ጠበብት አያሌው: መላከ ገነት አፍወርቅ | አለቃ ኪ/ወልድ? ጸጋዬ ደምሴ | የጎጃም መምሬዎች |
| ይገባኛል ባይነታቸው | የቄርሎስ ተከይነት:: | የጥንቱ ተዋሕዶ:: | በቅብዓት የባሕርይ አምላክ ሆነ:: |
| የተገኙበት ሥፍራ | ኤርትራ:-ደብረ ቢዘንና ሸዋ:- ደብረ ሊባኖስ | ሸዋ:-ደብረ ሊባኖስ | ጎጃም :- ደብረ ወርቅ |
| ነገረ-ክርስቶስ | ክርስቶስ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ÷ ከሁለት አካል አንድ አካል በተዋሕዶ:: የቃል የሆነው የሥጋ÷ የሥጋ የሆነው የቃል! ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆነ በተዋሕዶ! | አንድ አካል ሁለት ባሕርያት *በመገናዘብ* የሥጋ ባሕርይን ቃል ገንዘቤ ብሎ ይጠቀምበታል! | ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ በቅብዓት! |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ተዋሕዶ-በተዓቅቦ ሲሉ ውላጤ እንደሌለበት ለማመልከት ነው! | ተዋሕዶ-በተዓቅቦ ሲሉ የሁለቱ ባሕርያት በተናጥል መገኘትን ለማመልከት ነው! ከፍተኛ ትኩረታቸው በተዓቅቦ ላይ ስለሆነ «ተዋሕዶ-በተዓቅቦ» የሚለው ሥያሜ ተስማሚያቸው ነው! | |
| | «አምላክ ሰው ሆነ! ሰውም አምላክ ሆነ! ሲሉ ያለ ጠባይዕ (የባሕርይ ግብር) ለውጥ መሆኑን ይናገራሉ:: | «በመገናዘብ» የሚለውን ቃል ከሁለቱ አንዱ ባሕርይ የሌላውን ባሕርይ ገንዘቡ አድርጎ ይጠቀምበል የሚልን ሃሳብ ለመግለጽ ይጠቀሙበታል:: | |
| | አካላዊ ቃል ራሱ:- ቀቢ÷ ቅብና ቅብዓት ነው:: ሥጋ በተዋሕዶ ከበረ:: | አብ ቀቢ: ወልድ በሥጋ ባሕርይ ቅብ፥ መንፈስ ቀዱስ ቅብዓ ነው:: በተዋሕዶ ወልድ -ዋሕድ÷ በቅብዓት ክርስቶስ ሆነ! | ቅብዓት እንደ ተዋሕዶ ሆነለት! ሥጋ በቅብዓት ከበረ! አብ ቀቢ÷ ወልድ ቅብ÷ መንፈስ ቅዱስ |
| | ክርስቶስ ሁለት ልደት አለው:: ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአባቱ 'የባሕርይ ልጅ'÷ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከድንግል ማርያም:: | ክርስቶስ ሦስት ልደት አለው:: ከዘላለም 'የባሕርይ ልጅ'÷ በጊዜ ውስጥ የማርያም ልጅ እና ከመንፈስ ቅዱስ 'የፀጋ ልጅ' ነው:: | ኢየሱስ ወልድ የሆነው በቅብዓት ነው! ብለው ያምናሉ:: |

ደጋፊ ማብራሪያ ቁ 2

ስለ አካል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምሬዎች ዘንድ ያለውን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተቀናበረ ጠቅላላ ማብራሪያ:-



## Bibliography


Ayala Tekla Haymanot, *The Ethiopian Church and its Christological Doctrine,* Addis Ababa, Graphic Printers, 1982.

Ayaliew Tamiru, '*Mech Telemedena Ketekula Zemdina'(Amharic)*, Addis Ababa, Tinsie Zegubaie Press, Meskerem 1953 E.C.

Ayaliew Tamiru, Yethidke Ber, (Amharic) Addis Ababa, Tinsaie Zegubaie Press, 1979 E.C.

Aymro Wondmagegnehu and Joachim Motovu (eds.), *The Ethiopian Orthodox Church*, Addis Ababa: Berhanena Selam H.S.I Pr, 1970.

Bahiru Zewde, *A Short History of Ethiopia and the Horn*, Addis Ababa, Addis Ababa University, 1998. 123

Crummey, Donald, *Priests and Politicians*, Great Britain, Oxford University Press, 1972.

______. *The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life*, Addis Ababa, B.S.P.E, 1997.

_______. *The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith, Order of Worship and Ecumenical Relations,* Addis Ababa, Tinsaie Zegubaie Press, July 1996.

______. National Library and Archive,(Amharic) Level No. 481.

Dowley, Tim, *The History of Christianity*, Hong Kong, Lion Publishing, 1990.

Ethiopaian Orthodox Tewahido Church Menbere Patririaric (Holy Synod), Lique Gubae (Assembly of Scholars), *Haymanot Abew (Amharic),* Addis Ababa, 1975 (Tir 30, 1967E.C.).

Erickson Millard J. *Christian Theology*, Grand Rapids, Michigan Baker Book House, 1985.

Erickson, Millard J. *The Word Became Flesh*, Grand Rapids, Michigan, Baker Book House, 1991.

Ferguson Sinclair, David F. Wright, J.I. Packer (eds), *New Dictionary of Theology*, England, InterVarsity Press, 1988.

Guthrie, D & T. A. Motyer (Eds), *New Bible Commentary*, Grand Rapids, Inter-Varsity Press, 1970.

Habte Marriam Workneh, *Timihirte Kiristina(Amharic)*, Addis Ababa, Tinsaie Zegubaie Press, 1979 E.C

Kefyalew Merahi (Kessis), *The Contribution of the Orthodox Tewahido Church: To the Ethiopian Civilization*, Addis Ababa, Commercial Press, April 27,1999.

Kidane Wold Kifle, *Methafe Sewasew Wegise Mezgebe Kalate Haddis (Amharic)*, Addis Ababa, Artistic Press, 1948.

Kerilos, (Arc Bishop), *Firie Haymanot(Amharic)*, Asmara, Fire Haymanot Press, 1976 E.C

Little Paul e., *Know What You Believe*, Singapore, SU Publishers, 1986.

Morris, Leon, *The Gospel According to John*, Grand Rapids, WM. B. EERDMANS Publishing Co. 1986)

Mekibib Girma Yesus (ed), *YeAkcimares Metsihaf*, Addis Ababa, Ethiopian Birana Metsihaft Microfilm Organization, Yekatit 30, 1980 E.C. 152-153.

Melke Tsedek, (Beshop of Sewasewe Birhan Higher Spiritual School),T*imihrite Kiristina (Amharic), 2nd book,* Addis Ababa, Tinsaie Printing Press, 1991 (1984 E.C).

Meseret Sebhat Leab, *Semha Tesideke Beherawi(Amharic)*, Addis Ababa, Artistic Matemia Bet, 1951 E.C.

Sergew Hable Sillassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History, to 1270,* Addis Ababa, United Printers, 1972

Seyefe Selassie Yohanes, *The Ethiopian Orthodox Tewahido Betekristian Meserete Haymanote (Amharic)*, Addis Ababa, Tinsayi Zegubai Printing Press, 1982 E.C.

Shenouda III, H.H. (PoP), *The Nature of Christ*, J.C. Center, Dar El-Kawmia, March 1997.

Stott, John, *The Cross of Christ*, England, InterVarsity Press, 1989

Strauss, Stephen J. *Perspectives on the Nature of Christ in The Ethiopian Orthodox Church: A Case Study in Contextualized Theology,*(unpublished Ph.D. Dissertation), Deerfield, Illinois, December 1997.

Tesafazghi Uqbit, *Current Christological Positions of E.O.C. Theologians*, Rome: Pontifica Institutum Studiorum Orientalium, 1973.

War, Timothy, The *Orthodox Church*, Mary Land, Penguin Books, 1964.

Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania, *New World Translation of the Holy Scripture*, New York, Watch Tower Bible and Tract Society of New York, INC, 1961

Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania, *Bmder lay Bgnet Lezelalm Mnor Tchlalh* (Amh.), New York, Watch Tower Bible and Tract Society of New York, INC, 1991

**Magazines:**

ናሁ አዳም (ጸሐፊ) "ክርስትና በኢትዮጵያ" መሠረት ስብሐት ለአብ (አዘጋጅ) ጮራ መጽሔት ቁ 4፥ 10፥ 11 እና 12

ነቅዓ ጥበብ(ጸሐፊ) "አለቃ ኪዳነ ወልድና አገልግሎታቸው" ጸጋዬ ደምሴ (አዘጋጅ) ጮራ መጽሔት ቁ 19

**ቃለ መጠይቅ:**


መላከ ገነት አፈወርቅ (የሊቃውንት ጉባዔ አባል):- በመኖሪያ ቤታቸው፥ ሐምሌ 10/1992 ዓ/ ም

አቶ ጸጋዬ ደምሴ (የጮራ መጽሔት አዘጋጅ):- የጮራ መጽሔት ዝግጅት ቢሮ ፥ ሕዳር 7/1993 ዓ/ም

መሠረታዊና ምጥን የሥነ መለኮት መጽሐፍ ነው። ወንጌልን በኢትዮጵያ ምድር ለማሰራጨት አውድን በሚገባ ያገናዘበና በነገረ-ክርስቶስ ዙሪያ የሚነሱ የስህተት ትምህርቶችን ለመከላከል ጠቀሜታው ያላቀ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እጅግ ወሳኝ የሆኑ የነገረ-ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችንና ቃላትን በመተርጎም እንዲሁም በማብራራት ኢትዮጵያ ከአይሁድ፥ ከፋርስና ከመሳሰሉት አገሮች ጋር ያላትን ታሪካዊ ቁርኝት ይተነትናል። መጽሐፉ በሥነ መለኮት ዙሪያ ከኩነኔያዊ አንድምታ በፊት በንጹሕ አእምሮ ንጽጽር ማካሄድ እንደሚገባ በሚመጥን ሥነ ጽሑፋዊ ጥንካሬና ጥልቀት ቀርቦልናል።

በቋንቋ አጠቃቀምም በኩል የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ በማካተቱ ደራሲው በሥነ መለኮት ቃላት አጠቃቀም ረገድ ትልቅ ባለውለታችን ሲሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና በአብያተ ክርስቲያና ሁሉ የክርስትናን እውነት ለመግለጽ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ደገፋ ሶዶሮ
የጌ/ቃ/ህ ቤ/ክ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት
አካዳሚክ ዲን



ስለ ደራሲው፦